

# ወደ ውኃውና ወደ መንፈሱ ወንጌል መመለስ

ፓውል ሲ. ጆንግ

# Worldwide websites of The New Life Mission

The Official Website of The New Life Mission
www.nlmission.com or
www.bjnewlife.org

Please find your vernacular websites below.
You can download Christian e-books and request Christian books for free.
Feel free to visit our websites below right now!

**A**
www.nlmafghanistan.com
www.nlmafrikaans.com
www.nlmalbania.com
www.nlmamharic.com
www.nlmangola.com
www.nlmarabemirates.com
www.nlmarabic.com
www.nlmargentina.com
www.nlmarmenia.com
www.nlmaruba.com
www.nlmaustralia.com
www.nlmaustria.com

**B**
www.nlmbahamas.com
www.nlmbahrain.com
www.nlmbangladesh.com
www.nlmbelarus.com
www.nlmbelgium.com
www.nlmbengali.com
www.nlmbenin.com
www.nlmbhutan.com
www.nlmbolivia.com
www.nlmbotswana.com
www.nlmbrasil.com
www.nlmbriton.com
www.nlmbrunei.com
www.nlmbulgalia.com
www.nlmburkinafaso.com
www.nlmburundi.com

**C**
www.nlmcameroon.com
www.nlmcanada.com
www.nlmcebuano.com
www.nlmchichewa.com
www.nlmchile.com
www.nlmchin.com
www.nlmchina.com
www.nlmcolombia.com
www.nlmcongo.com
www.nlmcostarica.com
www.nlmcotedivoire.com
www.nlmcroatia.com
www.nlmczech.com

**D**
www.nlmdenmark.com
www.nlmdioula.com
www.nlmdominica.com
www.nlmdrcongo.com
www.nlmdutch.com

**E**
www.nlmecuador.com
www.nlmegypt.com
www.nlmelsalvador.com
www.nlmequatorialguinea.com
www.nlmethiopia.com

**F**
www.nlmfinland.com
www.nlmfrance.com
www.nlmfrench.com

**G**
www.nlmgabon.com
www.nlmgeorgian.com
www.nlmgerman.com
www.nlmgermany.com
www.nlmghana.com
www.nlmgreek.com
www.nlmgrenada.com
www.nlmguatemala.com
www.nlmgujarati.com

**H**
www.nlmhaiti.com
www.nlmhindi.com
www.nlmholland.com
www.nlmhonduras.com
www.nlmhungary.com

◎ Some of these websites may not work because they are still under construction.

# Worldwide websites of The New Life Mission

I
www.nlm-india.com
www.nlmindonesia.com
www.nlmiran.com
www.nlmiraq.com
www.nlmisrael.com
www.nlmitaly.com

J
www.nlmjamaica.com
www.nlmjapan.com
www.nlmjavanese.com

K
www.nlmkannada.com
www.nlmkazakhstan.com
www.nlmkenya.com
www.nlmkhmer.com
www.nlmkinyarwanda.com
www.nlmkirghiz.com
www.nlmkirundi.com
www.nlmkorea.com

L
www.nlmlatvia.com
www.nlmluganda.com
www.nlmluo.com

M
www.nlmmadi.com
www.nlmmalagasy.com
www.nlmmalayalam.com
www.nlmmalaysia.com
www.nlmmarathi.com
www.nlmmauritius.com
www.nlmmexico.com
www.nlmmindat.com
www.nlmmizo.com
www.nlmmoldova.com
www.nlmmongolia.com
www.nlmmyanmar.com

N
www.nlmnepal.com
www.nlmnewzealand.com
www.nlmnigeria.com
www.nlmnorthkorea.com
www.nlmnorway.com

P
www.nlmpakistan.com
www.nlmpanama.com
www.nlmperu.com
www.nlmphilippines.com
www.nlmpoland.com
www.nlmportugal.com
www.nlmportuguese.com
www.nlmprcongo.com

Q
www.nlmqatar.com

R
www.nlmromania.com
www.nlmrussia.com
www.nlmrwanda.com

S
www.nlmsaudiarabia.com
www.nlmserbian.com
www.nlmshona.com
www.nlmsingapore.com
www.nlmslovakia.com
www.nlmslovene.com
www.nlmsolomon.com
www.nlmsouthafrica.com
www.nlmspain.com
www.nlmspanish.com
www.nlmsrilanka.com
www.nlmsuriname.com
www.nlmswahili.com
www.nlmswaziland.com
www.nlmsweden.com
www.nlmswiss.com

T
www.nlmtagalog.com
www.nlmtaiwan.com
www.nlmtamil.com
www.nlmtanzania.com
www.nlmtelugu.com
www.nlmthailand.com
www.nlmtogo.com
www.nlmtonga.com
www.nlmturkey.com

U
www.nlmuganda.com
www.nlmukraine.com
www.nlmurdu.com
www.nlmusa.com

V
www.nlmvenezuela.com
www.nlmvietnam.com

Z
www.nlmzambia.com
www.nlmzimbabwe.com
www.nlmzou.com

# የውኃና የመንፈስ ወንጌል ኃጢያቴን በሙሉ አፅድቶልኛል

የውኃና የመንፈስን ወንጌል «በዕውኑ ከውኃና ከመንፈስ እንደገና ተወልዳችኋልን?» በሚለው የመጀመሪያ መፅሐፌ ውስጥ መፅሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረው መንገድ መሰረት መስክሬኣለሁ::

ይህ መፅሐፍ የመጀመሪያው ተቀፅላ ሲሆን በዚህ መፅሐፍ ውስጥ እግዚአብሔር በፈቀደው መልኩ ዳግም ስለመወለድ እውነት በጥልቀት ገብቼ ለማብራራት ሞክሬአለሁ::

የውኃና የመንፈሱን ወንጌል በአሁኑ ወቅት በጣም ከተስፋፉት ወንጌሎች ጋር በማነፃፀርም ስለ እውነተኛው ወንጌል ያላችሁን መረዳት ለመጨመር እሞክራለሁ ከሁሉም በላይ ደግሞ በአሁኑ ጊዜ ያሉት ስነ ኃይማኖቶች የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን በመጠቀም ብዙ ሰዎች የእውነተኛውን ወንጌል ብርሃን እንዴት እንዲያጡ እንዳደረጉ ለማሳየት እሞክራለሁ::

አሁን እግዚአብሔር ወደ ሰጠን ውብ ወደሆነውና ወደተባረከው የውኃና የመንፈስ ወንጌል እንመለስ::

# ወደ ውኃውና ወደ መንፈሱ ወንጌል መመለስ

## ፓውል ሲ. ጆንግ

ሔፍዚባህ አሳታሚ ድርጅት
የአዲስ ህይወት ንፁስ ክፍል
ሴኡል፣ ኮሪያ

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡

*ወደ ውኃውና ወደ መንፈሱ ወንጌል መመለስ*

---

የታተመው © 2012 by The New Life Mission
መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው የዚህ መጽሐፍ የትኛውም ክፍል ከባለቤቱ የጽሁፍ ፈቃድ ውጪ ፎቶ ኮፒ ማድረግን፣ መቅዳትን ወይም ማንኛውንም መረጃ በሚይዝ ወይም ይዞ የሚያስቀር ሲስተምን ጨምሮ በማንኛውም መልክ በኤሌክትሮኒክ ወይም በመካኒካል ወይም በማንኛውም መንገድ ማባዛት ወይም ማሰራጨት ክልክል ነው::
የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት *ከ1954ቱ የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ* ነው

ISBN 978-89-6532-757-8

**Website :** http://www.nlmission.com
http://www.bjnewlife.org
http://www.nlmbookcafe.com
**E-mail :** newlife@bjnewlife.org

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# ምስጋና

በዚህ በጨለማው ዘመን በእግዚአብሄር ቤተክርስቲያን አማካይነት ከውሃና ከመንፈስ የሆነውን ወንጌል እንድንሰብክ ስለፈቀደልን ጌታን አመሰግነዋለሁ ሁሉም ዳግመኛ ይወለዱ ዘንድ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በዚህ በዚህ መፅሐፍ አማካይነት በዚህ አለም ላይ ለሚኖሩ ነፍሳቶች ሁሉ ስንሰብክ ጌታ እንደሚባርከን እርግጠኛ ነኝ::

ሠራተኞችንና የእግዚአብሄርን ሥራ የመስራት ችሎታም ስለሰጠን ደግሞ ጌታን አመሰግናለሁ መፅሐፉን ለተረጎመው ለአቶ አብርሃም ተመስገን ስህተትን በማረም ረገድ ለሮዝ ዋላስ አርትኦት በማድረግ በኩል ደግሞ ለእህት ሲ. ሳንግሚንፐ ለሬቨረንድ ሳሙኤል ጄ. ኪምና ለሬቨረንድ ጆን ኬ. ሺን ልባዊ አድናቆቬን ልገልጥ እወዳለሁ ለዚህ መፅሐፍ መታተም እገዛ ላደረጉት ሌሎች የወንጌሉ ሠራተኞች ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን እገልጣለሁ::

የመጀመሪያው መፅሐፌ ቀጣይ የሆነው ይህ መፅሐፍ ከውሐና ከመንፈስ የሆነውን ወንጌልና የሐሰተኛውን ወንጌል አመጣጥና ጭብጥ ይበልጥ አጥርቶ ይገልጣል::

የእግዚአብሄር ፈቃድ በዚህች አለም ላይ ይፈፀም ዘንድ በዚህች አለም ላይ የሚኖሩ ነፍሳቶች ሁሉ የውሐውንና የመንፈሱን ወንጌል ወደ ማመን እንዲመጡ ወደ እግዚአብሄር እፀልያለሁ:: ✉

**ፓውል ሲ. ጆንግ**

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::




«ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአሔር መንግስት ሊገባ አይችልም::» (ዮሐንስ 3:5)

# መቅድም

## ክርስትና ብርሃኑን አጥቷል

ይህ ዘመን ነፍሳት ሁሉ በስቃይ ውስጥ ያሉበትና በአያሌው የሚያለቅሱበት ዘመን ነው:: መንፈሳዊ ስቃይ ሁሉ የሚመጣው ከሰው ልጅ መንፈሳዊ ውድቀት የተነሳ ነው:: በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በኖህ ዘመን ክፋት የበዛው *«የእግዚአብሔር ልጆችም የሰውን ሴቶች ልጆች መልካሞች እንደሆኑ አዩ ከመረጡአቸውም ሁሉ ሚስቶችን ለራሳቸው ወሰዱ» (ዘፍጥረት 6:2)* ሚለው እውነታ ምክንያት እንደሆነ ተጽፎዋል::

በእውነት ቃሎች ዳግም የተወለዱ የእግዚአብሄር ልጆች እውነተኛውንና የተሟላውን የወንጌል እውቀት ትተው እውነትን በሰው አስተሳሰቦች የተቀላቀለትን የሐሰተኛ ክርስቲያኖችን ቃሎች በልቦቻቸው ውስጥ በመቀበላቸው በርካታ አስመሳይ ቤተክርስቲያኖች ተወለዱ ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ አለ *«መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም እርሱ ሥጋ ነውና ዘመኖቹም መቶ ሀያ አመት ይሆናሉ::» (ዘፍጥረት 6:3)*

ኢየሱስ ዳግም የተወለዱትን ደቀ መዛሙርቱን «የዓለም ብርሃን» ይላቸዋል ምክንያቱም ኢየሱስ ብቻ ሊሰጠው የሚችለውን ብርሃን አግኝተዋልና:: ሆኖም ግን የዘመኑ ክርስቲያኖች ይህ የህይወት ብርሃን የላቸውም:: ብርሃኑ አሁንም ድረስ በጨለማ የሚያበራ ቢሆንም ጨለማው አሁንም ድረስ አልተቀበለውም::

በመሆኑም የዘመኑ ክርስትና ተራ ወደሆነ ሐይማኖትነት

ወርዶዋል ስለዚህ ዛሬ ከማንኛውም ጊዜ ይበልጥ ብዙ ክርስቲያኖች ያሉ ቢሆኑም ሁሉም አልዳኑም እነርሱ ሁልጊዜም መጽሐፍ ቅዱስን ያጠናሉ ይማሩማል ነገር ግን ፈጽሞ ወደ እውነት እውቀት አይደርሱም ግብዝ በሆነው የሐይማኖት ሕይወት ውስጥ ይንከባለላሉ ልቦቻቸውም በድንቁርናና በሁከት ውስጥ ይቀበዘበዛሉ አብዛኞቹ የዘመኑ ክርስቲያኖች እንዴት ዳግም እንደሚባረኩና ይህ በረከትም ምን እንደሆነ አያውቁም::

እነዚህ ሁሉ የባከኑ ጥረቶች ከስነ መለኮት ትምህርት ስህተቶች የፈለቁ ናቸው በክርስትና ታሪክ ውስጥ በርካታ የሐይማኖት መሪዎች የእግዚአብሄርን ቃል በራሳቸው የስጋ አስተሳሰቦቻቸው መሰረት ተርጉመውታል አቀናብረውታልም::

ክርስትናን በብዙ የቤተክርስቲያን ድርጅቶች ከፋፍለውታል ተከታዮቻቸውንም አብዝተዋል በቤተክርስቲያን ድርጅቶቻቸው የአገዛዝ ስርአት መሰረትም በእነርሱ ላይ ሰልጥነዋል በስነ መለኮት ትምህርትም ሐሰተኛ አስተምህሮቶቻቸውን አጽድቀዋል ተከታዮቻቸውንም የስነ መለኮት ትምህርቶች ተብሎ በሚጠራው አለማዊና ገናና ስርአት መሰረት አስልጥነዋል::

ከዚህ የተነሳ በሐይማኖታዊው ክርስትና ውስጥ አስቸጋሪ በሆነው የሐጢያቶች ሸክም ስር ሆኖ ከመሰቃየትና ከማልቀስ በቀር ከሐጢያቶቹ መዳን የሚችል ማንም የለም እነርሱ የአምልኮት መልክ ያላቸው ነገር ግን ሐይሉን የካዱ ናቸው (2ኛ ጢሞቴዎስ 3:5) ከውጭ ሲታዩ ቅዱሳን ይመስላሉ!

የዘመኑ ክርስትና ግን «በቅሚያና በስስት የተሞላ» ነው (ማቴዎስ 23:25) ይህ ሁሉ የሆነው ዲያብሎስ የማታለል ዘሮችን በመዝራቱ ነው መናፍቅ የሆነው ክርስትና ራሱን በትክክለኛነት ካባ ውስጥ ደብቋል እውነተኛዎቹን የሕይወት ቃሎች መንገድ ይቃወማል ያደናቅፋልም::

# የኑፋቄ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜና አመጣጡ

በክርስቲያን ቤተክርስቲያን ውስጥ መናፍቃን የሚባሉት ኢየሱስን አዳኛቸው አድርገው የሚያምኑ ነገር ግን በወንጌል እውነት ቃሎች የማያምኑ ሰዎች ናቸው እነርሱ የዲያብሎስን ውሸቶች ይከተላሉ ከመተላለፎቻቸውም ፈጽሞ አልተዋጁም በራሳቸው ሐጢያተኝነትም ታስረዋል እውነተኛው ወንጌል «የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል» ነው «ከውሃውና ከመንፈሱ ደህንነት ዳግም የሚወለድበት እምነት» የሌለው ሰው ሁሉ በእግዚአብሄር አይን መናፍቅ ነው::

እውነተኛው ወንጌል የእግዚአብሄር አንድያ ልጅ የሰው ስጋ ለብሶ ወደዚህ አለም መምጣቱና የሰው ዘር ወኪል በሆነው በአጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁ ነው እርሱ ሰዎችን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸውና ከፍርድ ለማዳን የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል እነዚህን ሐጢያቶችም በመስቀል ላይ ተሸክሞዋል ተሰቅሎዋልም::

ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል *«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሄር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና» (ዮሐንስ 3:16)* እኛ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን የእግዚአብሄር ልጆች ለማድረግ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ፈጽሞ እንዳነጻ ማመናችን የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው::

ዛሬ ግን አብዛኞቹ ክርስቲያኖች የእርሱን ጥምቀት አሳንሰው በኢየሱስ መስቀል ብቻ በማመን መዳን እንደሚችሉ ያምናሉ የእግዚአብሄር ልጅ የሆነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ደሙን ባፈሰሰና በሞተ ጊዜ ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንዳስወገደ ይናገራሉ ይህ በተጨባጭ ከውሃውና ከመንፈሱ ዳግም እንድንወለድ ከሚያደርገን እውነተኛ ወንጌል በእጅጉ

የራቀ አስመሳይ ወንጌል ነው ስለዚህ ክርስትና በነገረ መለኮት ትምህርት ሕጸጽ ጎርፍ በመጠረጉ መናፍቅ ሆንዋል::

ዲያብሎስ አዳም የእርሱን ውሸቶች በማመኑና ከለእግዚአብሄር ቃሎች በመራቁ አጋጣሚውን በመጠቀም የሰውን ዘር ከእውነተኛ ሕይወት ወደ ሐሰተኛ ወንጌል ነዳው ሰይጣን ሰው ለረጅም ዘመን በውሸቶችና በሐሰተኛ ወንጌል ረግረግ ውስጥ አፍኖ በመያዝ ለጥፋት፣ ለሐጢያትና ለሞት ኮንኖታል በተመሳሳይ መንገድ ዲያብሎስ የእርሱን ውሸቶች እውነት አድርጎ የሚቀበለውን ሰው ሁሉ ይፈትናል ኑፋቄ ውስጥ እንዲወድቅ ያደርገዋል በኑፋቄ ውስጥም አስሮ ያስቀምጠዋል እውነትን ይማሩ ዘንድ ለመፍቀድም አሻፈረኝ ይላል::

ይህ የሰሜናዊው የእስራኤል መንግስት የመጀመሪያ ንጉስ ኢዮርብዓም ከሰራቸው የሐጢያት ስራዎች ጋር ይመሳሰላል እርሱ ሕዝቡ መቅደሱ ወዳለበት ወደ ደቡቡ መንግስት ሊያፈገፍግ ይችላል የሚል ፍራቻ ነበረው ስለዚህ እግዚአብሄር ቤዛ እንዲሆናቸው ለእስራኤሎች የሰጠውን የመስዋዕት ስርአት ለወጠው::

የወርቅ ጥጆች በመስራትም ሕዝቡ እንዲሰግድላቸው አስገደደ ክርስትናንም ወደ መናፍቅ ሐይማኖትነት ለወጠ በይሁዳ እንዳለው በአልም ራሱ በመረጣቸው ቀኖች ለእስራኤሎች በአላቶችን ደነገገ የሌዊ ልጆች ካልነበሩት ሰዎች መካከልም ካህናትን በመሾም ሕዝቡን ሁሉ ከእውነተኛው የስርየት ስርአት አራቃቸው ስለዚህ ክርስትና ተቀየረ እስከ አሁን ድረስም በዚያም መንገድ ቀጠለ ይህ አሳዛኝ ነገር ነው::

በውኑ ኢየሱስ ከሐጢያት ያዳነን በመስቀሉ ደም ብቻ ነውን? በክርስቶስ ስቅለት ብቻ የሚያምን ሰው ሐጢያቶቹ ሊነጹለት ይችላልን? አይችሉም የኢየሱስ ደቀመዛሙርት

የኢየሱስ ደም ሙሉ ወንጌል ነው ብለው ፈጽሞ አልተናገሩም ዮሐንስ የሕይወት ቃልና እውነተኛ ብርሃን የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዳየና እንደዳሰሰው መስክሮዋል ኢየሱስ ክርስቶስ «በውሃና በደም» እንደመጣም መስክሮዋል::

ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ዘር ሁሉ የሐጢያት ቁርባን ለመሆን ወደዚህ አለም መጣ ለዚህ አላማም በዮርዳኖስ ወንዝ በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉም በራሱ ላይ ወሰደ ከዚያም በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ የሐጢያትን ደመወዝ ከፈለ መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ «በውሃ ብቻ ሳይሆን በውሃና በደም እንደመጣ» (1ኛ ዮሐንስ 5፡6-8) እና ኢየሱስ አምላክ እንደሆነም የሚመሰክረው መንፈስ እንደሆነና እነዚህ ሦስቱም ማለትም «መንፈሱ ውሃውና ደሙ በአንድ እንደሚስማሙ» ይነግረናል አለምን ማሸነፍ የሚችል እውነተኛ እምነት ሊኖራቸው የሚችሉት ደቀመዝሙሩ ዮሐንስ ያመናቸውን እምነቶች የሚጋሩ ሰዎች ብቻ ናቸው::

## ኑና አብረንም እንመርምር

ከእነዚህ ከሦስቱ አንዱን ብናስወግድ መዳን እንችላለን? በፍጹም! መንፈሱ፣ ውሃውና ደሙ አንድ ናቸው ከእነዚህ ከሦስቱ አንዱን ካስወገድን ወንጌሉ ፍጹም ወንጌል ሊሆንና እኛ ም ሐጢያት አልባ ልንሆን አንችልም ሰው ሐጢያቶቹ ሁሉ ወደ ኢየሱስ በተላለፈበት የኢየሱስ ጥምቀት የማያምን ከሆነ ፈጽሞ ሐጢያት አልባ መሆን ይችላልን?

እግዚአብሄር ጥሪ አቅርቦልናል *«ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነፃለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች እሺ*

*ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ እንቢ ብትሉ ግን ብታምፁም ሰይፍ ይበላችኋል የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሯልና::» (ኢሳይያስ 1:18-20)*

አሁን ከተጻፋት የእግዚአብሄር ቃሎች ጋር እንዋቀስ የእርሱ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አላስወገደምን? ያንንስ ያደረገው እንዴት ነው? አምላክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ስጋ ለብሶ ወደዚህ አለም በመምጣት በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ አስወገደ::

የእግዚአብሄርን የእውነት ቃል በደስታ ለሚታዘዙ ሰዎች እግዚአብሄር የሺህ አመቱን በረከቶችና በመንግስተ ሰማይም የዘላለምን ሕይወት ፈቅዶላቸዋል ነገር ግን የእርሱን ፍቅርና ደህንነት ለመቀበል አሻፈረኝ የሚሉ ወይም በእምነት ወደ እርሱ መቅረብ ያቃታቸው ሰዎች ይፈረድባቸውና ለዘላለም ወደ እሳት ባህር ይጣላሉ::

ስለዚህ በዚህ ክፉ ቀንና ዘመን ከፈተናና ከኑፋቄ ኩነኔ ጸድቶ ለመኖር ሁላችንም እውነተኛውን ወንጌል መከተል ይገባናል የዲያብሎስን ውሸቶችና የዚህን አለም ርኩሰት ማሸነፍ የምንችለው የእውነትን ቃል በመቀበል ከሙሉ ልባችን በማመንና ከውሃና ከመንፈስ ዳግም እንደተወለድን በመመስከር ብቻ ነው ኢየሱስ እንደተናገረውም *«እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐንስ 8:31-32)* አለምን ማሸነፍ ከሐጢያቶች ከውኾንብርና በውስጣችን ካለው ባዶነት ነጻ መውጣት የምንችለው «ከውሃና ከመንፈስ» ዳግም ስንወለድ ብቻ ነው::

እውነተኛው ብርሃን ሲበራ ጨለማ ይገፈፋል ብርሃንና ጨለማ አብረው ሊኖሩ አይችሉም ይህ ዘመን ምንም ያህል

በዚህ ጨለማ ውስጥ ጠልቶ ቢቀበርም እናንተም ምንም ያህል ውኸርንብር ውስጥ ብትሆኑና ባዶ ብትሆኑ ልባችሁን «ዳግም ለምትወለዱበት ለውሃውና ለመንፈሱ ወንጌል» በሰጣችሁበት ቅጽበት ልባችሁ በእውነት ብርሃን ይሞላል *«በክርስቶስ ፊት የእግዚአብሔርን የክብሩን እውቀት ብርሃን እንዲሰጥ በልባችን ውስጥ የበራ በጨለማ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነውና።» (2ኛ ቆሮንቶስ 4:6)*

## ወደ «ውኃውና መንፈሱ ወንጌል» እንመለስ

ቀደም ባለውና «በውኑ ከውሃውና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም ተወልዳችኋልን?» በሚለው መጽሐፌ ውስጥ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፈውን ወንጌል ተናግሬአለሁ የእርሱ ተከታይ የሆነው ይህ መጽሐፍ ዛሬ የተስፋፋትን የሐሰት ወንጌሎች ከእውነተኛው ጋር በማነጻጸር ላይ የሚያተኩር ነው ይህንን በማድረግ በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ውስጥ ያለውን «የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል» እውነት ጥልቅ ምልከታ በማቅረብ እውነተኛ ክርስቲያኖችን ከነገረ መለኮት ጽንሰ ሐሳቦች ሕጸጾች ለመመለስ ተስፋ አድርጋለሁ የእግዚአብሄርን እውነት የሚቃወሙትን ሐሰተኛ ወንጌልና የኑፋቄ ትምህርቶች ታሪካዊ ስረ መሰረቶችና ጭብጥ በማቅረብም የወንጌልን እውነት በግልጽ ወደ መረዳት እንድትመጡ እመራችኋለሁ ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ።

ውድ የሆኑት አጋር የእግዚአብሄር አገልጋዮችና እኔ ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል እስከ አለም ዳርቻ ድረስ መስበክ እንፈልጋለን ስለዚህ ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ከተለያዩ ማዕዘኖች የሚመለከቱ ተጨማሪ መንፈሳዊ

መጽሐፎችን በእንግሊዝኛ ቋንቋ እናሳትማለን::

የሐጢያት ደህንነት ቀድሞውኑም ተጠናቋል የሰማይ ደጅም ተከፍቷል የእውነትን ቃል የሚቀበል በመጽሐፍ ቅዱስ የሚያረጋግጠውና «በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል» የሚያምን ሰው ራሱን ከሐሰተኛው የዲያብሎስ ወንጌል መጠበቅና ከሐጢያቶቹ ሁሉ መዳን ይችላል የእግዚአብሄርን በረከቶች መቀበልና መንግስተ ሰማይ መግባትም ይችላል በሙሴ የተመሩት የእስራኤል ሕዝቦች ከግብጽ ባርነት ነጻ እንደወጡ ሁሉ እናንተም እነዚህን ሁለት መጽሐፎች እንድታነቡ በደህንነት ቃሎችም እምነት እንዲኖራችሁና የእግዚአብሄር ልጆች እንድትሆኑ ተስፋዬና ጸሎቴ ነው::

ጌታ *«እናንተ የተጠማችሁ ሁሉ ወደ ውኃ ኑ ገንዘብም ሌላችሁ ኑና ግዙ ብሉም ኑ ያለ ገንዘብም ያለ ዋጋም ወይን ጠጅና ወተት ግዙ» (ኢሳይያስ 55:1)* በማለት ከልቡ እየጠራን ነው ሁላችንም «ወደ ውሃውና መንፈሱ ወንጌል» እንመለስ! ከሚመጣው የእግዚአብሄር ፍርድ አምልጠን ወደ ጸጋውና ግሩም ባርኮቶች ወዳሉበት ወደ እርሱ አለም እንግባ! ✉

# ማውጫ

1. እውነተኛው ዳግም የመወለድ ወንጌል ትርጉም
(ዮሐንስ 3:1-6) ---------------------------------------------- 20

2. በክርስትና ውስጥ ያሉ አስመሳይ ክርስቲያኖችና
መናፍቃን (ኢሳይያስ 28:13-14) ------------------------------- 72

3. እውነተኛው መንፈሳዊ ግርዘት
(ዘፀዓት 12:43-49) ------------------------------------------ 126

4. እውነተኛና ትክክለኛ የሐጢያት ኑዛዜ
እንዴት እንደሚደረግ
(1ኛ ዮሐንስ 1:9) --------------------------------------------- 186

5. አስቀድሞ በመወሰንና በመለኮት ምርጫ ፅንሰ ሐሳብ
ውስጥ ያለው ስህተት
(ሮሜ 8:28-30) ---------------------------------------------- 200

6. የተለወጠው ክህነት
(ዕብራውያን 7:1-28) ---------------------------------------- 256

7. የየኢየሱስ ጥምቀት ለቤዛነት አስፈላጊ የሆነ ሒደት ነው
(ማቴዎስ 3:13-17) ------------------------------------------ 312

8. የአብን ፈቃድ በእምነት እንፈፅም
(ማቴዎስ 7:21-23) ------------------------------------------ 352

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፓውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# ስብከት 1

# እውነተኛው ዳግም የመወለድ ወንጌል ትርጉም

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ..ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡



«ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና፡፡» (ገላትያ 3፡27)

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡

# እውነተኛው ዳግም የመወለድ ወንጌል ትርጉም

**« ዮሐንስ 3:1-6 »**

**«ከፈሪሳውያንም ወገን የአይሁድ አለቃ የሆነ ኒቆዲሞስ የሚባል አንድ ሰው ነበረ እርሱም በሌሊት ወደ ኢየሱስ መጥቶ:- መምህር ሆይ! እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ከሆነ በቀር አንተ የምታደርጋቸውን እነዚህን ምልክቶች ሊያደርግ የሚችል የለምና መምህር ሆነህ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደመጣህ እናውቃለን አለው:: ኢየሱስም መልሶ:- እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በስተቀር የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም አለው:: ኒቆዲሞስም ሰው ከሽመገለ በኋላ እንዴት ዳግም ሊወለድ ይችላል» ሁለተኛ ወደ እናቱ ማኅፀን ገብቶ ይወለድ ዘንድ ይችላልን? አለው:: ኢየሱስም መለሰ፣ እንዲህ ሲል:- እውነት እውነት እልሃለሁ፣ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም:: ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው፣ ከመንፈስ የተወለደም መንፈስ ነው::»**

## በመፅሐፍ ቅዱስ መሠረት እንደገና የመወለድ ትርጉም ምንድን ነው?

በዚህ ምድር ላይ በኢየሱስ በማመን እንደገና ለመወለድ የሚፈልጉ ብዙዎች አሉ:: ሆኖም ግን በመጀመሪያ ልነግራችሁ የምፈልገው ነገር ቢኖር ዳግም መወለድ የእኛ ውሳኔ አይደለም

በሌላ አነጋገር ዳግም ውልደት በምንሰራቸው ሥራዎች አማካይነት የሚመጣ ነገር አይደለም::

*ዳግም መወለድ ከስጋዊ ስሜትና ለውጥ ጋር የተዛመደ ነውን?*

*አይደለም:: ዳግም መወለድ ተዛምዶው ከመንፈሳዊ ለውጥ ጋር ነው:: ይህም ኃጢአተኛ ቅዱስ ሆኖ ሲወለድ እንደማለት ነው::*

ብዙ ክርስትያኖችም ይህን አልተረዱትም:: አንዳንዶች ብዙ ቤተ ክርስትያናትን ስለገነቡ፣ አንዳንዶች ደግሞ እንደ ክርስቶ መልዕክተኞች በመሆን በመስበካቸው፣ ሌሎችም እንዲሁ በዓለም ላይ ያልተደረሱ ቦታዎች ድረስ በመሄድ ስለ ኢየሱስ በመናገራቸው፣ እንዲሁም አንዳንዶች ሳያገቡና ለእነሱ የእግዚአብሔር ስራ የሚመስላቸውን እየሰሩ ለረዥም ጊዜ በመቆየታቸው ዳግም መወለድ የሚችሉ ይመስላቸዋል::

ይህ ብቻ አይደለም ለቤተክርስቲያናቸው በርካታ ገንዘብ የሚለግሱ ሰዎችም አሉ ምናልባትም በየቀኑ የቤተክርስቲያናቸውን ወለል የሚያፀዱም ይኖራሉ በአጠቃላይ ጊዜያቸውንና ንብረታቸውን ለቤተክርስቲያን ያውላሉ እነዚህ ጥረቶቻቸው ሁሉ የሕይወትን አክሊል እንደሚያስገኝላቸው ያምናሉ እግዚአብሄር ጥረቶቻቸውን ተቀብሎላቸው ዳግም ይወለዱ ዘንድ እንዲፈቅድላቸው ተስፋ ያደርጋሉ::

ቁም ነገሩ ዳግም ለመወለድ የሚሹና ራሳቸውን የሰጡ

በርካታ ሰዎች መሆናቸው ነው እነዚህ በየቦታው ይገኛሉ አንድ ቀን እግዚአብሄር እንደሚባርካቸውና ዳግም ይወለዱ ዘንድ እንደሚፈቅድላቸው ተስፋ በማድረግ ተግተው ይሰራሉ እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች በተለያዩ የሐይማኖት ተቋማቶች ሴሚናሪዎችና ሳናቶሪዬሞች ውስጥ ይገኛሉ እነርሱ ዳግም ስለመወለድ እውነቱን አለማወቃቸው የሚሳዝን ነው::

ስለዚህ ዳግም ለመወለድ የሚያስፈልገውን መሠረት እየገነቡ መሆናቸውን በማመንና «እኔም እንደ ቄስ ዌዝሊ አንድ ቀን ዳግም እወለዳለሁ» ብለው በማሰብ ጥረቶቻቸውን ሁሉ በእነዚህ ስራዎች ላይ ያከማቻሉ ዮሐንስ 3፡8ን ካነበቡ በኋላ ጥቅሱ የዳግም ውልደት በረከት ከየት እንደሚመጣ ወይም ወዴት እንደሚሄድ ማንም ሊያውቅ አይችልም የሚል ነው በማለት ይተረጉሙታል::

ከዚህም የተነሳ ኢየሱስ አንድ ቀን ዳግም እንድወለድ ይረዳኛል በሚል ተስፋ በጥንካሬ ይሰራሉ:: አንዳንዶችም እንደሚከተለው ያስባሉ፡- ብዙዎች «በዚህ ሁኔታ ሙከራዬን ከቀጠልሁ አንድ ቀን ኢየሱስ ዳግም እንድወለድ ይፈቅድልኛል ዳግም መወለዴን እንኳን ሳላውቅ ዳግም እወለዳለሁ አንድ ቀን ጠዋት ዳግም ተወልጄ ከእንቅልፌ እነቃለሁ ሰማይ እንደምገባም አውቃለሁ» ብለው ያስባሉ እንደ እነዚህ ያሉ ተስፋዎችና እምነት ምንኛ ፍሬ ቢስ ናቸው! በዚህ መንገድ መቼም ቢሆን ዳግም ልንወለድ አንችልም! ከሲጋራና ከመጠጥ ስለተላቀቅን ወይም ደግሞ ቤተ ክርስትያን በየዕለቱ ስለሄድን ብቻ ዳግም ልንወለድ አንችልም:: ኢየሱስ እንዳለው ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት «ከውኃና ከመንፈስ መወለድ አለብን::» ውኃውና መንፈሱ ደግሞ ዳግም ለመወለድ የእግዚአብሔር ብቸኞቹ ቅድመ ሁናቴዎች ናቸው::

ማንም ሰው በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ዳግም

ስለመወለድ የማያምን ከሆነ ቅዱስ ለመሆን የሚያደርገው ጥረት በሙሉ አደጋ ውስጥ ይሆናል፡፡ በስጦታ፣ በአስራት ወይም ደግሞ በአገልግሎት ማንም ቢሆን ዳግም ሊወለድ አይችልም፡፡ ምናልባትም ዳግም የተወለደውንና ያልተወለደውን የሚያውቀው እግዚአብሔር ብቻ ስለሆነ እርሱ ዳግም መወለድ ወይም አለመወለዴን አላውቅም ብሎ ያስብ ይሆናል፡፡

ይህን ማሰቡ ለርሱ የተወሰነ ምቾት እንዲሰማው ሊያደርገው ይችል ይሆናል ዳግም መወለዳችን ምናልባት በአካል አይታወቀን ይሆናል ነገር ግን በመንፈሳዊ ሕይወታችን በሚገባ ይታወቀናል በእውነት ዳግም የተወለዱት ምዕመናን በእግዚአብሄር ቃል በውሃው በደሙና በመንፈሱ ቃሎች እንደገና የተወለዱት ናቸው ነገር ግን ዳግመኛ ያልተወለዱ ይህንን እውነት ሊያስተውሉት አይችሉም ኒቆዲሞስም አልቻለም፡፡

ስለሆነም፣ በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ያለውን የምህረት ወንጌል፣ የእውነት ቃል ማድመጥ አለብን፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል የምናደምጥና የምናማር ከሆነን፣ እውነታውን ከዚያው እናገኘዋለን፡፡ ስለሆነም በጥንቃቄ ለማድመጥ አእምሮኣችንን ክፍት ማድረጋችን በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

*«ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል፤ ድምፁንም ትሰማለህ፣ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም፤ ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲህ ነው፡፡» (ዮሐንስ 3:8)*

ዳግም ያልተወለደ ሰው ይህን አንቀጽ በሚያነብበት ወቅት፣ «አሃ! እኔ ዳግም በምወለድበት ጊዜ ያንን ማወቅ እንደማልችል ኢየሱስ ተናግሮዋል!» በማለት ያስባሉ ይህ ሃሳብም ምቾት ይሰጣቸዋል፡፡ ይህ ግን እውነት አይደለም፡፡ ምናልባትም እኛ ነፋሱ ከየት እንደሚመጣና ወዴትም እንደሚሄድ አናውቅ ይሆናል እግዚአብሔር ግን ሁሉን ያውቃል፡፡

ዳግም ውልደትን ካገኙት ሰዎች መካከልም እንዲሁ ይህን

በመጀመሪያ ላይ የማይረዱት አሉ። ይህ መረዳት የሚቻል ነገር። እንዲሁም በዚህ አይነቱ ሰው ልብ ውስጥ ወንጌሉ አለ ይህም ወንጌል በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ምህረትን የማግኛው ወንጌል ነው።

ይህ ዳግም ውልደትን ያገኙ ሰዎች ምስክርነት ነው። እርሱ ወንጌልን የሚሰማው፡- «አ! ኃጢኣት የለብኝም። ስለሆነም ድኜ ዳግም ውልደትን አግኝቻለሁ።» ከዚያም የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሲጠብቅና ሲቀበል፣ እርሱ ቅዱስ የእግዚአብሔር ልጅ ይሆናል።

ምናልባትም አንድ ሰው «ዳግም ተወልደሃልን?» ተብሎ ሲጠየቅ «አልተወለድኩም።» «ድነሃልን?» ሲባል ደግሞ «አዎን፣ መዳኔን አምናለሁ።» ብሎ የሚመልስ ይኖራል። ሆኖም ግን ይህ እርስ በርሱ የሚቃረን አባባል ነው አይደለምን? ምናልባትም እንደዚህ ያመነው አንድ ሰው ዳግም ሲወለድ በሥጋውም መለወጥ ይኖርበታል ብሎ ስላሰበ ነው።

እንደዚህ ያሉ ሰዎች ዳግም መወለድን ስር ነቀላዊ የሆነ የአኗኗር ለውጥ እንደሆነ አድርገው ይመለከቱታል እውነቱ ግን እነዚህ ሰዎች ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን ወንጌል ያልተረዱ መሆናቸው ነው።

ዳግም የመወለድን ትርጉም ያልተረዱ ብዙ ሰዎች አሉ። ይህ በጣም አሳዛኝ ነው በዚህ መታለል ውስጥ እየተንቀሳቀሱ ያሉት ተራ ምዕመናን ብቻ ሳይሆኑ አብዛኞቹ የቤተክርስቲያን መሪዎችም ጭምር ናቸው እኛ ዳግም የተወለድን ለእነዚህ ሰዎች ከልባችን እናለቅስላቸዋለን።

እኛ ይህን ያህል ካዘንን በሰማይ ያለው ኢየሱስ ምን ያህል ሕመም ይሰማው ይሆን? ሁላችንም በኢየሱስ የጥምቀትና የመስቀሉ ላይ ደም ወንጌል በማመን እንደገና እንወለድ።

ዳግም መወለድ ማለትና መዳን ማለት ተመሳሳይ ናቸው።

ሆኖም ግን ይህን እውነታ የማያውቁ ብዙ ሰዎች አሉ ዳግም መወለድ ማለት በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ያለው ሐጢያት ከውሃና ከመንፈስ በሆነው ወንጌል በማመን ታጥቦዋል ማለት ነው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ በከፈለው መስዋዕትነት በማመን ፃድቅ መሆን ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው ዳግም ከመወለዱ በፊት ሙሉ በሙሉ ኃጢኣተኛ ሲሆን ከተወለደ በኋላ ግን ኃጢኣት የሌለበት አዲስ ሰው ነው፡፡ በምህረቱ ወንጌል በማመንም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኗል ማለት ነው፡፡

ዳግም መወለድ ማለት የኢየሱስን ጥምቀት መልበስ፣ በመስቀል ላይም አብሮት መሠቀልና በትንሳኤውም አብሮ መነሳት ማለት ነው፡፡ እንዲሁም ደግም ይህ ማለት አንድ ሰው በጥምቀቱ ቃሎችና በኢየሱስ መስቀል አማካይነት ፀድቋል ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው ከእናቱ ማህፀን ሲወጣ ጀምሮ ኃጢኣተኛ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሰው ከውሃና ከመንፈስ የመወለድን እውነተኛ ወንጌል ሲሰማ ያን ጊዜ ዳግም ይወለድና ይፀድቃል፡፡

እንደዚህ ያለ ሰው ከውጪ ሲታይ የተለየ ሰው ላይመስል ይችላል በውስጥ በመንፈሱ ግን ዳግም ተወልዶዋል ዳግም መወለድ ማለት ይህ ነው ይህንን እውነት የሚውቁት በጣም ጥቂቶች ናቸው ከአስር ሺህ አንድ እንክን አይሆኑም እውነተኛ ውን የዳግም ውልደት ትርጉም የተረዱት በጣም ጥቂቶች ስለመሆናቸው ከእኔ ጋር ትስማማላችሁን?

ከውሃና ከመንፈስ የሆነውን ወንጌል አምነው ዳግም የተወለዱ በተጨባጭ ዳግም የተወለዱን ከተራ ክርስቲያኖች መለየት ይችላሉ፡፡

# ነፋሱን የሚቆጣጠረው ኢየሱስ ነው

*ማን እንደዳነ የሚያውቀው ማነው?*

*ዳግም የተወለዱት ብቻ ናቸው፡፡*

*«ነፋስ ወደሚወደው ይነፍሳል ድምፁንም ትሰማለህ ነገር ግን ከወዴት እንደ መጣ ወዴትም እንዲሄድ አታውቅም ከመንፈስ የተወለደ ሁሉ እንዲህ ነው፡፡»* ኢየሱስ ሲናገር የነበረው ዳግም ውልደትን ስላላገኙ ሰዎች ነው፡፡ ዳግም የተወለዱት ስለ ዳግም ውልደት ያውቃሉ ኒቆዲሞስ ግን ይህን አያውቅም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ዳግም የተወለዱትን ያውቃል ዳግም የተወለዱትም እንዲሁ ያውቃሉ፡፡

ሆኖም ግን አነዚያ ዳግም ውልደትን ያላገኙት ልክ ነፋሱ ከየት እንደመጣና ወዴት እንደሚሄድ እንደማያውቁት ሁሉ ዳግም ውልደትንም እንዴት ለማግኘት እንደሚችሉ አያውቁም፡፡

ይህን ለመረዳት ችላችኋልን? ነፋሱን የሚያንቀሳቅሰው ማነው? እግዚአብሔር ነው፡፡ ነፋሱንስ የፈጠረው ማነው? አሁንም እግዚአብሔር ነው፡፡ የመሬትን የአየር ፀባይና የነፋስና የዝናብን መለዋወጥ የሚቆጣጠረውስ ማነው? ሕይወት ላላቸው ነገሮች በሙለ እስትንፋስን የሚሰጥስ ማነው? ባጠቃላይም በዚህ ምድር ላይ ያሉ ነገሮችም ሙሉ አድርጎ የፈጠራቸው ማነው? ይህን ሁሉ ያዘጋጀው ኢየሱስ ነው፡፡ ኢየሱስም እግዚአብሔር ነው፡፡

የውኃውን የደሙንና የመንፈሱን የወንጌል ቃል ካላወቅን

ዳግም ውልደትን ልናገኝ አንችልም እንዲሁም ደግሞ ለሌሎች መንፈሳዊነትን ለመስበክ ያዳግተናል፡፡ ኢየሱስ አንድ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ዳግም ውልደትን ሊያገኝ እንደማይችል አስተምሮናል፡፡

እኛ ሁላችንም በኃያሉ የውኃና የመንፈስ ወንጌል ማመን አለብን ይህም ዳግም ውልደትን እናገኝ ዘንድ ያስችለናል፡፡ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል በሚያምኑት ሰዎች ልብ ውስጥ መንፈሱ ገብቶ እዚያው ይቆያል፡፡

ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ኃጢኣት በሙሉ ለማስወገድ ሲል በዮርዳኖስ ተጠምቆ በመስቀል ላይ በመድማት ለኛ ኃጢኣት እርሱ ከፍሎልናል ዳግም እንድንወለድ በሚያደርገን ብርቱ የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ማመን አለብን ከውሃና ከመንፈስ በሆነው ወንጌል በሚያምኑ ሰዎች ልቡና ውስጥ መንፈሱ ይገባል አብሮዋቸውም ይኖራል ይህ ዳግም የመወለጃ ድነት ነው በኢየሱስ ጥምቀትና የመስቀሉ ላይ ደም ኃጢኣት መስተሰረዩን ስናምን ይህ ዳግም ውልደት ነው፡፡

በዘፍጥረት 1:2 ላይ እንደተፃፈውም፡- *«ምድርም ባዶ ነበረች አንዳችም አልነበረባትም፡፡ ጨለማም በጥልቁ ላይ ነበር የእግዚአብሔርም መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ ነበር፡፡»* የእግዚአብሔር መንፈስ በውኃ ላይ ሰፍፎ እንደነበረ ተፅፏል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ከምድር ውጭ ይንቀሳቀስ ነበር፡፡

ይህም ማለት መንፈስ ወደ ኃጢኣተኞች ልብ ሊገባ አይችልም ማለት ነው፡፡ ዳግም ያልተወለደ ሰው ልብ በሁከት በኃጢኣት ጭለማም የተሞላ ነው፡፡ እግዚአብሔር «ብርሃን ይሁን አለ!» ከዚያም ብርሃን ሆነ ስለዚህ የእግዚአብሄር መንፈስ እንደዚህ ባለው ሰው ልብ ውስጥ ሊኖር አይችልም፡፡

እግዚአብሄር የሐጢያተኞችን ልብ ለማብራት የወንጌሉን ብርሃን ላከ እግዚአብሔር «ብርሃን ይሁን አለ» ብርሃንም ሆነ፡፡

የእግዚአብሄር መንፈስ በሰዎች ልብ ውስጥ ማደር የሚችለው በዚህ ጊዜ ብቻ ነው::

ስለዚህ የእግዚአብሄር መንፈስ የሚበራው ከውሃና ከመንፈስ የሆነውን ወንጌል አምነው በተወለዱት ልቦች ውስጥ ነው «ዳግም የመወለዳቸው» ትርጉም ይህ ነው በልቦቻቸው ዳግም የተወለዱት ከውሃና ከመንፈስ የሆኑትን የደህንነት ቃሎች አድምጠው ስላመኑ ነው!

አንድ ሰው ዳግም ሊወለድ የሚችለው እንዴት ነው? ኢየሱስ ለፈሪሳዊው ኒቆዲሞስ ሲያስረዳ፡- *«አንድ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም::»* ብሎ አስረድቶታል:: ኒቆዲሞስም ሲመልስ «እኛ ከውኃና ከመንፈስ የምንወለደው እንዴት ነው? ዳግምስ ወደ እናታችን ማኅፀን በመግባት እንደገና እንወለዳለንን?» ብሎ ጠየቀው በእርግጥም እርሱ ይህን የተረዳው ቃል በቃል ሲሆን የሰው ልጅ በትክክል እንዴት ዳግም ሊወለድ እንደሚችል አልተገነዘበም::

ኢየሱስ እንዲህ አለው «አንተ መምህር ሆነህ ሳለህ ይህ ምን ማለት እንደሆነ አታውቅምን?» ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ አንድ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሄር መንግስት እንደማይገባ እንደማያየውም ነገረው ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ የነገረው ዳግም የመወለድን እውነት ነበር::

ዳግም ውልደትን ሳያገኙ በኢየሱስ የሚያምኑ መኖራቸው እውነት ነው ብዙ ክርስቲያኖች እንደ ኒቆዲሞስ ዳግም ያልተወለዱ ናቸው::

ኒቆዲሞስ ልክ እንደዛሬዎቹ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሁሉ በዚያን ወቅት የእስራኤላውያን መንፈሳዊ መሪ ነበር ልክ በዘመኑ ቋንቋ ከአንድ አገር የምክር ቤት አባል ጋር የሚነፃፀር ነበር በሐይማኖታዊ መስፈርቶችም የዕብራውያን መምህር ነበር

እርሱ የአይሁዶች ሐይማኖታዊ መሪ ነበር የተዋጣለት ሊቀ ሊቃውንትም ነበር፡፡

በዚያን ዘመን በእስራኤል ዛሬ ካሉት ትምህርት ቤቶች ጋር የሚወዳደር ተቋም ስላልነበር ሰዎች ሁሉ «ከምሁራኑ» ትምህርትን ለመቅሰም ወደ ቤተ መቅደስ ወይም ምኩራቦች ይሄዱ ነበር የሕዝቡ አስተማሪዎች እነዚያ ምሁራኖች ነበሩ ልክ እንደ ዛሬው ያን ጊዜም ብዙ የሐሰት አስተማሪዎች ነበሩ ራሳቸው ዳግም ሳይወለዱ ሰዎችን ያስተምሩ ነበር፡፡

በአሁኑም ጊዜ ዳግም ውልደትን ያላገኙ ብዙ የኃይማኖት መሪዎችፐ የቤተክርስቲያን አስተዳዳሪዎችፐ ሰባኪዎችና ዲያቆናት አሉ ልክ እንደ ኒቆዲሞስም የዳግም ውልደትን ትርጉም አያውቁትም ብዙዎች ዳግም ለመወለድ ሁለተኛ ጊዜ ወደ እናታችን ማህፀን መግባት እንዳለብን ያስባሉ፡፡

ዳግም መወለድ እንዳለባቸው ቢያውቁም እንዴት ዳግም መወለድ እንደሚችሉ ግን አያውቁም፡፡

ከድንቁርናቸው የተነሳ በእጃቸው በመንካት እንዲያው በከንቱ የዝሆንን ማንነት ለመለየት እንደሚፍጨረጨር አይነ ስውር መመሪያቸው በግል ስሜቶቻቸውና ተሞክሮዎቻቸው ላይ የተመሠረተ ነው በቤተክርስቲያን ውስጥ ስለ አለማዊ እሴቶች ይሰብካሉ ብዙ ታማኝ ሰዎች ለዚህ በመገዛታቸው ዳግም ከመወለድ ተገልለዋል፡፡

ዳግም መወለድ ከምንሰራቸው በጎ ምግባራት ጋር የሚያገናኘው ምንም ነገር የለም እኛ ዳግም ውልደትን ልናገኝ የምንችለው በውሃው፣ በደሙና በመንፈሱ ወንጌል ላይ ባለን እምነት ብቻ ነው ከኃጢኝተኛነት ወደ ጻድቅነት ሊቀይረን የሚችለው ይህ የእግዚአብሔር ወንጌል ብቻ ነው፡፡

ኢየሱስ እንዲህ ሲል ተናግሯል- «ስለ ምድራዊ ነገር ተናግሬ ያላመናችሁኝ በሰማይ ስላለ ነገር ብነግራችሁ እንዴት

ታምኑኛላችሁ?» ኢየሱስ በእርሱ ጥምቀት አማካይነት ለሐጢያቶቻችን ሁሉ የሆነው ሥርየት የመጠናቀቁን እውነት በነገራቸው ጊዜ አላመኑትም እነርሱ ያላመኑት ምን ነበር? ደህንነታቸው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ሞቱ መረጋገጡን አላመኑም ስለ «ሰማያዊ ነገሮች» ቢነግራቸው ሰዎች እንደማያምኑት በተናገረ ጊዜ ይህንን ማለቱ ነበር፡፡

ኢየሱስ እኛን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ለማንፃት በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ በመስቀል ላይም ሞተ ከዚያም ሐጢያተኞች ዳግም ይወለዱ ዘንድ መንገዱን ለማዘጋጀት ከሙታን ተነሳ፡፡

ስለሆነም ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ ሲያስረዳ ከብሉይ ኪዳን ጠቅሶለታል *«ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም፣ እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲያው ወዷልና» (ዮሐንስ 3:13-15)* ሙሴም በምድረ በዳ እባቡን እንደ ሰቀለ ሁሉ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ ይፈልጋል፡፡

ኢየሱስ *«ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲያ ወዷልና»* ሲል ምን ማለቱ ነው? እርሱ ይህን ጥቅስ ከብሉይ ኪዳን የወሰደው የእርሱ ጥምቀትና ደም እንዴት የሰው ልጅን ከኃጢአት ቀንበር ነፃ እንደሚያወጣው ለማሳየት ነው፡፡

ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከመሞቱና ከመንጠልጠሉ በፊት አስቀድሞ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅ የአለምን ሐጢያት መውሰድ ነበረበት ኢየሱስ ሐጢያት አልባ ስለሆነ በመስቀል

ላይ ሊሰቀል አይችልም እርሱ በመስቀል ላይ እንዲሰቀል በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቅና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ መውሰድ ነበረበት::

ሐጢያተኞችን በሙሉ ከኩነኔ ማዳን የሚችለው ሐጢያቶቻችንን በራሱ ላይ ተሸክሞ ለእነዚያ ሐጢያቶች ዋጋ ሲከፍል ብቻ ነው ኢየሱስ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም በመወለድ የሚገኘውን ደህንነት ሰጥቶናል::

ስለዚህ እነዚያ ኢየሱስ አዳኛቸው መሆኑን የሚያምኑ ሰዎች የጥምቀቱን ልብስ ይለብሳሉ ከእርሱም ጋር ይሞታሉ አብረውትም ዳግም ይወለዳሉ ኒቆዲሞስም ይህን እውነታ የተረዳው በኋላ ላይ ነበር::

## እባቡ እንደተሰቀለ ሁሉ

*ኢየሱስ የተሰቀለው ለምንድን ነው?*

*በጥምቀቱ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ ስለወሰደ ነው::*

ሙሴ በምድረ በዳ ከነሐስ የተሰራውን እባብ የሰቀለበትን ታሪክ ታውቃላችሁን? ታሪኩ በዘኁልቁ 21 ላይ በዝርዝር ይገኛ ል ቃሉ እስራኤሎች ከግብፅ ከወጡ በኋላ በጣም ተስፋ ቆርጠው ስለነበር በሙሴ ላይ እንዳንጎራጎሩ ይናገራል::

ከዚህ የተነሳ በሕዝቡ መካከል ተናዳፊ እባቦችን ሰደደ እነርሱም በየድንኳኖቻቸው ገብተው እየነደፉ ገደሉዋቸው ከተነደፉ በኋላ አካላቸው ማበጥ በመጀመሩ ብዙዎች ሞቱ::

ሕዝቡ መሞት ሲጀምር መሪያቸው ሙሴ ወደ እግዚአብሔር ፀለየ «እግዚአብሔር ሆይ! እባክህ አድነን» እግዚአብሔርም ከነሐስ የእባብ ቅርፅ ሰርቶ በእንጨት ላይ እንዲሰቅለው አዘዘው ማንም ወደተሰቀለው እባብ የተመለከተ ሁሉ እንደሚድን ነገረው ለሕዝቡም የእግዚአብሄርን ቃሎች አወጀ::

በእርሱ ቃሎች አምኖ ወደ ናሱ እባብ የተመለከተ ሁሉ ይፈወስ ነበር ልክ እንደዚሁ እኛም በዲያብሎስ ከተነደፍንበት መርዝ መፈወስ ይኖርብናል የእስራኤል ልጆች ሙሴን አድምጠው በእንጨት ላይ የተሰቀለውን የናሱን እባብ በመመልከታቸው ተፈወሱ::

እባቡ በእንጨት ላይ የመሰቀሉ ምስጢር በሰው ዘር ሐጢያቶች ሁሉ የመጣው ኩነኔ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ አማካይነት በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ መጫኑን የሚገልጥ ነው እርሱ በአለም ላይ ያሉትን ሐጢያተኞች ሁሉ ቅጣት ለመክፈል ኩነኔውን በራሱ ላይ ተሸከመ በዚህም የሐጢያቶቻችንን ቅጣት በሙሉ አስወገደ::

ኢየሱስ ክርስቶስ «ከእባቡ መርዝ» ከሰይጣን ፈተናዎች የተነሳ ሊሞቱ የተፈረደባቸውን ሰዎች ሁሉ ለማዳን ወደዚህ አለም መጣ የሐጢያቶቻችንን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል በእርሱ የሚያምኑትንም ለማዳን ከመነሳቱ በፊት መጠመቅና በመስቀል ላይ መሞት ነበረበት::

ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው እኛን ወደ ገሃነም እሳት ልንጣል የነበርነውን ሰዎች ለማዳን ነው ስለሆነም እኛን ለማዳን ሲል በጥምቀቱ ኃጢአታችንን በሙሉ ወደ ራሱ ማስተላለፍና በመስቀል ላይም መሰቀል ነበረበት እንዲሁም ደግሞ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ ይድኑ ዘንድ በትንሳኤው አንፅቷቸዋል::

በብሉይ ኪዳን ዘመን የነበሩት እስራኤሎች በአላማ ላይ

የተሰቀለውን አይተው እንደዳኑ ሁሉ ዛሬም በኢየሱስ የሚያምኑና እርሱ በጥምቀቱና በደሙ አማካይነት የሐጢያቶቻቸውን ዋጋ እንደከፈለላቸው እምነቱ ያላቸው ሁሉ ድነው ዳግም ሊወለዱ ይችላሉ፡፡

ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ በዮርዳኖስ በመጠመቁ፣ በመስቀል ላይ በመሞቱና ከሙታን በመነሳቱ ለአለም ሐጢያቶች በሙሉ በቂ ክፍያ ከፍሎዋል አሁን በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ በምህረቱ አማካይነት በደህንነት በረከት ሊባረኩ ይችላሉ *«ከሰማይም ከወረደው በቀር ወደ ሰማይ የወጣ ማንም የለም እርሱም በሰማይ የሚኖረው የሰው ልጅ ነው» (ዮሐንስ 3:13)* ኢየሱስ ለሐጢያቶቻችን ካሳ ለመክፈል ተጠመቀ በመስቀል ላይም ደሙን አፈሰሰ የሰማይንም ደጆች ከፈተልን ኢየሱስ በዮሐንስ 14:6 ላይ እንዲህ ብሏል:- *«እኔ መንገድም እውነትም ሕይወትም ነኝ፡፡ በእኔ በቀር ማንም ወደ አብ ሊመጣ አይችልም፡፡»*

ኢየሱስ የተጠመቀውና በመስቀል ላይ የተሰቀለው ለእኛ ለሰው ልጆች የመንግስተ ሰማያትን በር ለመክፈት ስለሆነ ማንም በእርሱ ደህንነት የሚያምን ሁሉ ይድናል ኢየሱስ ለኃጢአታችን አንዴ ከፍሎልናል ስለሆነም ማንም በውኃው በደሙና በመንፈሱ እውነት የሚያምን ሁሉ መንግስተ ሰማይ ይገባል፡፡


ኢየሱስ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል አድኖናል ዳግም መወለድ የሚመጣው በኢየሱስ ጥምቀትና ደም እንደዚሁም እርሱ አምላክ የመሆኑን እውነት በማመን ነው *«ሙሴም በምድረ በዳ እባብን እንደሰቀለ እንዲሁ በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ» (ዮሐንስ 3:14)* ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ኢየሱስ መሰቀል ያስፈለገው ለምንድን ነው? እንደ እኛ እርሱም ኃጢአትን ስለሰራ ነውን?

እርሱ እንደ እኛ ደካማ ነበርን? እርሱም እንደ እኛ ያልተሟላ ነበርን? አይደለም እርሱ እንደዚያ አልነበረም፡፡

ታዲያ ሊሰቀል የተፈረደበት ለምንድን ነው? ይህ የሆነው እኛን ለማዳንና ለሐጢያቶቻችን ሁሉ ካሳ ለመክፈል ነው እርሱ የተጠመቀውና በመስቀል ላይም ደሙን ያፈሰሰው እኛን ከኃጢአቶቻችን ሁሉ ለማዳን ነው፡፡

የደህንነትና ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድ እውነት ይህ ነው ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀሉ ላይ ለሚያምኑት ሁሉ አዲስ ህይወትን ሰጥቷል ይህም ለኃጢአቶቻችን ማካካሻ ነው፡፡

## የውኃውና የመንፈሱ ትርጉም




መፅሐፍ ቅዱስ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ባለው ደሙ ባመንን ጊዜ ዳግም ውልደትን እንዳገኘን ይነግረናል የእግዚአብሔር ልጆች መሆንና ዳግም ውልደትን ማግኘት የሚቻለው የሐጢያቶቻችን ካሳ በሆነው በእግዚአብሔር ቃል፣ በውኃው፣ በደሙና በመንፈሱ ወንጌል ብቻ ነው፡፡

በመፅሐፍ ቅዱስ መሰረትም «ውኃ» የሚወክለው የኢየሱስን ጥምቀት ነው (1ኛ ጴጥሮስ 3:21) እንዲሁም ደግሞ

«መንፈስ» ማለት ኢየሱስ እግዚአብሔር ነው ማለት ነው ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ አማካይነት የሐጢያቶቻችንን ዋጋ ለመክፈል የሰውን ዘር ሥጋ ለብሶ ወደዚህ አለም መጣ ይህ ዳግም የመወለድ እውነት ነው፡፡

እንዲሁም ደግሞ የዳግም መወለድ እውነት ኢየሱስ ስጋን ለብሶ ወደ ምድር መምጣቱንና ኃጢአቶቻችንንም በጥምቀቱና በደሙ እንዳነፃልን ማመን ነው፡፡

ኃጢአቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ ወደራሱ ከወሰደ በኋላ የኃጢአትንም ደሞዝ መስቀል ላይ በመሞት ከፍሎልናል በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመድማትም *በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ አድኖዋቸዋል፡፡*

የኢየሱስ ጥምቀትና ሞት እኛን ከሐጢያቶቻችን ያዳኑን በመሆናቸው ደህንነትን እንደሚያመላክቱ መገንዘብ ይኖርብናል የእግዚአብሄርን መንግስት ሊያዩና ወደዚያ ሊገቡ የሚችሉት ከውሃና ከመንፈስ የተወለዱ ብቻ ናቸው ኢየሱስ በውኃው፣ በደሙና በመስቀሉ ከኃጢአቶቻችን በሙሉ አድኖናል ይህን ታምናላችሁን?

ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ ለመክፈል ወደ ምድር የመጣ ሰማያዊ ካህን ነው እርሱ ተጠመቀ በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ ከሙታንም ተነሳ ከዚህ የተነሳ በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ መድሃኒት ሆነላቸው፡፡

በዮሐንስ 10፡7 ላይ ሲናገርም *«እኔ የበጎች በር ነኝ»* ይላል ኢየሱስ በሰማይ በር ቆሞዋል በሩን ለኛ የሚከፍትልን ማነው? እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡

ኢየሱስ የእርሱን የደህንነት እውነት ሳያውቁ በእርሱ የሚያምኑትን ፊት ይነሳቸዋል በእርሱ ጥምቀት፣ ደምና መንፈስ የማያምኑ ዳግም እንዲወለዱ አይፈቅድላቸውም በተፃፈው የእርሱ ቃል ከማያምን፣ የእርሱን ቅድስና ለመቀበል

እምቢተኛ ከሆነና እርሱን እንደ አምላክ ከማያውቀው ከማንኛ ውም ሰው ፊቱን ያዞራል፡፡

የተፃፈው እውነት ኢየሱስ ለአለም ሐጢያቶች በሙሉ ካሳ ለመክፈል ስጋ ለብሶ ወደዚህ አለም መምጣቱን፣ መጠመቁንና በመስቀል ላይ መሞቱን ይናገራል እርሱ በመስቀል ላይ የሞተው የእኛን ፍርድ ለመውሰድ ነው ከተሰቀለም በኋላ በሦስተኛው ቀን ተነሳ ይህንን እውነት ለማመን እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ወደ ውጭ ተጥሎ ይጠፋል *«የኃጢኣት ደሞዝ ሞት ነው፡፡»*

ነገር ግን እነዚያ በእርሱ ጥምቀትና ደም አማካይነት በመቤዡት በረከት የሚያምኑና በልባቸው የተቀደሱ መንግስተ ሰማያት መግባት ተፈቅዶላቸዋል ይህ በውሃው፣ በደሙና በመንፈሱ ዳግም የምንወለድበት ወንጌል ነው ሰማያዊው ወንጌል ከውሃና ከመንፈስ ዳግም መወለድ ነው ዳግም ሊወለዱ የሚችሉት በኢየሱስ ጥምቀትና ደም የሚያምኑ ብቻ ናቸው በውሃው በደሙና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ሐጢያት አልባ ናቸው በትክክል ዳግም የተወለዱትም እነርሱ ናቸው፡፡

ኒቆዲሞስ እውነቱን እንዳልተረዳ ሁሉ ዛሬም አብዛኛው ሕዝብ እውነተኛውን ወንጌል ሳያውቅ በኢየሱስ ያምናል ኒቆዲሞስ በማህበረሰቡ ዘንድ ተሰሚነት የነበረው አባል ነበር ነገር ግን እውነተኛውን ወንጌል ከኢየሱስ ሰማ በኋላም ኢየሱስ ሲሰቀል ሬሳውን ለመቅበር መጣ በዚያን ጊዜ ኒቆዲሞስ በሙሉ ልቡ አምኖ ነበር፡፡

ዛሬም ስለ ውሃውና ስለ ኢየሱስ መንፈስ የተነገረውን የማናውቅ በጣም ብዙ ነን ከዚህም በላይ እውነተኛውን ወንጌል የመስማት ዕድል አግኝተው እንኳን እውነቱን ያልተቀበሉ ብዙ ሰዎች አሉ ይህ የሚያሳዝን ነው፡፡

ኢየሱስ ሁላችንም ዳግም እንድንወለድ አስችሎናል ዳግም

እንድንወለድ ያደረገን ምንድነው? ውሃው፣ ደሙና መንፈሱ ናቸው ኢየሱስ ሲጠመቅ ሐጢያቶቻችንን ወስዶ በመስቀል ላይ ሞተ ከዚያም ከሙታን ተነሳ::

በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉም ዳግም የመወለድን በረከት ሰጥቷል ኢየሱስ በእርሱ ለሚያምኑት ሁሉ ዳግም መወለድን የፈቀደ አዳኝ ነው ሁልጊዜም ሰማይን፣ ምድርንና በሁለቱ መካከል ያሉትን ነገሮች ሁሉ ከፈጠረው ከኢየሱስ ጋር ትሆኑ ዘንድ ፀልዩ::

በዮሐንስ 3:16 ላይ እንደተፃፈውም *«በእርሱ የሚያምን ሁሳ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ»* በኢየሱስ በማመን ዘላለማዊ ሕይወትን አግኝተናል በውሃና በመንፈስ በማመናችን ዳግም ተወልደናል የደህንነት ወንጌል በሆነው የኢየሱስ ጥምቀትና ደም ካመንን ኢየሱስም አዳኝና አምላክ መሆኑን ካመንን መዳን እንችላለን::

ነገር ግን በዚህ እውነት ካላመንን ለዘላለም ወደ ሲዖል እንወርዳለን ኢየሱስ ለኒቆዲሞስ *«ስለምድራዊ ነገር ነግሬህ ያላመንሽኝ በሰማይ ስላለው ነገር ብነግርህ እንዴት ልታምነኝ ትችላለህ?»* ብሎ የተናገረውም ለዚህ ነው::

እግዚአብሔር ያደረገልን ምንድን ነው? በኢየሱስ ባገኘነው ደህንነት ዳግም መወለድ አስችሎናል ኢየሱስ ከዓለም፣ ከዲያብሎስና ከዓለም ኃጢአቶች በሙሉ አድኖናል ኢየሱስ የዚህን አለም ሐጢያተኞች ከሐጢያት ፍርድ ለማዳን በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶችን በሙሉ ወስዶ በመስቀል ላይ ተሰቀለ ከዚያም ከሙታን ተነሳ::


በዚህ ደህንነት ማመን አለማመን የእኛ ምርጫ ነው ዳግም የምንወለድበት ደህንነት የሚመጣው በኢየሱስ ጥምቀትና ደም አማካይነት የሚገኘውን ደህንነት በማመን ነው::

እግዚአብሄር ሁለት በረከቶችን እንደሰጠን ተናግሮዋል

አንደኛው ጥቅል በረከት ሲሆን የተፈጥሮን ነገሮች ፀሐይንና አየርን ያካትታል ይህ ጥቅል በረከት የተባለበት ምክንያት ለሐጢያተኛውም ለፃድቁም ሁሉ የተሰጠ በመሆኑ ነው ታዲያ ይህ ልዩ በረከት ምንድነው? ልዩ የሆነው በረከት ሐጢያተኞችን በሙሉ በሐጢያቶቻቸው ምክንያት ከሚመጣው ሞት የሚያድነውና ከውሃና ከመንፈስ ዳግም መወለድ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ ልዩ በረከት ነው ልዩ በረከት ምንድን ነው? ልዩው በረከት ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል እንደገና መወለድ ነው ይህም ኃጢአተኞችን በሙሉ በኃጢአታቸው ከመሞት የሚያድን ነው፡፡

## ልዩው በረከት




በዮሐንስ 3:16 ላይ እንደተፃፈው *«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ህይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ አለሙን እንዲያ ወዷልና»* ይህ የእግዚአብሔር ልዩ በረከት ነው ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የሰው ስጋን ለብሶ መጥቷል እንዲሁም በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመሞትም ኃጢአቶቻችንን በሙሉ አንጽቶልናል ይህ

የእግዚአብሔር ልዩ በረከትና እውነት ነው።

ኢየሱስ እኛን ማዳኑ፣ ከሐጢያተኝነት ወደ ፃድቅነት መለወጡ እውነት ነው ይህንን እውነት በማመን ብቻ የእግዚአብሄርን የተለየ በረከት ታገኛላችሁ ይህንን ሁሉ ታምናላችሁን?

በሕይወት ዘመናችሁ ሁሉ ምንም ያህል በታማኝነት ብትኖሩም ይህንን ልዩ የእግዚአብሄር በረከት ከገፋችሁ እምነታችሁ ሁሉ ከንቱ ይሆናል።

ሁልጊዜ ወንጌልን በምሰብክበት ወቅት የኢየሱስ ጥምቀትና የመስቀሉ ላይ ደም ለመዳናችን መሠረታዊ ነገሮች መሆናቸውን ሳልጠቅስ አልፌ አላውቅም በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ ማንኛ ውም መፅሐፍ የ«እግዚአብሔር ልዩ በረከት» ማለት እኛ እየተነጋገርንበት ያለው በኢየሱስ ዳግም መወለድ መሆኑን ሳይጠቅስ ያለፈ የለም በኢየሱስ ጥምቀትና በስቅለቱ አማካይነት የሆነውን የሐጢያተኞች መዳን በተሻለ መንገድ የሚገልጠው የእግዚአብሄር በረከት ነው።

የኢየሱስ ጥምቀትና የእርሱ በመስቀል ላይ መሞት የእግዚአብሔር ልዩ በረከቶች ናቸው በዓለም ላይ ያሉት የሐሠት ሰባኪዎች ስለዚህ የሚናገሩት ምንም ነገር የላቸውም እነዚህ የውሸት ሰባኪዎችም በሚያበራ የመላዕክት ልብስ ተሸፍነው የክርስትናን ስነ-ኃይማኖታዊ ባህሪና ስነ ምግባር ሸክፈው ይመጣሉ አዎን ይህ እውነት ነው የሚሰሩት ተዓምራትም ወይም ደግሞ ህሙማንን መፈወሳቸው በሙሉ ከእግዚአብሔር ልዩ በረከት ጋር እስካልተዛመዱ ድረስ ክፉ ድርጊቶቻቸው ናቸው።

ለኃጢአተኞች የስርየትን ወንጌል የሰጠው የእግዚአብሔር ልዩ በረከት ነው በዚህ የበረከት ወንጌልም እግዚአብሔር እኛ ዳግም እንድንወለድ ፈቅዶልናል በጥምቀቱ፣ በደሙ በሞቱና

በትንሳኤውም አዲስ ሰዎች አድርጎናል ከኃጢአት የነፃን የእግዚአብሔር ልጆች አድርጎናል፡፡

በዚህ ታምናላችሁን? —አዎን— በእውነት ተባርካችኋልን? —አዎን— የኢየሱስ ጥምቀት፣ ደሙና መስቀሉ በውኃውና በመንፈሱ የተሰጡን የእግዚአብሔር ልዩ በረከቶች ናቸው ይህ የልዩው በረከት ወንጌል ነው በልዩው በረከት ስላዳነን ጌታ የተመሰገነ ይሁን፡፡

ዛሬ በርካታ ክርስቲያኖች ከጥምቀትና ከደም ከውሃና ከመንፈስ የሆነውን ዳግም የመወለድ ወንጌል ይህንን የተለየ የእግዚአብሄር በረከት አለማወቃቸው ያሳዝናል በገዛ ራሳቸው ቃለ እግዚአብሄርና ሐይማኖታዊ ምግባሮች መንገዱን ለማግኘት በእውር ድንብር ይሞክራሉ ምንኛ ደንቁረዋል!

ክርስትና ለረጅም ጊዜ አብሮን ቆይቷል ተሐድሶ ከመጣ አምስት መቶ አመታቶች ይሆኑታል ነገር ግን አሁንም በኮርያና በቀረው አለም ዳግም የመወለድን እውነትና የእግዚአብሄርን ልዩ በረከት የማያውቁ ብዙዎች አሉ፡፡

ሆኖም ግን እኛ ያለነው አሁን በዓለም መጨረሻ ላይ ስለሆነ እርሱ እውነቱን ያሳውቃቸዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ አምናለሁም

ኃጢአተኞች ጻድቃን እንዲሆኑና መንግስተ ሰማያትም እንዲገቡ የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመቀበል እንደገና መወለድ አለባቸው ብዙ ክርስቲያኖች ዳግም ለመወለድ ጠንክረው እየሞከሩ ነው፡፡

ሆኖም ዳግም የመወለድን እውነተኛ ትርጉም ሳያውቁ የሚያምኑ ከሆነ እምነታቸው ከንቱ ነው መንግስተ ሰማይ ለመግባት ዳግም መወለድ ይኖርብናል ይላሉ ነገር ግን ዳግም ስለመወለድ እውነት ፍንጩ እንኳን የላቸውም፡፡

በታማኝነት ስለሚያምኑና እሳቱ በልባቸው ውስጥ

ስለሚሰማቸው ዳግም መወለድ እንደሚችሉ ይገምታሉ በግል ስሜቶች ወይም በሐይማኖታዊ ምግባሮች ላይ ተመርኩዞ ዳግም ለመወለድ መሞከር ወደ ተሳሳተ እምነት ሊመራ ይችላል፡፡

## ወደ እውነተኛ ዳግም ውልደት የሚመራን የእግዚአብሄር ቃል

*በእምነትና በኃይማኖት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?*

*እምነት ማለት ኢየሱስ ሊያድነን ያደረገልንን ማመን ሲሆን፣ ኃይማኖት በራስ አስተሳሰቦችና ምግባሮች ላይ መደገፍ ነው፡፡*

በ1ኛ ዮሐንስ 5:4-8 ላይ በግልፅ እንደተፃፈው እኛ ዳግም ውልደትን ለማግኘት የምንችለው በውኃው፣ በደሙና በመንፈሱ ስናምን ብቻ ነው ዳግም መወለድ ካለብን፣ ዳግም ልንወለድ የምንችለው በተፃፈው የእግዚአብሔር ቃል፣ በእውነቱ ብቻ መሆኑን በአእምሮአችን ማስታወስ አለብን ራዕዮች፣ በልሳን መናገር ወይም በስሜት ላይ የተመሠረቱ ልምምዶች በጭራሽ ዳግም ወደ መወለድ ሊያደርሱን አይችሉም፡፡

በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይም ኢየሱስ ሲናገር ማንም ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት እንደማይችል ይናገራል አንድ ሰው ዳግም

ለመወለድ በኢየሱስ ሁለት ጊዜ ማመን አለበት በመጀመሪያ አንድ ሰው ኢየሱስን ኃይማኖቱ በሚያዘው መንገድ በማመን፣ በእግዚአብሔር ህግ መሰረት ኃጢአተኛ መሆኑን ይገነዘባል አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ በኢየሱስ ሲያምን ያንን የሚያደርገው በእግዚአብሄር ሕግና እርሱም ምን ያህል ክፉ ሐጢያተኛ እንደሆነ በመገንዘብ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ ያሉት አብዛኞቹ ኃይማኖቶች እንደሚያምኑት በኢየሱስ ማመን አያስፈልገንም ክርስትና ኃይማኖት አይደለም ክርስትና በእምነት ዘላለማዊ ህይወት የሚገኝበት መንገድ ነው፡፡

ኢየሱስን በሐይማኖት መልክ የሚያምን ማንም ሰው ባዶ እጁን ይቀራል በሐጢያት፣ በሁከትና በባዶነት የተሞላ ልብ ይዞ ይቀራል ይህ እውነት አይደለምን? በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተጠቀሱት ፈሪሳውያን ግብዝ ሆነን መቅረት አንፈልግም፡፡

ዳግም መወለድ የማይፈልግ ሰው የለም ነገር ግን አንድ ሰው ክርስትናን በሐይማኖት መልክ የሚያምን ከሆነ ሐጢያት የተሞላ ልብ ያለው ግብዝ ሆኖ ይቀራል ዳግም የመወለድን እውነት ማወቅ አለብን፡፡

ዳግም ሳይወለድ ክርስትናን በሐይማኖት መልክ የሚያምን ማንኛውም ሰው ልቡ በግራ መጋባትና በባዶነት የተሞላ ይሆናል አንድ ሰው በኢየሱስ አምኖ ዳግም ያልተወለደ ከሆነ እምነቱ የተሳሳተ ነው ስለዚህ በሰው ሁሉ ፊት ቅዱስ መስሎ ለመታየት የሚሞክር ነገር ግን የማይሳካለት ምስኪን ሆኖ ይቀራል፡፡ ክርስትናን በሐይማኖት መልክ ማመናችሁን እስከቀጠላችሁ ድረስ ሁልጊዚም ሐጢያተኛና ግብዝ ትሆናላችሁ ከሐጢያቶቻችሁ ነፃ መውጣት ከፈለጋችሁ ከውሃ፣ ከደምና ከመንፈስ በሆነው የተፃፈ የወንጌል እውነት ማመን ይኖርባችኋል፡፡

# የቤዛነትን ምስጢር በኢየሱስ ጥምቀት በኩል መፈለግ

*ዳግም እንድንወለድ ያደረገን ምንድን ነው?*

*የኢየሱስ ጥምቀት፣ የመስቀሉ ላይ ሞትና ትንሳኤው ናቸው::*

መፅሐፍ ቅዱስ ማንም ሰው ፈፅሞ በማይለወጠው የእግዚአብሄር ቃል አማካይነት ዳግም ሊወለድ እንደሚችል ይነግረናል አሁን ደግሞ የሃዋርያውን ጴጥሮስ ቃል በ1ኛ ጴጥሮስ 3:21 ላይ እንመልከት *«ይህም ውሃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ ያድነናል::»*

የኢየሱስ ጥምቀት እኛን የሚያድነን እውነተኛ ተምሳሌት እንደሆነ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተመዝግቦዋል በኢየሱስ የሚያምኑ ሁሉ ማወቅ ያለባቸው ስለ ራሳችን ጥምቀት ሳይሆን ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ነው የኢየሱስ ጥምቀት ለእኛ ለሐጢያተኞቹ አዲስ ሕይወትን ሰጥቶናል እመኑት ዳግም ትወለዳላችሁ የደህንነትንም በረከት ታገኛላችሁ::

ደህንነት የሚገኘው በኢየሱስ ጥምቀት በማመን መሆኑን በመረዳት ልንድን፣ ፃድቅ ልንሆንና የዘላለምን ሕይወት ልናገኝ እንችላለን በሌላ አነጋገር በእግዚአብሄር ቃሎች አማካይነት ዳግም እንወለዳለን::

ዳግም መወለድ ማለት ለሁለተኛ ጊዜ መወለድ ማለት ነው ብዙዎቻችን የምንጀምረው በኃይማኖት መልክ በኢየሱስ በማመን ነው ሆኖም ግን እውነቱን በምንገነዘብበት ወቅት ዳግም

እንወለዳለን *«እርሱ ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና።» (ማቴዎስ 1:21)*

በኢየሱስ ስናምንና እርሱም ለሰው ልጆች ምን እንዳደረገ ስንረዳ፣ ከኃጢአቶቻችን በሙሉ ነፅተን እንደ አዲስ ሰው ዳግም እንወለዳለን በመጀመሪያ በኃይማኖት መልክ በኢየሱስ አመንን በመቀጠልም ከውኃው፣ ከደሙና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም ስለመወለድ በሰማን ጊዜ እንደገና ተወለድን።

ዳግም እንድንወለድ የሚያደርገን እውነት ምንድን ነው? በመጀመሪያ የኢየሱስ ጥምቀት፣ በመቀጠልም በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ፣ በመጨረሻም ከሙታን መነሳቱ ናቸው ዳግም መወለድ ማለት ኢየሱስን እግዚአብሔርና አዳኝ አድርጎ ማመን ማለት ነው በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሰዎች እንዴት ዳግም እንደሚወለዱ እንመልከት።

## በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበረው የኃጢአት ማካካሻ: እጅን የመጫንና ደምን የማቅረብ ሥርዓት

በብሉይ ኪዳን ዳግም የመወለድ ወንጌል ምንድነው? በመጀመርያ በዘሌዋውያን ምዕራፍ 1 ላይ ስለ ዳግም ውልደት የተፃፈውን እናንብብ።

ዘሌዋውያን 1:1-5 እንዲህ ይላል *«እግዚብሔርም ከመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሙሴን ጠርቶ እንዲህ ሲል ተናገረው ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው ከእናንተ ማናቸውም ሰው ለእግዚአብሔር መባን ሲያቀርብ መባችሁን ከእንስሳ ወገን ከላሞች ወይም ከበጎች ታቀርባላችሁ መባውም የሚቃጠል መሥዋዕት ከላሞች መንጋ ቢሆን ነውር የሌለበትን ተባቱን ያቀርባል በእግዚአብሔር ፊት እንዲሰምር በመገናኛው ድንኳን*

*ደጃፍ ያቀርበዋል እጁንም በሚቃጠለው መስዋዕት ራስ ላይ ይጭናል ያስተሰርይለትም ዘንድ የሰመረ ይሆንለታል በሬውንም በእግዚአብሔር ፊት ያርደዋል የአሮንም ልጆች ካህናቱ ደሙን ያቀርባሉ ደሙንም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ባለው በመሠዊያው ላይ በዙሪያው ይረጩታል፡፡»*

እግዚብሔር በዘሌዋውያን ላይ እስራኤላውያን መስዋትን በማቅረብ እንዴት ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረትን ይመሰርቱ እንደነበር ይነግረናል ይህ ሁላችንም ልናውቀውና ልንረዳው የሚገባን እውነት ነው ስለሆነም እነዚህን ቃላት እንከልሳቸው፡፡

እግዚአብሔር በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ሙሴን ጠርቶ አናገረው ያናገረውም የእስራኤላውያንን የኃጢአት ስርየት ነበር የእስራኤል ሕዝብ ሕጉን ያለ መታዘዝ ሐጢያቶችን በሰሩ ጊዜ ነውር የሌለበትን እንስሳ በእግዚአብሄር ፊት በማቅረብ ሐጢያቶቻቸውን ማስተሰረይ ችለው ነበር፡፡

እነዚህ ለመስዋዕት የሚቀርቡት እንስሳትም እግዚአብሔር ከመረጣቸው ወገን ሆነው ነውር የሌለባቸው ነበሩ እንዲሁም ደግሞ መስዋዕቶቹ የሚቀርቡት እግዚአብሔር በደነገገው ስርዓት መሰረት ብቻ ነበር የመስዋዕቱም ስርዓት ከዚህ እንደሚከተለው ነበር፡-

በብሉይ ኪዳን አንድ ሰው ኃጢአትን ቢሰራ በእግዚአብሄር ፊት ለሰራው ለሐጢአት ስርየት የሚሆን መስዋዕት ማቅረብ ነበረበት በመጀመሪያ መስዋዕቱ ነውር የሌለበት ይሆናል በመቀጠል ደግሞ ኃጢአተኛው እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ በመጫን ኃጢአቱን በሙሉ ወደ መስዋዕቱ ማስተላለፍ አለበት፡፡

መስዋዕቱ ከታረደም በኂላ ደሙ ግማሹ በመሰዊያው ቀንዶች ላይ የቀረውም መሬት ላይ ይፈስሳል እግዚአብሄር የደህንነት በረከት አድርጎ ለሕዝቡ የሰጠውና በተቀደሰው ድንኳን ውስጥ የሚከናወነው ስርአት ይህ ነበር፡፡

የእግዚአብሄር ሕጎችና ትዕዛዛቶች እነርሱ «ማድረግ የሚገባቸውን» ወይም «ማድረግ የማይገባቸውን» የሚያሳዩ 613 አንቀፆችን ይዘዋል እግዚአብሄር ሕጉንና ትዕዛዛቱን ለሕዝበ እስራኤል ሰጠ ሕዝቡ የእግዚአብሄር ሕግና ትዕዛዛት ትክክል እንደሆኑ ቢያውቁም ሊኖሩባቸው አልቻሉም ምክንያቱም ሁሉም የተወለዱት ከአዳም የወረሱዋቸውን አስራ ሁለት አይነት ሐጢያቶች ይዘው ነበርና፡፡

ስለሆነም በእግዚአብሔር ፊት ትክክኛ ነገር ማድረግ አልቻሉም እስራኤሎች ጻድቃን የመሆን አቅምም አጥተው ነበር ከሐጢያት ነጻ ወጥተው ለመኖር አጥብቀው ቢሞክሩም ሐጢያቶችን ከመስራት ሊቆጠቡ አልቻሉም ሐጢያተኞች ሆኖ መወለድና መሞት የሰው ዘር ሁሉ ዕጣ ፈንታ ነው፡፡

ነገር ግን እግዚአብሄር ወሰን በሌለው ምህረቱ ሐጢያቶቻቸውን ማስተሰረይ የሚችሉበትን የመስዋዕት ስርአት ለሕዝቡ ሰጠ የእስራኤል ሕዝብና የአለም ሕዝብ በሙሉ ከሐጢያቶቻቸው መዳን ይችሉ ዘንድ በቅዱሱ ድንኳን ውስጥ የሚደረገውን ስርአት አቀረበላቸው፡፡

እግዚአብሔር የመስዋዕት ስርአቱን ለሕዝቡ ሰጥቶ መስዋዕቱን ያገለግል ዘንድ የሌዊን ቤት መረጠ ከ12ቱ የእስራኤል ነገዶች መካከል ለእስራኤል ሕዝብ የመስዋዕት አገልጋይ ሆኖ የተመረጠው የሌዊ ቤት ብቻ ነበር፡፡

ሙሴና አሮንም የሌዊ ቤት ነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ በተቀደሰው ድንኳን ውስጥ የሚቀርበውን መስዋዕት የሚያስተዳድሩ ሕጎችንና ስርአቶችን መዝግቦዋል ይህም እጆችን በመጫን የሚደረግ የስርየት ወንጌል ነው፡፡

ስለዚህ ሌዋውያን የሚያከናውኑትን የመስዋዕት ስርዓት በተጨባጭ ስናስተውል ዳግም ልንወለድ እንችላለን በተቀደሰው ድንኳን ውስጥ የሚቀርበውን መስዋዕት በሚመለከት

የእግዚአብሄርን ቃል ማጥናት የሚገባን ለዚህ ነው ይህ የብሉይ ኪዳን እጅግ አስፈላጊው ክፍል ነው በመጨረሻም ወደ አዲስ ኪዳን በመምጣት በውኃና በመንፈስ አማካይነት ዳግም የመወለድ በረከቶች አሉን፡፡

## የኃጢአት ሥርየት በብሉይ ኪዳን

*የእግዚአብሔር ባህሪያት ምን ምን ናቸው?*

*ፍትህና ፍቅር*

እግዚአብሔር ከሌዊ ነገድ የሆነውን ሙሴን ወደ መገናኛው ቅዱስ ድንኳን ጠርቶ ወንድሙን አሮንን ሊቀ ካህን አድርጎ ሾመው የሕዝቡን ኃጢአቶች ወደ መስዋዕቱ የሚያስተላልፈው አሮን ነበር፡፡

በዘሌዋውያን 1:2 ላይ እንደተፃፈውም እግዚአብሔር ለሙሴ ያለው ይህንን ነው *«ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፡- ከእናንተ ማናቸውም ሰው ለእግዚአብሔር መባን ሲያቀርብ መባችሁን ከእንስሳ ወገን ከላሞች ወይም ከበጎች ታቀርባላችሁ»* እዚህ ላይ እግዚአብሔር ለመስዋዕት የሚቀርቡትን ቁርባኖች ዘርዝሮዋል ከሕዝቡ ማናቸውም ለሐጢያቶቹ ስርየቶችን ማግኘት ከፈለገ ከመንጋው ወይፈን ወይም በግ ማቅረብ ነበረበት፡፡

እንዲሁም ደግሞ *«መባውም የሚቃጠል መሥዋዕት ከላሞች መንጋ ቢሆን፥ ነውር የሌለበትን ተባቱን ያቀርባል፤*

*በእግዚአብሔር ፊት እንዲሰምር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ያቀርበዋል::» (ዘሌዋውያን 1:3)*

እግዚአብሔር መስዋዕቱን የሚቀበለው በኃጢአቶቹ ምክንያት መሞት በነበረበት ሰው ህይወት ፈንታ ነው እስራኤላውያን እጆቻቸውን ለመስዋዕት በሚያቀርቡዋቸው እንስሶች ራሶች ላይ በመጫን ሐጢያቶቻቸውን ማስተላለፍ ይችሉ ነበር ግለሰቡ ለመስዋዕት የሚሆኑትን እንስሶች ማቅረብ የነበረበት በገዛ ፈቃዱ ነበር አሁን ደግሞ ቁጥር 4 የሚለውን እንመልከት::

*«እጁንም በሚቃጠለው መስዋዕት ራስ ላይ ይጭናል ያስተሰርይለትም ዘንድ የሰመረ ይሆንለታል»* መስዋዕቱ በእግዚአብሔር ተቀባይነት ይኖረዋል አንድ ኃጢአተኛ እጁን በሚያቀርበው መስዋዕት አናት ላይ በመጫን ኃጢአቶቹን በሙሉ ወደ መስዋዕቱ ያስተላልፋል ስለዚህ ኃጢአተኛው በእግዚአብሔር ፊት በመስዋዕቱ አናት ላይ እጆቹን መጫን ነበረበት ያን ጊዜ ይህንን ተቀብሎ ለሐጢያቶቹ ስርየትን ይሰጠዋል::

ከዚያም መስዋዕቱን ያቀረበው ግለሰብ እንስሳውን ያርደውና ደሙን በመሰውያው ቀንዶች ላይ ይቀባዋል የቀረውንም ደም በመሰውያው ፊት በመሬት ላይ ያፈስሰዋል ለሐጢያቶቹ ዋጋ ለመክፈልና ከእነርሱም ነፃ ለመውጣት እግዚአብሄር ባስቀመጣቸው ሕጎች መሠረት መስዋዕቱን ማቅረብ ይኖርበታል::

በዘሌዋውያን 1:5 ላይ እንደተፃፈውም *«በሬውንም በእግዚአብሔር ፊት ያርደዋል የአሮም ልጆች ካህናቱ ደሙን ያቀርባሉ ደሙንም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ባለው በመሠዊያው ላይ በዙሪያው ይረጩታል»* በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በአራቱም ማዕዘኖች ላይ ባሉ ቀንዶች ላይም ደሙ ይረጫል::

እጆቹን በሚቃጠለው መስዋዕት እንስሳ አናት ላይ በመጫን ኃጢአቶቹን በሙሉ ካስተላለፈ በኋላ ኃጢአተኛው መስዋዕቱን ማረድ ሲኖርበት ሊቀ ካህኑም ደሙን በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ይረጨዋል የመሰዊያው ቀንዶች የሚያመለክቱት የኃጢአትን ፍርድ ነው ደሙንም በቀንዱ ላይ መርጨት ማለት መስዋዕቱ በኃጢአተኛው ፈንታ ለኃጢአተኛው በደል ሲል እንደሚደማ ያሳያል እግዚአብሔርም በቀንዶቹ ላይ የተረጨውን ደም ሲመለከት የኃጢአተኛውን ኃጢአቶች በሙሉ ያስተሰርያል፡፡

መስዋዕቱ መድማት ያለበት ለምንድን ነው? ለዚህ ምክንያቱ *«የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6፡23)* ስለሆነና የስጋ ህይወት ያለውም በደም ውስጥ ስለሆነ ነው *«ደም ሳይፈስ ስርየት የለም» (ዕብራውያን 9፡22)* ስለዚህ ከመስዋዕቱ እንስሳ የሚፈስሰው ደም የሐጢአት ደመወዝ ሞት ነው የሚለውን የእግዚአብሄር ሕግ ይፈጽማል፡፡

የቀረበው ደም መምጣት የሚገባው ከሐጢያተኛው መሆኑ ተገቢ ነበር ነገር ግን የሐጢያት መስዋዕቱ ለሐጢያቶቹ ስርየት ይሆን ዘንድ በእርሱ ምትክ መፍሰስ ነበረበት ያን ጊዜ ናህኑ የሐጢያት ዋጋ እንደተከፈለ ለማሳየት ደሙን በመሰውያው ቀንዶች ላይ ይቀባዋል፡፡

በአዲስ ኪዳን ላይ ራዕይ 20፡11-15ን ካነበብን ቀንዶቹ የሚያመለክቱት የፍርድ መፅሐፍን መሆኑን እንረዳለን ስለሆነም፣ በቀንዶቹ ላይ ደም ማኖር ማለት በፍርድ መፅሐፍ ላይ ደምን እንደማኖር ነው ይህም የሚመሰክረው የሐጢያቶች ፍርድ እጆችን በመጫንና በሐጢያት መስዋዕቱ ደም አማካኝነት መፈፀሙን ነው፡፡

# ኃጢአቶቻችን የሚመዘገቡት በሁለት ቦታ ነው

የሰው ዘር ኃጢአቶች በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት በሁለት ቦታዎች ይመዘገባሉ አንደኛው በልቦቻቸው ጽላቶች ሲሆን ሌላው ደግሞ በእግዚአብሔር ፊት በሚከፈተው የፍርድ መፅሐፍ ላይ ነው::

በኤርምያስ 17:1 ላይ እንደተፃፈውም *«የይሁዳ ኃጢአት በብረት ብርዕና በተሾለ ዕብነ አልማዝ ተጽፎኣል በልባቸው ጽላትና በመሠዊያቸው ቀንዶች ተቀርጾኣል::»*

በዘሌዋውያን 17:11 ላይ እንዲህ ይላል *«የሥጋ ህይወት በደሙ ውስጥ ነውና፤ ደሙም ከሕይወቱ የተነሣ ያስተሰርያልና በመሠዊያው ላይ ለነፍሳችሁ ማስተሰረያ ይሆ ዘንድ እኔ ለእናንተ ሰጠሁት»* ደም የስጋ ሕይወት ነው እንዲሁም ደግሞ የኃጢአቶቻችን ዋጋ ሊከፈል የሚችለው በዚህ ደም ብቻ ነው ስለዚህ በመሰዊያው ቀንዶች ላይ ደም ይረጭ ነበር በሕጉ መሠረት ሁሉም በደም ይነጻሉ ደም ሳይፈስም ስርየት አይኖርም:: (ዕብራውያን 9:22)

*«የሚቃጠለውንም መስዋዕት ይገፍፈዋል በየብልቱም ይቆርጠዋል የካህኑም የአሮን ልጆች በመሠዊያው ላይ እሳት ያነድዳሉ በእሳቱም ላይ እንጨት ይደረድራሉ የአሮንም ልጆች ካህናቱ የተቆረጡትን ብልቶች ራሱንም ስቡንም በመሠዊያው ላይ በእሳቱ ላይ ባለው በእንጨቱ ላይ ይረበርቡታል የሆድ እቃውንና እግሮቹን ግን በውኃ ያጥባል ካህኑም ሁሉን የሚቃጠል መስዋዕት የእሳት ቁርባን አድርጎ በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን በመሰዊያው ላይ ያቃጥለዋል::» (ዘሌዋውያን 1:6-9)*

ያን ጊዜ ካህናቶቹ የሚቃጠሉትን መስዋዕቶች ቆራርጠው በሚቃጠለው መሰውያ ላይ ያኖሩዋቸዋል ይህ ስርአት ሰዎች

በእግዚአብሄር ፊት ሐረጢያት በሰሩ ጊዜ ምዚያ መንገድ መሞት መድማትና ወደ ሲያል እሳቶች መጣል እንደነበረባቸው የሚያመላክት ነው ነገር ግን ሕዝቡ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ያገኙ ዘንድ በሐጢያት መስዋዕቱ ላይ ፍርድ ይተላለፋል፡፡

የሚቃጠሉት ቁርባኖች የእግዚአብሄር የጽድቅ ሕግ ፍርድ ስርአት ነበሩ እግዚአብሄር ሁለቱንም ሕጎን ማለትም የጽድቅን ሕግና የፍቅርን ሕግ ለሰው ዘር ሁሉ ማስተሰረያ በሆነው ስርአት ውስጥ አካንቶዋቸዋል፡፡

እግዚአብሄር ጻድቅ ስለሆነ እነርሱን መዳኘትና የሞት ውሳኔ መስጠት ነበረበት ነገር ግን እርሱ ሕዝቦቹን ስለወደዳቸው ሐጢያቶቻቸውን ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ እንዲያስተላልፉ ፈቀደላቸው በአዲስ ኪዳንም ጌታችን አብዝቶ ስለወደደን ለእኛ ለሐጢያተኞች የሐጢያት ቁርባን ይሆን ዘንድ ተጠመቀ ተሰቀለም የኢየሱስ ጥምቀትና የመስቀል ላይ ሞቱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ደምስሶዋል፡፡

## በየቀኑ ለሚሰራ ኃጢአት የሚደረግ ስርየት በብሉይ ኪዳን

*በብሉይ ኪዳን ያለው ነውር የሌለበት መስዋዕት የሚወክለው ማንን ነው?*

*ኢየሱስ ክርስቶስን ነው፡፡*

በዘሌዋውያን 4፡27 ላይ የተጻፈውን እንመልከት- *«ከአገሩ ሕዝብም አንድ ሰው ኃጢኣትን ሳያውቅ ቢሰራ እግዚአብሐሬርም አትስራ ያለውን ትዕዛዝ ቢተላለፍ፣*

*ቢበድልም ለእርሱም የሠራው ኃጢአት ቢታወቀው፣ ስለ ሠራው ኃጢኣት ነውር የሌለበትን እንስት ፍየል ለቁርባን ያመጣል እጁንም በኃጢአት መስዋዕት ራስ ላይ ይጭናል የሚቃጠልም መሥዋዕት በሚታረድበት ስፍራ የኃጢአትን መሥዋዕት ያርዳል ካህኑም ከደምዋ በጣቱ ወስዶ ለሚቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ቀንዶች ላይ ያደርገዋል ደሙንም ሁሉ ከመሠዊያው በታች ያፈስሰዋል ስቡም ሁሉ ከደኅንነት መሥዋዕት ላይ እንደሚወሰድ ስብዋን ሁሉ ይወስዳል ካህኑም ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል ካህኑም ስለ እርሱ ያስተሰርያል እርሱም ይቅር ይባላል::» (ዘሌዋውያን 4:27-31)*

የአዳም ዘሮች፣ የእስራኡል ሕዝብና የአለም ሕዝብ ሁሉ በዚህ ምድር ላይ የተወለዱት በሐጢያት ተሞልተው ነው ስለዚህ ልቦቻችን በሐጢያት ተሞልተዋል በሰው ልብ ውስጥ ሁሉም አይነት ሐጢያቶች አሉ ክፉ አስተሳሰቦች፣ ምንዝርና፣ ዝሙቶች ነፍስ መግደል፣ ስርቆት፣ ስስትና ስንፍና::

አንድ ሐጢያተኛ በቀን ውስጥ የሰራቸውን ሐጢያቶች ለማስተሰረይ ከፈለገ ነውር የሌለበትን መስዋዕት ወደ መገናኛው ድንኳን ይዞ መምጣት አለበት ከዚያም ሐጢያቶቹን ለማስተላለፍ እጆቹን በእንስሳው ራስ ላይ መጫን፣ መስዋዕቱን ማረድና በእግዚአብሄር ፊት ያቀርብለት ዘንድ ደሙን ለካህኑ መስጠት አለበት ከዚያም ካህኑ ሐጢያተኛው የሐጢያቶቹን ስርየት ያገኝ ዘንድ ቀሪውን የመስዋዕት ስራ ያከናውናል::

ሰዎች ከእግዚአብሄር ሕግና ትዕዛዛት ውጭ ሐጢያት እንደሰሩ ወይም እንዳልሰሩ አያውቁም እኛ በእግዚአብሄር ሕግና ትዕዛዛት አማካይነት ራሳችንን ስንመለከት ሐጢያቶቻችንን እንገነዘባለን ሐጢያቶቻችን የሚኮነኑት በራሳችን መለኪያዎች በእግዚአብሄር ሕግና ትዕዛዛት ነው::

ተራው የእስራኤል ሕዝብ ሐጢያትን የሚሰራው ፈልጎ ሳይሆን በልቡ ውስጥ ሁሉንም አይነት ሐጢያቶች ይዞ ስለተወለደ ነው ሰው በድክመቶቹ ምክንያት የሚሰራቸው ሐጢያቶች መተላለፎች ተብለው ይጠራሉ ሐጢያት የሰውን መተላለፎችና በደሎች ሁሉ ያካትታል።

ሰብአዊ ፍጡራን ሁሉ ጎዶሎ ፍጡራን ናቸው የእስራኤል ሕዝቦችም እንደዚሁ ጎዶሎ ስለነበሩ ሐጢያተኞች ነበሩ ሐጢያቶችንም ሰርተዋል የሰው መተላለፎችና በደሎች በሙሉ በሚከተለው መንገድ ሊመደቡ ይችላሉ በአእምሮዋችን ውስጥ ክፉ አስተሳሰቦች ሲኖሩ ሐጢያቶች ተብለው ይጠራሉ እነዚህን ሐጢያቶች ስንተገብራቸው ደግሞ መተላለፎች ተብለው ይጠራሉ የአለም ሐጢያቶች ሁለቱንም ያካትታሉ።

በብሉይ ኪዳን ሐጢያቶች በእጅ መጫን ወደ መስዋዕት እንስሳው ራስ ላይ ይተላለፋሉ ከዚያ በኋላ ሐጢያተኛው ሐጢያት አልባ ይሆናል ስለዚህም በሐጢያቶቹ ምክንያት መሞት አያስፈልገውም በመሆኑም የመስዋዕቱ ስርአት የእግዚአብሄር ቅን ፍርድና ፍቅር ጥላ ነበር።

እግዚአብሄር ከአፈር ስለፈጠረን ከመጀመሪያውም አቧራ ነበርን ደምን በመሰውያው ቀንዶች ላይ ማኖርና የቀረውንም ከመሰውያው በታች ማፍሰስ ማለት እስራኤሎች ለሐጢያቶቻቸው ካሳ ከፍለዋል ሐጢያቶችንም ሁሉ ከልቦቻቸው ጽላቶች ላይ ሰርዘዋል ማለት ነው።

*«ካህኑም ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን ስቡን በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል»* በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስቡ የሚያመላክተው መንፈስ ቅዱስን ነው ስለዚህ ሐጢያቶቻችንን ለማስተሰረይ የሐጢያቶቻችንን ስርየት እግዚአብሄር ተገቢ ነው ብሎ በወሰነው መንገድ በልቦቻችን ውስጥ መቀበል ይኖርብናል።

እግዚአብሄር የሐጢያት ቁርባኖቹ ጠቦት ፍየል ወይም ጥጃ መሆን እንዳለባቸው ለእስራኤሎች ነግሮዋቸዋል የብሉይ ኪዳን የሐጢያት ቁርባኖች የተመረጡ ቁርባኖች ነበሩ ጥጃ ንጹህ እንስሳ ነበር የሐጢያት ቁርባኖች ነውር የሌለባቸው የሚሆኑበት ምክንያት ለሰው ዘር ሁሉ የሐጢያት መስዋዕት ለመሆን በመንፈስ ቅዱስ የተጸነሰውን ኢየሱስ ክረረስቶስን ስለሚገልጥ ነበር።

የብሉይ ኪዳን ሰዎች ነውር በሌለበት የሐጢያት መስዋዕት ራስ ላይ እጆቻቸውን በመጫን ሐጢያቶቻቸውን አስተላልፈዋል ካህናትም ሐጢያቶቻቸውን ለመካስ መስዋዕቱን አገልግለዋል የእስራኤል ሕዝቦች የሐጢያቶቻቸውን ስርየት ያገኙት በዚህ መልኩ ነበር።

## በስርየት ቀን የሚደረግ ሥርዓት

*የእስራኤል ሕዝቦች በሥርየት ቀን መስዋዕት ማቅረብ ያስፈለጋቸው ለምንድን ነው?*

*ምክንያቱም እስከሚሞቱ ድረስ ሐጢያት በመስራት ስለሚቀጥሉ በየቀኑ የሚያቀርቡት መስዋዕት በእግዚአብሄር ፊት ስለማይቀድሳቸው ነው።*

ነገር ግን ሐጢያት በሰሩ ጊዜ ሁሉ መስዋዕት ማቅረብ

ስለነበረባቸው ሐጢያቶቻቸውን ለማስተሰረይ የሚያስፈልጉዋቸውን መስዋዕቶች በሙሉ ማቅረብ አይቻላቸውም ስለዚህ ቀስ በቀስ ቸልተኞች ሆኑ በየቀኑ ሐጢያቶቻቸውን ማስተሰረይ ማለቂያ የሌለው ተግባር መስሎ ስለታያቸው ይህንን ስርአት ፈጽመው ማስወገድ እንዳለባቸው ተሰማቸው::

ምንም ያህል ጠንክረን ብንሞክር ለሐጢያቶቻችን የሚበቃ መሰውዋዕትን ፈጽሞ ማቅረብ አንችልም ስለዚህ ለሐጢያቶቻችን የሚሆነው እውነተኛው ናሳ እግዚአብሄር ባዘጋጀልን የደህንነት ሕግ ልባዊ በሆነው እምነታችን አማካይነት ይኖርበታል::

ምንም ያህል በእግዚአብሄር ሕግ ለመኖር ብንሞክር በድካሞቻችን ምክንያት ምን ያህል ጎዶሎዎችና ደካሞች እንደሆንን ይበልጥ ተገንዝበናል ስለዚህ እግዚአብሄር ለእስራኤል ሕዝብ የአመቱን ሐጢያቶች በአንድ ጊዜ የሚያስተሰርዩበትን መንገድ ሰጣቸው:: (ዘሌዋውያን 16:17-22)

በዘሌዋውያን ውስጥ እንዲህ ተጽፎዋል *«ይህም የዘላለም ሥርዓት ይሁንላችሁ በዚህ ቀን ትነፁ ዘንድ ማስተስረያ ይሆንላችኋልና በሰባተኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን ራሳችሁን አስጨንቋት የአገር ልጅም በእናንተ መካከል የተቀመጠ እንግዳ ሥራን ሁሉ አትሥሩበት በእግዚአብሔርም ፊት ከኃጢኣታችሁ ሁሉ ትነጻላችሁ:: ታላቅ ሰንበት ይሆንላችኋል፣ ራሳችሁንም ታዋርዳላችሁ፤ የዘላለም ሥርዓት ነው::» (ዘሌዋውያን 16:29-31)*

ስለዚህ ሊቀ ካህኑ በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን ሕዝቡ በአመቱ ውስጥ ለሰሩዋቸው ሐጢያቶች በሙሉ የስርየትን መስዋዕት ሲያቀርብ የእስራኤል ሕዝብ በአመት አንድ ጊዜ የአእምሮ ሰላምን ያገኛል ሐጢያቶቻቸው በመንጻታቸውም

አእምሮዋቸው በዚያ ቀን ሰላም ይሆናል።

ሊቀ ካህኑ አሮን የእስራኤል ሁሉ ወኪል ሆኖ በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን የስርየቱን መስዋዕት ያቀርባል በዚህ ጊዜ ሌሎቹ ካህናቶች ወደ ቅዱሱ ድንኳን መግባት አይችሉም በመጀመሪያ አሮን ለእስራኤል ሕዝብ ከማስተሰረዩ በፊት ለራሱና ለቤተሰቡ የስርየት መስዋዕትን ማቅረብ ነበረበት ምክንያቱም እርሱና ቤተሰቦቹም ሐጢያት ሰርተዋልና።

ለሕዝቡ መስዋዕትን የሚያቀርበው እንዲህ ነበር *«ሁለቱንም አውራ ፍየሎች ወስዶ በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ አጠገብ በእግዚአብሔር ፊት ያቆማቸዋል አሮንም በሁለቱ ፍየሎች ላይ ዕጣ ይጥልባቸዋል አንዱን ዕጣ ለእግዚአብሔር ሌላውንም ዕጣ ለሚለቀቅ። አሮንም የእግዚአብሔር ዕጣ የሆነበትን ፍየል ያቀርባል ሥለ ኃጢአትም መስዋዕት ያደርገዋል የመለቀቅም ዕጣ የሆነበትን ፍየል ያስተሰርይበት ዘንድ ለመለቀቅም ወደ ምድረ በዳ ይሰድደው ዘንድ በሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት ያቆመዋል።» (ዘሌዋውያን 16:7-10)*

አሮን የራሱንና የቤቱን ኃጢአት በሙሉ ካስተሰረየ በኋላ «በሁለቱ ፍየሎች ላይ ዕጣ ይጥላል» አንዱ ፍየል ለእግዚአብሔር ሲሆን አንደኛው ደግሞ ወደ ምድረ በዳ የሚባረረው *«አዛዜል»* ነው።

በመጀመሪያ ከሁለቱ አውራ ፍየሎች አንዱ ለእግዚአብሔር ይቀርባል እዚህም ሊቀ ካህኑ ሕዝቦቹን ሁሉ በመወከል ኃጢአቶቻቸውን ወደ ፍየሉ ራስ ለማስተላለፍ እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ ይጭናል።

ደሙ በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ ወዳለው የስርየት መክደኛ ይወሰድና ሰባት ጊዜ ይረጫል የእስራኤል ልጆችም ባለፈው አመት ለሠሩዋቸው ሐጢያቶቻቸው ሁሉ ይቅርታን ያገኛሉ የእስራኤል ልጆች በሐጢያቶቻቸው ከመሞት ፋንታ ሊቀ ካህኑ

ሐጢያቶችን ለሐጢያት መስዋዕት ሆኖ በቀረበው ራስ ላይ ይጭናሉ እርሱም የእነርሱን ፍርድ ይወስዳል ከዚያም አሮን በሕይወት ያለውን ፍየል በእግዚአብሄር ፊት ይሰዋዋል ለሕዝቡ የሚቀርበው መስዋዕጥ ይህ ነበር፡፡

## ለሕዝቡ

በሕዝቡ ፊትም አሮን እጆቹን በሁለተኛው ፍየል አናት ላይ በመጫን በእግዚአብሔር ፊት ይናዘዛል «አቤቱ የእስራኤል ሕዝቦች ዝሙትን፣ ምንዝርን፣ ስርቆትን፣ ወዘተ... እንዲሁም ደግሞ ጣዖትንም አምልከዋል ሰንበትን በቅደስና አልጠበቁም ስምህንም ያለ አግባብ ጠርተውታል እንዲሁም ደግሞ ሕግጋቶችህን አላከበሩም» አመቱን ሙሉ የተሰሩት የሕዝቡ ሐጢያቶች ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ ይተላለፉ ነበር፡፡

ዘሌዋውያን 16:21ን እናንብብ *«አሮንም ሁለቱን እጆቹን በህያው ፍየል አናት ላይ ይጭናል በላዩም የእስራኤልን ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢአታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል በፍየሉም ራስ ላይ ያሸክመዋል በተዘጋጀውም ሰው እጅ ወደ ምደረ በዳ ይሰድደዋል»* በዚህም ይህ ፍየል በምድረ በዳ እየተቅበዘበዘ የእስራኤላውያንን ኃጢአቶች እንደተሸከመ ይሞታል የሚለቀቀው ፍየል ማለትም *«አዛዜል»* በዕብራይስጥ «ማውጣት» ማለት ነው ለሐጢያት የቀረበው መስዋዕት በሕዝበ እስራኤል ሁሉ ምትክ በእግዚአብሄር ፊት ይባረራል ማለት ነው፡፡

የእስራኤላውያን ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ፍየሉ የተላለፈው በአሮን እጆችን የመጫን ሥርዓት ነበር በዚህ መንገድ እስራኤሎች ከሐጢያቶቻቸው ይቅርታን አግኝተዋል ሊቀ ካህኑ

በፍየሉ ላይ እጆቹን ሲጭን ሲመለከቱና ወደ ምድረበዳ ሲጋዝ ሲያዩ በስርየቱ ስርአት ያመኑ እስራኤሎች በሙሉ ለሐጢያቶቻቸው ስርየትን ስለ ማግኘታቸው እርግጠኞች ነበሩ የብሉይ ኪዳን ስርአቶች በሙሉ የአዲስ ኪዳን «ዳግም የመወለድ ወንጌል» ጥላ ነበሩ::

በብሉይ ኪዳን እጆችን መጫንና የመስዋዕቱ ደም ከሐጢያት የሚዳንባቸው ወንጌል ነበሩ ይህ በመሰረቱ በአዲስ ኪዳንም ያው ነው::

## በአዲስ ኪዳን ያለው የቤዛነት ወንጌል

በአዲስ ኪዳን የሕዝቡ ሐጢያቶች በሙሉ ስርየትን ያገኙት እንዴት ነበር?

በማቴዎስ 1:21-25 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«እርሱም ሕዝቡን ከኃጢአታቸው ያድናቸዋልና ስሙን ኢየሱሰ ትለዋለህ በነቢይ ከጌታ ዘንድ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈፀም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኖአል ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው የሚል ነው ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቅቶ የጌታ መልአክ እንዳዘዘው አደረገ እጮኛውንም ወሰደ የበኩር ልጅዋንም እስክትወልድ ድረስ አላወቃትም ስሙንም ኢየሱስ አለው::»*


ጌታችን ኢየሱስ የሰውን ዘር ሁሉ ከሐጢያት ለማዳን በአማኑኤል ስም ወደዚህ አለም መጣ ኢየሱስ የሰውን ሐጢያቶች በሙሉ ለመውሰድ መጣ የሰው ዘር አዳ ለመሆንም የሰው ስጋ ለ ብሶ መጣ ደህንነታችንንም አጠናቀቀ ከሐጢያትም ለዘላለም ነጻ አወጣን::

## ዳግም የመወለጃው ወንጌል

ኢየሱስ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ነጻ ያወጣን እንዴት ነበር? ይህንን ያደረገው በጥምቀቱ አማካይነት ነው እስቲ ማቴዎስ 3:13ን እንመልከት *«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ከውኃ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው አለ::» (ማቴዎስ 3:13-17)*

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ 30 አመት ሲሆነው በዮርዳኖስ ወዳለው ወደ አጥማቂው ዮሐንስ መጣ በእርሱም ተጠመቀ የሐጢያተኞችንም ሐጢያቶች ሁሉ ወሰደ እንዲህ በማድረጉም የእግዚአብሄርን ጽድቅ ፈጸመ::

## ኢየሱስ በዮርዳኖስ የተጠመቀው ለምንድን ነበር?



አሁን ሰማያዊው ሊቀ ካህን ከሰው ዘር የመጨረሻ ሊቀ ካህን ጋር የተገናኘበትን ትዕይንት እንመልከት እዚህ ላይ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ባስተሰረየው ጥምቀት አማካይነት የእግዚአብሄርን ጽድቅ ማየት እንችላለን፡፡

ኢየሱስን ያጠመቀው አጥማቂው ዮሐንስ ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ እጅግ የላቀ ሰው ነበር ኢየሱስ መስክሮዋል ሊቀ ካህኑ አሮን በስርየት ቀን እጆቹን በሐጢያት መስዋዕቱ ላይ በጫነ ጊዜ የሕዝቡ ሐጢያቶች ስርየትን እንዳገኙ ሁሉ በአዲስ ኪዳንም ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ስርየትን አግኝተዋል፡፡

ዳግም የመወለጃው ወንጌል ለሐጢያቶች ሁሉ ምሉዕ የሆነ የስርየት ወንጌል ነው ስለዚህ በኢየሱስ ጥምቀት በኩል የሆነው የቤዛነት ወንጌል የአለምን ሕዝብ ሁሉ ያዳነ እግዚአብሄር ጽድቁን ለመፈጸም ያስቀመጠው ወንጌል ነው ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች ለማስተሰረይ እጅግ ተገቢ በሆነ መንገድ ተጠመቀ፡፡

«ጽድቅን ሁሉ» መፈጸም ማለት ምን ማለት ነው? ይህ ማለት እግዚአብሄር የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ እጅግ ተገቢ በሆነ መንገድ አንጽቶዋቸዋል ማለት ነው *«የእግዚአብሔር ፅድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና፡፡» (ሮሜ 1:17)*

የእግዚአብሔር ፅድቅ በአጥማቂው ዮሐንስ በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመሞት የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ያስወግድ ዘንድ አንድ ልጁን ወደዚህ ምድር ለመላክ በወሰነው ውሳኔው ውስጥ ታይቷል፡፡

በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሔር ፅድቅ የተገለፀው በኢየሱስ ጥምቀትናበደሙ ነው እኛ ፃድቃን የሆንነው ኢየሱስ ከሁለት ሺህ አመታት በፊት በዮርዳኖስ ወንዝ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ስለወሰደ ነው የእግዚአብሄርን ደህንነት በልባችን ስንቀበል የእግዚአብሄር ፅድቅ በትክክል ይፈፅማል፡፡

*«ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ከውኃ ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው አለ።» (ማቴዎስ 3:15-17)*

ይህ ምንባብ የልጁ ጥምቀት የደህንነትን ፅድቅ ሁሉ እንደፈፀመ እግዚአብሄር ራሱ መመስከሩን ይገልጣል እግዚአብሄር «በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀው ኢየሱስ በእርግጥም ልጄ ነው» እያለ ነው ልጁ የተጠመቀው ለሰው ዘር ሁሉ ስርየትን ለመስጠት እንደሆነ እግዚአብሄር መስክሮዋል ይህንን ያደረገው የተቀደሰው የልጁ የኢየሱስ ስራ ከንቱ እንዳይሆን ነው።

ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅና የዓለም ሐጢያተኞች አዳኝ ነው እግዚአብሔር *«በእርሱ ደስ የሚለኝ»* ብሎዋል ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ መታዘዙና በጥምቀቱ አማካይነት የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ መውሰዱ እውነት ነው።

ጥምቀት የሚለው ቃል ትርጉሙ «መታጠብ፣ ማስተላለፍ፣ መቀበር» ማለት ነው ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ኃጢአቶቻችን በሙሉ ወደ እርሱ ስለተላለፉ አሁንም ቢሆን ከኃጢአቶቻችን እንድን ዘንድ በዚህ ወንጌል ማመን አለብን።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉት የደህንነት ትንቢቶች ሁሉ ፍጻሜ በአዲስ ኪዳን የተከናወነው በኢየሱስ ጥምቀት አማንይነት ነበር ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ያሉት ትንቢቶች በመጨረሻ በአዲስ ኪዳ ን ውስ ወዳጆቻቸውን አግኝተዋል በብሊይ ኪዳን የእስራኤል ሕዝብ በአመት አንድ ጊዜ የሐጢያቶቻቸውን ስርየት እንዳገኙ ሁሉ በአዲስ ኪዳንም የሕዝቡ ሐጢያቶች ወደ ኢየሱስ ተላልፈው ለዘላለም ነጽተዋል።

ዘሌዋውያን 16:29 የማቴዎስ 3:15 ፍፃሜ ነው ኢየሱስ የተጠመቀው የሰው ልጆችን ኃጢአት በሙሉ ለመውሰድ ነበር ለጥምቀቱ ምስጋና ይግባውና ዘላለማዊ በሆነው የሐጢያት ይቅርታ የሚያምኑ ሁሉ ይድናሉ ኃጢአቶቻቸውም በሙሉ ከልባቸው ጽላቶች ላይ ተደምስሰዋል::

ምንም ያህል የተቀደሰ ሕይወት ብትኖሩም የኢየሱስን ጥምቀትና የመስቀል ላይ ሞቱን እውነት በልባችሁ ካልተገነዘባችሁና ካላመናችሁ ፈጽሞ ከሐጢያቶቻችሁ ልትነጹ አትችሉም የእግዚአብሄር ቃል የተፈጸመውና ሐጢያቶቻችን የተደመሰሱት በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት ብቻ ነው በሌላ አነጋገር እውነተኛ ደህንነት የሚገኘው በሐጢያቶቻችንን ቤዛነት አማካይነት በኢየሱስ ጥምቀት አማንይነት ነው::

አሁን የምታደርጉት ምንድን ነው? ከልባችሁ ይህንን ደህንነት ትቀበላላችሁ ወይስ አትቀበሉም? ይህ የሰው ልጅ ቃል ሳይሆን የእግዚአብሔር ቃል ነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሞተው በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችሁን ሁሉ ስለወሰደ ነው::


በሮሜ 8:3-4 ላይ እንዲህ ተጽፏል *«ከሥጋ የተነሳ ስለደከመ ለሕግ ያልተቻለውን እግዚአብሔር የገዛ ልጁን በኃጢአተኛ ሥጋ ምሳሌ በኃጢአትም ምክንያት ልኮ አድርጎአልና እንደ መንፈስ ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋ ፈቃድ በማንመላለስ በእኛ የሕግ ትእዛዝ ይፈጸም ዘንድ ኃጢአትን በሥጋ ኮነነ::»*

እኛ ከሥጋ ድካም የተነሳ የእግዚአብሄርን ሕጎችና ትዕዛዛቶች መጠበቅ ስለማንችል ኢየሱስ የሥጋን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ በመውሰድ አስወገዳቸው ይህ የኢየሱስ ጥምቀት እውነት ነው የኢየሱስ ጥምቀት በመስቀል ላይ ለሚሆነው ሞቱ መንገድ ጠረገ ይህ ትክክለኛው የእግዚአብሄር

ወንጌል ጥበብ ነው::

በኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞት ብቻ ታምኑ የነበራችሁ ከሆናችሁም አሁኑኑ ተመልሳችሁ በኢየሱስ ጥምቀት አማካንይነት የደህንነትን ወንጌል በልባችሁ ተቀበሉ የእግዚአብሄር ልጆች መሆን የምትችሉት ያኔና ያኔ ብቻ ነው::

## የጥንቱ ወንጌል




ይህ እግዚአብሄር የገለጠልን የኢየሱስ ጥምቀት የሞቱና የትንሳኤው ወንጌል ነው ኢየሱስ በዮርዳኖስ በመጠመቅ ሐጢያትን በአንድ ጊዜ አስወግዶ በዚህ አማካይነት ይህንን እውነት ለሚያምኑ ሁሉ ደህንነትን ሰጥቷል በዚህ ላይ ባለን እምነትም ወደፊት የምንሰራቸው ሐጢያቶቻችንም በሙሉ ተወግደዋል::

በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ የሚያምን ሁሉ ለዘላለም ከዓለም ኃጢአቶች በሙሉ ይድናል ታምናላችሁን? መልሳችሁ «አዎ! አምናለሁ» ከሆነ ያን ጊዜ በተጨባጭ ፃድቃን ትሆናላችሁ::

ኢየሱስ ከተጠመቀ በኋላ የሆኑትን ነገሮች እናጠቃልል

በዮሐንስ 1:29 ላይ *«እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»* ተብሎ ተፅፏል፡፡

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሄር በግ እንደነበር አጥማቂው ዮሐንስ መስክሮዋል አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ ባጠመነቀው ጊዜ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ አስተላልፎዋል አጥማቂው ዮሐንስ ራሱ ኢየሱስን ስላጠመቀው *«እነሆ የአለምን ሐጢያት የሚያስወግድ የእግዚአብሄር በግ»* ብሎ መመስከር ቻለ ኢየሱስ ተጠምቆ የአለምን ሐጢያቶች ወሰደ ዳግም የመወለድ ወንጌል ይህ ነው፡፡መጥምቁ ዮሐንስ ኢየሱስ የዓለምን ኃጢት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ መሆኑን መስክሯል፡፡ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀ ጊዜ መጥምቁ ዮሐንስ የዓለምን ኃጢኣት በሙሉ ወደ እርሱ አስተላልፏል፡፡ ስለሆነም መጥምቁ ዮሐንስም ራሱ ኢየሱስን ያጠመቀ በመሆኑ *«እነሆ የዓለምን ኃጢኣት የሚያስወግድ የእግዝኢብሔር በግ!»* ብሎ ሊመሰክር ችሏል፡፡ ኢየሱስ በጥምቀቱ የዓለምን ኃጢኣት በሙሉ ወደ ራሱ አስተላለፏል፤ ይህም ዳግም የመወለጃው ወንጌል ነው፡፡

| አዳም ⟶ | አብርሃም ⟶ | የኢየሱስ ጥምቀት ⟶ | አሁን ⟶ | የዓለም መጨረሻ |
|---|---|---|---|---|
| 4000 ዓ.ዓ. | 2000 ዓ.ዓ. | 30 ዓ.ም. | 2000 ዓ.ም. | ? ዓ.ም. |

⟸ የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ⟹

*«እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!» (ዮሐንስ 1:29)* ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ በጥምቀቱ አማካኝነት ወስዷል፡፡

ከተወለዳችሁ ጊዜ ጀምሮ እስከ አስር ዓመታችሁ ድረስ

የሰራችኋቸው ኃጢአቶች ከዓለም ኃጢአቶች ጋር ተጨምረዋል እነዚያ ኃጢአቶችም ወደ ኢየሱስ እንደተላለፉ ታምናላችሁን? —አዎን አምናለሁ፡፡— ከ11-20 ዓመት እድሜያችሁ ድረስ የሰራችኋቸው መተላለፎችስ? እነዚያም ኃጢአቶችም ወደ ኢየሱስ መተላለፋቸውን ታምናላችሁን? —አዎን እናምናለን፡፡—

ወደ ፊት የምትሰሯቸውም ኃጢአቶች ከዓለም ኃጢአቶች ጋር የሚቆጠሩ መሆኑንስ ታውቃላችሁን? —አዎን ከዓለም ኃጢአቶች ጋር ይጨመራሉ — እንደዚያ ከሆነ፣ እነርሱም ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል ማለት ነዋ? —አዎን ተላልፈዋል— የዓለም ኃጢአቶች በሙሉ በጥምቀቱ አማካኝነት ወደ ኢየሱስ መተላለፋቸውን ታምናላችሁን? —አዎን እናምናለን —ከዓለም ኃጢአቶችስ ለመዳን ትፈልጋላችሁን? መዳን ከፈለጋችሁ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ እመኑ አንዴ ካመናችሁ ትድናላችሁ ይህን ታምናላችሁን? ይህ ዳግም ከመወለድ የሚገኝ እውነተኛ ደህንነት ነው የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ ዳግም ለመወለድ የሚያበቃ እውነተኛ ወንጌል ነው ለአለም ሐጢያቶች ሁሉ ከእግዚአብሄር የተሰጠ በረከት ነው፡፡

በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ደሙ አማካይነት ዳግም በመወለድ ደህንነት ማመንና የእርሱን ፍቅር ቀና ብሎ መመልከት እውነተኛ እምነት መያዝና በእርግጠኝነትም ዳግም መወለድ ነው እናንተ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጻፉትን ቃሎች መቀበል ብቻ ይኖርባችኋል፡፡

# ኃይማኖትና እምነት

*ዳግም በተወለዱ ልቦች ውስጥ ምን ምስክር አለን?*

*ኢየሱስ ኃጢአቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱና በደሙ ማስወገዱን ማመናችን ነው።*

የኃይማኖት ትርጉም ንፁህ የሆነውን የእግዚአብሄር ቃል ትቶ በራስ አስተሳሰብ በኢየሱስ ማመን ነው ከሐጢያት መዳን ግን ከራስ አስተሳሰቦች የሚመነጭ አይደለም እምነት ማለት የራስን አስተሳሰብ ክዶ በብሉይና በአዲስ ኪዳን ቃሎች በሙሉ ማመን ማለት ነው በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፈውን እንዳለ መውሰድና በውሃና በደም አማካይነት ደህንነትን መቀበል ነው ይህም የሚሆነው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ በማመን ነው አንድ ሰው ሊድን የሚችለው የእውነተኛ ውን ወንጌል ጥበብ በልቡ በመቀበል ነው።

ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ሐጢያቶቻችን ሊሻገሩ አይችሉም ደም ሳይፈስም ስርየት የለም ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን ወደ መስቀሉ ከመውሰዱና ደሙን ለእኛ ከማፍሰሱ በፊት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ ራሱ አሻግሮዋል በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ እንደዚሁም በወንጌል አማካይነት ዳግም ስለመወለድ ስናምን ከዚህ አለም ሐጢያቶች በሙሉ ነፃ እንወጣለን።

እውነተኛ እምነት ማለት ኢየሱስ ክርስቶስ በተጠመቀ ጊዜ

ሙሉ በሙሉ ከኃጢአቶቻችን እንዳነፃን ማመን ማለት ነው ለሐጢያቶቻችን ሁሉ የተፈረደውን ፍርድ በመስቀል ላይ እንደወሰደው ማመን ማለት ነው ፅድቅን በተሞላው የእግዚአብሄር ደህንነት ማመን አለብን እግዚአብሄር አብዝቶ ስለወደደን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ አማካይነት አዳነን በዚህ ወንጌል ስናምን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ እንድናለን ከፍርድ ነፃ ወጥተን በእግዚአብሄር ፊት ፃድቃን እንሆናለን::

«አቤቱ አምናለሁ እኔ ደህንነት የማይገባኝ ብሆንም በኢየሱስ ጥምቀት፣ በስቅለቱና በትንሳኤው አምናለሁ» ዳግም ለተወለድንበት የወነጌል በረከት ጌታን ማመስገን ይኖርብናል ባልተበረዘው ዳግም የመወለድ ወንጌል ማመን እውነተኛ እምነት ነው::

ዳግም የምንወለድበት እውነት ይህ ነው *«እንግዲያስ እምነት በመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10:17) «እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው» (ዮሐንስ 8:32)* እውነቱን በትክክል ማወቅ ይኖርብናል ይህንን በሚመሰክሩት ውሃ፣ ደምና መንፈስም ማመን ይኖርብናል:: (1ኛ ዮሐንስ 5:5-8)

*«እውነትም አርነት ያወጣችኋል»* እነዚህ ኢየሱስ ስለ ውኃውና ስለ ደሙ የተናገራቸው ቃሎች ናቸው አርነት ወጥታችኋልን? እኛ ታማኞች ነን ወይስ ኃይማኖተኞ ነን? ኢየሱስ የሚፈልገው ኢየሱስ የሚፈልገው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም በሚያስወልደው ወንጌል ላይ እምነት ያላቸውን ሰዎች ብቻ ነው::

በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደም የምታምኑ ከሆናችሁ በልባችሁ ኃጢአት የሌለባችሁ ቅዱሳን ናችሁ ማለት ነው ነገር ግን በኢየሱስ የምታምኑት የሐይማኖት

ክፍል አድርጋችሁት ከሆነ አሁንም እየኖራችሁ ያላችሁት በሐጢያት ውስጥ ነው ምክንያቱም በኢየሱስ ደህንነት ሙሉ እምነት የላችሁምና የሐይማኖት ሰዎች በየጊዜው የንስሐ ፀሎት በመፀለይ ከሐጢያቶቻቸው ለመዳን ይሞክራሉ::

ከዚህ የተነሳ እንደ እነዚህ አይነት ሰዎች ሙሉ በሙሉ ከሐጢያቶቻቸው ሊድኑ አይችሉም በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ንስሐ ቢገቡ እንኳን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ በሆነው ሞቱ አማካይነት የሚገኘውን የተሟላ የሐጢያት ስርየት መተካት አይችሉም የወደፊቶቹን የአለም ሐጢያቶች እንኳን ሳይቀር ባስወገደው የኢየሱስ ወንጌል በማመን እንዳን::

ደግሜ እነግራችኋለሁ በየቀኑ ንስሐ መግባት ዳግም የምንወለድበትን ወንጌል በጭራሽ ሊተካው አይችልም ክርስቲያኖች በሙሉ ዳግም ለመወለድ በሚያበቃው ወንጌል አማካይነት ለሐጢያቶቻቸው ስርየትን ለማግኘት አሁኑኑ ማመን ይኖርባቸዋል::

ሙሉ በሙሉ ለኃጢኣቶቻችን ንስሐ መግባት አንችልም ንስሐ ሰውን ወደ እግዚአብሄር መምራት አይችልም ነገር ግን ነፍሱን ሊያፅናና ይችላል የሐሰት ንስሐ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ከቁም ነገር የማያስገባ የአንድ ወገን ኑዛዜ ነው እግዚአብሄር ከእኛ የሚጠብቀው ይህንን አይደለም::

እውነተኛ ንስሐ ምንድን ነው? ወደ እግዚአብሔር መመለስ ነው ኢየሱስ ወደሰጠው የደህንነት ቃል መመለስና ቃሉንም እንደተፃፈው ማመን ማለት ነው እኛን የሚያድነን ወንጌል የኢየሱስ ጥምቀት፣ ስቅለትና ትንሳኤ ወንጌል ነው በዚህ ወንጌል ሙሉ በሙሉ ስናምን እንድናለን የዘላለምንም ሕይወት እናገኛለን::

ዳግም የምንወለድበት ጥበበ-ወንጌል ይህ ነው ይህም ዳግም እንድንወለድ በሚፈቅድልን በኢየሱስ ጥምቀት፣ በደሙና

በእግዚአብሄር መንግስት ወንጌል ማመን ነው::

ኢየሱስ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ዳግም መወለድ እንዳለብን ሲነግረን በእርሱ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ሞት በማመን እንደገና መወለድ እንዳለብን እያስረዳን ነበር ያን ጊዜ ወደ እግዚአብሄር መንግስት መግባትና መኖር እንችላለን በቃሉ ማመን ይኖርብናል ለሐጢያታችን ስርየት የሚመሰክሩት ሁለቱ ነገሮች የኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ ዳግም የምንወለድባቸው ቃሎች ናቸው::

አሁንስ ዳግም በምንወለድበት ወንጌልና በሐጢያቶቻችን ስርየት ታምናላችሁን? በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ የሚኖረን እምነት ከዓለም ኃጢኣት በሙሉ ያድነናል በዚህ እምነትም ዳግም ልንወለድ እንችላለን መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱና በደሙ የዓለምን ኃጢኣት በሙሉ እንዳስወገደ የሚነግረን ከሆነ በዚህ አምነን ዳግም የማንወለደው ለምንድን ነው?

እነዚያ ዳግም ለመወለዳችን ምስክሮች በሆኑት ሁለት ነገሮች በኢየሱስ ጥምቀትና በስቅለቱ የሚያምኑ በትክክል ዳግም ተወልደዋል በእግዚአብሄር ልጅ የሚያምንም በራሱ ምስክር አለው::

የጦር አዛዡ ንዕማን ሙሉ በሙሉ ከለምፁ ለመፈወስ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ሰባት ጊዜ እንደተጠመቀ ሁሉ (2ኛ ነገስት ምዕራፍ 5) ኢየሱስም በዮርዳኖስ የአለምን ሐጢያቶች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳስወገደና ከዚያ የተነሳም የዘላለም ሕይወት እንደሰጠን ማመን ይኖርብናል::

ኢየሱስ ስለወደደን ከአለም ሐጢያቶች ሁሉ ድነን የሐጢያት ስርየት በሚያስገኘው ወንጌል በማመን የዘላለም ሕይወት እናገኛለን ሁላችንም ዳግም ለመወለድ በሚያበቃው ወንጌል በማመን የእግዚአብሄርን ደህንነት እናግኝ:: ✉

# ስብከት 2

# በክርስትና ውስጥ ያሉ

# አስመሳይ ክርስቲያኖችና

# መናፍቃን

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።



«ነገር ግን ሐሰተኞች ነቢያት ደግሞ በሕዝቡ መካከል ነበሩ እንዲሁም በመካከላችሁ ደግሞ ሐሰተኞች አስተማሪዎች ይሆናሉ፤ እነርሱም የዋጃቸውን ጌታ እንኳን ክደው የሚፈጥንን ጥፋት በራሳቸው ላይ እየሳቡ የሚያጠፉ ነቀፋን አሹልከው ያገባሉ፤ ብዙዎችም በመዳራታቸው ይከተሉአቸዋል፤ በእነርሱም ጠንቅ የእውነት መንገድ ይሰደባል፡፡ ገንዘብንም በመመኘት በተፈጠረ ነገር ይረቡባችኋል፤ ፍርዳቸውም ከጥንት ጀምሮ አይዘገይም ጥፋታቸውም አያንቀላፋም፡፡» (2ኛ ጴጥሮስ 2፡1-3)

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡

# በክርስትና ውስጥ ያሉ አስመሳይ ክርስቲያኖችና መናፍቃን

**« ኢሳይያስ 28:13-14 »**

**«ስለዚህ ሄደው ወደ ኋላ እንዲወድቁ እንዲሰበሩም ተጠምደው እንዲያዙ የእግዚአብሔር ቃል ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ይሆንላቸዋል ስለዚህ በኢየሩሳሌም ያለውን ሕዝብ የምተገዙ ፌዘኞች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ::»**

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ መናፍቅነት

*መፅሐፍ ቅዱስ «መናፍቅ»ን እንዴት ይገልጸዋል?*

*መጽሐፍ ቅዱስ መናፍቅ ማለት በኢየሱስ እያመነ በልቡ ኃጢአት ያለበት ሰው ነው ይላል::*

በአሁኑ ጊዜ በተለይም በማደግ ላይ ባሉ ሃገራት ብዙ አሳሳች ዜናዎችን የሚያሰራጩ ዜና ዘጋቢዎች አሉ ጋዜጠኞች

ይመስላሉ ነገር ግን ብዙውን ጊዜ ሰለባዎቻቸው ያደረጉትን ድርጊት እንደሚያጋልጡ በመዛት ከተጠቂዎቻቸው ገንዘብ ይዘርፋሉ አስመሳይ የሚለው ቃል እውነተኛ የሚመስል ነገር ግን ትክክለኛ ያልሆነ ነገር ማለት ነው በሌላ አነጋገር እውነተኛ ማንነቱ ከውጫዊ ገፅታው ሙሉ በሙሉ የተለየ አንድ ነገርን ይጠቁማል::

«መናፍቅ» እና «አሳሳች» የሚባሉት ቃላት በተለይም በክርስትያን ቤተ ክርስትያኖች ይዘወተራሉ::

መናፍቅ ምን ማለት እንደሆነና «አስመሳይ» የተባለውም ምን እንደሆነ ለመግለጥ ያሉት አሳማኝ ማብራሪያዎች ጥቂት ናቸው እነዚህን አስተሳሰቦች ከመፅሐፍ ቅዱስ ጋር በጥብቅ በተቆራኘ መልኩ የሚስተምሩ ብዙም የሉም::

በዚህ የተነሳ መፅሐፍ ቅዱስ «ኑፋቄን» እንዴት እንደገለጠው ለማብራራትና በርዕሰ ጉዳዩ ላይ አንዳች ብርሃንን ለመፈንጠቅ እገደዳለሁ በቀን ተቀን ሕይወት ውስጥም ያሉትን አንዳንድ የኑፋቄ ምሳሌዎች መጠቆምና አብረን እንድናስባቸው ማድረግ እሻለሁ በእግዚአብሄር አምናለሁ የሚል ማንኛውም ሰው በሕይወቱ ቢያንስ አንድ ጊዜ ስለ ኑፋቄ ማሰብ ይኖርበታል::

ቲቶ 3:10-11 መናፍቅ የሆነን ሰው ሐጢያትን በማድረግ የተጠፈረ ራሱን የኮነነ እረፍት የለሽ ግለሰብ አድርጎ ይገልጠዋል መናፍቅ ራሱን ሐጢያተኛ አድርጎ የኮነነ ግለሰብ ነው ስለዚህ በኢየሱስ እያመኑ በልቦቻቸው ውስጥ ግን ሐጢያት ያለባቸው በእግዚአብሄር ፊት መናፍቃን ናቸው::

ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት ኃጢኣቶችን በሙሉ ወስዷል:: መናፍቃን ግን ለሐጢያተኞች ደህንነትን በሚያመጣው እውነተኛ ወንጌል ለማመን እምቢተኞች በመሆናቸው ከሐጢያተኞች ጎራ ተሰልፈው ራሳቸውን ይኮንናሉ::

መናፍቃን ናችሁን? ትክክለኛና የታመነ ሕይወት መኖር ከፈለግን ስለዚህ ነገር ማሰብ ይኖርብናል::

ስለ ውኃውና ስለ መንፈሱ ወንጌል እስካሁን ሳትሰሙ በኢየሱስ ብታምኑ እንኳን ራሳችሁን ሐጢያተኛ አድርጋችሁ እየኮነናችሁ አይደለምን? ራሳችሁን እንደ ሐጢያተኛ የምትቆጥሩ ከሆነ ፍፁም የሆነውን የእርሱን ደህንነትና የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመናቅ ኢየሱስን እያሳዘናችሁ ነው::

አንድን ሰው በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኛ ብሎ መጥራት ያ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም ማለት ነው:: እነዚያ «ጌታ ሆይ! ኃጢኣተኛ ነኝ!» ብለው የሚናዘዙት ሰዎች እምነታቸውን እንደገና ማጤን ይኖርባቸዋል::

ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ መሉ በሙሉ ከዘላለም ኩነኔ አድኖዋችሁ ሳለ በኢየሱስ እያመናችሁ እንዴት ሐጢያተኞች ነን ትላላችሁ? ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችሁን በሙሉ ወስዶ በመስቀል ላይ ፈርዶባቸው ሳለ ነፃ የሆነውን የደህንነት ስጦታ በመካድ እንዴት ራሳችሁን እንደ ሐጢያተኛ ትቆጥራላችሁ?

እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች መናፍቃን ናቸው ምክንያቱም ከእግዚአብሄር ቃል ተነጥለው ሐጢያተኞች ለመሆን ፈቅደዋል በእግዚአብሄር ፊት መናፍቅ መሆንን ለማስወገድ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ማወቅ ይኖርባችኋል ማንም በኢየሱስ የሚያምን ሆኖ ዳግም ውልደትን ያላገኘ ሁሉ በልቡ ኃጢአት ስላለበት መናፍቅ ነው::

እግዚአብሔር የራሳችንንም ጨምሮ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ስላስወገደ ይህንን የደህንነት በረከት ቸል ብንል በእግዚአብሄር ፊት መናፍቃን ነን በእርግጥ ፃድቃን ለመሆን ከፈለግን በኢየሱስ የጥምቀት ወንጌልና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ማመን ይኖርብናል::

# የመናፍቅነት መነሻ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

*ለአንድ ካህን በጣም አስፈላጊው መስፈርቱ ምንድን ነው?*

*ዳግም መወለድ አለበት::*

1ኛ ነገስት 12:25-26ን እንመልከት *«ኢዮርብዓምም በተራራማው በኤፍሬም አገር ሴኬምን ሠርቶ በዚያ ተቀመጠ፤ ደግሞም ከዚያ ወጥቶ ጵኒኤልን ሠራ ኢዮርብዓምም በልቡ:- አሁን መንግስቱ ወደ ዳዊት ቤት ይመለሳል»* ኢዮርብዓም ከሰለሞን ባሮች አንዱ ነበር ሰሎሞን በኋለኛው ዘመኑ ከእግዚአብሄር በራቀ ጊዜ ኢዮርብዓም በንጉሱ ላይ አመፀ በኋላም የሰለሞን ልጅ በሆነው በሮብአም ዘመን የአስሩ የእስራኤል ነገዶች ንጉስ ሆነ::

ኢዮርብዓም የእስራኤል ንጉስ ሲሆን የመጀመሪያ ተግባሩ ሕዝቦቹን ቤተ መቅደሱ ወደሚገኝበት ወደ ይሁዳ እንዳይመለሱ ማድረግ ነበር::

ይህንን ለማድረግም አዲስ ሃሳብን ይዞ ብቅ አለ:: በቤቴልና በዳን ሁለት የወርቅ ጥጆችን ሰርቶ ሕዝቡ እነሱን እንዲያመልክ አዘዘ:: 1ኛ ነገስታት 12:28 *«ንጉሱ ተማከረ ሁለት የወርቅ ጥጆችንም አሰራ»* አንዱን በቤቴል ሌላውን ደግሞ በዳን አቆመ ይህንን ማድረግ አስከፊ ሐጢአት ቢሆንም ለሕዝቡ እንዲሰግዱላቸው ነገራቸው እንዲሁም ደግሞ አምልኮውን የሚመሩ ካህናትንንም መርጦ ነበር::

*«ከዚህም በኋላ ኢዮርብዓም ከክፉ መንገድ አልተመለሰም ነገር ግን ለኮረብታዎቹ መስገጃዎች አብልጦ ከሕዝብ ሁሉ*

*ካህናትን አደረገ የሚወድደውንም ሁሉ ይቀድስ ነበር እርሱም ለኮረብታዎች መስገጃዎች ካህን ይሆን ነበር» (1ኛ ነገስት 13:33)* ይህ የመናፍቅነት መነሻ ነው::

ዛሬም እንዲሁ መናፍቃን የእግዚአብሄርን ስራ ለመስራት ራሱን በፈቃደኝነት ያቀረበውን ማንኛውንም ሰው ለክህነት ይሾሙታል ከስነ መለኮት ትምህርት ቤት የተመረቀ ማንኛውም ሰው ከውሃና ከመንፈስ ባይወለድ እንኳን አገልጋይ ወንጌላዊ ሚሲዮናዊና ሽማግሌ ሊሆን ይችላል::

ዳግም ያልተወለደ ሰው እንዴት አገልጋይ ሊሆን ይችላል? የዚህን አይነቱ ሰው ካህን ሆኖ ከተሸመ እርሱን የመረጠችው ቤተክርስቲያን የመናፍቃን ማምረቻ ፋብሪካ ትሆናለች::

እስቲ ስለ ኑፋቄ አመጣጥ ደግመን እናስብ በመጀመሪያ ኢዮርብዓም የፖለቲካዊ ስልጣኑን ለማራዘም ሲል በእግዚአብሔር ፋንታ የወርቅ ጥጆችን ምትክ አድርጎ አቆመ ሁለተኛ ካህን ለመሆን ፈቃደኛ የሆነውን ማንኛውንም ሰው ቀደሰ በሌላ አነጋገር ተራ የሆኑ ሰዎችን ካህናት አድርጎ ቀደሰ ዛሬም ይኸው ምግባር ቀጥሎዋል::

የመናፍቅነት ታሪክም ከኢዮርብዓም ጊዜ አንስቶ እንደቀጠለ ነው ማንም ከውኃና ከመንፈስ ዳግም ያልተወለደ ሰው ካህን ሊሆን አይገባውም::

ማንም ከስነ ኃይማኖታዊ ኮሌጅ የተመረቀ ሁሉ አገልጋይ ወይም ደግሞ ወንጌላዊ ሊሆን ይችላልን? በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ሳያገኙ እግዚአብሔርን ለማገልግል ይችላሉን? በፍፁም አይችሉም የእግዚአብሔር አገልጋይ ሊሆኑ የሚችሉት ከእርሱ ተቀባይነትን ያገኙት ብቻ ናቸው እነዚያ በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ያገኙትም ከውኃና ከመንፈስ ዳግም የተወለዱት ብቻ ናቸው::

በ1ኛ ነገስት 12:25-26 እና በ1ኛ ነገስት ምዕራፍ 13 ላይ

እንደተፃፈውም የኢዮርብዓም ኃጢኣት እግዚአብሔርን አስቆጥቶታል ሁላችንም ይህን ታሪክ ልናውቅ ይገባናል ይህን የማታውቁ ካላችሁም ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሙሉውን ታሪክ ልትረዱት ይገባል::

በአገልግሎታችሁ እግዚአብሔርን በወርቅ ጥጃዎች መተካትና አለመተካታችሁን አስቡበት እናንተ በማንኛውም አጋጣሚ ሊሆን ይችላል ተከታዮቻችሁ ከውኃና ከመንፈስ ወደሆነው ዳግም የመወለድ ወንጌል እንዳይመለሱ በአጋጣሚ እንኳን በምድራዊ በረከቶች ላይ ትኩረት ታደርጋላችሁን?

በኢየሱስ የሚያምኑ ከሆነ ከበሽታቸው እንዲሚድኑ ለተከታዮቻችሁ ትናገራላችሁን? በባህሪያቸውም ሊባረኩ እንደሚችሉ ትነግራችኋላችን? ዳግም ያልተወለዱትን የቤተክርስትያናችሁ አገልጋዮችና ሠራተኞች አድርጋችሁ በመሾም ትክክለኛው የሐይማኖት ድርጅት የእናንተ ብቻ እንደሆነ ትናገራላችሁን? እንደዚህ የምታደርጉ ከሆነ በእግዚአብሄር ፊት የኢዮርብዓምን ኃጢአት እየሰራችሁና ቁጣውን እየቀሰቀሳችሁ ነው::

## መናፍቃን የወርቅ ጥጆችን አምላክ ያመልካሉ

ዛሬም ጭምር የወርቅ ጥጃዎችን የሚያመልኩ ብዙ መናፍቃን አሉ ሰሎሞን ሊባረክ የቻለው ለእግዚአብሔር በሺህ የሚቆጠር መስዋዕትን ስላቀረበለት ነው ብለው ሲናገሩ ይሰማሉ 1ኛ ነገስት 3:3-5 እንደሚለውም *«ሰሎሞንም እግዚአብሔርን ይወድድ ነበር በአባቱም በዳዊት ስርዓት ይሄድ ነበር ብቻ በኮረብታ መስገጃ ይሠዋና ያጥን ነበር ገባዖን ዋና የኮረብታ መስገጃ ነበረችና ንጉሡ ይሠዋ ዘንድ ወደዚያ ሄደ ሰሎሞንም*

*በዚያ መሠዊያ ላይ አንድ ሺህ የሚቃጠል መስዋዕት አቀረበ እግዚአብሔርም በገባዖን ለሰሎሞን በሌሊት በሕልም ተገለጠለት እግዚአብሔርም፡- ምን እንድሰጥህ ለምን አለ፡፡»*

«ሰሎሞን አንድ ሺህ የሚቃጠል መስዋዕት አቀረበ» በሚል የማጭበርበሪያ ስልት ከተከታዮቻቸው ገንዘብ ይዘርፋሉ ምስኪን የሆኑ ተከታዮችም ገንዘባቸውን ይዘረፋሉ የወርቁን ጥጆች አምላካቸው አድርገው የሚያቀርቡ ትላልቅ የቤተክርስቲያን ሕንፃዎችን ለመገንባት በምፅዋት መልክ የሰጡትን ገንዘባቸውን ይነጠቃሉ ይህንን የሚያደርጉት ቤተክርስቲያኖቻቸው በጣም ጠባብ ስለሆኑ ሳይሆን ከተከታዮቻቸው ገንዘብን መዝረፍ ስለፈለጉ ነው፡፡

የወርቅ ጥጃዎችን በመሰራት ከተከታዮቻቸው ገንዘብን የሚዘርፉት መናፍቃን ናቸው እኛ በእግዚአብሔር የምናምን ሰዎችም በዚህ የምንታለል አንሆንም ማለት ነው የወርቅ ጥጃን ለሚያመልኩ ሰዎች ገንዘብ ከሰጣችሁ ያ ገንዘብ ለእግዚአብሄር የተሰተ አይደለም ነገር ግን እንደ ኢዮርብአም በስስት የተሞሉትን አስመሳይ ካህናቶች ኪስ የሚያደልብ ነው እንደ እነዚህ ባሉት መናፍቃን ወጥመድ ውስጥ በጭራሽ መግባት የለባችሁም፡፡

ታዲያ እግዚአብሔር ሰሎሞን ባቀረባቸው አንድ ሺህ የሚቃጠሉ መስዋዕቶች ለምን ተደሰተ? ምክንያቱም ሰሎሞን ሐጢያቶቹን ስላወቀ በሐጢያቶቹ የተነሳም መሞት እንዳለበት ስለተረዳና ከእምነት የሆኑ መስዋዕቶችን ስላቀረበ ነው ከእግዚአብሄር ለሆነው ደህንነት ምስጋናውን ለመግለጥ አንድ ሺህ የሚቃጠሉ መስዋዕቶችን አቀረበ ከውሃና ከመንፈስ የሚገኘ ውን ቤዛነት እያሰበ አንድ ሺህ መስዋዕቶችን አቀረበ፡፡

ስለሆነም አሁን ሁለተኛ በእንደነዚህ አይነት አሳሳች ካህናት መታለል አይኖርባችሁም፡፡

# እነዚያ ዳግም ሳይወለዱ የሚያገለግሉትም መናፍቃን ናቸው

*መናፍቃን ዳግም ስለመወለድ ምን ይላሉ?*

*በራዕዮች፣ በሕልሞችና በተለያዩ መንፈሳዊ ልምምዶች አማካይነት ዳግም እንደተወለዱ ይናገራሉ::*

ራሳቸው በእምነት ዳግም ውልደትን ሳያገኙ ሌሎች ዳግም ውልደትን ያገኙ ዘንድ ያስተምራሉ እነዚህ በሙሉ መናፍቃን ናቸው:: ትክክለኛውን የውኃና የመንፈስ ወንጌልም የማያውቁ ከመሆናቸው የተነሳ ዳግም መወለድ አይችሉም ሆኖም ግን ሌሎች ዳግም እንዲወለዱ ያስተምራሉ ይህ በጣም ሊያስቅ የሚችል ነገር ነው::

አሳሳች ካህናት የውሸት ወንጌልን ይሰብካሉ ይህም የውኃውንና የመንፈስን ወንጌል ያዛባዋል:: ለሰዎችም የገዛ ራሳቸውን ሐጢያቶች በየቀኑ እንዲያስወግዱ ይነግሩዋቸዋል::

«ወደ ተራራዎች ሄዳችሁ ጸልዩ ጹሙ ራሳችሁንም ለእግዚአብሔር ሥራ ቀድሱ ማልዳችሁ ጸልዩ ታዛዥ ሁኑ ለቤተክርስቲያናት ግንባታ በርካታ ገንዘብ ለግሱ ነገር ግን የራሳችሁን ሐጢያቶች እናንተው ማስተካከል እንዳለባችሁ አስቡ» እያሉ ያስተምራሉ::

በአንድ ወቅት አንድ ሰው ዳግም ስለመወለዱ ሲመሰክር ሰምቻለሁ በሕልሙ በሰልፍ መስመር ላይ ቆሞ ነበር የእርሱ

ተራ ሲደርስም ኢየሱስ ስሙን ጠራው ይህ ዳግም ለመወለዱ ምስክር እንደሆነም ተናገረ ነገር ግን የእርሱ እምነት ትክክለኛ ነውን? ኢየሱስ እንደዚያ አላለም::

በዮሐንስ 3 *ላይ «አንድ ሰው ከውኃና ከመንፈስ እንደገና ካልተወለደ በስተቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት አይችልም»* ተብሎ ተጽፏል:: እውነተኛ ካህናት መሆን የሚችሉት ከውሃና ከመንፈስ የተወለዱ ብቻ ስለመሆናቸው እግዚአብሔር እግዚአብሄር ተናግሮዋል በሕልሞች በቅዠቶች በመንፈሳዊ ስሜቶች ወይም ለንስሐ በሚፀለዩ ፀሎቶች አማካይነት ዳግም እንደሚወለድ የሚያምን ማንኛውም ሰው መናፍቅ ነው::

ዛሬ ብዙ ሰዎች በተጻፈው የእግዚአብሔር ቃል አያምኑም ከውኃና ከመንፈስ ከመወለድ ፋንታ የኃይማኖት ትምህርቶቻቸውን ይደግፋሉ ከውኃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን ወንጌል ለመስበክ እምቢተኛ የሆኑ አስመሳይ ክርስቲያኖችና መናፍቃን ናቸው::

## የተሃድሶ ሰዎችና አሁን ያለው ክርስትና

*እውነተኛው ወንጌል ከተሳሳቱ ኃይማኖቶች ጋር መደባለቅና መበላሸት የጀመረው መቼ ነው?*

*የሮማው ገዥ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ የሚላንን ጉባኤ በ313 ዓ.ም. ባደረገ ጊዜ ነው::*

የክርስትና ኃይማኖቶች የተመሰረቱት የት ነው? የተለያዩ ኃይማኖቶች ማለትም ሜቶዲስት፣ መጥምቃውያን፣ ሉተራን፣ ቅድስናና ሙሉ ወንጌል ያሉት የኃይማኖት ድርጅቶች የተነሱት መቼ ነው? ይህ ተሃድሶ የመጣው ከ500 ዓመታት በፊት ነው።

የመጀመሪያዎቹ ኢየሱስ በምድረ ላይ በነበረ ጊዜ ሲከተሉት የነበሩት ናቸው «ክርስትያን» ማለት «የክርስቶስ ተከታዮች» ማለት ነው።

የጥንት ክርስትያኖች ኢየሱስ በዚህ አለም ላይ በነበረበት ጊዜ የተከተሉት ናቸው «ክርስቲያኖች» ማለት «ክርስቶስን የሚከተሉ» ማለት ነው ሐዋርያቱና የቤተ ክርስትያን መሪዎች እስከ 313 ዓ.ም. ድረስ እውነተኛውን ወንጌል ይከተሉ ነበር ሆኖም ግን ከታላቁ ቆስጠንጢኖስ የሚላኑ ጉባኤ በኋላ ክርስትያኖችና ጣዖት አምላኪዎች መገናኘት ጀመሩ ውጤቱም ለ1000 ዓመት የዘለቀ የጨለማ ዘመን መከሰቱ ነበር።

በኋላም በ16ኛው ምዕተ አመት መጀመሪያ ላይ ማርቲን ሉተር ተሃድሶን አመጣ «በእምነት የሚኖረው ፃድቅ ብቻ ነው» በማለት ተሐድሶን አወጀ ጥቂት ቆይቶም በ1500-1600 መካከል እንደ ጆን ካልቪንና ጆን ኖክስ ያሉ የተሐድሶ ሰዎች እንቅስቃሴውን ከካቶሊክ ሐይማኖት አራቁት የተሐድሶን ቅዱሳን ብቻ በእምነት መኖር አለባቸው» በኋላም ትንሽ ቆይቶ በ1500 እና በ1600 መካከል እንደ ጆን ካልቪንና ጆን ኖክስ ያሉ የተሃድሶ መሪዎች እንቅስቃሴውን ከካቶሊክ እንዲወጣ አደረጉት። ተሐድሶ ያደረገው ነገር ነገር ቢኖር ይህንን ነው።

ተሐድሶ ከሮማውያን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የተገነጠሉ አዳዲስ አብያተ ክርስቲያኖችን ለመመስረት የተደረገ ጥረት ብቻ ነበር የተሐድሶ ሰዎች በካቶሊክ ሐይማኖት ላይ ያደረጉት አንዳች መሠረታዊ የክህደት ሙከራ አልነበረም።

አላማቸው ከውሃና ከመንፈስ የመወለድን እምነት

ማስተዋወቅ ሳይሆን ራሳቸውን ከሮማውያን ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ግዞትና ንቅዘት ነፃ መውጣት ነበር የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ይህንን እንቅስቃሴ የፕሮቴስታንት አንጃ ብለው ጠርተውታል ተቃዋሚዎች ማለት ነው::

በወቅቱ የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን የሞቱ ቅድመ አያቶቻቸውን ወደ ሰማይ መላክ የሚችሉት በርካታ ገንዘብ አውጥተው ኢንደልጀንስን እንዲገዙ በማሳሰብ ለሕዝቡ ልመናን አቀረበች ሉተር የካቶሊክ ሐይማኖት ከስር መሠረቱ ስህተት እንደነበር አላወቀም እርሱ ለማድረግ የሞከረው ነገር የሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን የቅዱስ ጴጥሮስ ሕንፃ ግንባታን በገንዘብ ለመደገፍ ኢንደልጀንሶችን መሸጥ እንድታቆም ማድረግ ብቻ ነው::

ከዚህ የተነሳ በዘመኑ የፕሮነስታንት ቤተ ክርስትያን ውስጥ በርካታ የካቶሊክ ቅሪቶችን ማየት እንችላለን የህጻናት ጥምቀት በሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ከኑዛዜ ጋር የሚመሳሰሉ የንስሐ ፀሎቶች ስርአተ ቅዳሴዎች ከስነ መለኮት ትምህርት ቤቶች ለተመረቁ ብቻ እውቅናን መስጠት ግርማ ሞገስ ያላቸውና ታላላቅ ቤተ ክርስቲያናት! እነዚህ ሁሉ የሮም ካቶሊክ ቅሪቶች ናቸው::

ከተሃድሶው ዘመን ማለትም ከ1500 ዓ.ም. ጀምረን ስንቆጥር የፕሮቴስታንት ኃይማኖት የ500 ዓመት እድሜ ይኖረዋል:: ይህ ዓመትም ተሃድሶው ከተመሰረተ 481ኛ ዓመቱ ነው፡ ማርቲን ሉተር በቤተክርስትያን ላይ ያመፀው ከ481 ዓመት በፊት መሆኑን ብዙዎቻችሁ አትገነዘቡት ይሆናል ስለዚህ የፕሮቴስታንት ሃይማኖት በንፅፅር ከተቀመጡት ወጣቶቹ አንፃር እኔ ብቻ ነኝ ትክክል ማለት አይችልም የክርስትና ተሃድሶ አሁንም ድረስ በመካሄድ ላይ ነው መቀጠልም ይኖርበታል::

ሆኖም ግን በአእምሮአችን መያዝ ያለብን አንድ ነገር አለ:: ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገቡ የሚችሉት ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም ውልደትን ያገኙት ብቻ ናቸው እኛም ይህን እንስበክ! የኢየሱስን ወንጌል፣ የውኃውን፣ የደሙንና የመንፈሱን ወንጌል ትሰብካላችሁን? ይህ ካልሆነ እናንተ የእግዚብሔር አገልጋዮች አይደላችሁም ማለት ነው እግዚአብሔር እኛ እንድናምንበት የሚፈልገው «የውኃውና የመንፈሱን ወንጌል» ነው ይህም ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይ ኒቆዲሞስን ያስተማረው ነገር ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገረው ስለ ውኃውና መንፈሱ ወንጌል ብቻ ነውን? ወይስ ለማህበረሰቡ በጎ ነገር ስለማድረግና የተቀደሰ ሕይወት ስለመኖርም ይናገራል? በእርግጥ ሁለተኛ ውም በጣም ጠቃሚ ነው ሆኖም ግን እናንተ ይህን ለማድረግ የምትችሉት ከውኃውና ከመንፈሱ ዳግም ውልደትን ካገኛችሁ በኋላ ነው የእግዚአብሔር ፍላጎት እኛ በወንጌሉ እንድናምን ዘንድ ነው::

## የመናፍቃን ትምህርት

*መናፍቅ ማነው?*

*በኢየሱስ ቢያምንም ኃጢአተኛ እንደሆነ የሚያስብ ሰው ነው::*

አስመሳይ ክርስትናና መናፍቃዊ እምነት በዓለም ላይ መስፋፋት የጀመረው መቼ ነው?

በ1ኛ ነገስት ምዕራፍ 12-13 ላይ በተጻፈው መሠረት የእስራኤል ሕዝቦች በንጉስ ኢዮርብዓም አማካኝነት በሁለት መንግስት ከመከፈላቸው በፊት ድረስ ያመልኩ የነበሩት አንድ እግዚአብሔርን ብቻ ነበር ክርስቶስ ወደዚህ አለም ከመምጣቱ በፊት ካለው ከዚያን ጊዜ ጀምሮ መናፍቃዊ እምነት መስፋፋት ጀመረ በነዚያ ጊዜያትም ብዙ መናፍቃን በምድር ላይ ተስፋፍተው ነበር።

መጽሐፍ ቅዱስም በኢሳይያስ ምዕራፍ 28 ላይና በቲቶ 3፡10-11 ላይ ስለ አሳሳች የክርስትና ትምህርቶቻቸው ይናገራል መናፍቃን በኢየሱስ የሚያምኑ ሆነው በልባቸው ግን አሁንም ድረስ ኃጢአት እንዳለባቸው የሚያስቡት መሆናቸውን መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ማንም እንደዚህ የሆነ ሰው ሁሉ መናፍቅ ነው።

እንዲሁም በኢሳይያስ 28፡9-10 እንደተጻፈውም የሚያስተምሩት፣ *«እውቀትን ለማን ያስተምረዋል? ወይስ ወሬ ማስተዋልን ለማን ይሰታል? ወተትን ለተዉ ወይስ ጡትን ለጣሉ ነውን? ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ይሆንላቸዋል።»*

መናፍቃን ትእዛዝን በትእዛዝ ላይ ሥርዓትንም በሥርዓት ላይ ይጨምራሉ ይህ ምን ማለት ነው? ይህ ማለት «በኢየሱስ በማመን ዳግም ተወልደናል ከሚሉ ተጠንቀቁ ተጠንቀቁ ተጠንቀቁ» ማለት ነው እነርሱ ምንም ቢሆን፣ የሚነግሯችሁ እንድትጠነቀቁ ብቻ ነው እነርሱም ሌላ ነገር እንዳታዳምጡ እንዲሁም ወደ ሌላ ቦታ እንዳትሔዱና ለመናፍቃን እንዳትጋለጡ ይመክራሉ።

እምነታቸው ከእግዚአብሄር ቃል የተለየ እንደሆነ የሚናገሩትን የማይጋፈጡዋቸው ለምንድነው? ይህ በጣም

የሚያሳዝን ነው ቀጥተኛ ክርስትያኖች ለመሆን ይፈልጋሉ ሆኖም ግን መናፍቃን ናቸው የሚሏቸውን ሰዎች የሚያሸንፉበት ሃይል የላቸውም እውነተኛ ክርስትያን በእግዚአብሔር ቃል በመጠቀም የመናፍቃንን ቃል ሊያሸንፍ ይችላል::

ዛሬ ትክክል ነን የሚሉ ክርስቲያኖች እምነታቸው የተለየ ስለሆነ ብቻ ዳግም የተወለዱትን «መናፍቃን» እንደሆኑ አድርገው ያወግዙዋቸዋል እኛ በውኃና በመንፈስ ወንጌል እያመንን እንዴት መናፍቃን ልንሆን እንችላለን?

መናፍቃን ተብለው የተጠሩት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የሚሰብኩ ከሆኑ እውነተኛ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ናቸው ልክ እንደዚሁ ኦርቶዶክስ ክርስቲያኖች ነን የሚሉ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማይሰብኩ ከሆነ መናፍቃን ናቸው::

«በኦርቶዶክሳዊነትና» እና «በኑፋቄ» መካከል ያለው ልዮነት ያረፈው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል በመስበካቸውና በኢየሱስ አምነው በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት የሚኖር በመሆን አለመሆኑ ላይ ነው በእግዚአብሄር ቃል የሚያምኑና ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የተወለዱ ከሆኑ እንዴት መናፍቃን ሊሆኑ ይችላሉ?

በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም በማመን ከኃጢኣታችን ሙሉ በሙሉ መንፃት መናፍቅነት ነውን? እንዲሁም ደግሞ በኢሱስ የውኃና የመንፈስ ወንጌል አለማመን «ኦርቶዶክስ» መሆን ነውን?

ከመፅሐፍ ቅዱስ ርቀው ሳሉ «ኦርቶዶክስ» ክርስቲያኖች ነን ነን የሚሉ በርካታ ሐይማኖቶች አሉ እነርሱ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተዘረዘረው መሠረት ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ከመወለድ ርቀዋል ምክንያቱም የኢየሱስን ጥምቀት (ውሃውን)

በመካድ በመስቀል ላይ የፈሰሰውን ደም ብቻ የሚሰብኩ ናቸው!

የተሐድሶ ሰዎች በሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ አምፀው ከሮም ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በመውጣት የፕሮቴስታንትን እንቅስቃሴ እንደመሠረቱ ሁሉ እኛም እውራን በሆኑ ክርስቲያኖችና በአስመሳይ ካህናቶች ላይ ማመፅ ይኖርብናል አይኖቻችንን ለእውነተኛው ወንጌል ሊከፈቱ የሚችሉት እውነተኛ እምነት የሚኖረንና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ሙሉ በሙሉ የምንድነው ያን ጊዜ ብቻ ነው::

*መናፍቃን ላለመሆን ማስወገድ ያለብን ነገር ምንድን ነው?*

*ከውኃና ከመንፈስ ዳግም ውልደትን ማግኘት አለብን::*

መፅሐፍ ቅዱስ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ደም ወንጌል የሚያምኑት ብቻ እውነተኛ እምነት እንዳላቸው ይነግረናል:: ኢየሱስም ይህንን በዮሐንስ 3:1-12 ላይ ለኒቆዲሞስ ተናግሮታል::

መናፍቃን ተከታዮቻቸውን ሁልግዜም በእምነታቸው እንዲቀደሱ ይነግሩዋቸዋል ንጋት ላይ እንዲፀልዩና ጠንክረው እንዲሰሩም ይመክሩዋቸዋል ይህ እውር የሆኑ ሰዎች እንዲሮጡ የመምከር ያህል ነው::

ምንም ያህል በትጋት የምትጸልዩ ብትሆኑም ከውኃና ከመንፈስ ዳግም ውልደትን እስካላገኛችሁ ድረስ ምንም ጥቅም አይኖረውም እኛ ከውኃና ከመንፈስ የተወለዱት በሙሉ ቅዱሳን

ናቸው ብለን ስንል መናፍቃን ደግሞ ሮሜ 3:10ን *«ጻድቅ የለም አንድስ እንኳ»* የሚለውን ጥቅስ በመያዝ ሊከራከሩ ይሞክራሉ ይህንን ጥቅስ በመያዝም አማኞችን በመናፍቃን ጎራ ይመድቧቸዋል::

ሆኖም ግን መናፍቃን ራሳቸው ናቸው የዚህ ቃል ትርጉም እንደምናስበው ቀላል አይደለም እነዚህ መናፍቃን ሙሉውን መፅሐፍ ቅዱስ አላነበቡትም ሐዋርያው ጳውሎስ በዓለም ላይ ፃድቅ ሰው እንደሌለ ተናግሮዋል እርሱ ይህንን የጠቀሰው ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ የሰውን ዘር ሁሉ በእግዚአብሄር ማዳን ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ከማዳኑ በፊት በአለም ላይ ፃድቅ ሰው የሚባል እንዳልነበረ ከሚናገረው ከብሉይ ኪዳን ነበር ነገር ግን በኢየሱስ የዳኑት ፃድቃን ይሆናሉ::

ሙሉውን ምዕራፍ ብናነበብ እውነታውን እንረዳዋለን:: መናፍቃን ሁልግዜም ተከታዮቻቸውን ከነሱ የተለየ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች እንዲጠነቀቁ ይመክራሉ ራሳቸውን እንደ «ኦርቶዶክስ» ከሚያዩ ቤተ ክርስትያናት ውጭም ተከታዮቻቸውን ሌላ ቦታ ከማምለክ ይከለክሏቸዋል::

በዚህም እነዚህ ሰዎች ዳግም መወለድ የማይችሉና እውነተኛውን ወንጌል ለመስማት የማይችሉ ይሆናሉ እነዚህ የገሃነምን ወንዶችና ሴቶች ልጆች እያፈሩ ያሉት የሐሰት አስተማሪዎች አስተምህሮቶች ናቸው እነርሱም በእግዚአብሔር ይፈረድባቸዋል መናፍቃን ወደ እግዚአብሔር መመለስ አለባቸው::

መናፍቃን እነማን ናቸው? የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል በማመን የዳኑት ናቸው ወይስ በኢየሱስ እናምናለን እያሉ ከውኃና ከመንፈሱ ዳግም ያልተወለዱት?

ቲቶ 3:11 በኢየሱስ እያመኑ ነገር ግን *«በራሳቸው የፈረዱ»* መናፍቃን እንደሆኑ ይናገራል *«ራሳቸውን እንደ*

*ኃጢአተኛ»* የሚቆጥሩት ኃጢአተኞች መሆናቸውን ይናገራል::

እነርሱ ተከታዮቻቸውን ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የምንወለድበት ወንጌል ወደሚሰበክባቸው የተሐድሶ ስብሰባዎች እንዳይሄዱ ስተምሩዋቸዋል አደገኛ ነው ይሉዋቸዋል አንድ «ኦርቶዶክስ» የሆነ ሰው የሚጣረሱ አመኔታዎችን እንዴት ሊፈራ ይችላል? እነርሱ ፈሪዎች የሆኑት እውነት ስለሌላቸው ነው *«ስርአት በስርአት ስርአት በስርአት ላይ መሆን አለበት»* መናፍቅ ካህናት አንድን ሃሳብ ከዚህ መፅሐፍ አንድን ሃሳብ ደግሞ ከሌላ መፅሐፍ እንዲሁም ደግሞ የተለያዩ ኃሳቦችን ከተለያዩ ፈላስፋዎችና መፅሐፍት በመውሰድና እየቀላቀሉ በመጠቀምም ንግግራቸውን እውነት ለማስመሰል ይሞክራሉ::

ተከታዮቻቸው ደናቁራን እንደሆኑ ስለሚያምኑ አለማዊ ትምህርቶችን ሊያስተምሩዋቸው ይሞክራሉ እውነተኛ ቤተክርስቲያን የእግዚአብሄርን ቃል ትሰብካለች ምዕመናንንም ከእግዚአብሄር ቃል ያስተምሩዋቸዋል ሰዎች ወደ ቤተክርስቲያን የሚመጡት የአለምን መንገዶች ለመማር ሳይሆን በአለም ውስጥ ሊደመጡ የማይችሉትን ሰማያዊ ነገሮች ለማድመጥ ነው::

ሰዎች ወደ ቤተ ክርስትያን የሚገቡት ሐጢያተኞች ሆነው ነው ነገር ግን ሐጢያት የሌለባቸው ፃድቅ ምዕመናን ሆነው ከቤተክርስቲያን መውጣት ይሻሉ መናፍቅ የሆኑ ካህናት የሚያስተምሩዋቸው ምንድነው? እነርሱ ለተከታዮቻቸው የእግዚአብሄር ባሮች እውነተኛውን ወንጌል በሚሰብኩባቸው የተሐድሶ ስብሰባዎች ላይ እንዳይገኙ ይነግሩዋቸዋል ተከታዮቻቸው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም እንዲወለዱ ያግዱዋቸዋል::

ይህ በጣም የሚያሳዝን ነገር ነው እነዚህ ሰዎች ተከታዮቻቸውን ሊያታልሉ ይችሉ ይሆናል ሆኖም ግን እግዚአብሔርን መቼም ቢሆን ለማታለል አይችሉም::

*የሐሰት ካህናቱ ተከታዮቻቸውን ከውኃና ከመንፈስ ዳግም ውልደትን እንዲያገኙ ሊረዱ ይችላሉን?*

*አይችሉም። ሌሎች ደሰግም እንዲወለዱ ማድረግ የሚችሉት ዳግም የተወለዱ ሰዎች ብቻ ናቸው።*

እናንተ መናፍቃን በእውነት የእግዚአብሔር አገልጋዮች ከሆናችሁ መንፈስ ሲወቅሳችሁ አታዳምጡምን? መመለስ ይኞርባችኋል ተከታዮቻችሁ እውነተኛ የእግዚአብሄር ባሮች ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን ወንጌል በሚሰብኩበት የመነቃቃት ስብሰባ ላይ እንዳይገኙ እንቅፋት መሆናችሁን አቁሙ መናፍቃንተከታዮቻቸውንየሚያስተምሯቸው ነገረ መለኮትን ብቻ ነው ስለዚህ ሌሎች ፅንሰ ሐሳቦች ሲገጥሙዋቸው ይደቆሳሉ ይህ ያሳዝናል አስመሳይ ካህናቶች ከእግዚአብሄር ቃል ው ጭ የማገልገል ብቃት አላቸው በተዛባው አመኔታቸው ላይ ብቻ ተመስርተው ይሰብካሉ ያማክራሉ ያገለግላሉ የእግዚአብሄርን ቃል ሳይዙ የሚያገለግሉና የሚሰብኩ መናፍቃንና ሞያተኞች ናቸው። (ዮሐንስ 10፡13)

አስመሳይ አገልጋዮችም መናፍቃን ናቸው ምክንያቱም ውስጣዊና የውጫዊ ማንነታቸው የተለያየ ነው አንዳንድ ሰዎች ከተመሠረቱት የሐይማኖት ድርጅቶች ጋር የማይስማሙትን ቤተክርስቲያናት መናፍቅ ቤተክርስቲያናት ብለው ይገልጡዋቸዋል ሆኖም እነዚያ ቤተክርስቲያናት ከማንኛውም

የሐይማኖት ድርጅት ጋር ሕብረት መፍጠር አይፈልጉም ምክንያቱም አብዛኞቹ ቤተክርስቲያናት ከመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች በጣም ርቀው የሚንቀሳቀሱ ናቸውና።

መናፍቃን የራሳቸውን የሐጢያት ችግሮች ሳይፈቱ ተከታዮቻቸው መዳን እንደሚኖርባቸው ይነግሩዋቸዋል እነርሱ የኢዮርብአምን ሐጢያት እየፈፀሙ ነው በልቡ ውስጥ ገናም ሐጢያት እያለበት የእግዚአብሄርን ስራዎች ለመስራት የሚሞክር ማንኛውም ሰው የእርሱ ሐጢያቶችና የእግዚአብሄር ቅድስና ፈፅሞ እንደማይጣጣሙ መገንዘብ ይኖርበታል መናፍቅ መሆኑንም ማወቅ አለበት።

ስለሆነም ሰባኪም ሆነ የቤተክርስትያን አገልጋይ ኃጢአተኛ ነኝ ብሎ የሚያስብ ከሆነ መናፍቅ መሆኑን መረዳት አለበት እርሱም የእግዚአብሔርን የደህንነት ወንጌል የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል የማያውቅ በመሆኑም ኃጢአተኛ ነው አንድ ሰው መፅሐፍ ቅዱስን ከመናፍቅ ተምሮ ለሌላ ሰው ቢያስተምርም እርሱም መናፍቅ ይሆናል ማለት ነው።

ዛፍን በፍሬው ልናውቀው እንችላለን በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ የፀደቁ ፅድቅን ሲያፈሩ ገናም ሐጢያተኞች የሆኑት ግን የሚያፈሩት ሐጢያተኝነትን ነው *«እንዲሁም መልካም ዛፍ መልካም ፍሬን ያፈራል መጥፎ ዛፍም የሚያፈራው መጥፎ ፍሬን ነው።» (ማቴዎስ 7:17)*

## መናፍቅ ካህናት በስብከቶቻቸው የሚያስተምሩት ምንድን ነው?

*መናፍቅ ካህናት በስብከቶቻቸው የሚስተምሩት ምንድን ነው?*

*ስነ-ኃይማኖትንና የሰውን አሳብ ነው::*

የውሸት ካህናት ለማንኛውም ነገር ይጠነቀቃሉ በጣም ይጠነቀቃሉ! በጣም የሚጠነቀቁትም የእውነት ቃል፣ እውነተኛ ው ከውኃና ከመንፈስ ወንጌል ዳግም የመወለጃው ቃል ስለሌላቸው ነው::

መናፍቃን ከዚህ ጥቂት፣ ከዚያም ጥቂት ነገሮችን ይወስዳሉ ሰዎችንም ያስታሉ የወንጌልን እውነተኛ ፍቺ ሳያውቁም::

*«እውቀትን ለማን ያስተምረዋል? ወይስ ወሬ ማስተዋልን ለማን ይሰታል? ወተትን ለተዉ ወይስ ጡትን ለጣሉ ነውን? ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ትእዛዝ በትእዛዝ፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ሥርዓት በሥርዓት፣ ጥቂት በዚህ ጥቂት በዚያ ይሆንላቸዋል::» (ኢሳይያስ 28:13)*

ትእዛዝ በትእዛዝ ሲናገሩም «ወንድም ይህ ቃል በግሪኩ እንዲህና እንዲያ በዕብራይስጡም እንዲህና እንዲያ ማለት ነው እንዲህና እንዲያ የሚባሉ ፅንሰ ሐሳቦች አሉ» ይላሉ ግልፅ የሆነ የደህንነት ፅንሰ ሐሳብ ከገጠማቸው ሰዎችን እንዲጠነቀቁ ያስጠነቅቁዋቸዋል እነርሱ እንዲህ ይላሉ «ማርቲን ሉተር እንዲህ ብሎዋል ጆን ካልቪንን እንዲህ ብሎዋል ጆን ኖክስም

እንዲህና እንዲያ ብሎዋል ሁሉም በራሳቸው መንገድ ጥሩ አድርገዋል ብለን እናስባለን፡፡»

እነርሱ የሚናገሩትንም ሆነ የሚያምኑትም አያውቁም እውነተኛ እምነት ያለው ሰው እውነትን ግልፅ በሆነ መንገድ ማብራራት ይችላል እውነተኛ ምዕመናን ዳግም በተወለደውና ዳግም ባልተወለደው መካከል ያለውን ልዩነት በግልፅ መናገር ይችላሉ እኛ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን ወንጌል በግልፅ እንሰብካለን፡፡

ሆኖም ግን መናፍቃን ግራ የተጋቡ ናቸው፡፡ እምነታቸውም እንደ ሌሊት ወፍ ነው የሌሊት ወፍ ቀኑን በብርሃን ጎጆዋ ውስጥ ተቀምጣ የምትውል ስትሆን የምትወጣውም በሌሊት ነው መናፍቃንም ይህንና ያንን ፅንሰ ሐሳብ ይወዳሉ በዚህና በዚያም ያምናሉ እውነት ምን እንደሆነ በጭራሽ አያውቁም መናፍቅ የሆነ ካህን ሲያል ሲገባ ተከታዮቹም መራራ ከሆነው ፍፃሜ ጋር ያጅቡታል ስለዚህ ብዙ ሰዎች ማብቂያቸው ሲያል ነው ምክንያቱም በሐሰተኛ ነቢያቶች አምነዋልና፡፡


ካህናችሁ ከውኃና ከመንፈስ ዳግም ውልደትን አግኝቷልን? እርሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በተጻፈው መሠረት ዳግም የመወለድን ወንጌል ያስተምራልን? ይህን የሚያደርግ ከሆነ ዕድለኞች ናችሁ የማያደርግ ከሆነ ትኮነናላችሁ ዳግም ካልተወለዳችሁ ከውሃና ከመንፈስ የሖነውን ወንጌል ማድመጥ ይህንን የሚያብራሩትን መፅሐፎች ማንበብና ዳግም መወለድ አለባችሁ፡፡

መናፍቃን ከውኃና ከመንፈስ ዳግም የምንወለድበትን ወንጌል አይወዱትም «ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣው የኛን ኃጢአት ለማስወገድ ነው ያደረገውም ይህንኑ ነው አሁንም ድረስ ኃጢአታችንን እያነጻልን ነው ወደፊትም ይህንኑ

ያደርጋል» እያሉ ይሰብካሉ ይህ እንዴት እውነት ሊሆን ይችላል? ቅዱሳን ነን ብለው ይናገራሉ ግን እያደረጉ ያሉት ኃጢአትን ነው በሆነ ቅፅበት ቅዱሳን ሆነው ከዚያ በኋላ ግን ዳግም ኃጢአተኞች ሆነው ይቀራሉ::

ሐሳዊ የስነ መለኮት ትምህርት አለ እርሱ እውነት አይደለም አሁን ፃድቅ ሆኖ በኋላ ሐጢያተኛ የሚሆን ማንኛ ውም ሰው መናፍቅ ሐሳዊ ነቢይ ነው ራሱን የሚኮንንና የሚያቆሽሽም እንደዚያው ነው::

## የእግዚአብሔር እርግማን በመናፍቃን ተከታዮች ላይ ነው




መናፍቃን ታማኞች አይደሉም:: ስለዚህ ተከታዮቻቸው ወደ እነርሱ መጥተው ዳግም መወለድ የሚቻለው እንዴት እንደሆነ ሲጠይቁዋቸው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም እንዲወለዱ ሊመሩዋቸው አይችሉም በፈንታው ለተከታዮቻቸው ሰዎች በስሜት ዳግም ሊወለዱ እንደሚችሉና ዳግም ሲወለዱም እንደማያውቁ ይነግሩዋቸዋል ይህ አስቂኝ ነው::

ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይ ሲናገር *«አንድ ሰው ከውኃና ከመንፈስ እስካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን*

መንግስት ሊወርስ አይችልም» ይላል ሆኖም ግን በአሁኑ ጊዜ በዚህ መንገድ ዳግም ውልደትን ያገኙት ሰዎች መናፍቃን ተብለዋል፡፡

መናፍቅ ካህናት ትሁታን ስለሆኑ ራሳቸውን ፃድቃን ብለው ሊጠሩ እንደማይችሉ ይናገራሉ ለተከታዮቻቸውም «ሰባኪው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን በረከት ለመስበክ ባቀደባቸው ማናቸውም የመነቃቃት ስብሰባዎች ላይ አትገኙ ዳግም ከተወለዳችሁ መናፍቅ ትሆናላችሁ ይህች ቤተክርስቲያንም ታወግዛችኋለች ከእኛ ጋር ለመቆየት ከፈለጋችሁ ሐጢያተኞች ሆናችሁ ቆዩ ጊዜው ሲደርስ እግዚአብሄር ፃድቃን ያደርጋችኋል» ብለው ይነግሩዋቸዋል የሚነግሩዋቸው ይህንን ነው በተጨባጭ እየነገሩዋቸው ያሉት ዳግም ለመወለድ ወይም ለአለመወለድ የምትወስኑት እናንተው ናችሁ በማለት ነው፡፡

መናፍቃን ለተከታዮቻቸው እንደሚሉትም «እናንተ ከእኛ ጋር ልትቆዩ ትችላላችሁ ሆኖም ግን ዳግም መወለድ የእናንተ ኃላፊነት ነው ስለሆነም ይህንን በራሳችሁ መሞከር አለባችሁ፡፡ አሁን እንዳላችሁ ቆይታችሁም ያኔ ወደ እግዚአብሔር ፊት መሄድ ትችላላችሁ ያኔም እውነታውን ትረዳላችሁ ከዚያን በኋላም ምን ሊከሰት እንደሚችል የማውቀው ነገር የለም ሆኖም ግን ይህ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን ነው ስለሆነም ከዚህ ቤተ ክርስትያን መራቅ የለባችሁም» ይህ እውነት ይመስላችኋልን?

እነዚህ መናፍቃን ካህናት ከዚህ ጥቂት ከዚያ ጥቂት ይቆነጥሩና የራሳቸውን ፅንሰ ሐሳቦች ያደራጃሉ ይህም ለእነርሱ ብቸኛው እውነት ይሆናል እነርሱ ስለ ውሃውና ስለ መንፈሱ የሚነግረንን የእግዚአብሄር ቃል አያውቁትም፡፡

መናፍቃን መጽሐፍ ቅዱስን የሚተረጉሙት በራሳቸው አስተሳሰብ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን መተርጎም ያለብን በዚያ

በተጻፈው መሠረት ነው እነርሱ ግን መፅሐፍ ቅዱስ የሚተረጉሙት በራሳቸው መንገድ ነው በክርስትና ውስጥ በርካታ የቃለ እግዚአብሄር ምሁራንና የእምነት ድርጅቶች የበዙት ለዚህ ነው::

ብዙ የሃይማኖት ድርጅቶችና የቃለ እግዚአብሄር ምሁራን ያሉ በመሆናቸው ስፍር ቁጥር የሌላቸው የኑፋቄ መፅሐፎች አሉ አስመሳይ ካህናት በሚሰብኩበት ጊዜ ከዚህኛው መፅሐፍ ጥቂት ከዚያኛው መፅሐፍ ደግሞ ጥቂት ይጠቅሳሉ እውነተኛ ካህናት ግን ከመፅሐፍ ቅዱስ ብቻ ይሰብካሉ::

መናፍቃን በብዙ ብልጣ ብልጥ መንገድ ከተከታዮቻቸው ገንዘብን ያጭበረብራሉ በዚህ አለም ላይ ጥሩውን እየተመገቡ አምሮባቸው ይኖራሉ መጨረሻቸውም ሲዖል ይሆናል ምክንያቱም ዳግም አልተወለዱምና እግዚአብሄር ለእነርሱ ያዘጋጀላቸው ፍፃሜ ይህ ነው::

በመጀመሪያ እግዚአብሔር ታግሶዋቸዋል ነገር ግን ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን በረከት ለመቀበል አጥብቀው እምቢተኛ የሆኑ ፍፃሜያቸው ሲዖል ይሆናል::

እግዚአብሔር መናፍቃንን ይዳኛል መናፍቃን አጥብቀው በእግዚአብሄር ያምናሉ መጀመሪያ ላይም በርካታ የመፅሐፍ ቅዱስ ኮሜንታሪ ቅፆችንና የስነ መለኮት መፅሐፎችን አሟጠው ያነባሉ ከዚያ ግን ጥቂት በጥቂት ከሰዎች ትምህርቶች ስለሚሰብኩ ተከታዮቻቸው ፈፅሞ ዳግም ሊወለዱ አይችሉም::

መናፍቃን በምድራዊ ስራዎቻቸው ላይ እጅግ የላቀ ትኩረት ወደ ማድረጉ ያዘነብላሉ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የምንወለድበትን ወንጌል የማይሰብክ ማንኛውም አገልጋይ በእግዚአብሄር ፊት መናፍቅ ነው::

እነርሱ ተከታዮቻቸውን ያስጨንቁዋቸዋል 40 ቀን ሌሊቱን ሁሉ እንዲፀልዩ 100 ቀን የማለዳ ፀሎትና የተራራ ላይ ፀሎቶች

እንዲያደርጉ በየጊዜው እንዲፆሙ ለመነቃቃት ስብሰባዎችም አንድ ሺህ የሚቃጠሉ መስዋዕተ ምፅዋቶችን እንዲለግሱ ያስገድዱዋቸዋል እያንዳንዱ ምዕመን ምን ያህል ምፅዋት እንደሰጠ የሚያሳይ ሰንጠረዥም ያዘጋጃሉ የስራዎቻቸውን ፍሬዎች በማየት ብቻ መናፍቃን መሆናቸውን ማየት እንችላለን::

የእግዚአብሔር እርግማን በተከታዮቻቸው ላይም ይወርዳል:: ዳግም ውልደትን ሳያገኙ የሚሰብኩ ሰባኪያንና የእነርሱ ተከታዮችም በሙሉ የእግዚአብሔር እርግማን ይደርስባቸዋል::

## መናፍቃን የተከታዮቻቸውን አእምሮ ለማንበብ ይፈልጋሉ

*መናፍቃን የተከታዮቻቸውን*
*አእምሮ ለማንበብ ለምን ይሞክራሉ?*

*ይህን የሚያደርጉት ዳግም ውልደትን*
*ስላላገኙና በውስጣቸውም መንፈስ*
*ስለሌለባቸው ነው::*

መናፍቅ ካህናት በየቀኑ ያለቅሳሉ እነርሱ የበላይ ዲያቆናትንና የሴት ዲያቆናትን ሽማግሌዎችን ተራ ዲያቆናትንና ምዕመናንን እንኳን ሳይቀር ያስደሰቱ መሆናቸውን እርግጠኞች መሆን አለባቸው ከዚህ የተነሳ በየቀኑ ይበልጥ ግብዞች ይሆናሉ::

እንደ ፈሪሳውያንም ሁል ጊዜ ለመኖር ይፈልጋሉ:: «ቅዱስና መሓሪው...» በማለትም ብዙውን ጊዜ ስብከታቸውን ይጀምራሉ ልባቸው በኃጢአት የተሞላ ቢሆንም በአፋቸው ግን ቅዱስ ሆነው ለመታየት ይሞክራሉ በዚህም ይበልጥ ተመጻዳቂዎች ይሆናሉ::

በአንድ ወቅት አንድ ሰባኪ እንዲህ አለ «በውስጣችሁ መንፈስ ሳይኖር ማገልገል እርግማን ነው» ይህ ማለት መዳን ሳይኖር የእግዚአብሄርን ስራ መስራት መናፍቅነት ነው የተረገመ ሕይወት ነው ማለት ነው እናንተ ከእነዚህ መናፍቃን አንዱ ከሆናችሁ ከውሃና ከመንፈስ መወለድ ይኖርባችኋል::

በኢየሱስ እያመነ ዳግም ያልተወለደ ማንኛውም ሰው መናፍቅ ነው ከዚህ በተጨማሪም እያንዳንዱ ሰው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ወደምንወለድበት ወንጌል መመለስ አለበት ወንጌልን ለሌሎች መስበክ የሚችለው ከውሃና ከመንፈስ የተወለደ ፃድቅ ብቻ ነው::

## መናፍቃን የሚጮኹት ለሰላም ብቻ ነው

*የመናፍቃን ካህናት*
*ተከታዮቻቸውን የሚያስደስቱት*
*እንዴት ነው?*

*ሁል ግዜም ለሰላም ይጮኃሉ እንዲሁም ደግሞ*
*ምንም እንኳን ኃጢአተኞች ቢሆኑም*
*ወደ እግዚአብሔር መንግስት*
*እንደሚገቡ ይናገራሉ::*

ኢሳያስ 28:14-15 እንዲህ ይላል *«ስለዚህ በኢየሩሳሌም ያለውን ሕዝብ የምትገዙ ፌዘኞች ሆይ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ እናንተም:- ከሞት ጋር ቃል ኪዳን አድርገናል ከሲኦልም ጋር ተማምለናል በሐሰትም ተሰውረናልና የሚትረፈረፍ መቅሰፍት ባለፈ ጊዜ አይደርስብንም ስላላችሁ::»*

እዚህ ላይ ፌዘኞቹ እነማናቸው? የራሳቸውን የተሳሳተ ሃሳብ እየቀላቀሉ የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩት ናቸው የትኛውም የኃይማኖት ሊቅ እንዲሁም ደግሞ ማንኛውም ካህን ምንም ነገር የሚያስብ ቢሆንም ማስተማር ያለበት የመፅሐፍ ቅዱስን ቃል ብቻ ነው መናፍቅ ካህናትም መፅሐፍ ቅዱስን የሚያስተምሩት እነሱ በተመቻቸው መንገድ ነው ፌዘኞቹ እነዚህ ናቸው::

*«ከሞት ጋር ቃል ኪዳን አድርገናል ከሲኦልም ጋር ተማምለናል በሐሰትም ተሰውረናልና የሚትረፈረፍ መቅሰፍት ባለፈ ጊዜ አይደርስብንም ስላላችሁ::»*

መናፍቃን እርግማኑ እንደማይደርስባቸው ይናገራሉ እንዲሁም ደግሞ ሰዎችንም በእነዚህ ነገሮች እንዳይጨነቁ ይመክራሉ ጥፋትና ገሃነም እየጠበቃቸውም እንዳይጨነቁ ይነግሯቸዋል ጥፋትና ገሃነም ለእነርሱ የሉም ማለት ነው ስለሆነም እናንተ ለመኖር የምትፈልጉ ከሆነ ከእነዚህ መናፍቃን ተጠብቃችሁ መኖር አለባችሁ::

መናፍቃን ከውኃና ከመንፈስ መወለድ እንደሌለባችሁ ይናገራሉ ይህ እውነት ነውን? በፍጹም፣ ይህ እውነት አይደለም ዳግም ከውኃና ከመንፈስ እስካልተወለዳችሁ ድረስ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት አትችሉም::

ወደ እግዚአብሔር መንግስት አለመግባትስ መልካም ነውን? ይህም ማለት አንድን ሰው በገሃነም ለመቃጠል ትፈልጋለህን? ብሎ ከመጠየቅ ጋር ተመሳሳይ ነው ለሁለቱም

ጥያቄዎች መልስ ሊሆን የሚችለው አይደለም ነው በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል አምነን አንድ ላይ ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንግባ፡፡

መናፍቅ ካህናት ሰዎችን እነርሱ በኢየሱስ የሚያምኑ ከሆኑ ብቻ ምንም እንኳን ኃጢአተኞች ቢሆኑም ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት እንደሚችሉ ይሰብካሉ፡፡

ኃጢአተኞች ነን እያላችሁም ኢየሱስ እንዴት ለእናንተ ኃጢኣት ሊጨነቅላችሁ ይችላል? ኃጢአተኛ ወደ መንግስተ ሰማያት ሊገባ ይችላልን? ኃጢአተኞች ገሃነምን ሊያመልጡ ይችላሉን? መጽሐፍ ቅዱስ በኢየሱስ የምታምኑ ከሆናችሁ በውስጣችሁ ኃጢአት ቢኖርም ወደ መንግስተ ሰማያት ትገባላችሁ የሚል ነገር አለን?

መናፍቃን ከሞት ጋር ኪዳን ገብተናል ስለሆነም ሞት ወደ እኛ አይመጣም ይላሉ ኃጢአተኛ በልቡ ኃጢአት ያለበት ቢሆንም፣ በኢየሱስ የሚያምን ከሆነ ከኃጢኣት ፍርድ ሊድን እንደሚችል ይናገራሉ በእርግጥም እንዲህ ሊሆን የሚችል ይመስላችኋልን?

መናፍቅ ካህናት በኢየሱስ ስለሚያምኑ ሐጢያተኞች ሆነው ቢቀሩ ምንም እንዳልሆነና ወደ ሲዖልም እንደማይወርዱ በመንገር ሰዎችን ያማልላሉ፡፡

መናፍቃን ካህናት ዳግም ውልደት ያላገኙ ሰዎችን ዲያቆናት አገልጋዮችና ሽማግሌዎች አድርገው ይሾሙዋቸዋል እነዚህ ሁሉ መጨረሻቸው ሲዖል መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል ምክንያቱም በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አያምኑምና እነርሱ ማድረግ ያለባቸው በተከታዮቻቸው ውስጥ በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመንን ማስረፅ ነው፡፡

ሐጢያተኞች ብትሆኑም ኢየሱስ ይጠነቀቅላችኋል? ሐጢያተኛ ሰማይ ይገባልን? ሐጢያተኛ ብትሆኑ እንኳን ወደ

ሲያል መውረድን ማስወገድ ትችላላችሁን? ምንም እንኳን በልባችሁ ውስጥ ሐጢያት ቢኖርም በኢየሱስ ካመናችሁ ሲያል እንደማትወርዱ በመፅሐፍ ቅዱስ ተፅፎዋልን? ኃጢአት ኖሮበት ቅዱስ የሆነስ አለን? ይህም ሊሆን የሚችል አይደለም። ይህ የመናፍቃንና የሐሰት ካህናት ትምህርት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ *«የኃጢት ደሞዝ ሞት ነው።» (ሮሜ 6፡23)* ይላል ይህ የእግዚአብሔር ሕግ ነው እርሱ ሐጢያተኞችን ሁሉ ወደ ሲያል ይልካቸዋል ሆኖም ከዚህ አስከፊ ዕጣ ፈንታ በተቃራኒ ከውሃና ከመንፈስ የተወለዱትን ሁሉ ሰማይ ይቀበላቸዋል።

*«ከሞት ጋር ቃል ኪዳን አድርገናል፤ ከሲኦልም ጋር ተማምለናል በሐሰትም ተሰውረናልና የሚትረፈረፍ መቅሰፍት ባለፈ ጊዜ አይደርስብንም ስላላችሁ።»* መናፍቃን በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት ቢኖር እንኳን ወደ ሲያል እንደማይወርዱ የሚጠቀሙ ቃሎችን ይናገራሉ አጥብቀውም ያምናሉ ሐሳዊና እውነተኛ ካልሆነ ስነ መለኮት ጀርባ ስለተደበቁ እግዚአብሄር እነርሱን ለመርዳት የሚደርገው አንዳች ነገር የለም እነርሱ በራሳቸው የቃለ እግዚአብሄር እውቀት ብቻ ያምናሉ በእግዚአብሄር ቃል በማመን ፋንታ በራሳቸው የቃለ እግዚአብሄር እውቀት ስለሚያምኑ ለሲያል የተመደቡ መናፍቃንና ሐጢያተኞች ናቸው ቁጥራቸው በርካታ መሆኑ ምንኛ ያሳዝናል።

# መናፍቃን ፍላጎታቸው ከገንዘብ ጋር ነው

*የመናፍቅ ካህናት አላማ ምንድን ነው?*

*ከተከታዮቻቸው የሚችሉትን ያህል ገንዘብ መሰብሰብ ነው::*

መናፍቃንና አሳሳች ካህናት ዋና ፍላጎታቸው ገንዘብ ላይ ብቻ ነው እነሱ ስግብግቦች ናቸው «ይህ ሰው እኔ ቤተ ክርስትያን ሲመጣ የሚከፍለው ገንዘብ ምን ያህል ነው?» እርሱ ስለሚሰጠው መስዋዕት ነው የሚያስቡት:: ይህ ልክ የወርቅ ጥጃን እንደማምለክ ነው ጸሎታቸውም «ጌታ ሆይ፣ እባክህን ብዙ ገንዘብ አገኝ ዘንድ እርዳኝ» አይነት ነው አሳሳች ካህናትም ሰዎች በዚህ መንገድ እንዲጸልዩ ያስተምራሉ::

እንዲሁም ደግሞ፣ «በኢየሱስ የምታምኑ ከሆናችሁ ብዙ ገንዘብ ታገኛላችሁ መካን ከሆናችሁ ትፀንሳላችሁ በንግድ ስራችሁም ይሳካላችኋል» ይላሉ::


ከዚህ የተነሳ ብዙ ሰዎችበእነዚህ አሳሳች ካህናቶች ይታለላሉ ገንዘባቸውንም ይዘረፋሉ ከነችግሮቻቸውም ወደ ሲዖል ይወርዳሉ ይህ ተገቢ አይደለም በኑፋቄ እስራት ውስ የነበረ ሰው ወደ አእምሮው ሲመለስ ለእነዚህ አጭበርባሪዎች ምን ያህል ገንዘብ እንዳበረከተ ሲያውቅ ይገረማል እነርሱን በመከተሉና በመልፋቱ መሞኘቱን ሲያውቅ ራሱን ይወቅሳል::

መናፍቃን ተገቢ ሐይማኖት ነው ብለው የሚያስቡትን በመተግበር ረገድ ግለት ይታይባቸዋል ተከታዮቻቸውም ራሳቸውን ለማለዳ ጸሎት ልዩ ለሆኑ መዋጮዎች ለአስራትና ለሳምንታዊ ስጦታዎች አሳልፈው ይሰጣሉ ከተከታዮቻቸው

ገንዘብን የሚወስዱባቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ::

ተከታዮቻቸውም በሃይማኖታቸው ላይ ጠንክረው የሚሰሩ ቢሆንም ማንም ከውኃና ከመንፈስ እንዴት መወለድ እንደሚችሉ ስላላስተማራቸው በልባቸው ውስጥ ኃጢአት አለ:: አንዳንዶች ስለዚህ ጉዳይ ይጠይቁዋቸዋል ነገር ግን በጭራሽ ቀጥተኛ መልስ አያገኙም ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ያልተወለደ ማንኛውም ሰው መናፍቅ ነው::

## አሳዛኝ መናፍቃንና ተከታዮቻቸው




«ኦ፣ እናንተ አሳዛኝ መናፍቃን! በመጀመሪያ ለራሳችሁ ምህረት ስሩ!» የአስመሳይ እምነት ትልቁ ምልክት የኢዮርብዓምን የወርቅ ጥጃ ማምለክ ነው መናፍቃን በብሉይ ኪዳን ጊዜ በመጀመሪያ ያደረጉት ነገር ህንጻዎችን መገንባትና የወርቅ ጥጃዎችንም በውስጣቸው ማስቀመጥ ነው:: **(1ኛ ነገስት 12:25-33)**

በአሁኑ ጊዜም ትላልቅ ቤተ ክርስትያናትን በማሰራት ከተከታዮቻቸው ላይ ገንዘብ ይሰበስባሉ እንዲሁም ደግሞ

ለዋናው ቤተ ክርስትያን ማሰሪያ የሚሆን ብር ይሰጧቸው ዘንድ ተከታዮቻቸውን ከባንክ ሳይቀር ገንዘብ እንዲበደሩ የሚያደርጉም አልጠፉም የተከታዮቻቸውን ስሜት ካነሳሱም በኋላ የገንዘብ መሰብሰቢያ ሳህኖችን በሕዝቡ መሃል ያዞራሉ በዚህንም ጊዜ ሳህኑ በገንዘብ በወርቅ ቀለበቶችና በወርቅ ሰዓቶች የሚሞላበት ጊዜም አለ መናፍቃን የሚሰሩት በዚህ መንገድ ነው በእያንዳንዱ የመናፍቃን ቤተ ክርስትያንም ይህ የተለመደና ተመሳሳይ ነው::

ከውጭ ሲታዩ ለመንፈሳዊ ነገር በጣም ፍላጎት ያላቸው ይመስላሉ ሆኖም ግን ውስጣቸው ሲታይ ፍላጎታቸው በሙሉ ከገንዘብ ጋር የተያያዘ ነው ለገንዘብ ብቻ ከሚጨነቁ ቤተ ክርስትያናት እንድትርቁ እጠይቃችኋለሁ ሃብታሞች ብቻ በክብር ልዩ እንክብካቤ ወደሚያገኙበት ቤተ ክርስትያን ባትሔዱ ይመረጣል የስጦታውን ገንዘብ መጠን መናገርም ስህተት ነው፤ እነዚህ መናፍቃን ግን እከሌ ይህን ያህል ሰጠ በማለት ሌላውም በፉክክር እንዲሰጥ በህዝብ ፊት ይናገሩታል::

መናፍቃን ለተከታዮቻቸው የሚያታልሉ ቃላትን ይነግሯቸዋል::

«በኢየሱስ ካመናችሁ ትድናላችሁ::»

«ራሳችሁን የእግዚአብሔርን ስራ ለመስራት አዘጋጁ ብዙ በሰራችሁም ቁጥር ይበልጥኑ የተባረካችሁ ትሆናላችሁ» ብለው ይሰብካሉ::

«ሽማግሌ ሆናችሁ ካገለገላችሁ በቁሳዊ በረከት ትባረካላችሁ::»

ስለሆነም ተከታዮቻቸው ሽማግሎች ለመሆን ይፎካከራሉ ሌላ ምንም አይነት ልዩ ነገር ከሌለ በሽምግልና ለማገልገል የሚፎካከሩት እነማን ይሆኑ ነበር? ሽማግሌዎቹም እንደዚሁ የገንዘብ መዋጮ እንዲያደርጉ ይጠበቅባቸዋል::

እነርሱ የሚመረጡት ምን ያህል በቤተክርስቲያኒቱ

ትምህርት በጥልቀት ያምናሉ በማህበረሰቡ ውስጥስ ምን ያህል ተሰሚነት አላቸው ለቤተክርስቲያንስ ምን ያህል ገንዘብ ያበረክታሉ? በሚል መስፈርት አይደለምን? ይህ እውነት ነው።

መናፍቃን የሚጨነቁት ስለ ገንዘብ ብቻ ነው ፍላጎታቸውም ትላልቅ ቤተ ክርስትያንን በመገንባት ላይ ነው ገንዘብ እስከ ሰጡ ድረስ ተከታዮቻቸው ወደ ገነት ወይም ገሃነም ቢገቡ ጉዳያቸው አይደለም።

መናፍቃን የሚሰሩት ለእንጀራቸው ነው ሕዝቦቻቸውንም ቁንጠና በሆኑ ማዕረጎች ያጠምዱዋቸዋል ለተከታዮቻቸውም በዘፈቀደ ማዕረጎችን ይሰጣሉ (ሕዝቅኤል 13፡17-19) የዚህ አላማው እነርሱን ከቤተክርስቲያን ጋር ለማቆራኘትና ሐብትን ለማብዛት ነው መናፍቃን የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል አይሰብኩም ራሳቸውን ለማበልፀግ ይሞክራሉ።

አንድ ቤተ ክርስትያን ለጥቂት ወራት ብቻ ይከታተል የነበረ ሰውም በቀላሉ ዲያቆን ሊሆን ይችላል ከዚህም በላይ ትምህርቱን በሚገባ ካወቀና አስተማማኝ የገንዘብ ምንጭ ካለው ወደ ሽማግሌነት ማዕረግ ከፍ ይላል ይህም እግዚአብሄርን በወርቅ ጥጃ ከተካው የኢዮርብአም ሐጢያት አሳፋሪ ወግ ጋር የተያያዘ ነው።


መናፍቃን የሚያመልኩት የወርቅ ጥጃዎችን ነው ሰዎቻቸውንም ዳግም እንዲወለዱ አያደርጉም ከተከታዮቻቸው ገንዘብ የሚወስዱትም በቁሳዊ በረከት ተስፋዎች በማባባል ነው ቤተክርስቲያናቸው አስተማማኝ በሆነ የገንዘብ መሠረት ላይ እስካለች ድረስ ተከታዮቻቸው ሲዖል ቢወርዱ ግድ የላቸውም።

## የመናፍቃን ስብከቶች አሳማኝነት ይጎድላቸዋል

መናፍቃን በሚናገሩት ነገር ላይ ልበ ሙሉነት ሰለሌላቸው በሚያስተምሩበት ጊዜ «ምናልባት» ወይም «ይሆናል» የሚሉትን ቃላት በተደጋጋሚ ሲጠቀሙ ይታያሉ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ሙሉ እምነት ስለሌላቸውም በሚያስተምሩት ነገር ላይም አያምኑም የሚያስተምሩበት የእምነት ዘዴም የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት ያደረገ አይደለም «እንዲህ ሊባል ይችላል...» በማለትም ይሰብካሉ ሙሉ በሙሉ በእርግጠኝነትና በግልፅም አይሰብኩም ተከታዮቻቸውን ውሸት ከሚያስተምሯቸው ይልቅ ምንም ነገር ባያስተምሯቸው ይሻላል::

መናፍቃን ሰዎች ከውኃና ከመንፈስ ዳግም እንዲወለዱ አይመሩዋቸውም::

## መናፍቃን የሚጫወቱት የሐሰት ነቢያትን ተግባር ነው




የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 7 በኢየሱስ አምነው ገሃነም ስለሚገቡ ሰዎች ይናገራል መናፍቃን በመጨረሻው ቀን

በእግዚአብሔር ፊት ይከራከራሉ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ እንደተጻፈውም፣ *«በዚያ ቀን ብዙዎች፡- ጌታ ሆይ፣ ጌታ ሆይ፣ በስምህ ትንቢትን አልተናገርንምን፣ በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን፣ በስምህስ ብዙ ተዓምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል፡፡ የዚያን ጊዜም፡- ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ ዓመፀኞች! ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ፡፡» (ማቴዎስ 7:22-23)*

ኢየሱስ የሰው ልጆችን ኃጢአት በሙሉ እንዳስወገደ አያምኑም እንዲሁም ደግሞ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌልም አያምኑም፡፡

አመፀኞችም ናቸው ይህ ምን ማለት ነው? ይህም ማለት ሰዎቹ በልባቸው ውስጥ ኃጢኣት ያለባቸው ቢሆኑም በኢየሱስ ማመን እንዳለባቸው ይናገራሉ በዚህ ላይ ስህተቱ ምንድን ነው ብላችሁ ልትጠይቁ ትችላላችሁ ሆኖም ግን ይህ በእግዚአብሔር ፊት በጣም ትልቅ ኃጢኣት ነው፡፡

አንድ ሐጢያተኛ በኢየሱስ የማመንን አስፈላጊነት ቢሰብክ ወደ ዳግም ውልደት አይመራቸውም ምክንያቱም እርሱ ራሱ ከውሃና ከመንፈስ አልተወለደም ስለዚህ መናፍቃን የሚፈሩት በኢየሱስ የሚያምኑ ሐጢያተኞችን ብቻ ነው አመፅን መለማመድ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሐጢያት መስራት ነው፡፡

መናፍቃን በእግዚአብሔር ቃል አያምኑም እንዲሁም ደግሞ የተፃፈውን ወንጌል በትክክል አያስተምሩም የሚያደርጉት ነገር ቢኖር ከተከታዮቻቸው ገንዘብን መዝረፍ ብቻ ነው ራሳቸው ዳግም ውልደትን ሳያገኙ ሌሎችን ዳግም እንዲወለዱ ለመምራት ይሞክራሉ፡፡ በኢየሱስ ቢያምኑም ኃጢአተኞች ናቸው፡፡ በዚህ መንገድ አመፅን ይለማመዳሉ፡፡

# መናፍቃን የጻድቃን ተቃራኒዎች ናቸው

*ዳግም የተወለዱትንና ያልተወለዱትን ለመለየት የምንችለው እንዴት ነው?*

*ይህን ለመለየት የምንችለው ኃጢአተኞች መሆንና አለመሆናቸውን በመጠየቅ ነው፡፡*

ኃጢአተኞች ነን በሚሉ የሐሰት ሰባኪዎች እንዳትታለሉ፡፡ ገንዘባችሁንም አትስጧቸው ጥራችሁና ግራችሁ ያመጣችሁትን ገንዘባችሁን ለእነዚያ ሐጢያተኞች አትስጡ፡፡

ከሐጢያታችሁ ነፃ እንድትወጡ ለማይረዱዋችሁ ሰባኪዎች ለምን ገንዘብ ትለግሳላችሁ? ለቤተ ክርስትያን ገንዘብ መስጠት የምትፈልጉ ከሆነም ኃጢኣታችሁ ሙሉ በሙሉ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን እስከሚሰረይ ድረስ ጠብቁ፡፡

በስነ ስዕል ውስጥ ቅዧዎች እንዳሉ ሁሉ በሕይወት ውስጥም ቅዧዎች አሉ ለምሳሌ በልብ ውስጥ ያሉ ሐጢያቶችን የማያስወግዱ ቅዧ ሐይማኖቶች አሉ አንድ ቅዧ የሆነ ሐይማኖትን ለይታችሁ የምታውቁት እንዴት ነው? ቅዧ የሆነ ነገር ከውጭ ሲታይ እውነተኛ የሚመስል ነገር ግን ከእውነተኛ ው ነገር የተለየ ነው፡፡

ለራሳችሁ መወሰን ይኖርባችኋል እውነተኛ ሰባኪዎች እነማን ናቸው? መናፍቃንስ እነማን ናቸው? ትክክለኛ የኦርቶዶክስ እምነትስ ምንድን ነው? ኦርቶዶክስ ማለት በኢየሱስና በምህረቱ የሚያምን ቀጥተኛ አማኝ ማለት ነው

ኦርቶዶክሶች በልባቸው ኃጢኣት የለባቸውም እነርሱ በልቦቻቸው ውስጥ ሐጢያት አለ።

እንደነዚህ አይነት ሰዎች ሁሉስ መናፍቃን ናቸውን? አዎን ናቸው እንዲሁም ደግሞ ወደ መፅሐፍ ቅዱስ እንመለስ ማንም በኢየሱስ አምኖ ዳግም ውልደትን ያላገኘ ሁሉ መናፍቅ ነው ዳግም የተወለዱት ኦርቶዶክሶች መሆናቸው ግልፅ ነው ስለሆም ዳግም ያልተወለዱት ደግሞ መናፍቃን ናቸው መናፍቃን በኢየሱስ እያመኑ በልባቸው ውስጥ ኃጢኣት ያለባቸው ናቸው።

መናፍቃን የፃድቃን ቅጂዎች ናቸው የቅዱሳን ተቃራኒዎች ናቸው ቅዱስ ለመሆን በኢየሱስ ማመን ያለባቸው እንደሆኑ ያውቃሉ ሆኖም ግን እነዚህ ሰዎች በልባቸው ውስጥ ኃጢኣት አለባቸው ራሳቸውም ኃጢአተኞች እንደሆኑ ያስባሉ እንደዚህም ሆነው ግን ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንደሚገቡና የሚያመልኩት እግዚአብሔርን እንደሆነ ይናገራሉ ፃድቃን ይመስላሉ ነገር ግን በቅጂዎች አንታለል።

## መናፍቃንን የእግዚአብሔር ፍርድ ይጠብቃቸዋል

*ንፁሁ ወንጌል የተቀየረው ለምንድን ነበር?*

*የውሸት ነብያትና መናፍቃን የሰውን የተሳሳተ እምነት ከእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ጋር በመቀላቀላቸው ነው።*

*«ፍርድ ሞልቶባት የነበረ የታመነችይቱ ከተማ እንዴት ጋለሞታ ሆነች! ጽድቅ አድሮባት ነበር አሁን ግን ገዳዮች አሉባት ብርህ ወደ ዝገት ተለወጠ፤ የወይን ጠጅሽ ከውኃ ጋር ተደባለቀ:: አለቆችሽ ዓመፀኞችና የሌቦች ባለንጀሮች ሆኑ ሁሉ ጉቦ ይወድዳሉ ዋጋም ለማግኘት ይሮጣሉ ለድሃ አደጉ አይፈርዱም የመበለቲቲም ሙግት ለእነርሱ አይደርስም ስለዚህ የእስራኤል ኃያል የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል:- በጠላቶቼ ላይ ቁጣዬን እፈፅማለሁ የሚቋቋሙኝንም እበቀላለሁ እጄንም በአንቺ ላይ አመጣለሁ ዝገትሽንም በጣም አነጻለሁ ቆርቆሮሽንም ሁሉ አወጣለሁ ፈራጆችሽንም እንደ ቀድሞ አማካሪዎችሽንም እንደ መጀመሪያው ጊዜ መልሼ አስነሣለሁ ከዚያም በኋላ የጽድቅ ከተማ የታመነችም ከተማ ተብለሽ ትጠሪያለሽ ጽዮን በፍርድ ከእርስዋም የሚመለሱ በጽድቅ ይድናሉ በደለኞችና ኃጢአተኞች ግን በአንድነት ይሠበራሉ እግዚአብሔርንም የሚተዉ ይጠፋሉ በወደዳችኋት የአድባር ዛፍ ታፍራላችሁና ስለ መረጣችኋትም አትክልት እፍረት ይይዛችኋልና ቅጠልዋ እንደረገፈ ዛፍ፣ ውኃም እንደሌለባት አትክልት ትሆናላችሁና ኃይለኛውም እንደተልባ ጭረት ስራውም እንደ ጥለሸት ይሆናል አብረውም ይቃጠላሉ እነርሱንም የሚያጠፋ የለም::» (ኢሳያስ 1:24-31)*

በሰብአዊ ፍጡር የምናምን ከሆነ እንደምናፍር እግዚአብሄር ነግሮናል ለራሳችን በመረጥነው ቤተክርስቲያንም እንደምናፍር ነግሮናል ይህ ሐፍረትም ውሃ እንደሌለው የአትክልት ስፍራ ቅጠል አልባ በሆነ ዛፍ ይመሰላል::

በእግዚአብሄር ቃል ከማመን ይልቅ በሰው ስርአት የሚያምኑ ሐሰተኛ ካህናትና ተከታዮቻቸው ገለባ ስራቸውም እሳት ይሆናል ሁለቱም በሲዖል ይቃጠላሉ ሁሉም የሐሰት ሰባኪዎችና መናፍቃን እንዲሁም ደግሞ ምህረትን ያላገኙና

ኃጢአተኞች እንዲሁም የጻድቃን ጠላቶች በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት ፍርድ ይጠብቃቸዋል።

በሃይማኖት ፍልስፍናዎች መሰረት የተቆረቆሩ ቤተ ክርስትያናት ከውጭ ሲታዮ ጠንካሮች ይመስላሉ ሆኖም ግን ውስጣቸው ሲገባ ባዶ ነው በእግዚአብሔር ቃል እምነትና ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድ ወንጌል ላይ ያልተመሰረተ ማንኛውም ቤተክርስቲያን ውሃ እንደሌለው የአትክልት ስፍራ ነው።

ዛፍ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ፍሬ ማፍራት የማይችል የሞተ ዛፍ ነው አንድ ጉድጓድ ውሃ ከሌለው ዳግመኛ ጉድጓድ አይደለም።

*«ኃይለኛውም እንደተልባ ጭረት ስራውም እንደ ጥለሸት ይሆናል አብረውም ይቃጠላሉ እነርሱንም የሚያጠፋ የለም»* እነዚያ መንፈስ የሌላቸው ለሌሎች ብርቱ መስለው ይታዩ ይሆናል ነገር ግን በእግዚአብሄር አይኖች ለሲያል እሳት የተሰበሰበ ገለባን ይመስላሉ።

ጌታ እንዲህ ብሎ ተናግሯል *«ጉበኛ ሆይ፣ ለሊቱ ምን ያህል ነው?» (ኢሳይያስ 21፡11)* ዘላለማዊ ህይወት ያገኙ ፃድቃን በጨለማው ሌሊት የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበክ ይገባቸዋል።

እግዚአብሔር ብርሃን ሲሆን ሰይጣን ደግሞ ጭለማ ነው። እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ፅድቅ ይመራል ሰይጣን ሰዎችን ወደ ሐሰተኛ የሁከት መቅደሶችና የሐሰት ቲዎሎጂ ይመራል።

በነቢዩ ኢሳይያስ ዘመንም የሰው ልጆች እምነት እንደአሁኑ ዘመን የተተራመሰ ነበር የእግዚአብሔርን ቃል ከሰው ልጆች አስተሳሰብ ጋር ቀላቅለው ነበር የእግዚአብሔርን ቃል ከሰው ልጆች ፍልስፍና ጋር በመቀላቀልም የእስራኤልን ሕዝብ ወደ ክፋት መርተዋል ከዚህ የተነሳ እግዚአብሄር ሊያተፋቸው ወሰነ።

*«ፈራጆችሽንም እንደ ቀድሞ አማካሪዎችሽንም እንደ መጀመሪያው ጊዜ መልሼ አስነሣለሁ»* በእግዚበአብሔር ፊት ተቀባይነት የሌላቸው ፀሎቶች የዚህን አይነት ናቸው።

እግዚአብሔር የተደባለቁ መስዋዕትን አይፈልግም። በሰው ልጅ አይን ሲታዩ ንጹህ ሊመስሉ ይችላሉ ሆኖም ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ከሌላቸው ነገሮች ጋር ተቀላቅለዋል።

እግዚአብሔር የእሰራኤልን ሕዝብ በተለይም መናፍቃንና አሳሳች ካህናትን እንዲሁም ተከታዮቻቸውን በሙሉ ቀጥቶኣቸዋል።

ዘጸአትን ወይም ዘኍልቁን ብናነብ እግዚአብሔር መጀመሪያ እንዳልዘለፋቸው ማየት እንችላለን እግዚአብሔር ሕዝበ እስራኤልን ረዳቸው ባረካቸውም ነገር ግን ኢያሱ ከሞተ በኋላ ከመሳፍንቶች ዘመን ጀምሮ ሕዝበ እስራኤል በጠላት ተወረሩ።

ሆኖም የራሳቸውን መንገድ መጓዝ መረጡ በዚያን ዘመን እግዚአብሄር ነቢዩን ኤርምያስን ልኮ እስራኤሎች ለባቢሎን እጃቸውን እንዲሰጡ ነገራቸው።

ኤርምያስ ለሕዝቡ እጃቸውን ለባቢሎን እንዲሰጡ ነገራቸው ይህ መንፈሳዊ ትርጉም አለው ፃድቁ መናፍቃንን የሚከተሉ ለውሃውና ለመንፈሱ ወንጌል እጃቸውን እንዲሰጡ የሚናገር የመሆኑን ሐቅ ያመላክታል።

# እግዚብሔር መናፍቃንን ይቀጣል

*እግዚብሔር መናፍቃንን የሚቀጣው ለምንድን ነው?*

*በእግዚብሔር ፈንታ ጣዖትን ስለሚያገለግሉ ነው፡፡*

የእግዚአብሔር ባሮች የእስራኤልን ሕዝብ የወቀሱት ለምንድን ነው? የመስዋዕት ስርአቱን ስለለወጡ ተራ ሰዎችን ካህናት አድርገው ስለሾሙና መስዋዕቶቹ የሚቀርቡባቸውን ቀኖች ስለቀየሩ ነው፡፡

እነርሱ የስርየቱን ቀን ከሰባተኛው ወር 10ኛው ቀን ወደ ስምንተኛው ወር አስረኛው ቀን ከመለወጣቸውም በላይ ከሌዋውያን ውጭ የሆኑ ካህናቶችንም ሾመዋል በዚህም ዳግም የመወለድን መንገድ ዘጉ፡፡


እግዚብሔር ሐሰተኛ ሰባኪዎችን ነቅፏል እግዚአብሄርን ከማገልገል ይልቅ የወርቅ ጥጆችን ያገለገሉ መናፍቅ ካህናት ሆነዋል፡፡

በእርግጥም ጣዖት የሚያመልኩትን ብቻ አይደለም ያስጠነቀቀው እኔና እናንተስ አንዳንድ ጊዜ ጣዖትን አናመልክምን? እኛም አንዳንድ ጊዜ ኃጢአትን እንሰራለን ነገር ግን በእግዚአብሄር ፀጋ ውስጥ ስላለን በደሎቻችን የከፉ ሐጢያቶች ሆነው አይታዩም በእግዚአብሔር ምህረት ግን እኛ የምንሰራቸው ኃጢኣቶች አይመዘገቡብንም ሆኖም ግን እግዚአብሔርን በወርቅ ጥጃ መተካት ግን ይቅር ሊባል የሚችል

ኃጢኣት አይደለም እንዲሁም የመስዋዕት ስርዓቱንም መቀየር እንዲሁ ይቅርታ ሊደረግለት የማይቻል ኃጢአት ነው፡፡

እነዚህ እንዴት የሚያስፈሩ ኃጢአቶች ናቸው! እነዚህ እጅግ የከፉ ኃጢኣቶች ናቸው እግዚአብሔርን በወርቅ ጥጆች የለወጠ ሰው እንዴት ይቅር ሊባል ይችላል? የእግዚአብሄርን ቁጣ ያመጣው የኢዮርብአም ሐጢያት እንደነበረ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተፅፎዋል፡፡

## መናፍቃን በሕገወትነት መስዋዕትን ያቀርባሉ




እግዚአብሄር በብሉይ ኪዳን ቁጣውን እንደገለጠ ሁሉ አሁንም እርሱን የሚቃወሙትን ሐጢያተኞች ያጠፋል እግዚአብሄር የወርቅ ጥጆችን ከማምለክ የማይመለሱትን እንደሚረግም ለእስራኤል ሕዝብ ተናግሮዋል፡፡

የእስራኤል ነገስታትና መናፍቅ ካህናት እግዚአብሄርን በመቃወም የመስዋዕት ስርአቱን የናቁትን ለክህነት ሾመዋል ያልተረጋጋ አእምሮ የነበረው ንጉስ ኢዮርብአም ከሌዊ ቤት ያልሆነ አንድ ሰው ካህን አድርጎ ሾሞ ነበር፡፡

ካህናት መሆን የሚችሉትና በድንኳኑ ውስጥ የሚያገለግሉት

ከሌዊ ቤት የሆኑ ብቻ ናቸው ለማገልገል የሚችሉ ሰዎች ከሌዊ ወገን የሆኑት ብቻ ናቸው በግልጽ ሲቀመጥም አንድ ሰው ካህን ሊሆን የሚችለው የአሮን ዘር ከሆነ ብቻ ነው ይህ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕግ ነው ሆኖም ግን ኢዮርብዓም ከአሮን ዘር ውጭ የሆኑ ሰዎችን በመምረጥ ለወርቅ ጥጆች መስዋዕትን እንዲያቀርቡበት አድርጓል ይህ እግዚአብሔርን ምን ያህል እንዳስቆጣው መረዳት መቻል አለብን::

ዛሬም ዳግም ያልተወለዱ በቤተክርስቲያን ውስጥ አገልጋዮች ሽማግሌዎችና ዲያቆናት ሊሆኑ ይችላሉ ይህ የእግዚአብሔርን ህግ የሚጻረር ነው ያለ ሕጉ በሚደረግ መስዋዕት እግዚአብሔር የሚደሰት ይመስላችኋልን? መናፍቃን የወርቅ ጥጃዎቻቸውን መሰባበርና ወደ እግዚአብሄር በመመለስ ዳግም ሊወለዱ ይገባቸዋል::

ኢሳይያስ 1:10-17 እንዲህ ይላል *«እናንተ የሰዶም አለቆች ሆይ፣ የእግዚአብሔርን ቃል ስሙ እናንተ የገሞራ ሕዝብ ሆይ፣ የአምላካችንን ሕግ አድምጡ የመስዋዕታችሁ ብዛት ለእኔ ምን ይጠቅመኛል? ይላል እግዚአብሔር የሚቃጠለውን የአውራ በግ በመስዋዕትንና የፍሪዳን ስብ ጠግቤኣለሁ የበሬና የበግ ጠቦት የአውራ ፍየልም ደም ደስ አያሰኘኝም በእኔ ፊት ልትታዩ ብትመጡ ይህን የመቅደሴን አደባባይ ለመርገጥ አትችሉም ከእጃችሁ የሚሻ ማነው? ምናምንቴውን ቁርባን ጨምራችሁ አታምጡ እጣን በእኔ ዘንድ አፀያፊ ነው መባቻችሁንና ሰንበታችሁን በጉባኤም መሰብሰባችሁን አልወድድም በደልንም የተቀደሰውንም ጉባኤ አልታገሰምም መባቻችሁንና በዓላቶቻችሁን ነፍሴ ጠልታለች ሸክም ሆነውብኛል ልታገሳቸውም ደክሜአለሁ እጃችሁንም ወደ እኔ ብትዘረጉ አይኔን ከእናንተ እሰውራለሁ ልመናንም ብታበዙ አልሰማችሁም እጆቻችሁ ደም ተሞልተዋል ታጠቡ ሰውነታችሁንም አንጹ*

*የስራችሁን ክፋት ከአይኔ ፊት አስወግዱ ክፉ ማድረግን ተዉ መልካም መስራትን ተማሩ ፍርድን ፈልጉ የተገፋውንም አድኑ ለድሃ አደጉ ፍረዱለት ስለመበለቲቱም ተሟገቱ::»*

ይህንን ምንባብ በጥንቃቄ ካነበብነው የእስራኤል የሐይማኖት መሪዎች በጣም ራሳቸውን የሰጡ እንደነበሩ ማየት እንችላለን ነገር ግን ያንን ያህል ራሳቸውን የሰጡ ቢሆኑም የተሳሳቱ መስዋዕቶችን በማቅረባቸውና የእግዚአብሄርን ሕግ ባለመታዘዛቸው ጠፍተዋል::

መስዋዕትን ሲያቀርቡ የእግዚአብሔርን ሕግ አልጠበቁም የእግዚአብሄርንም ቃል አልታዘዙም እነዚህ መሪዎች ራሳቸውን በእግዚአብሄር ፊት ስፍር ቁጥር የሌላቸውን መስዋዕቶች አቅርበዋል በመቅደሱ ውስጥ ደም እንደ ጎርፍ እንደፈሰሰ መፅሐፍ ቅዱስ ይናገራል::

ሆኖም ግን እግዚአብሔር ያደረጉትን ሲመለከት ድርጊታቸው ልክ እንደ ገሞራ ሐጢያት መሆኑን ተናግሮዋል በፊቱ መስዋዕቶችን ያቀርቡ እንደነበር ተመልክቷል ነገር ግን ሐጢያት እየሰሩ ነበር ፈፅሞ መስዋዕትን አለማቅረብ የተሻለ እንደነበርም ተናግሮዋል::

በወርቅ ጥጆቹ ፊት መስዋዕቶችን ሲየቀርቡ እግዚአብሄር ሐጢያታቸውን ይቅር ማለት አልቻለም ዳግመኛም ሊታገሰው አልቻለም እነርሱ መስዋዕቶችን ማቅረብ የሚገባቸው እርሱ ባዘዘው መንገድ መሆን እንዳለበትም ነግሮዋቸዋል እንደዚያ ካልሆነ ጨርሶ መስዋዕቶችን ባያቀርቡ የተሻለ ነበር::

መስዋዕቶቻቸው በትክክለኛው መንገድ ለእግዚአብሔር የቀረቡ አልነበሩም ከዚህ የተነሳ ካህናቶቹ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአትን ሰሩ ሐጢያታችሁ ሳይታጠብ እግዚአብሄርን ማገልገልና ስራውን መስራት በእርሱ ፊት የከፋ ሐጢያት መሆኑን ማወቅ ይኖርባችኋል::

# መናፍቃን ልክ እንደ ትምህርት ቤት መምህራን ናቸው

*መናፍቃን ምን ያስተምራሉ?*

*ስለ ዳግም ውልደት ሳይሆን ስለ ስነ ምግባር ያስተምራሉ፡፡*

መናፍቃን መድረክ ላይ ሲወጡ ማራኪ መስለው ስለሚታዩ ብዙዎች በገፅታቸው ይታለላሉ የክህነት ልብሳቸውን ሲለብሱም በጣም መስህብ ያላቸው ናቸው አነጋገራቸውም ምክንያታዊ ይመስላል ሁልጊዜም ስብከቶቻቸውን የሚያጠናቅቁት ሕዝቡ ደግ እንዲሆን በመምከር ነው ይህ ምን አይነት ስብከት ነው? በእነርሱ ስብከቶችና በትምህርት ቤት አስተማሪዎች ትምህርቶች መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

የእግዚአብሔር ቤተ ክርስትያን ሰዎች ዳግም ውልደትን የሚያገኙበትና እግዚአብሔርን የሚያመልኩበት ቦታ ነው እውነተኛዋ ቤተ ክርስትያን የዚህ አይነቷ ቤተ ክርስትያን ብቻ ነው እውነተኛ የእግዚአብሄር ቤተ ክርስትያን በእግዚአብሔር ፊት እንዴት መልካም ሆኖ እንደሚቀረብ ለማስተማር አትሞክርም የእውነተኛዋ ቤተክርስቲያን ሰባኪ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ይሰብካል ምንም ያህል ደካማ ብትሆኑም እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችሁን ሁሉ አጥቦ አስወግዶታል፡፡

መናፍቅ የሆነ ሰባኪያን ተከታዮቻቸውን «ይህን አድርጉ፣ ይህን አታድርጉ» እያሉ ያስተምራሉ በተከታዮቻቸው ላይ ሸክምን ይጭናሉ፤ ራሳቸውን ግን አይመለከቱም፡፡

መናፍቅ የሆነ ሰባኪ ለልጁ ውድ የሆነ ቫዮሊን ይገዛለታል ልጁንም ለትምህርት ወደ ውጪ ይልካል አንድ ካህን ይህን

እንዴት ሊከፍል ይችላል? ገንዘቡን የሚያገኘው ከየት ነው? ይህን ያህል ገንዘብም ካለው ለምን ወንጌል ለመስበክ አያውለውም? ሰባኪ ውድ መኪና መንዳት ያስፈልገዋልን? ገዝፎ ለመታየትም ውድና ዘመናዊ መኪናዎችን መንዳት አለበትን? ውድ መኪናን የሚነዳ ካህን ሌባ ነው ተከታዮቹ ምግባቸውን እንኳን መግዛት ሳይችሉ እንዴት እርሱ ውድ መኪና ይይዛል? መናፍቅ የሆነውን ሰባኪ በድርጊቶቹ ለይተን ልናውቀው እንችላለን::

መናፍቅ የሆኑ ካህናት ከፍተኛ ገንዘብ ይጠይቃሉ ይህ በይፋ የሚከፈል ነው የትምህርት ክፍያ፣ ለመፅሐፎች የሚከፈሉ ክፍያዎች፣ ለልጅ ማሳደጊያ የሚሆኑ ክፍያዎች፣ የጉብኝት ክፍያዎች ይከፈላቸዋል::

አንዳንዶቹ በቂ ክፍያ አልተከፈለንም ብለው ያጉረመርማሉ በወር 10,000 ዶላር ያገኛሉ ተጨማሪ ገንዘብም ይሻሉ 10,000 ዶላር አነስተኛ ደመወዝ ነውን? አንድ ሰው የውሃውንና የመንፈሱን እውነት ሲሰብክ ሊያኖረው የሚችለውን ብቻ ካገኘ ሊበቃው ይገባል::

እውነተኛ ሰባኪ መፅናናትንና ሰላምን ከእግዚአብሄር ይቀበላል ውስጡ ሰላም የሌለው መናፍቅ የሆነ ሰባኪ ግን የገንዘብ ካሳ ይጠይቃል እነዚህን አይነቶቹ ሰባኪዎች የሚያመልኩት የወርቅ ጥጃዎችን ነው::

የእግዚአብሔር ቤተ ክርስትያን አንዳንድ ጊዜ ፅዮን ተብላ ትጠራለች እንደ ፅዮን ያለ ውብ ቤተ ክርስትያን የለም የእግዚአብሔር ቤተ ክርስትያን የውኃና የመንፈስ ወንጌል የሚሰበክበት ነው::

ኢሳይያስ 1:21 ላይ እንደተጻፈውም:- *«ፈርድ ምልቶባት የነበረ የታመነችይቱ ከተማ እንዴት ጋለሞታ ሆነች! ጽድቅ አድሮባት ነበር፣ አሁን ግን ገዳዮች አሉባት»* ኢሳይያስ

የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስትያንን *«ፍርድ ሞልቶባት የነበረች»* ብሎ ይጠራታል።

እግዚአብሔር ትክክልና ፍትሃዊ ነው። እኛ ፍፁማን ስላለሆንን እንዲሁም ደግሞ ከኃጢአት ጋር አብረን የተወለድን የአዳምና የሔዋን ዘሮች በመሆናችን ኢየሱስ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ሊያድነን ወደ ምድር መጥቷል እግዚአብሔር ይህን ያህል ፍትሐዊ ነው።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ሰዎች ሙሉ አለመሆናቸው በተረዱ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር በመምጣት መስዋዕትን አቅርበዋል «በዚህና በዚህ ምክንያት ስህተትን ሰርቻለሁ ይህ ስህተት ነበር» በዚህም በየዕለቱ ከሚሰሩት ኃጢአት ይድኑ ነበር።

በተመሳሳይ መንገድም በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ዘር ሐጢያቶች ለአንዴና ለዘላለም ለማስወገድ ወደዚህ አለም መጥቶ በመጠመቅ ተሰቀለ።

ነገር ግን በአዲስ አመት አገልግሎት ወቅት ብዙ ሰዎች «እግዚአብሔር ሆይ፣ ባለፈው ዓመት የሰራሁትን ኃጢአት ይቅር በለኝ። በአዲሱ ዓመትም ባርከኝ።» እያሉ ይፀልያሉ ያለቅሳሉ እነዚህን ሰዎች መናፍቃን ናቸው።

ታዲያ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለዱ እውነት ምንድን ነው? ኢየሱስ ከ2000 ዓመታት በፊት ወደዚህ ምድር በመምጣት የዓለምን ኃጢኣት በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አንጽቷል እኛንም ለዘላለም አድኖናል በውኃውና በደሙም ከአለም ሐጢያቶች በሙሉ አድኖናል በየቀኑ ይቅርታን የምንለምን ከሆንን እርሱ ምን ይለናል?

*«ፍርድ ሞልቶባት የነበረ የታመነችይቱ ከተማ እንዴት ጋለሞታ ሆነች! ጽድቅ አድሮባት ነበር፣ አሁን ግን ገዳዮች አሉባት»* ማንም ራሱን ኃጢኣተኛ ብሎ የሚጠራ መናፍቅ ነው።

# መናፍቅ ካህናት ከውኃና ከመንፈስ የመወለጃውን ወንጌል ለመስበክ አይችሉም

*እግዚአብሔር የኃጥአንን ፀሎት ይሰማልን?*

*አይሰማም:: ኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር ስለሚለያቸው ሊሰማቸው አይችልም::*

እግዚአብሔር በእርሱ እያመኑ ይቅርታን የሚጠይቁትን ነፍሰ ገዳዮች ብሎ ይጠራቸዋል ይቅርታን ስለሚጠይቁና ሐጢያተኞች መሆናቸውን ስለሚናገሩ ኢየሱስ ዳግመኛ መጥቶ ለሐጢያቶቻቸው እንዲሞትላቸው ይጠብቃሉን? የኢየሱስ ጥምቀትና መስቀሉ የደህንነት ጭብጥ ናቸው::

በ1ኛ ጴጥሮስ 3:21 ላይ የኢየሱስ ጥምቀት የደህንነት ምሳሌው መሆኑን ይናገራል ኢየሱስ ክርስቶስ አንዴ የሞተው ለሰው ልጆች ኃጢኣት ሲል ነው የሰው ልጆችን ኃጢአት በሙሉ ለአንዴና ለዘላለሙ ካስወገደ በኋላ ከሶስት ቀን በኋላ ተነስቷል አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦዋል::

ኢየሱስ ክርስቶስ አንዴ ተጠምቆ አንዴ በመስቀል ላይ በመሞት ከኃጢአት ለዘላለም አድኖናል 30 ዓመት ሲሞላውም በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ ከአለም ሐጢያቶች ያድነን ዘንድም አንድ ጊዜ ሞተ ይህ ፍርድ ለዘላለም መሰጠቱትን የሚያሳይ አይደለምን?

መናፍቃን ኃጢአተኞች ነን ብለው ሲናገሩ በተመሳሳይ ጊዜ ኢየሱስ ለኃጢኣታቸው ዳግም እንዲሰቀል እየጠየቁት ነው

በእርግጥም እነርሱ ይቅርታ በጠየቁ ቁጥርም ይህን ማድረግ አያስፈልገውም።

በልባቸው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ለዘላለም ከሐጢያት ድነው ፃድቃን ይሆናሉ የእግዚአብሄርን በረከትና የዘላለምን ሕይወት ለመቀበልም ወደ ሰማይ ይሄዳሉ ፃድቁን የሚገናኝ ሁሉ በውሃውና በመንፈሱ ድኖ ከእግዚአብሄር ብሩካን ሕዝቦች አንዱ ይሆናል።

ኢሳይያስ 1:18-20ን እናንብብ *«ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚብሔር ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነፃለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ የምድርን በረከት ትበላላችሁ እምቢ ብትሉ ግን ብታምፁም ሰይፍ ይበላችኋል የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሯልና።»*

የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል የምንታዘዝ ከሆነ የምድሪቱን በረከት እንደምንቀበል ነገር ግን እምቢተኞችና አመፀኞች ከሆንን ሰይፍ እንደሚበላን እግዚአብሄር ይነግረናል።

አምላካችን «ኑና እንነጋገር ደካሞች ናችሁን? በደለኞች ናችሁን? ራሳችሁን አብዝታችሁ ትወዳላችሁን? ሕጉ የሚናገረውን ማድረግ ተስኖዋችኋልን? የምታውቁትን መተግበር አልቻላችሁምን? እንግዲያውስ ወደ እኔ ኑ በዚህም ኃጢኣታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነፃለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትነጣለች» ይለናል ይህ ማለት እግዚአብሔር ሐጢያተኞችን በፅድቅ አድኖ ፃድቃን አድርጎዋቸዋል ማለት ነው።

እግዚአብሔር አዳምንና ሔዋንን ሲፈጥር ምንም ኃጢኣት አልነበረም ነገር ግን ሰይጣን ወደ ትዕይንቱ መጣ በእግዚአብሄር ላይ እንዲያምፁ ፈተናቸው የሰው ዘር በሙሉም ሐጢያት እንዲሰራ በማድረግ ሐጢያተኞች አደረጋቸው በመጀመሪያ

አዳምና ሔዋን በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች አልነበሩም የሚኖሩትም ከእግዚአብሄር ጋር በኤድን ገነት ውስጥ ነበር ነገር ሐጢያተኞች ሆኑ ስለዚህ አሁን እግዚአብሔር እየጠራን ነው ኑና እንዋቀስ እያለን ነው ኑና እንዋቀስ!

«በዚህ ዓለም ምን ያህል ኃጢአት ሰርታችኋል? ከመሞታችሁ በፊትስ ምን ያህል ሐጢያት ትሰራላችሁ?»

«ኦ! እግዚአብሔር ኃጢአትን አለመስራት የሚቻል አይደለም ምንም ያህል በጥንካሬ የምንሞክር ብንሆን ልንቀደስ አንችልም።»

«እሺ፣ እስከ አሁን ድረስ ምን ያህል ኃጢአትን ሰርታችኋል?»

«እሺ ጌታ ሆይ! ሁሉን ነገር ለማስታወስ አልችልም ሆኖም ግን በአእምሮዬ ውስጥ የቀሩ ጥቂት አሉ ያን ጊዜ ታስታውሰዋለህን? ስለምን እየተናገርሁ እንደሆነ ታውቃለህ... ሌላ ጊዜም የሰራሁትን ታውቃለህ....»

ከዚያም እግዚአብሔር እንዲህ በማለት ይቀጥላል፡- «እሺ ቀጥል ንገረኝ ይህ ብቻ ነውን? ከዚህ ውጭ ምን ያህል እንዳሉ ታውቃለህ? ሆኖም የምታስታውሳቸው ሐጢያቶች በሙሉ የረሳሃቸውን ሐጢያቶች ወደፊት የምትሰራቸውን ሐጢያቶች ሁሉ እንኳን ሳይቀር ለዘላለም አስወግጄአቸዋለሁ የአንተን ብቻ ሳይሆን የልጆችህንና የልጅ ልጆችህን ሐጢያቶች በሙሉ አስወግጄአለሁ እኔ ፃድቅ አምላክ ነኝ ሐጢያቶችን ለአንዴና ለዘላለም አስወግጄአለሁ።» ከአዳም ሐጢያት ጀምሮ በምድር ላይ እስከሚኖረው የመጨረሻ ሰው ሐጢያቶች ድረስ ያሉትን የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ያስወገደው እግዚአብሄር አልፋና ዖሜጋ ፊተኛና ኋለኛ ነው።

«እኔ አዳኝና ሁሉን ቻይ አምላክ ነኝ።»

«እኔ ይሆዋ፣ መሐሪው እግዚአብሔር ነኝ።»

«ምህረት ለሚገባቸው ምህረትን እሰጣቸዋለሁ ርህራሄ ለሚገባቸውም ርህራሄን እሰጣቸዋለሁ።»

የእርሱን ምህረት ከለመንንና ለእርሱ እውነተኞች ከሆንን የእግዚአብሄር ርህራሄ ይሰጠናል አባታችን ሁላችንንም ሊባርከን ይሻል ሁላችንም ፃድቃን እንድንሆን ይፈልጋል በፍቅሩና በርህራሄው ፃድቅ ልጆቹ ሊያደርገን ይፈልጋል።

*ዳግም ከተወለድን በኋላ እግዚአብሔር ምን እንድናደርግ ይፈልጋል?*

*ወንጌልን በመላው ዓለም እንድንሰብክ ይፈልጋል።*

እርሱ ልክ እንደ በረዶ ነጭ እንድንሆን ይፈልጋል ኢየሱስ የሰው ልጆችን ኃጢአት በጥምቀቱና በደሙ ለአንዴና ለዘላለሙ አንጽቷል ቤተክርስቲያን የምዕመናኑን ሁሉ የሐጢያትና የሕይወት ችግሮች በሙሉ ለመፍታት የማትችል ከሆነ የእግዚአብሄር እውነተኛ ቤተክርስቲያን ተብላ ልትጠራ አትችልም።

ሰዎች ወደ ካህናት በመቅረብ «ኃጢአት አለብኝ ምን ላድርግ? በየዕለቱ ለኃጢኣቴ ፀሎትን አደርጋለሁ ሆኖም ግን ኃጢአቶቼ ሊወገዱልኝ አልቻሉም በዚህ ሁኔታ ለመቀጠልም አልፈልግም የሐይማኖት ሕይወቴን መቀጠል እንደምችል አላስብም» ካህኑም ለዚህ ግለሰብ ችግሮች ትክክለኛውን መልስ መስጠት የማይችል ከሆነ መናፍቅ ነው «የራስህ ጉዳይ ነው

ወደ ተራሮች ሄደህ ፀልይ የ40 ቀን ፆም ሞክር» ይለው ይሆናል፡፡

መናፍቅ ካህናት ወይም የሃይማኖት መሪዎች ቆሻሾች ስለሆኑ የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንኳን አያውቁትም የነፍሳቸው መጨረሻ ሲዖል ይሁን ወይም ሰማይ አያውቁም፡፡

እነዚህ መሪዎች በእግዚአብሔር ፊት ትክክል አይደሉም እነርሱ አስመሳይ ክርስቲያኖችና መናፍቃን ናቸው ከውጭ ሲታዩ በኢየሱስ የሚያምኑ ይመስላሉ ልባቸው ግን አሁንም በሐጢያት የተሞላ ነው ከሐጢያቶቻቸው አልታጠቡም እነርሱ ሐጢያቶችን ሁሉ ማስወገድ የሚችለውን የውሃና የመንፈስ ወንጌል አይሰብኩም በእነዚህ አንታለል፡፡

ቲቶ 3፡10-11 ስለ መናፍቃን ሲናገርም *«መለያየትን የሚያነሳ ሰው ጠማማ እንዲሆን በራሱ ላይ ፈርዶ ኃጢአትን እንዲያደርግ አውቀህ፣ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜም ከገሰጽኸው በኋላ እንዲህ ከሚመስል ሰው ራቅ»* ይላል በኢየሱስ አምነው ዳግም ስላልተወለዱ ራሳቸውን ሐጢያተኞች አድርገው ይኮንናሉ የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌል ባለመቀበላቸውም መጨረሻቸው ሲዖል ይሆናል፡፡

እነዚህ በክርስትና ውስጥ ያሉ መናፍቃን ናቸው በኢየሱስ እያመነ ነገር ግን በልቡ ውስጥ ሐጢያት ያለበት ሰው መናፍቅ ነው መናፍቃን ከእግዚአብሄር ተነጥለዋል በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ግን ከሐጢያታቸው ሁሉ ነፅተዋል በኢየሱስ እያመነ በልቡ ሐጢያት ያለበት ሰው ሰው ሁሉ መናፍቅ ነው በእግዚአብሄር እናምናለን እያሉ ገናም ሐጢያተኞች ከሆኑት መራቅ ይኖርብናል፡፡ ✉

# ስብከት 3

# እውነተኛው

---

# መንፈሳዊ ግርዘት

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ..ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::



«አሮንም እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል፣ በላዩም የእስራኤል ልጆች በደል ሁሉ፣ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢአታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል፤ በፍየሉም ራስ ላይ ያሸክመዋል፣ በተዘጋጀው ሰውም ወደ ምድረ በዳ ይሰድደዋል:: ፍየሉም ኃጢአታቸውን ሁሉ ወደ በረሀ ይሸከማል፤ ፍየሉንም በምድረ በዳ ውስጥ ይለቅቀዋል:: (ዘሌዋውያን 16:21-22)

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::

# እውነተኛው መንፈሳዊ ግርዘት

**« ዘፀዓት 12:43-49 »**

**«እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን አለ፡- ይህ የፋሲካ ሕግ ነው፣ ከእርሱ እንግዳ ሰው አይብላ በብር የተገዛ ባርያ ቢኖር ከተገረዘ በኋላ ከእርሱ ይብላ መፃተኛና ሞያተኛ ግን ከእርሱ አይብሉ በአንድ ቤትም ይበላ ከሥጋውም አንዳች ከቤት ወደ ሜዳ አታውጡ አጥንትም አትስበሩበት የእስራኤልም ጉባኤ ሁሉ ያድርጉት እንግዳ ሰውም በመካከላችሁ ቢቀመጥ ለእግዚአብሔርም ፋሲካን ሊያደርግ ቢወድድ አስቀድሞ ወንድ ሁሉ ይገረዝ፣ ከዚያ ወዲያ ይቅረብ ያድርግም እንደ አገር ልጅም ይሆናል ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ ለአገር ልጅ በእናንተ መካከልም ለሚቀመጡ እንግዶች አንድ ሥርዓት ይሆናል፡፡»**

*በብሉይ ኪዳን መሠረት እስራኤላውያን የእግዚአብሔር ልጆች ለመሆን የግድ ማድረግ ያ ለባቸው ነገር ምንድን ነው?*

*የግድ መገረዝ አለባቸው፡፡*

በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉት የእግዚአብሔር ቃሎች በእግዚአብሔር ለምናምን አስፈላጊና የከበሩ ናቸው ከእነዚያ ቃሎች አንዲት ሐረግ እንኳን መቀነስ አንችልም ምክንያቱም የእግዚአብሄር ቃሎች የሕይወት ቃሎች ናቸውና፡፡

ፋሲካን ማክበር የሚፈልግ ማንኛውም ሰው አስቀድሞ መገረዝ እንደሚኖርበት የዛሬው ምንባብ ይነግረናል እግዚአብሄር ይህንን ለእኛ የነገረበትን ምክንያት ማሰብ ይገባናል ያልተገረዘ ሰው ፋሲካን ማክበር አይችልም፡፡

በኢየሱስ ማመን ካለብን ይህንን ትዕዛዝ በመስጠት ረገድ የእግዚአብሄርን አላማ መረዳት ይኖርብናል ግርዘት ትርፍ ቆዳን የማስወገድ ስርዓት ነው እግዚአብሔር ለአብርሃምና ለዘሮቹ እንዲገረዙ የነገራቸው ለምንድነው? ምክንያቱ የእርሱ ሕዝብ የሚሆኑት ሐጢያታቸውን «ቆርጠው የጣሉት» ብቻ እንደሆኑ ተስፋ ስለሰጠ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር የእስራኤልን ሕዝቦች እንዲገረዙ ያዘዘው ለዚህ ነው የእስራኤል ሕዝቦች የእግዚአብሄር ሕዝቦች ለመሆን መገረዝ ነበረባቸው ይህ የእርሱ ትዕዛዝና የቅድስናም መሠረት ነበር እርሱም በግርዘት አማካይነት ሐጢያታቸውን በእምነት ላስወገዱት አምላክ ሆንዋል በተጨማሪም በአዲስ ኪዳን ሐጢያትን በእምነት ቆርጠው ለጣሉት አምላክ ሆኖላቸዋል፡፡

## ፋሲካ

*ፋሲካ ምንድን ነው?*

*እስራኤላውያን እግዚአብሔር ከግብፅ ባርነት ነጻ ያወጣቸውን ቀን የሚያስታውሱበት በዓል ነው።*

ለእስራኤል ሕዝቦች በጣም ጠቃሚው በዓል ፋሲካ ነበር ይህም እስራኤላውያን በግብፅ ለ400 ዓመት በባርነት ከኖሩ በኋላ እግዚአብሄር አርነት ያወጣበትን ቀን ለማስታወስና ለእግዚአብሔር ምስጋና ለማቅረብ የሚያከብሩት በዓል ነው እግዚአብሔር የፈርዖንን በትዕቢት ያበጠ ልብ ለማብረድ በሕዝቡ ላይ 10 ዓይነት ታላላቅ መቅሰፍትን አድርሶበታል በዚህም የእስራኤል ሕዝቦችን ከግብጽ ምድር አስወጥቶ ወደ ተስፋዋ ምድር ወደ ከንዓን መርቷቸዋል።

ሕዝበ እስራኤል የመጨረሻ መቅሰፍት ከሆነው የበኩራት ሞት የዳነው በተሰዋው ጠቦትና በግርዘት ነበር ስለዚህ ለምህረቱ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ በትውልዳቸው ሁሉ ፋሲካን እንዲያከብሩ ነገራቸው።

## ፋሲካን ለማክበር እስራኤላውያን ማድረግ የሚጠበቅባቸው ነገር ምንድን ነበር?

*ፋሲካን ለማክበር እስራኤላውያን ማድረግ የሚጠበቅባቸው ነገር ምንድን ነበር?*

*መገረዝ ነበረባቸው።*

ፋሲካን በመንፈሳዊ መልኩ ለማክበር የልብ ግርዘት እንደሚያስፈልገን መረዳት አለብን የእስራኤል ሕዝቦች እንኳን ፋሲካን ለማክበር መገረዝ ነበረባቸው።

በዘፀዓት 12:43-49 እንዲህ ተብሎ ተጽፎዋል *«እግዚአብሔርም ሙሴንና አሮንን አለ፦ ይህ የፋሲካ ሕግ ነው ከእርሱ እንግዳ ሰው አይብላ በብር የተገዛ ባርያ ቢኖር ከተገረዘ በኋላ ከእርሱ ይብላ መፃተኛና ሞያተኛ ግን ከእርሱ አይብሉ በአንድ ቤ ትም ይበላ ከሥጋውም አንዳች ከቤት ወደ ሜዳ አታውጡ አጥንትም አትስበሩበት የእስራኤልም ጉባኤ ሁሉ ያድርጉት እንግዳ ሰውም በመካከላችሁ ቢቀመጥ ለእግዚአብሔርም ፋሲካን ሊያደርግ ቢወድድ አስቀድሞ ወንድ ሁሉ ይገረዝ ከዚያ ወዲያ ይቅረብ ያድርግም እንደ አገር ልጅም ይሆናል ያልተገረዘ ሁሉ ግን ከእርሱ አይብላ ለአገር ልጅ በእናንተ መካከልም ለሚቀመጡ እንግዶች አንድ ሥርዓት ይሆናል»* ለእስራኤላውያን ሲናገርም ፋሲካን ለማክበር ከፈለጉ መገረዝ እንዳለባቸው አዝዟቸዋል።

ፋሲካን ለማክበር የሚታረደውን የበግ ስጋ ለመብላት

የተፈቀደላቸው እነማን ነበሩ? ፋሲካን ለማክበር የሚችሉት የተገረዙት ብቻ ነበሩ።

የፋሲካው በግ ሁላችንም እንደምናውቀው የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ የሚያስወግደው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያለው ግርዘት ምንድን ነው? ግርዘት የወንድን ሸለፈት ቆርጦ መጣል ነው ኢየሱስ ክርስቶስም ወደዚህ አለም በተወለደ በ8ኛው ቀን ተገርዟል በፋሲካ ስርአት የሚሳተፉ ሁሉ መገረዝ እንዳለባቸው እግዚአብሄር አዞዋል ማንኛውም ያልተገረዘ ሰው በፋሲካ ላይ ጨርሶ መሳተፍ እንደማይችል ግልፅ አድርጓል።

ስለዚህ እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት እያንዳንዱ ሰው መገረዝ አለበት በኢየሱስ የምታምኑም ከሆነ በአዲስ ኪዳን ያለውን የግርዘት ትርጉም ማወቅ አለባችሁ።

## እግዚአብሔር አብርሃምን ያደርግ ዘንድ ያዘዘው ሥርዓት ምንድን ነው?

*አብርሃምና ዘሮቹ የእግዚአብሔር ልጆች መሆን የቻሉት እንዴት ነው?*

*በመገረዝ ነው።*

በዘፍጥረት ላይ እግዚአብሔር ለአብርሃም ተገልጦለት ከእርሱና ከዘሮቹ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ በምዕራፍ 15 ላይም


እግዚአብሔር የአብርሃም ዘሮች እንደ ከዋክብት እንደሚበዙና ለመኖሪያቸውም የከነዓን ምድርን እንደሚሰጣቸው ቃል ገብቶላቸዋል፡፡

እንዲሁም በምዕራፍ 17 ላይ ደግሞ አብርሃምና ዘሮቹም የእርሱን ኪዳን በመጠበቅ የሚገረዙ ከሆነ እርሱ አምላካቸው እንደሚሆንና እነርሱም ሕዝቦቹ እንደሚሆኑ ቃል ገብቶላቸዋል ይህ እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዘሮቹ ጋር የተጋባው ኪዳን ነው አምነው መገረዛቸው የእርሱ ሕዝብ እንዲሆኑ እንደሚያደርጋቸውና በእርግጥም አምላካቸው እንደሚሆን እግዚአብሄር ተስፋ ሰጥቷል፡፡

ዘፍጥረት 17፡7-8 ላይ እንዲህ ይላል *«ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸውም ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ አምላክ እሆን ዘንድ፡፡ በእንግድነት የምትኖርባትን ምድር የከነዓን ምድር ሁሉ ለዘላለም ግዛት ይሆንን ዘንድ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ እሰጣለሁ አምላክም እሆናቸዋለሁ፡፡»*

ግርዘቱም እግዚአብሔር ከአብርሃምና ከዘሮቹ ጋር ለገባው ቃል ኪዳን ምልክት ነው፡፡

## መንፈሳዊ ግርዘት ምንድን ነው?



አብርሃም በእግዚአብሔር ቃል በማመኑ እግዚአብሔር ፃድቅና የራሱ ልጅ አደረገው በእግዚአብሔርና በአብርሃም መካከል ለነበረው ቃል ኪዳንም ምልክቱ ግርዘት ነበር፡፡

*«በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ኪዳኔ ይህ ነው ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ፡፡» (ዘፍጥረት 17:10)*

ስጋዊ ግርዘት ማለት ሸለፈትን ቆርጦ መጣል ማለት ነው ይህ በመንፈሳዊ መልኩ በእርሱ ጥምቀት ባለን እምነት አማካይነት ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ወደ ኢየሱስ ማሻገርን ያመላክታል በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት የመጣውን ደህንነት በመቀበል ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ባስወገደልን ጊዜ በመንፈሳዊ መልኩ ተገርዘናል በአዲስ ኪዳን ግርዘት በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት ሐጢያቶችን ሁሉ ቆርጦ ማስወገድ ነው፡፡


ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ግርዘት የተባለው በአዲስ ኪዳን የኢየሱስ ጥምቀት ነው ሁለቱም የእርሱ ሕዝብ የሚያደርጉን እግዚአብሄር ኪዳናት ናቸው ስለዚህ የብሉይ ኪዳን ግርዘትና የአዲስ ኪዳኑ የኢየሱስ ጥምቀት አንድና ተመሳሳይ ናቸው፡፡

የአብርሃም ዘሮች ሸለፈቶቻቸውን ቆርጠው በጣሉ ጊዜ የእግዚአብሄር ሕዝብ እንደሆኑ ሁሉ እኛም ሐጢያትን ሁሉ ከልባችን ስናስወግድ የእግዚአብሄር ልጆች እንሆናለን ይህንን የምናደርገው በአለም ላይ ሐጢያት እንደሌለ በማመን ነው ምክንያቱም ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያትን ሁሉ አስወግዷልና፡፡

የኢየሱስ ጥምቀት ኃጢኣቶቻቸውን በማስወገድ ሐጢያተኞችን ሁሉ ፃድቃን አድርጎዋቸዋል በግርዘት ጊዜ ከሰውነታችን ትንሽ የቆዳ ክፍል ተገልፍፎ እንደሚወድቅ ሁሉ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ የሰው ልጆች ኃጢኣትም እንዲሁ ተገልፍፎ ወድቋል

ይህንን የሚያምኑ በመንፈሳዊ መልክ ሊገረዙና ፃድቅ የእግዚአብሄር ሕዝብ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

## ሰዎች ራሳቸውን ከእግዚአብሄር እንዲለዩ የሚያደርግ የሐሰት እምነት




እግዚአብሔር ለአብርሃም ያልተገረዘ ሰው ከሕዝቡ መካከል ተለይቶ እንደሚጠፋ ነግሮታል መንፈሳዊ ግርዘትስ ምንድን ነው? ግርዘት ከአካል ክፍል የተወሰነ ቆዳን ገፍፎ መጣል ከሆነ መንፈሳዊ ግርዘት ደግሞ ሐጢያትን ሁሉ ከልባችን ውስጥ ማስወገድና በጥምቀቱ አማካይነት ወደ ኢየሱስ ማሻገር ነው፡፡

የኢየሱስ ጥምቀት የአለም ሐጢያቶች ከእኛ ተወግደው ወደ ኢየሱስ የተሻገሩበት የሰው ዘር መንፈሳዊ ግርዘት ነው ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀው ሐጢያትን ሁሉ በሚያስወግደው መንፈሳዊ ግርዘት አማካይነት የሰውን ዘር ሁሉ ለማዳን ነው፡፡

የሰው ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተሻግረዋል እግዚአብሄር አብርሃም የያዕቆብና የዘሮቻቸው ሁሉ አምላክ በመሆን ከአብርሃምና ከዘሮቹ ጋር ቃል ኪዳን ተጋብቶ

ሸለፈቶቻቸውን እንዲያስወግዱ አደረገ በዚህም በግርዘት አማካይነት ሐጢያቶቻቸውን ለሚያስወግዱ ሁሉ አዳን አምላክ ሆነ፡፡

ኃጢአትን የሚያስወግደው ግርዘት ምንድን ነው? ግርዘቱ እግዚአብሄር ከአብርሃምና ለደህንነታቸውም በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ በሆነው ሞቱ አምነው ዳግም ከተወለዱት ጋር ያደረገው ቃል ኪዳን ነው በዚህ ሁኔታ የእርሱ ሕዝብ እንድንሆን መብት ሰጥቶናል ስለዚህ እርሱ ለተገረዙት አምላክ ነው፡፡

እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ አለው *«የስምንት ቀን ልጅ ይገረዝ በቤት የተወለደ ወይም ከዘራችሁ ያይደለ በብርም ከእንደግዳ ሰው የተገዛ ወንድ ሁሉ በትውልዳችሁ ይገረዝ በቤትህ ተወለደ በብርህም የተገዛ ፈጽሞ ይገረዝ ቃል ኪዳኔም በስጋችሁ የዘላለም ቃል ኪዳን ይሆናል፡ የቁልፈቱን ስጋ ያልተገረዘ ቁላፍ ሰው ሁሉ ያች ነፍስ ከወገንዋ ተለይታ ትጥፋ ቃል ኪዳኔን አፍርሳለችና፡፡» (ዘፍጥረት 17:12-14)*

በመንፈሳዊ ግርዘት ውስጥ ሳያልፍ ወደ ኢየሱስ ለመቅረብ የሚሞክር ማንኛውም ሰው ከሕዝቡ ተለይቶ ይጠፋል በአዲስ ኪዳን መንፈሳዊ ግርዘት የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ወደ እርሱ የተሻገሩበት የኢየሱስ ጥምቀት ነው፡፡

ማንም በኢየሱስ የሚያምን ሰው ሁሉ፤ ለመዳንና የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆንም በብሉይ ኪዳን ላይ ባለው የግርዘት ሥርዓትና በአዲስ ኪዳን ባለው የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ማመን አለበት ለኛም በኢየሱስ ለምናምን በአዲስ ኪዳን ያለው የኢየሱስ ጥምቀትና በብሉይ ኪዳን ያለው ግርዛት ተመሳሳይ ናቸው፡፡

የግርዘትን እውነተኛ ትርጉም መረዳት ከተሳነን ወይም ዳግም እንድንወለድ የሚፈቅድልንን ደህንነት በመንፈሳዊ ግርዘት

አማካይነት በልቦቻችን ካልተቀበልን እምነታችን ከንቱ ይሆናል ለእግዚአብሄር ታማኞች እንደሆንን እናስብ ይሆናል ነገር ግን ይህ እምነት ቤታችንን በአሸዋ ላይ እንደመገንባት ነው።

እግዚአብሔር በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ እንዲገረዙና በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነትም በደህንነት እንዲያምኑ ነግሮዋቸዋል ያለ ግርዘት እኛ የእርሱ ሕዝቦች ልንሆን አንችልም ካልተገረዝን ከሕዝቡ እንገለላለን ስለዚህ በገንዘብ የተገዛም ይሁን መፃተኛ ማንኛውም ሰው ፋሲካን ከመውሰዱ በፊት መገረዝ እንዳለበት እግዚአብሄር ደንግጓል።

ከእስራኤላውያን የሚወለዱትም ጭምር በዚህ ፋሲካ ላይ ለመሳተፍ መገረዝ ግዴታቸው ነበር እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር የገባው ቃል ኪዳንም በኢየሱስ ለሚያምኑ ሁሉ የሚያገለግል መሆን አለበት።

በዘፀዓት ምዕራፍ 12 ላይ የፋሲካውን ስጋና መራራውን ቅጠል የተመገበው ሕዝበ እስራኤል ቀደም ብሎ ተገርዟል የፋሲካውን ሥጋ የመብላት መብት የተሰጣቸው የተገረዙት ብቻ ናቸው።

የእስራኤል ሕዝቦች የፋሲካውን ስጋ በበሉና የጠቦቱን ደም በቤቶቻቸው መቃንና ጉበን ላይ በቀቡ ጊዜ አስቀድመው ተገርዘው እንደነበር ማወቁ ይጠቅመናል።

አንድ ሰው በእግዚአብሔር ሕግ መሰረት ካልተገረዘ ከሕዝቡ ይገለልና የእግዚአብሄር ልጅ የመሆን መብቱን ያጣል ይህ ማለት በመንፈሳዊ ግርዘት ያለ ማመን ሐጢያት ሰዎችን ወደ ጥፋት ይነዳል ማለት ነው መዳን የሚችሉት በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት መንፈሳዊ ግርዘትን ያገኙ ብቻ ናቸው።

*«አሁን ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ ያድነናል» (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)*
ኢየሱስ በዮርዳኖስ ሲጠመቅ ኃጢአታችሁ በሙሉ ወደ እርሱ መተላለፉን ታምናላችሁን? በኢየሱስ ጥምቀት፣

በደሙና በመንፈሱ በትክክል የምታምኑ ከሆናችሁ መንፈሳዊ ግርዘት እንዳገኛችሁና በዚህም ቅዱሳን የእግዚአብሔር ልጆች እንደሆናችሁ ትገነዘባላችሁ በመስቀል ላይ የፈሰሰው የኢየሱስ ደም ያለ ጥምቀቱ ትርጉም የለሽ በመሆኑ መንፈሳዊ እውነት ላይ እምነት ይኖራችኋል፡፡

በኢየሱስ ጥምቀት በማመን መንፈሳዊ ግርዘትን ሳታገኙ በኢየሱስ መስቀል ብቻ የምታምኑ ከሆናችሁ ራሳችሁን ከእግዚብሔር ምህረት የራቃችሁ ሆናችሁ ታገኙታላችሁ በልባችሁ ውስጥ አሁንም ኃጢአት እንዳለ ታገኛላችሁ፡፡

የእግዚአብሔር ምህረት የተጀመረው ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ወንዝ በተቀበለው ጥምቀቱ ሲሆን የተፈፀመውም በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ መሆኑን መገንዘብ አለብን ይህንን ለማድረግ የእውነት ቃሎች የሆኑትን የኢየሱስን ጥምቀትና ደሙን ደህንነታችን አድርገን በልባችን መቀበል ይኖርብናል፡፡

በዚህ እምነት ከጨለማው ሃይል ድነን የብርሃን ልጆች ልንሆን እንችላለን ይህ እምነት በተጨባጭ ዳግም የተወለዱትን ከተራ ምዕመናን ይለያቸዋል፡፡

ጌታችን ኢየሱስ እርሱን እንድንታዘዘው ይጠይቀናል እርሱ የዓለምን ኃጢአቶች በጥምቀቱና በደሙ አጽድቷል ስለዚህ የእግዚአብሔር ሕዝብ የመሆንን ምልክት ለመያዝ በኢየሱስ ጥምቀት ማመን አለብን ይህን ማድረግ ከተሳነን ከእርሱ ጋር እንቆራረጣለን፡፡


የቤዛነት ደህንነት ማለት በብሉይ ኪዳን ያለው ግረዘትና በአዲስ ኪዳን ያለው የኢየሱስ ጥምቀት ነው ሙሉ በሙሉ ልንድን የምንችለው በመንፈሳዊው ግርዘት (የኢየሱስ ጥምቀት) እና በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ (የፋሲካው በግ ደም) ስናምን ብቻ ነው፡፡

በብሉይ ኪዳን ያለው የስጋ ግርዘት በአዲስ ኪዳን ካለው

የኢየሱስ ጥምቀት ጋር የተገናኘ ነው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ ቃሎች በሙሉ ባልንጀራ እንዳላቸው ኢሳይያስ 34:16 ይነግረናል *«በእግዚአብሔር መጽሐፍ ፈልጉ አንብቡም አፌ አዝዞኣልና መንፈሱም ሰብስቦኣቸዋልና ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም ባልንጀራውንም የሚያጣ የለም::»*

እያንዳንዱ በብሉይ ኪዳን ያለ ቃል በሙሉ ከአዲስ ኪዳን ጋር የተገናኘ ነው አንዱም የእግዚአብሔር ቃል አጣማጁን አያጣም::

## ትክክል ባልሆነ መንገድ በሞኝነት የሚያምኑትን በሚመለከትስ




በዚህ ዘመን በፋሲካው በግ ደም ብቻ የሚያምኑ ብዙዎች ናቸው እንዲህም እያሉ ይጠይቃሉ «ግርዘት ስትሉ ምን ማለታችሁ ነው? ይህ የሚሰራው በብሉይ ኪዳን ጊዜ ለነበሩ እስራኤላውያን ብቻ ነው በአዲስ ኪዳን ዘመን ስጋችንን ቆርጠን መጣል አይኖርብንም::»

በእርግጥ ይህ እውነት ነው እኔም እያልኩ ያለሁት ስጋችንን መገረዝ አለብን አይደለም ሐዋርያው ጳውሎስ

መንፈሳዊ ግርዛትን በግልፅ አብራርቶታል እኔም እየተናገርኩ ያለሁት የልብን ግርዘት ነው፡፡

የስጋ ግርዘት እንድታደርጉ እየነገርኋችሁ አይደለም የስጋ ግርዘት ለእኛ ምንም ትርጉም የለውም ነገር ግን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ለመዳን ወደ ኢየሱስ መምጣትና በጥምቀቱ በማመን በመንፈሳዊ መልክ መገረዝ ይኖርብናል፡፡

አንድ ሰው ዳግም ይወለድ ዘንድ በመንፈስ መገረዝ አለበት ማንም በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ በመንፈስ መገረዝ አለበት ይህም ከኃጢኣት የምንነፃበትና ቅዱሳን የምንሆንበት ብቸኛው መንገድ ነው እኛ ከኃጢኣት በሙሉ በሙሉ ልንነፃ የምንችለው በመንፈስ ከተገረዝን በኋላ ነው ስለሆነም በኢየሱስ ጥምቀት በማመን በልባችን መንፈሳዊ ግርዛት መቀበል አለብን፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ በመንፈሳዊው ግርዘት ያምናል ሲናገርም፡- *«ግርዛትስ የልብ ነው» (ሮሜ 2:29)* ብሏል ማንም ሰው ከኃጢኣት ይነጻ ዘንድም መገረዝ አለበት፡፡

ኃጢኣቶቻችሁ ከእናንተ ላይ ከተወሰዱ በኋላ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋልን? በአዲስ ኪዳንም ቢሆን በኢየሱስ የሚያምኑ በኢየሱስ ጥምቀት በማመን መገረዝ ይኖርባቸዋል፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ይህንን ነገር በመልዕክቶቹ ውስጥ ግልፅ አድርጓል እግዚአብሔር የሰው ዘር በሙሉ ከአለም ሐጢያት አድኖ ሕዝቡ አድርጓቸዋል የእስራኤል ልጆች ሸለፈታቸውን በማስወገድ የእግዚአብሄር ሕዝብ እንደሆኑ ሁሉ በጥምቀቱ በማመን ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ወደ ኢየሱስ ስናሻግር የእርሱ ልጆች እንሆናለን፡፡

እግዚአብሔር የራሱ ሕዝብ አድርጎ የሚቀበለን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ላይ ያለንን እምነት ሲያይ ነው ይህ እምነት በመንፈሳዊ መልኩ እንድንገረዝ ያደርገንና ወደ ደህንነት ይመራናል፡፡

# ደህንነት ለሐጢያተኞች የሚሰጠው በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ አማካይነት ነው

*ደህንነት በኢየሱስ የተሟላው እንዴት ነው?*

*በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባለፈች ሕይወቱ ነው::*

የኢየሱስ ክርስቶስ ደህንነት የተሟላው በእርሱ የጥምቀት ውኃና ለኃጢአተኞች ሲል በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ ነው የበጉ ደም ፍርድ ነበር የኢየሱስ ጥምቀትም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ ራሱ ያሻገረበት መንፈሳዊ ግርዘት ነበር::

ዛሬ የክርስቲያን ቤተ ክርስትያናት ይህንን የመንፈሳዊ ግርዘት እሳቤ ማቃለል አይገባቸውም ምንም እንኳን በዚህ ዘመን የብሉይ ኪዳን ግርዘት ለእኛ ያለው ትርጉም አነስተኛ ቢሆንም የኢየሱስ ጥምቀት በጭራሽ ቸል ሊባል አይገባውም::

ኃጢአቶቻችሁ በሙሉ በኢየሱስ ጥምቀት መወገዳቸውንና የኢየሱስ ጥምቀትም ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ እንዳዳናችሁ ነግሬያችኋለሁ ይህን ታምናላችሁን? የኢየሱስን ጥምቀት ቸል ካላችሁት ዳግም የምትወለዱበትን ወንጌል በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት የሆነውን ምሉዕ የደህንነት ወንጌል በጭራሽ አታውቁትም::

ሐዋርያው ዮሐንስ የሰበከው ወንጌል ከኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ካፈሰሰው ደሙ ወንጌል የተለየ አይደለም በ1ኛ ዮሐንስ 5:6 ላይ ሲናገርም *«በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶሰ በውኃውና በደሙ*

*እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም»* ይላል፡፡

ኢየሱስ የመጣው በውኃ በመንፈስና በደም መሆኑን ይናገራል በውኃው ብቻ ሳይሆን እንዲሁም በደምም ብቻ ሳይሆን በሁለቱም- በውኃውና በደሙ ነው የመጣው እነዚህ ሶስት ፍሬ ነገሮች - የኢየሱስ ጥምቀት በመስቀል የፈሰሰው ደሙና የሙታን ትንሳኤው አንድ ናቸው እነዚህም የደህንነታችን ማረጋገጫ ናቸው፡፡

## ስለ ኢየሱስ ጥምቀትና ስለ ደሙ መጽሐፍ ቅዱስ በተደጋጋሚ የሚናረው ለምንድን ነው?

*የእስራኤል ሕዝቦች ይድኑ የነበረው ለፋሲካ በሚያርዱት በግ ደም ብቻ ነበርን?*

*አይደለም፡፡ ፋሲካን ከማክበራቸው በፊት ይገረዙ ነበር፡፡*

የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ እኛን ከውኃና ከመንፈስ ዳግም ለመወለድ የሚያስችሉን ነገሮች ናቸው በዘፀዓት ምዕራፍ 12 ላይ እንደሚናገረው «ለራሳችሁ በግን ውሰዱ በደጃፋችሁም ከደሙ ጥቂት ጠብታዎችን ወስዳችሁ ርጩት ደሙንም ስመለከት አልፋችኋለሁ፡፡»

ይህንን እያወቅን በፋሲካው የበግ ደም ብቻ በማመን ልንድን እንችላለንን? በአዲስ ኪዳንስ ስለ ኢየሱስ ጥምቀት በተደጋጋሚ የተነገረው ለምንድነው? ሐዋርያት እንዲህ ብለዋል

*«በጥምቀትም ከእርሱ ጋር ተቀበራችሁ» (ቆላስያስ 2:12) «ከኢየሱስ ጋር አንድ ትሆን ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና» (ገላትያ 3:27) «ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል።» (1ኛ ጴጥሮስ 3:21)*

ሐዋርያቱ ጳውሎስና ጴጥሮስ እንዲሁም ሌሎቹም የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በሙሉ ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ተናግረዋል ሁሉም የሚጠቅሱት ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁን ነው እንዲሁም ከውሃውና ከመንፈሱ የመወለድ እውነት በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ማመን ነው።

እውነቱን ለመናገርም እኔም ራሴ ከ10 ለሚበልጡ ዓመታት ጥምቀቱን ሳልቀበል በኢየሱስ ደም ብቻ ነበር የማምነው። ሆኖም ግን ይህ እውቀቴ በልቤ ውስጥ ያለውን ኃጢአት ሊያስወግድልኝ አልቻለም በኢየሱስ የማምነው በሙሉ ልቤ ነበር ሆኖም ግን በልቤ ውስጥ ኃጢአት ሞልቶበት ነበር።

ከ10 ዓመታት በኋላም የመንፈሳዊ ግርዘትን (የኢየሱስን ጥምቀት) ተረዳሁ ከዚያም ዳግም ተወለድሁ በብሉይ ኪዳን ግርዘት የሚያመለክተው በአዲስ ኪዳን የኢየሱስን ጥምቀት የመሆኑን እውነት የተረዳሁት ያን ጊዜ ብቻ ነው ከዚያ በኋላ በዚህ አመንኩኝ አሁንም ድረስ የማምነው በዚህ ነው።

«በአዲስ ኪዳን በጥምቀቱና በደሙ በሁለቱም ማመን ትክክለኛ እምነት ነውን? በመጽሐፍ ቅዱስ መሰረትስ እምነቴ ትክክል ነውን?» ዳግም ከተወለድሁ በኋላ ስለ እነዚህ ነገሮች ተገረምሁ።

ምንም እንኳን በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ መልዕክት ባምንም «ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ኃጢአቶቼ በሙሉ ወደ እርሱ የመሻገራቸውን እውነት ማመን ትክክል ነው ወይስ ኢየሱስ ያዳነን በመስቀል ላይ ሞቱ ብቻ ነው ብሎ ማመኑ ነው ትክክል? ኢየሱስ አምላኬና አዳኜ መሆኑን ማመን ብቻ በቂ

አይደለምን?» የሚሉ ጥያቄዎች በአእምሮዬ ውስጥ ነበሩ ዘፀአት 12ን ሳነብ በዚህ ጉዳይ ላይ አተኮርሁ::

ዛሬ ብዙ ሰዎች ዘፀአት 12ን ያነባሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መድህናቸው ሆኖ መሞቱን ከማወጃቸው በፊት ሁለት ጊዜ አያስቡም በኢየሱስ ደም ማመን ትክክል እንደሆነ ያስቡና የእምነታቸውን እውነት ይመሰክራሉ ኢየሱስ የተቀባ የእግዚአብሄር ልጅ መሆኑን ያለማወላወል ሊያምኑና ሊናገሩ ይችላሉ ነገር ግን አሁንም ሐጢያተኞች ናቸው ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝ መሆኑን ቢያምኑ በልቦቻቸው ውስጥ አሁንም ሐጢያት ቢኖር እንኳን እንደሚድኑ ያስባሉ::

የዚህን አይነቱ እምነት እውነተኛ እምነት አይደለም ይህ እምነት ብቻውን ዳግም እንዲወለዱ አይረዳቸውም ፃድቃን የሚያደርገን የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ ብቻ ነው::

ዘፀዓት ምዕራፍ 12 የሚለው ምንድን ነው? «ጥምቀቱን በመተው በኢየሱስ የመስቀሉ ላይ ደም ብቻ ማመን ችግር አይኖረውምን?» ብዬ እያሰብኩ መፅሐፍ ቅዱሰን ለማንበብ ገለጥኩ ዘፀዓትን እንኳን አንብቤ ሳልጨርስ የደህንነት እውነታው በኢየሱስ ደም ብቻ ማመን ሳይሆን በጥምቀቱም ጭምር እንደሆነ ተረዳሁ በመፅሐፍ ቅዱስ አማካይነት የልብ ግርዘትን እንዳገኘን ማረጋገጫ አግኝቻለሁ::

*ብዙ ክርስትያኖች አሁንም ድረስ ኃጢአተኞች የሆኑት ለምንድን ነው?*

*በኢየሱስ ጥምቀት ስለማያምኑ ነው::*

ከዘፀዓት 12:47-49 እንደተረዳሁትም አንድ ሰው የፋሲካውን ስጋ ለመመገብ የሚፈቀድለት ከተገረዘ በኋላ ነው እግዚአብሔር በቁጥር 49 ላይ *«ለአገር ልጅ በእናንተ መካከል ለሚቀመጡ እንግዶችም አንድ ሥርዓት ይሆናል»* ብሎ የተናገረው ለዚህ ነው

ስለሆነም ማንም ያልተገረዘ ሁሉ የፋሲካውን በግ ስጋ አይበላም ይህ እኔ ያገኘሁት እውነታ ነው በተመሳሳይ መንገድም በኢየሱስ አዳኝነት ስናምን በመጀመሪያ ኃጢአቶቻችን በሙሉ እርሱ በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀ ጊዜ ወደ እርሱ መተላለፋቸውንና ኢየሱስ ክርስቶስም በመስቀል ላይ የሞተው ለእኛ ኃጢአቶች ፍርድን ለመቀበል እንደሆነ ማመን ይገባናል::

ኢየሱስ በጥምቀቱ አማካይነት ላስወገዳቸው ሐጢያቶች ይፈረድበት ዘንድ በመስቀል ላይ መሞቱን በተረዳሁ ጊዜ ከአለም ሐጢያቶችና መተላለፎች ሁሉ ያዳነንን የመንፈሳዊ ግርዘት ትርጉምንም ተረዳሁ::

በዚያ ቅፅበትም ኃጢአቶቼ በሙሉ መወገዳቸውን ተረዳሁ ልቤም እንደ በረዶ ነጣ በመጨረሻም የውኃውን የደሙንና የመንፈሱን ወንጌል ወደ ልቤ አስገባሁኝ::

ሁለት የሚያድኑን ነገሮች እንዳሉ ተረድቻለሁ እነርሱም በብሉይ ኪዳን ያለው ግርዘትና የጠቦቱ ደም ሲሆን በአዲስ ኪዳን ደግሞ በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ እርሱ መሻገራቸውና በመስቀል ላይ ደሙን ማፍሰሱ ናቸው የብሉይ ኪዳን ግርዘትና የአዲስ ኪዳን የኢየሱስ ጥምቀት ተመሳሳይና አንድ ናቸው::

ኢየሱስ ክርስቶስ ፍርድ የተፈረደበት ራሱ ኃጢኣትን ሰርቶ ሳይሆን በጥምቀቱ የዓለምን ኃጢአቶች የእኔንና የእናንተን ኃጢአት በመውሰዱ ነው አጥማቂው ዮሐንስ የሰው ዘር ወኪል ሆኖ ኢየሱስን እንዳመጠቀና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወደ

ኢየሱስ እንዳሻገረ የሚያምኑ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ያምናሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ የተገለፀ ቢሆንም ሰዎች የኢየሱስን ጥምቀት የማይቀበሉት ለምንድን ነው? ይህን በማድረጋቸውም በኢየሱስ የሚያምኑ ቢሆንም አሁንም ድረስ ኃጢአተኞች ናቸው በኢየሱስ የሚያምኑ ሊሆኑ ይችላሉ በኢየሱስ ምኑ ይሆናል ነገር ግን አሁንም ከኢየሱስ ተለይተዋል በኢየሱስ የሚያምኑ ቢሆንም ወደ ገሃነም የሚገቡ አሳዛኝ ኃጢአተኞች ናቸው።

በኢየሱስ የሚያምኑ ከሆኑ እንዴት አሁንም ድረስ ኃጢአተኞች ሊሆኑ ይችላሉ? እንደ ኃጢአተኛ የሚኖሩትስ ለምንድን ነው? ወደ ጥፋትስ የሚገሰግሱት ለምንድን ነው? ይህ በጣም የሚያሳዝን ነው ዘላለማቸውን የዓለም ኃጢአቶች በሙሉ በመንፈሳዊ ጥምቀቱ አማካይነት ለሰዎች ሁሉ የዘላለም ደህንነትን ወዳመጣላቸው ወደ ኢየሱስ የመሻገራቸውን እውነት ስለማያምኑ ሐጢያተኞች ሆነው ይኖራሉ።

ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ደም በማመናቸው ብቻ ሊድኑ የሚችሉ ይመስላቸዋል ሆኖም ግን የዚህን አይነት እምነት መቼም ቢሆን ሊያድናቸው አይችልም ለምን? ለዚህ ምክንያቱም ኃጢአታቸውን ወደ ኢየሱስ ለማስተላለፍ ባለመቻላቸው ነው!

እኛ ልንድን የምንችለው እግዚአብሔር ባዘዘው መሠረት በኢየሱስ ውኃና (ጥምቀት) በደሙ መንፈሳዊ ግርዘት ስናምን ብቻ ነው እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች መሆን የምንችለው ያን ጊዜና ያን ጊዜ ብቻ ነው።

ራሳችንን እንዲህ ብለን መጠየቅ ይኖርብናል «ለመንፈሳዊ ግርዘት በኢየሱስ ደም ብቻ የምናምን ከሆንን ሐጢያቶቻችን ሙሉ በሙሉ ሊወገዱ ይችላሉን?» መልሱን ለማግኘት ልባችንን ጠልቀን መመልከት ያስፈልገናል።

እኛ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ደህንነትን እንዳገኘን በብሉይ ኪዳንም ሰዎች የሚድኑት በግርዘትና በፋሲካው ጠቦት በኩል ነበር ከእግዚአብሄር ፍርድና ከዚህ ሐጢያተኛ አለም የዳንነው በዚህ መንገድ ነው የሚያምኑ የእግዚአብሄር ልጆች ይሆናሉ እግዚአብሄርም አባታቸው ይሆናል::

አንድ ሰው ሊድንና የእግዚአብሔር ሊሆን የሚችለው በሁለት ነገሮች ሲያምን ነው በግርዘትና በፋሲካው በግ ደም ይህም ማለት፡- በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ነው እንደ ኢየሱስ አባባል እውነቱ ይህ ነው ከውሃ ከደምና ከመንፈስ ዳግም የመወለድ ፍቺም ይህ ነው::

## በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰው የውኃና የመንፈሱ ደህንነት ምንድን ነው?

*ኃጢአተኞች በኢየሱስ ደም ብቻ በማመን ጻድቃን ሊሆኑ ይችላሉን?*

*በፍጹም አይችሉም::*

ኢየሱስ በሰማይ ያለውን መንግስቱን ትቶ ወደ ምድር መጥቷል ኢየሱስ 30 ዓመት በሞላው ጊዜ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በመጠመቅ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ አስወግዷል::

የኢየሱስ የመስቀሉ ላይ ደም ለዓለም ኃጢአተኞች በሙሉ የከፈለው መስዋዕትነት ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር

የመጣው እንደ አዳኝ ሆኖ የዓለምን ሕዝብ ከኃጢአት ለአንዴና ለዘላለሙ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ሊያድናቸው ነው፡፡

እኛ ዳግም የተወለድነው በደሙ ብቻ ነውን? አይደለም እኛ ከኃጢአት ልንድን የቻልነው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ነው በኢየሱስ ደም ብቻ የሚያምኑትን ሰዎች ጥያቄ ልጠይቅ እወዳለሁ «ኃጢአተኞች በኢየሱስ ደም ብቻ በማመን ጻድቃን ሊሆኑ ይችላሉን? ወይስ ጻድቃን የሚሆኑት በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ደም በማመናቸው ነው? ኃጢአቶቻችንን በሙሉ ወደ ኢየሱስ የምናስተላልፈው በእርሱ ጥምቀት ባለን እምነት ነው ወይስ በደሙ ብቻ ባለን እምነት ነው? እውነት መስሎ የሚታያችሁ የትኛው ነው? እኔ እየጠየኳችሁ ነው፡፡»

ከውኃውና ከመንፈሱ በትክክል ዳግም ለመወለድ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር በመንፈስ መምጣቱን የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ ሊያስወግድም በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ መጠመቁን እንዲሁም ደግሞ እነዚህን ኃጢአቶች ለማስወገድም በመስቀል ላይ መድማቱንና መሞቱን ማመን አለብን በዚህ መንገድ በእውነተኛው አዳናችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን በትክክል ዳግም መወለድ እንችላለን፡፡

ደግሜ እጠይቃችኋለሁ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተገለፀው እምነት ምንድን ነው? ይህ በኢየሱስ ደም የተገለጠ እምነት ነው ወይስ በጥምቀቱና በደሙ የተገለጠ እምነት ነው?

በኢየሱስ ደም የሚያምነው እምነት እንዲሚከተለው ነው ኢየሱስ ለአለም ሐጢያቶች በሙሉ ተፈርዶበታል ተኮንኖዋልም እርሱ ለሐጢያቶቻችን ስለተደቆሰና ስለቆሰለ ከአስከፊው ፍርድ ድነናል ሆኖም ግን ይህ ሙሉው እውነት አይደለም ይህንን ትምህርት ከመቀበላችን በፊት አንድ ጉዳይ እናጥራ ኢየሱስ ለምን መስቀል ላይ መሰቀል አስፈለገው?

መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአት ደሞዝ ሞት መሆኑን በግልፅ ይናገራል ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ ምንም አይነት ኃጢአትን አላደረገም የሰውን ስጋ ለብሶ በማርያም አካል ወደ ምድር የመጣው የቅዱስ አምላክ ልጅና የሐጢያተኞች መድህን የራሱን ሕዝብ አምሳያ ይዞ ነበር በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ከመሞቱ በፊትም በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ለመጠመቅ ያስፈለገው ለዚህ ነው እርሱ በተጠመቀ ጊዜም የእኛን የሰው ልጆች ኃጢኣት በሙሉ ወደራሱ አስተላልፏል ስለሆነም ያለ ጥምቀት እርሱም በመስቀል ላይ ለመድማት አይፈረድበትም ነበር፡፡

## የብሉይ ኪዳኑ ስርአተ - መስዋዕት

*መስዋዕት ሲቀርብ መሟላት ያሉባቸው ነገሮች ምን ምን ናቸው?*

*① ነውር የሌለበት ሕያው እንስሳ፣*
*② እጆችን በእንስሳው ራስ ላይ መጫን፣*
*③ የመስዋዕቱ ደም*

በተቀደሰው ድንኳን ውስጥ በሚከናወነው ስርአተ መስዋዕት አማካይነት ይህንን እውነት እንመልከት በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህኑ ለመስዋዕትነት በቀረበው እንስሳ ላይ እጆቹን በመጫን የራሱን ሐጢአት ወይም የሚወክለውን የእስራኤል ሕዝብ ኃጢአቶች ወደ መስዋዕቱ ያስተላልፋል ከዚያም መስዋዕቱ ታረዶ በመሰዊያው ላይ ይቀርባል ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ተምሳሌት ነው ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር

ሊልከው ቃል የገባው የመስዋዕት በግ ነው::

ኃጢአቶቻችሁ በሙሉ ወደ ኢየሱስ የተላለፉት መቼ ነው? ስለዚህ ጥያቄና ስለ መልሱ እንድታስቡ እፈልጋለሁ በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን እጃቸውን በመስዋዕቱ ራስ ላይ ሳይጭኑ (ይህም ማለት ኃጢአታቸውን ለመስዋዕትነት ወደቀረበው እንስሳ ሳያስተላልፉ) እንስሳውን ማረድ አይችሉም የሐጢያት መስዋዕቶቹ በመሰውያው ፊት ከመቅረባቸው በፊት ሐጢያቶችን ለመስዋዕት በቀረቡት እንስሶች ላይ ለማሻገር እጆችን የመጫን ስርአት ይከናወናል::

*«እጁንም በሚቃጠለው መስዋእት ራስ ላይ ይጭናል::» (ዘሌዋውያ 1:4)* በዘሌዋውያን ላይ እንደተጻፈውም መስዋዕቶች በሙሉ የእጆች መጫን ያስፈልጋቸዋል እጆቻቸውን በመስዋዕቱ ራስ ላይ በመጫን የእስራኤል ሕዝቦች ኃጢአቶቻቸውን ወደ እርሱ ያስተላልፋሉ እንዲሁም ደሙንና ስጋውንም በእምነት ለእግዚአብሔር በማቅረብ ከኃጢአቶቻቸው በሙሉ ይድናሉ በብሉይ ኪዳን ጊዜም እስራኤላውያን በእምነታቸው ድነው ነበር::

የሚቃጠለው መሰዋዕት በእግዚአብሔር ፊት ከመቅረቡ በፊት ኃጢአተኛው ኃጢአቶቹን በሙሉ ወደ መስዋዕቱ ያስተላልፍ ዘንድ እጆቹን በመስዋዕቱ ራስ ላይ መጫን ያስፈልገዋል ከዚያም መስዋዕቱ በኃጢአተኛው ፈንታ ይታረዳል በመሰዊያው አራቱ ቀንዶች ላይም ደሙ ይረጫል የቀረው ደምም ደግሞ በመሰዊያው ደጃፍ መሬት ላይ ይደፋል ኃጢአተኞች ምህረት ይደረግላቸው የነበረው በዚህ መንገድ ነበር::

በአዲስ ኪዳንም ኃጢአተኞች ከኃጢአታቸው በሙሉ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደም ባላቸው እምነት መዳን ይችላሉ በ1ኛ ዮሐንስ **5:1-10** ላይ አንድ

ኃጢአተኛ በኢየሱስ ጥምቀትና በበጉ ደም (የመስቀሉ ደም) ሲያምን ዳግም እንደሚወለድ ይናገራል፡፡

ስለሆነም አንድ ኃጢአተኛ ሊድን የሚችለው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደም የሚያምን ከሆነ ነው የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ ከመንፈስ ጋር ሲቆራኙ ከውኃና ከመንፈስ ለመወለድ አስፈላጊ ይሆናሉ፡፡

ወዳጆች በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ በማመን ልትድኑ ትችላላችሁን? በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ዳግም ለመወለድ እንችላለን ብለው የሚያስቡት ሰዎች በልባቸው ውስጥ ኃጢአት አለባቸው ነገር ግን እኛ ከሐጢያቶቻችን ልንድን የምንችለው በአዲስ ኪዳን የመንፈሳዊ ግርዘት ተምሳሌት በሆነውና በኋለኛ ው ዘመን በብሉይ ኪዳን ከተገለጠው ግርዘት ጋር ተመሳሳይ በሆነው የኢየሱስ ጥምቀት በማመን ነው፡፡

ሁሉም ኃይማኖቶች የራሳቸው ፍልስፍናዎች አሏቸው የውሸት እምነታቸውን እስካልተዉ ድረስ ወደ ገሃነም የሚገቡ መሆናቸውን እኛ ሁላችን እናውቃለን የፕሪስቤቴርያን ቤተ ክርስትያን አስቀድሞ በመወሰን ትምህርት ላይ ያተኩራል የሜቶዲስት ቤተ ክርስቲያን በስብዕና ላይ ያተኩራል የባፕቲስት ቤተ ክርስትያን በጥምቀት የቅድስና ቤተ ክርስትያን በተቀደሰ ሕይወት ላይ ያተኩራል እነዚህ ሁሉ ከእውነት ቃል ያፈነገጡ ናቸው፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተጻፈው የእውነት ቃል ዳግም ስለመወለድ የሚናገረው ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ እውነት በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ውስጥ እንደሚገኝ ይናገራል ማንም የእግዚአብሔርን ቃል የሚከተልና በትክክለኛው የውኃና የመንፈስ ወንጌል የሚያምን ሁሉ ምህረትን ያገኛል፡፡

# የኢየሱስ ጥምቀት ምስጢሩ ምንድን ነው?

*በአዲስ ኪዳን ያለ መንፈሳዊ ግርዘት ምንድን ነው?*

*የኢየሱስ ጥምቀት ነው፡፡*

የኢየሱስ ጥምቀት መንፈሳዊ ግርዘት ነው በብሉይ ኪዳን እግዚአብሄር ያልተገረዘ ማንኛውም ሰው ከሕዝቡ መካከል እንደሚቆረጥ ተናግሮዋል፡፡

በአዲስ ኪዳን ያለው የኢየሱስ ጥምቀት መንፈሳዊው ግርዘት መሆኑን ሁላችንም ማወቅ አለብን ኢየሱስ ይፋ በሆነው አገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ በአጥማቂው ዮሐንስ ስለተጠመቀ እኛም በእርሱ ጥምቀት በመንፈሳዊ መልክ መገረዝ እንችላለን ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐኝስ የተጠመቀባቸውን ምክንያቶች በጥንቃቄ ልናስብባቸው ይገባናል፡፡

*«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን- እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ፡- አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት፡፡» (ማቴዎስ 3:13-15)*

ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀው በዮርዳኖስ ወንዝ፣ «በሞት ወንዝ» ነው አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ ሲጭን ኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ወደ ውኃው ገብቶ ነበር ትክክለኛው የመጠመቂያ መንገድ ይህ ነው (ጥምቀት በውኃ ውስጥ መጥለም ነው) ኢየሱስ የአለምን

ሐጢያቶች ያስወግድ ዘንድ በብሉይ ኪዳን በተጠቀሰው መሠረት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ በእጅ የመጫን ስርአት መጠመቅ ነበረበት።

የኢየሱስ ጥምቀት በኢየሱስ ለሚያምኑት መንፈሳዊ ግርዘት ማለት ነው *«እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት» (ማቴዎስ 3:15)* ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ አስወግዶ አምላካችንና አዳኛችን መሆኑ ተገቢ ነበር እንደተፃፈውም ሐጢያቶቻችንን ሁሉ በጭንቅላቱ ላይ ተሸክሞ በመስቀል ላይ መሞቱም አስፈላጊ ነበር።

የኢየሱስ ጥምቀት ኃጥአንን በሙሉ ዳግም እንዲወለዱ የማድረግ ኃይል አለው ይህም የውኃውን የመንፈሱ ወንጌል ምስጢር ነው።

ኢየሱስ ማስተማር ሲጀምር ለመጀመሪያ ግዜ ያደረገው ነገር ቢኖር በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቅ ነበር ጥምቀት ማለት ደግሞ «መታጠብ፣ መጥለም፣ ማስተላለፍ» ማለት ነው።


እግዚአብሔር በሚፈልገው መንገድ በመጠመቅም ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአቶች ሁሉ ወደ ራሱ አስተላልፏል *«እነሆ የአለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ» (ዮሐንስ 1:29)* የኢየሱስ ጥምቀት ትርጉሙ በዚህ የሚያምኑ ሁሉ መንፈሳዊ ግርዘትን አግኝተዋል ማለት ነው።

በኋላም የዓለምን ኃጢአቶች እንደሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ ወደ መስቀሉ በማምራት ለኛ ለኃጢአተኞቹ ሲል ፍርድን ተቀብሎልናል በዚህም የዓለምን ኃጢአተኞች በሙሉ ከፍርድና ከኃጢአት አድኖኣቸዋል።

ስለዚህ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት፣ በብሉይ ኪዳን ግርዘትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ የሚምኑ ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ይድናሉ ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱና

በደሙ ሐጢያተኞችን ሁሉ አድኖዋል የመንፈሳዊው ግርዘት እውነት ይህ ነው።

## ደህንነት በደም ብቻ ነውን? አይደለም።




በ1ኛ ዮሐንስ 5፡4-8 ላይ እንዲህ ተጽፎዋል *«ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ዓለምን ያሸንፋልና ዓለምንም የሚያሸንፈው እምነታችን ነው ኢየሱስም የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆነ ከሚያምን በቀር ዓለምን የሚያሸንፍ ማን ነው? በውኃና በደም የመጣ ይህ ነው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ፤ በውኃውና በደሙ እንጂ በውኃው ብቻ አይደለም መንፈስም እውነት ነውና የሚመሰክረው መንፈስ ነው የሚመሰክሩትም መንፈሱና ውኃው ደሙም ሦስት ናቸውና ሦስቱም በአንድ ይስማማሉ።»*

ውድ ክርስትያኖች ስለ አዳኛችሁ የምትሰጡት ምስክርነት ምንድነው? በውኃና በመንፈስ ከመጣው ከእግዚአብሔር ልጅ ሌላ ማንም ሊሆን አይችልም።

አለምን የሚያሸንፍ ድል ምንድነው? በውኃና በደሙ የማመን ሐይል እንጂ ሌላ አይደለም ይህም በውኃና በደም የመጣው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የሚመሰክረውም መንፈስ ነው መንፈስ እውነት ነውና።

በምድር ላይ የሚመሰክሩ ሶስት ነገሮች አሉ ውኃው ደሙና መንፈሱ:: እነዚህ ሶስቱ በአንድ ይስማማሉ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው ስጋን ለብሶ ነው ከተጠመቀ በኋላም በመስቀል ላይ በመሞት እኛን ከዘላለማዊ ጥፋት አድኖናል ፈጣሪያችን እግዚአብሄር የሐጢያተኞች ሁሉ አዳኝ የመሆኑ ማረጋገጫ ሁላችንንም በሚያድነን የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ውስጥ አለ::

ኢየሱስ በስጋ ውስጥ ያለ መንፈስ ሆኖ ወደዚህ አለም መምጣቱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በራሱ ላይ ለመውሰድ በዮርዳኖስ ወንዝ መጠመቁና የሐጢያቶቻችንን ፍርድ በመቀበልም በመስቀል ላይ መድማቱ ማረጋገጫችን ነው በዚህም በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ አድኖዋል ያልተበረዘው የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ይህ ነው::

## ለእግዚአብሔር ማዳን የሚመሰክሩት ውኃውና ደሙ ምንድን ናቸው?

*በብሉይ ኪዳን ያለው ግርዘት*
*በአዲስ ኪዳን ያለው ተምሳሌቱ*
*ምንድን ነው?*

*የኢየሱስ ጥምቀት ነው::*

ውኃው የሚያመለክተው የኢየሱስ ክርስቶስን ጥምቀት ነው በብሉይ ኪዳን የኢየሱስ ጥምቀት ማለት ግርዘት ማለት

ነው በብሉይ ኪዳን ያለው የግርዘት ተምሳሌትም በአዲስ ኪዳን ያለው የኢየሱስ ጥምቀት ነው የዓለም ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ የመተላለፋቸው ምስክርም የእርሱ ጥምቀት ነው፡፡

ይህንን እውነት የሚያምን ማንኛውም ሰው በእግዚአብሄር ፊት ቆሞ በበጎ ሕሊና «አንተ አዳኜ ነህ ጌታዬ ሆይ እኔ በአንተ ጥምቀትና በደምህ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል አምናለሁ ስለሆነም እኔ ምንም ኃጢአት የለብኝም እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ አንተም አዳኜ ነህ» በእውነተኛ እምነት ይህንን ልንገልፅ እንችላለን ይህን ልንል የቻልንበት ምክንያቱም በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ባለን እምነት የተነሳ ነው፡፡

ዳግም እንድንወለድ የሚፈቅድልን ቃል ምንድነው? በልባችን ውስጥ የደህንነት ምስክር የሆነው የኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ ነው ከውሃውና ከመንፈሱ የምንወለድበት ወንጌል ይህ ነው፡፡

ውድ ክርስትያኖች በድጋሜ ልጠይቃችሁ «አንድ ኃጢአተኛ በክርስቶስ ደም በማመን ብቻ ሊድን ይችላልን?» በፍፁም አይችልም ደህንነት የሚጠይቀው በመስቀል ላይ መሞቱን ብቻ ማመን አይደለም ደህንነት የሚገኘውና ኃጢአተኞችም ዳግም ሊወለዱ የሚችሉት በውኃና በደም—በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል—በማመን ብቻ ነው አሁን ስለ ውኃው ማለትም ስለ ጥምቀቱ ወደሚያወራው የመፅሐፍ ቅዱስ ክፍል ልመልሳችሁ፡፡

1ኛ ጴጥሮስ 3:21-22 እንዲህ ይላል *«ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው እርሱም መላእክትና ሥልጣናት ኃይላትም ከተገዙለት በኋላ ወደ ሰማይ ሄዶ በእግዚአብሔር ቀኝ አለ፡፡»*

የኢየሱስ ጥምቀት ምሳሌ ሆኖ እንደሚያድነንና ከሐጢያት

ደህንነት የሚገኝበት ማረጋገጫ እንደሆነ ሐዋርያው ጳውሎስ መስክሮዋል የኢየሱስ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን ካለው ግርዛት ጋር ተመሳሳይ ነው በብሉይ ኪዳን ጊዜ የእስራኤል ሕዝቦች የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመከተል ብልታቸውን እንደተገረዙት ሁሉ በአዲስ ኪዳንም የኢየሱስ ጥምቀት ከኃጢኣታችን በሙሉ ያድነናል፡፡

በዚህም በብሉይ ኪዳ ላይ የነበረው ግርዘትና በአዲስ ኪዳን ያለው የኢየሱስ ጥምቀት ሁለቱም አንድና ተመሳሳይ ናቸው አሁንየሚያድነን ምሳሌ ያለ ሲሆን እርሱም ጥምቀት ነው ሁላችሁም የኢየሱስ ጥምቀትና በብሉይ ኪዳን ጊዜ የነበረው ግርዘት አንድ መሆናቸውን ታምናላችሁን? በ1ኛ ጴጥሮስ 3፡21 ላይ እንደተጻፈውም አሁን የሚያድነን ምሳሌ ያለ ሲሆን እርሱም ጥምቀት ነው ከተፃፈው የእግዚአብሄር ቃል ጋር መከራከር ትችላለችሁን?

እኛ በዚህ ዓለም የምንኖር ሰዎች ከኃጢአት ነጻ ልንሆን እንዴት እንችላለን? ይህ የሆነበት ብቸኛው ምክንያት ክርስቶስ ሁላችንም ከሐጢያት ደህንነት እናገኝ ዘንድ ፅድቅን ሁሉ ለመፈፀም ስለተጠመቀ ነው በማቴዎስ 3፡15 ላይ እንደተጻፈውም *«እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው፡፡»*

የዓለም ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ስለተሻገሩ በእርሱ የሚያምኑ ሁሉ አሁን ሐጢያት የለባቸውም ሁላችንም ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ አማካይነት ወደ ኢየሱስ የመሻገራቸውን እውነት በመቀበል ፃድቃን መሆን እንችላለን ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን ሁሉ በራሱ ላይ ወስዶ ከፍርድ ሊያድነን በመስቀል ላይ ሞተ፡፡

ውድ ጓደኞቼ ኃጢአተኞችን በሙሉ ከኃጢአት የሚያድኑት ሁለቱ ነገሮች ውኃውና ደሙ ናቸው ኢየሱስ በዚህ ዓለም ላይ

ለ3 ዓመታት ያህል ሲያገለግል ያደረጋቸው ሁለት ነገሮች ኃጢአታችንን በጥምቀቱ መቀበልና ለእነዚህም ፍርድን ለመቀበል በመስቀል ላይ መሞት ነበር፡፡

ዮሐንስ 1፡29 እንዲህ ብሎዋል *«እነሆ! የአለምን ኃጢኣት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ፡፡» (ዮሐንስ 1፡29)* ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠመቀው የእኛን ኃጢአት በሙሉ ለመቀበል ሲሆን በመስቀል ላይ ለመተላለፋችን በመሞትም አድኖናል ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው ፈጣሪ እንደመሆኑም እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን የሰጠውን የግርዘት ቃል ኪዳን ፈፅሟል፡፡

በልቡ የኢየሱስን ጥምቀት ውሃውንና ደሙን የሚያምን ማንኛውም ሰው ዳግመኛ ከውሃና ከመንፈስ ይወለዳል ጌታም በእርሱ ለምናምነው አዳኛችን ይሆናል ጌታ ይመስገን ሃሌ ሉያ! ኢየሱስ እግዚአብሔር በገባልን ቃል ኪዳን መሰረት ደህንነታችንን ፈፅሞልናል በዚህ ከዓለም ኃጢአቶች በሙሉ አድኖናል፡፡

## የሰውነትን ዕድፍ ማስወገድ አይደለም

*ስጋ በጊዜ ሒደት ሊቀደስ ይችላል ን?*

*አይችልም፡፡ እስከምንሞትበት ቀን ድረስ ስጋችን ኃጢአትን ማከማቸቱን ይቀጥላል፡፡*

1ኛ ጴጥሮስ 3፡21 እንዲህ ይላል *«ይህም ውኃ ደግሞ ማለት ጥምቀት ምሳሌው ሆኖ አሁን ያድነናል የሰውነትን*

*እድፍ ማስወገድ አይደለም ለእግዚአብሔር የበጎ ህሊና ልመና ነው እንጂ፣ ይህም በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሳኤ ነው።»*

አንድ ሰው ኢየሱስን አዳኜ ነው ብሎ ባመነ ጊዜ የስጋ ኃጢአት መስራት ያቆማል እያልን አይደለም ኃጢአት መስራታችንን እንቀጥል ይሆናል ሆኖም ግን ኃጢአቶቻችንን በሙሉ በኢየሱስ ጥምቀት በማመን ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍ ችለናል ለእነዚህ ኃጢኣቶችም ኢየሱስ ክርስቶስ ከ2,000 ዓመት በፊት በመስቀል ላይ በመሞት ፍርድን ተቀብሎልናል በእነዚህ ሁለት ሊተዉ በማይችሉ ነገሮች ማለትም በውኃውና በደሙ በማመን ከኃጢአቶቻችን እንድናለን።

ዳግም መወለድ ማለት ኢየሱስን የሰው ልጅ እንደሆነ አድርገን ከልባችን ማመን ማለት ነው የኃጢአት ይቅርታን ለማግኘት የምንችለውም በልባችን ነው ነገር ግን በኢየሱስ ጥምቀት በማመን በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ዋጋ የከፈለባቸውን አለማዊ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ማሻገር እንችላለን ሆኖም ግን በስጋችን መተላለፋችንና ኃጢኣት መስራታችንን እንቀጥላለን ሆኖም ግን የምንሰራቸው የስጋ ኃጢኣቶቻችን በሙሉ ይቅር ተብለዋል።

የኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀት ለዳኑት በሙሉ ምስክር ነው በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት የደህንነትን ወንጌል ወደ ልባችን ስናስገባ ዳግም እንወለድና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ፃድቃን እንሆናለን።

ይህ በብሉይ ኪዳን ያለው የአብርሃም እምነት ነው ይህ ሐዋርያው ጳውሎስ የተናገረለት ፅድቅ የሚገኝበት እምነት ሐዋርያው ጴጥሮስ የመሰከረለትም የደህንነት ምሳሌ ነው።

አብርሃም የእግዚብሔርን ቃል ስምቶ በማመን ፃድቅ እንደሆነ ሁሉ እኛም በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ሞቱ ስናምን እንድናለን።

ዮሐንስ 1:12 ላይ *«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣን ሰጣቸው»* ይላል በጥምቀቱና በደሙ አማካይነት ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ያዳነንን ኢየሱስ ክርስቶስን አዳኛችሁ አድርጋችሁ ተቀብላችኋልን? በውሃውና በእግዚአብሄር ልጅ ደም አማካይነት የተሰጠንን ደህንነት መቀበል አለብን::

ደህንነት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነውን? አይደለም ደህንነት የሚገኘው በውኃና በኢየሱስ ደም ነው:: በመጽሐፍ ቅዱስ እንደተጻፈው ደህንነት በኢየሱስ ደም ብቻ አለመሆኑ በግልፅ ተዘርዝሯል ደህንነት በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ነው::

የኢየሱስ ጥምቀት በአዲስ ኪዳን ያለ መንፈሳዊ ግርዘት ነው ይህም ኃጢአቶቻችን በሙሉ የሚያስወግድልን የደህንነት እውነታ ነው እርሱ ለዓለም ኃጢአቶች ፍርድን ተቀበለ ማለት ለእኛ ኃጢኣቶች ማለትም እኔና እናንተ ለምንሰራቸው ኃጢአቶች ፍርድን ተቀበለ ማለት ነው::

የሐጢያት ይቅርታ የሚገኝበትን የኢየሱስን ጥምቀትና የደሙን ወንጌል በመቀበል ለሐጢያቶቻችን ሁሉ ከመጣው ፍርድ ነፃ ወጥተናል በእምነታችንም በዚህ ዓለም ላይ ከምንሰራቸው ኃጢኣቶች በሙሉ ድነናል የኢየሱስን ጥምቀትና የመስቀሉ ላይ ደሙን በምንቀበልበትና በምናምንበት ጊዜ የሰራናቸው ኃጢኣቶች በሙሉ ይወገዱልናል በዚህ ታምናላችሁን? በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል አምናችሁ ዘላለማዊ ህይወትን እንደምታገኙ ተስፋ አደርጋለሁ በዚህ እመኑና ዘላለማዊ ሕይወትን ተቀዳጁ::

ሐዋርያው ጳውሎስ *«ግርዘትስ የልብ ነው»* ይላል *(ሮሜ 2:29)* በልባችን ልንገረዝ የምንችለው እንዴት ነው? በልባችን ልንገረዝ የምንችለው ኢየሱስ ስጋን ለብሶ በመንፈስ ወደዚህ

ምድረ መምጣቱን፣ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉም በጥምቀቱ ማስወገዱን፣ ለኛ ኃጢአትም በመስቀል ላይ መሞቱንና ከሞት በትንሳኤው ድል አድርጎ መነሳቱን ስናምን ነው::

ሐዋርያው ጳውሎስ ግርዘት የልብ መሆኑን ተናግሮዋል በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ማመን ነው በልባችሁ ለመገረዝ የምትፈለጉ ከሆናችሁም የኢየሱስን የጥምቀቱንና የደሙን ወንጌል ወደ ልባችሁ ማስገባት ይኖርባችኋል እናንተ በተጨባጭ እግዚአብሄር ልጆች መሆን የምትችሉት ያን ጊዜና ያን ጊዜ ብቻ ነው::

## መጥምቁ ዮሐንስ የተላከው ከእግዚአብሔር ነውን?

*መጥምቁ ዮሐንስ ማን ነበር?*

*ከአሮን ወገን የሆነ የመጨረሻው ሊቀ ካህንና የሰው ልጆች ሁሉ ተወካይ የነበረ ነው::*

እዚህ ላይ ኢየሱስ ክርስቶስን ያጠመቀው አጥማቂው ዮሐንስ ማን ነበር? ብለን መጠየቅ ያስፈልገናል መጥምቁ ዮሐንስ የሰው ልጆች ሁሉ ወኪል የሆነ ሰው ነበር ማቴዎስ 11:11-14 እንደሚናገረውም *«እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም በመንግስተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ መንግስተ ሰማያት ትገፋለች ግፈኞም ይናጠቁታል:: ነቢያት ሁሉና ሕጉ*

*እስከ ዮሐንስ ድረስ ትንቢት ተናገሩ ልትቀበሉትስ ብትወዱ ይመጣ ዘንድ ያለው ኤልያስ ይህ ነው።»*

ውድ ክርስትያኖች ኢየሱስ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከአጥማቂው ዮሐንስ የሚበልጥ እንደሌለ ተናግሮዋል አጥማቂው ሲወለድ እግዚአብሄር የሰጠው የመጀመሪያው ኪዳን ዘመን ማለትም የብሉይ ኪዳን ዘመን አብቅቷል ያበቃበትም ምክንያት የእግዚአብሄርን ኪዳን የሚፈፅመው ኢየሱስ ክርስቶስ በመጨረሻ ስለመጣ ነው።

ታዲያ እግዚአብሄርን ኪዳን መፈፀም የነበረበት ማ ነበር? ኢየሱስ ክርስቶስና መጥምቁ ዮሐንስ ናቸው መጥምቁ ዮሐንስ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ አስተላልፏል የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ሊቀ ካህን የነበረው ማነው? የአሮን ዘር የሆነውስ ማነው? ኢየሱስ ክርስቶስም ከመጥምቁ ዮሐንስ ሌላ ማንም እንዳልሆነ መስክሮአል መጥምቁ ዮሐንስ ከሴቶች ከተወለዱት ሁሉ ታላቅና የሰው ልጆች ሁሉ ተወካይ ነበር።

ያገኘናቸውን እውነታዎች እናሰላስላቸው ሙሴ አብርሃም ይስሐቅና ያዕቆብም ሁሉም የተወለዱት ከሴቶች ነው ሆኖም ግን ከብሉይ ኪዳንም ሆነ ከአዲስ ኪዳን ከሴቶች ከተወለዱት በሙሉ ታላቁ ማነው? እርሱ መጥምቁ ዮሐነስ ነው።

አጥማቂው ዮሐንስ የብሉይ ኪዳን የመጨረሻው ነቢይና የአሮን ዝርያ በመሆኑ አሮን በበሉይ ኪዳን በስርየት ቀን እጆቹን በመስዋዕቶቹ ላይ በጫነበት መንገድ በአዲስ ኪዳን የእግዚአብሄርን በግ አጠመቀው እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስን በማጥመቅ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ ወደ እርሱ አስተላልፏል እርሱ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር ኢየሱስ ክርስቶስን በማጥመቅ መንፈሳዊውን ግርዘት በሰው ዘር ልቦች ሁሉ ውስጥ ፈፀመ።

ከኢየሱስ ጥምቀት ጋር በጋራ የደህንነታችን ምስክር አድርገን በደሙም ማመን አለብን ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ የሰው ልጆችን ኃጢኣት በሙሉ ወስዷል ለእነርሱም ፍርድን ተቀብሏል እኛም የሚያስፈልገን ብቸኛወ ነገር በዚህ ማመን ነው ኢየሱስ ባደረገው ነገር አምነን እንድንድንም የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፡፡

ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን ወንጌል አንድ ጊዜ ወደ ልባችሁ ካስገባችሁ የአብርሃም ዘርና የእግዚአብሄር ልጆች ትሆናላችሁ የክርስቶስ የሆኑት ጥቂቶች ናቸው ክርስቶስን በልባቸው ገና ያልተቀበሉ ብዙዎች ናቸው፡፡

ጊዜውም እያለቀ ጭለማም ወደመስፈኑ ነው በኢየሱስ ወንጌል በማመን ኢየሱስ ወደ ልባችሁ እንዲገባ አድርጉ በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ያላችሁ እምነት በመንፈሳዊ ደህንነት እንድትባረኩ ያደርጋችኋል፡፡

መንፈሳዊው ቅባት የሚመጣው በደህንነት ወንጌል በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ወንጌል ስታምኑ እንደሆነ ሁልጊዜም አስታውሱ በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ወንጌል በማመን እንደ ብልሆቹ ደናግልቶች (ማቴዎስ 25፡4) መንፈሳዊ መብራትንና (የቤተክርስቲያን) ዘይትን (መንፈስን) ማዘጋጀት እንደምትችሉ ታውቁ ዘንድ እሻለሁ በኢየሱስ የሚያምኑት ወደ ቤተ ክርስትያን የሚሄዱት መንፈስ ቅዱስን በልባቸው ይዘው ነው፡፡

# ኢየሱስ የተጠመቀው ለማን ነው?

*ኢየሱስ የተጠመቀው ለምንድን ነው?*

*የሰው ልጆችን ኃጢአቶች በሙሉ ለማንጻት ነው።*

*«እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት።» (ማቴዎስ 3:14-15)*

ኢየሱስ የተጠመቀው የሰው ልጆችን ኃጢአት ለማንጻት ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅና የእኛም አዳኝ ነው እርሱ እኛን የሰራን ፈጣሪያችን ነው ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው በአብ በእግዚአብሔር ፍቃድ እኛን ሕዝቦቹ ለማድረግ ነው።

በብሉይ ኪዳን ነቢያት በሙሉ የተናገሩት ስለማን ነው? የብሉይ ኪዳን ነቢያቶች በሙሉ ኢየሱስ ወደዚህ አለም መጥቶ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንደሚያስወግድና ለዘላለም ከሐጢያት ነፃ እንደሚያደርገን ተናግረዋል።

ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን እንደተተነበየው ወደዚህ አለም መጥቶ ከአዳምና ከሔዋን ጀምሮ በምድር ላይ እስከሚኖረው የመጨረሻ ግለሰብ ድረስ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ አስወግዶዋል።

አሁን በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ያለውን ደህንነት ወደ ልባችሁ አስገቡ ይህ እውነት ስለመሆኑ ትጠራጠራላችሁን? አሁንም ድረስ በልባችሁ ኃጢአት አለባችሁን? *«እንዲህ ጽድቅን*

*ሁሉ መፈፀም ይገባናልና»* ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ የተጠመቀው ጽድቅን ሁሉ ለመፈፀም ነው፡፡

«ጥምቀት» የሚለው ቃል ራሱ ትርጉሙ «ማንጻት» ማለት ነው ኢየሱስ በዮሐንስ የተጠመቀው በብሉይ ኪዳን ባለው የእጅን የመጫን ስርዓት አይነት ነው፡፡

የሰው ልጆች ኃጢኣት በሙሉ ወደ ራሱ ከወሰደ በኋላ በዮርዳኖስ ወንዝ ውስጥ ጠለቀ ወንዙም ደግሞ ለኃጢኣተኞች ሞትንና ፍርድን የሚያመላክት ነው የክርስቶስ በውኃው ውስጥ መጥለቅም የእርሱን በመስቀል ላይ መሞት ያሳያል ከውኃው መውጣቱም ትንሳኤውን አመላካች ነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከሞተ ከሶስት ቀን በኋላ ሞትን ድል አድርጎ ተነስቷል፡፡

ኢየሱስ አዳኛችንና አምላካችን ነው ኢየሱስ የመጠመቁ፣ በመስቀል ላይ እስከ ሞት የመድማቱ፣ በሦስተኛው ቀን የመነሳቱና በእግዚአብሄር ቀኝ የመቀመጡ ሐቅ የሰውን ዘር ሁሉ ከሞት ለማዳኑ ግልጽ ማስረጃ ነው በዚህስ ታምናላችሁን?

የኢየሱስ ጥምቀት በአዲስ ኪዳን ያለው መንፈሳዊ ግርዘት ነው *«ግርዘትስ የልብ ነው»* የልብ ግርዘት የሚጠናቀቀው ሐጢያቶቻችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ የተሻገሩ የመሆናቸውን እውነትና የኢየሱስን ጥምቀት ስናምን ነው፡፡


በልባችሁ ተገርዛችኋልን? በልብ ግርዘት የምታምኑ ከሆናችሁ ኃጢኣቶቻችሁ በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሊወገዱላችሁ ይችላሉ በዚህም የተነሳ ኢየሱስ ጽድቅን በሙሉ በመፈፀም ለኃጢአተኞች በሙሉ ደህንነትን አረጋግጦላቸዋል፡፡

ውድ ክርስትያኖች እነዚህን የደህንነት ምስክርነቶች በልባችሁና በአእምሮአችሁ አስገቧቸው ይህ እውነት ነው የኢየሱስን የደህንነት ወንጌልም አንዴ ወደ ልባችሁ ካስገባችሁ ከኃጢአቶቻችሁ በሙሉ የነጻችሁ ትሆናላችሁ *«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያመኑት ለእነርሱ የእግዚብሔር ልጆች ይሆኑ*

*ዘንድ ስልጣን ሰጣቸው::» (ዮሐንስ 1:12)*

አሁንስ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መምጣትና በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ መጠመቅ ለምን እንዳስፈለገው ለመመልከት ችላችኋልን? በዚህስ አምናችኋልን? ኢየሱስ የተጠመቀው የልጆቹን ኃጢአት በሙሉ ለማስወገድ ነው ጥምቀቱም የግርዘት ጥምቀት ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ ልባችን መገረዝ እንዳለበት ሲነግረን የነበረውም ለዚህ ነው ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ በግልፅ ስላዳነን ይህንን በልባችን ከማመን በስተቀር ምርጫ የለንም እኛም በልባችን ላለው የእግዚብሔር ቃል «አዎን! አሜን!» ማለት ነው አለብን ይህ እውነት አይደለምን? በዚህስ አታምኑምን?

## ይህን እውነታ በልባችሁ ትቀበላላችሁን?




ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ከመጣ ከ2000 ዓመት በላይ ሆኖታል በዚህ የእግዚአብሄር ፀጋ ዘመን የውሃውንና የኢየሱስን ደም እውነት በልባችን መቀበል አለበን እኛ ልናደርገው ያለን አንዳች ሌላ ነገር የለም::

*«ግርዘትስ የልብ ነው»* በልባችን ባለው እምነት ልንገረዝ

ይገባናል ልንድን የምንችለው በእምነት ብቻ ነው በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን ይድኑ የነበረው በግርዘትና ለፋሲካው የሚታረደውን እንስሳ ደም በበራቸው ላይ በመርጨት ነበር፡፡

ደህንነትን ለማግኘት በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ የሚምኑ የእግዚአብሄርን ፍርድ አይፈሩም ምክንያቱም ያልፋቸዋልና ነው ሆኖም ግን እውነታውን ከልባቸው በማይቀበሉት ላይ የእግዚአብሔር ፍርድ ይጠብቃቸዋል በከንቱ በኢየሱስ የሚያምኑ ብዙ ሰዎች አሉ ከዚህ የተነሳ አሁንም የሐጢያቶቻቸው ባሮች ናቸው፡፡

እነዚህ ሰዎች እዚህ ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት እንዴት ነው? እስከአሁንም ድረስ ከኃጢኣት የሚሰቃዩት ለምንድን ነው? ይህ የሆነው የውኃውንና የደሙን ትርጉም በትክክል የማያምኑ በመሆናቸው ነው የኢየሱስን ጥምቀት በመተው እነርሱ የሚያምኑት በኢየሱስ ደም ብቻ ስለሆነም ጭምር ነው፡፡

በኢየሱስ ደም በማመን ብቻ ደህንነት ይገኛልን? መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ነገር ይነግረናልን? ብሉይ ኪዳንና አዲስ ኪዳን ይህን በተመለከተ የሚናገሩት ነገር ምንድን ነው? በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት ደህንነት የሚገኘው በእግዚአብሄር በግ ደም ብቻ ሳይሆን በኢየሱስ ጥምቀትም ነው፡፡ (1ኛ ዮሐንስ 5:3-6)

የምታምኑት በኢየሱስ ደም ብቻ ነውን? እንደዚህ የሚያደርጉ አሁንም በልባቸው ሐጢያት አለ የተሳሳተውን እምነታቸውን አሽንፈው ወደ እውነተኛው ወንጌል መመለስ አለባቸው፡፡

እነዚያ የማያምኑት ኢየሱስ በዮርዳኖስ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያትን ሁሉ እንደወሰደ ባለማወቃቸው መሳሳታቸውን መረዳት አለባቸው የኢየሱስን ጥምቀት ለመቀበል ቸልተኞች በመሆናቸው መሳሳታቸውን ማመን አለባቸው ኢየሱስ በጥምቀት አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች

በሙሉ መውሰዱን ወደ ልባቸው ማስገባት አለባቸው ደህንነት የሚገኘው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ስናምን ብቻ ነው በሌላ አነጋገር የዘላለምን ሕይወት ማግኘት የምንችለው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት ብቻ ነው፡፡

ውድ ክርስትያኖች እስካሁን ድረስ ስትኖሩ የነበራችሁት በኢየሱስ ደም ብቻ በማመን ነበርን? እንደዚህ ከሆነ በልባችሁ ኃጢአት መኖሩ እርግጥ ነው ኃጢኣትን ከሰራችሁ በልባችሁ ኃጢአት አለ ማለት ነው የእግዚአብሔርን ሕግ በመጠበቅ በቅድስና መኖር እንችላለን ብላችሁ የምታስቡ ከሆናችሁ ይህ ከስሜታዊነታችሁ የሚመጣ ፍላጎት ብቻ ነው ይህ አይነቱ እምነት ከእግዚአብሄር ቃል ጋር የሚስማማ አይደለም፡፡

## ገና በጣም አልረፈደም

*እውነቱ ነጻ የሚያወጣን ከምንድን ነው?*

*ከኃጢአትና ከሞት ሕግ ነው፡፡*

ገና በጣም አልረፈደም እናንተ ማድረግ ያለባችሁ በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ማመን ነው ያን ጊዜ ልባችሁ ይገረዝና ከሐጢያት ሁሉ ነፃ ትሆናላችሁ ከሐጢያት ሁሉ ነፃ መሆን ማለት የኢየሱስን ጥምቀትና የደሙን ወንጌል በማመን ድናችኋል ማለት ነው፡፡

ከሐጢያታችሁ ለመዳን በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ

ለማመን ፈቃደኞች ናችሁን? አንድ ጊዜ በዚህ ካመናችሁ ደህንነት ምን እንደሚመስል ታውቃላችሁ የአእምሮ ሰላምን ታገኛላችሁ ፃድቃን ልትሆኑ የምትችሉት ከዚህ በኋላ ብቻ ነው ይህም በስራችሁ ሳይሆን በእግዚአብሔር ቃል ባላችሁ እምነት ነው ከእናንተ አንዳችሁም ደህንነት ለማግኘት ገናም በኢየሱስ ደም ብቻ የምታምኑና ትምክታችሁም እርሱ ከሆነ በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙም እንድታምኑ እወተውታችኋለሁ::

ውድ ክርስትያኖች የሰው ዘር ሙሉ በሙሉ ከሐጢያት መዳኑ የተፈፀመው በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ወንጌል አማካይነት ነው መንፈስ እግዚአብሄር ነው እግዚአብሄር ወደዚህ ምድር የመጣው የሰብአዊ ፍጡር ስጋ ለብሶ ነው::

እግዚአብሔር በነብያቶቹ አማካይነት ስሙን ኢየሱስ ብለን ልንጠራው እንደሚገባን ተናግሮዋል እግዚአብሔር እንዲህ ይላል *«እነሆ ድንግል ትፀንሳለች ልጅም ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ይሉታል የተባለው ይፈፀም ዘንድ ይህ ሁሉ ሆኗል ትርጓሜውም እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው የሚል ነው::» (ማቴዎስ 1:23)*

እግዚአብሔር ወደዚህ ምድር የመጣው ኃጢአተኞችን ለማዳን ነው ኃጢአተኞችን በሙሉ ለማዳንም ሲል በጥምቀቱ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ወደ ራሱ አስተላልፏል ይህ የውኃውና የደሙ እውነትና ደህንነት ነው እኔም እዚህ ያለሁት ይህን እውነት ልነግራችሁ ነው እኛ የዳንነው በኢየሱስ ደም ብቻ ነውን? አይደለም እኛ የዳንነው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ነው::

በአሁኑ ጊዜም በኢየሱስ ጥምቀት የማያምኑ የሐሰት ነቢያትና ብዙ መናፍቃን አሉ ኢየሱስ እንዲህ ብሎዋል *«እውነትን ታውቃላች እውነትም አርነት ያወጣችኋል::» (ዮሐንስ 8:32)*

እውነቱን ማወቅ አለብን ኢየሱስ ለምን ስለጥምቀቱ እንደተናገረና እኛም ለምን ይህንን ማመን እንዳለብን ማወቅ ይገባናል በብሉይ ኪዳን እግዚአብሄር የእስራኤልን ልጆች ለምን እንዲገረዙ እንደነገራቸውና ለምን ስለ ፋሲካው ጠቦት ደም እንደነገራቸው ማወቅ ይኖርብናል፡፡

የምናውቀው የታሪኩን ገሚስ ብቻ በሚሆንበት ጊዜ በጭራሽ እውነቱን አንረዳም ኢየሱስ እንዲህ ብሎዋል *«እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም፡፡» (ዮሐንስ 3፡5)*

## በክርስቶስ መጠመቅ

*ከክርስቶስ ሞት ጋር ሕብረትን የምንመሰርተው እንዴት ነው?*

*ኃጢአቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ ወደ ኢየሱስ በማስተላለፍ ነው፡፡*

መጽሐፍ ቅዱስ የደህንነትን ምስጢር ይመሰክራል ይህ በኢየሱስ ደም ብቻ ነውን? አይደለም ይህ በእርሱ ደምና በጥምቀቱም ጭምር ነው ሐዋርያው ጳውሎስ ስለዚሁ ጉዳይ በሮሜ ምዕራፍ 6 ላይና እንደገናም በብዙዎቹ ሌሎች መልዕክቶች ውስጥ በተደጋጋሚ ተናግሮዋል፡፡

ሮሜ 6፡3-8ን እናንብብ *«ወይስ ከክርስቶስ ኢየሱስ ጋር*

*አንድ እንሆን ዘንድ የተጠመቅን ሁላችን ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ እንደ ተጠመቅን አታውቁምን? እንግዲህ ክርስቶስ በአብ ክብር ከሙታን እንደ ተነሳ እንዲሁ እኛም በአዲስ ሕይወት እንድንመላለስ ከሞቱ ጋር አንድ እንሆን ዘንድ በጥምቀት ከእርሱ ጋር ተቀበርን ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን ከእንግዲህስ ወዲያ ለኃጢአት እንዳንገዛ የኃጢአት ሥጋ ይሻር ዘንድ አሮጌው ሰዋችን ከእርሱ ጋር እንደ ተሰቀለ እናውቃለን የሞተስ ከኃጢኣቱ ጸድቆአልና ነገር ግን ከክርስቶስ ጋር ከሞትን ከእርሱ ጋር ደግሞ በህይወት እንደምንኖር እናምናለን።»*

ቁጥር 5ን እንመልከት *«ሞቱንም በሚመስል ሞት ከእርሱ ጋር ከተባበርን ትንሣኤውን በሚመስል ትንሣኤ ደግሞ ከእርሱ ጋር እንተባበራለን።»*

የእርሱ ሞት ማለት ሞታችን ነበር ምክንያቱም ሐጢያቶቻችን በሙሉ በጥምቀቱ አማካይነት ወደ እርሱ ተሻግረዋል ስለሆነም የኢየሱስ ጥምቀት በመስቀል ላይ የፈሰሰ ደሙን ከእኛ ጋር ያቆራኘዋል።

በዚህ እውነት ማመን ራሳችንን ከአዳኛችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ማቆራኘት ማለት ነው *(ሮሜ 6:23)* ስለዚህ የኢየሱስ የመስቀል ላይ ሞቱ የእኛም ሞት ነው እርሱም የተጠመቀው የእኛን ኃጢአቶች በሙሉ ወደራሱ ለማስተላለፍ ነው በዚህ እውነታ ማመንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ከአዳኛችን ጋር ህብረት መመስረት ነው።

# በኢየሱስ የምናምነው ኃይማኖታዊ የሕይወት መንገድ አካል አድርገን መሆን የለበትም

*«ለኢየሱስ ታማኝ ነው»*
*ማለት ምን ማለት ነው?*

*ይህ ማለት ኢየሱስ ለአንዴና ለመጨረሻ ኃጢአታችንን አስወግዶ በዚህ እውነት የሚያምነውን ሁሉ አድኗል ማለት ነው::*

ብዙ ሰዎች በኢየሱስ የሚያምኑት ሐይማኖታዊ በሆነ የሕይወት መንገድ ነው ወደ ቤተክርስቲያን ይሄዳሉ በመፀለይና ንስሐ በመግባትም እያለቀሱ ይኖራሉ በየቀኑ ሐጢያቶቻቸውን ይናዘዛሉ ይቅርታንም ይለምናሉ «ኢየሱስ በመስቀል ላይ ስለ እኔ እንደሞትህ አውቃለሁ አምናለሁም አዎ አምናለሁ» ብለው ይፀልያሉ::

እነርሱ ቀጣዩን ምንባብ በተሳሳተ መንገድ እንደተረዱት ግልፅ ነው *«በኃጢአታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው::» (1ኛ ዮሐንስ 1:9)*

ሐጢያቶቻቸውን በየቀኑ ስለሚናዘዙ ለሐጢያቶቻቸው ይቅርታን ማግኘት እንዳለባቸው ያስባሉ ነገር ግን ከላይ በተጠቀሰው ምንባብ ውስጥ የተጠቀሰው ሐጢያት የሚያወራው በየቀኑ ስለምንሰራቸው መተላለፎች አይደለም ምንባቡ የሚወራው ገና አለመዳናችንን ስንናዘዝ ለአንዴና ለመጨረሻ

ጊዜ ሐጢያቶቻችን ይቅርታ ስለማግኘታቸው ነው::

*«እንግዲያስ እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው» (ሮሜ 10:17) «እውነትንም ታውቃላችሁ፤ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐንስ 8:32)*

ውድ ክርስትያኖች እውነቱ ግልጽ ነው ኢየሱስ በዮርዳኖስ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ሳይወስድ በመስቀል ላይ መሞቱን የምታምኑ ከሆነ እምነታችሁ ከንቱ ናት አንድ ክርስቲያን ከሐጢያቶቹ በሙሉ መዳን ከፈለገ ሐጢያቶቹ ኢየሱስ በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ ለአንዴና ለመጨረሻ ወደ ኢየሱስ መሻገሩንና የሐጢያቶቻችንን ፍርድም በመስቀል ላይ እንደተሸከመ ማመን አለበት በሌላ አነጋገር በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ማመን አለበን::

*«መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋርያት ሥራ 4:12)* ኢየሱስ ክርስቶስ ኃጢአቶቻችንን በሙሉ በመወሰድ አዳኛችን ሆኗል፡ ኢየሱስ በወኃና በመንፈስ የመጣው እኛን ከዘላለማዊ ጥፋት ለማዳን ነው *«ሰው በልቡ አምኖ ይፀድቃል፣ በአፉ ተናግሮም ይድናልና» (ሮሜ 10:10)* አንተስ ኃጢአተኛ ነህ ወይስ ጻድቅ?

ገላትያ 3:27 እንዲህ ይላል *«ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና»* ይህ ጥቅስ ኢየሱስ የተሰቀለው የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ በጥምቀቱ ከወሰደ በኋላ መሆኑን ይናገራል ከሞትም በሶስተኛው ቀን በመነሳት አሁን በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጦኣል በእርሱ ለሚያምኑ ሁሉ እርሱ የምህረት ጌታቸው ሆኗል::

ኢየሱስ ባይጠመቅ ኖሮ በመስቀል ላይም በእኛ ፈንታ ባይደማልን ኖሮ አዳኛችን ሊሆን አይችልም ነበር ልንድን የምንችለው በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ስናምን ብቻ ነው::

# የሙሴ ልጅም እንኳ

*ሙሴ ወደ ግብፅ ሲጓዝ እግዚአብሔር ሊገድለው የነበረው ለምንድን ነው?*

*ልጆቹን ባለማስገረዙ ነው።*

የተወደዳችሁ ሆይ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደም ስላገኛችሁት የኃጢአታችሁ ስርየት ምስጢር እያደመጣችሁ ነው እነዚህን የእግዚአብሔር ቃሎች ማድመጥ መቻል ግሩም በረከት ነው።

ይህ የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ብቻ ነውን? በብሉይ ኪዳን ጊዜ ሰዎች የእግዚአብሄር ህዝቦች የሆኑት በግርዘትና በፋሲካው በግ ደም አማካኝነት ነበር አሁንም እኛ የእግዚአብሔር ልጆች ልንሆን የምንችለው በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ስናምን ብቻ ነው የዚህንም ማረጋገጫ እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን በሙሴ በኩል አሳይቶናል።

እግዚአብሄር ሕዝበ እስራኤልን ለማዳን ሕዝቡን ከግብፅ ያወጣ ዘንድ ለሙሴ ነገረው ስለዚህ ሙሴ በአማቱ በዮቴር ፈቃድ መሠረት የምድያምን ምድር ለቆ ከሚስቱና ከልጆቹ ጋር ወደ ግብፅ አቀና ቤተሰቡን በአህያ ላይ ባስቀመጠ ጊዜ እግዚአብሄር በሰፈረበት ቦታ ሊገድለው ፈለገ።

ሆኖም ግን ጠቢብ ባለቤቱ ሲፖራ ምክንያቱን ታውቅ ነበር እርሷም ጠፍጣፋ ድንጋይ አንስታ ልጁን ከገረዘችው በኋላ በሙሴ የተቆረጠውን ቆዳ እግር ስር በመጣል *«ስለ ግርዘቱ አንተ የደም ሙሽራ ነህ»* አለችው እግዚአብሔርም እንዲሄድ ፈቀደለት።

ይህም ማንኛውም ሰው የሙሴ ልጅ እንኳን ቢሆን ካልተገረዘ እግዚአብሄር በእርግጠኝነት ሊገድለው እንደሚችል የተናገረበት መንገድ ነው ግርዘት ለእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሄር ኪዳን ምልክት ነበር እነርሱ ከሕዝቡ መካከል ሳይገረዝ የቀረ ማንም ሰው ቢኖር የአለቃ ልጅ እንኳን ቢሆን እግዚአብሄር እንደሚያጠፋው ያውቁ ነበር ስለዚህ ልጁን ከሞት ለመከላከል እግዚአብሄር ሙሴን በዚህ መንገድ ተገናኘው::

ሲፓራ የልጇን ሸለፈት ቆርጣ በሙሴ እግር ስር ከጣለች በኋላ «አንተ የደም ሙሽራ ነህ» ያለችው እግዚአብሄር ከሰጠው የግርዘት መጠይቅ ጋር ለመስማማት እንደነበር መፅሐፍ ቅዱስ ይናገራል:: (ዘፀዓት 4:26)

ከእስራኤላውያን መካከል ማንም ያልተገረዘ ቢኖር ከሕዝቦቹ የተለየ ይሆናል የፋሲካውን በግ ስጋ ለመመገብና እንደ እግዚአብሔር ልጆች ለመቆጠር የሚችሉት የተገረዙት ብቻ ናቸው::

ሐዋርያው ጳውሎስ ከዕብራውያን ወገን ነበር በተወለደ በ8ኛው ቀንም ተገረዘ የተማረውም በታላቁ መምህር በገማልኤል እግር ስር ነበር በዚህም ኢየሱስ ክርስቶስ በዮርዳኖስ ለምን እንደተጠመቀና በመስቀል ላይም ለምን እንደተሰቀለ በትክክል ለመረዳት ችሏል በዚህም የተነሳ ሐዋርያው ጳውሎስ በመልዕክቶቹ በሙሉ ስለ ኢየሱስ ጥምቀት ጽፏል::

ሐዋርያው ጳውሎስ የኢየሱስ ደም የደህንነታችን ተፍፃሜት ስለመሆኑ በተደጋጋሚ ተናግሯል ደሙ የመቤዠቱ የመጨረሻ ደረጃ ሲሆን እውነተኛውም መንፈሳዊ ግርዘትም የኢየሱስ ጥምቀት ነበር ያለ ጥምቀቱ በኢየሱስ ደም ላይ ብቻ ማተኮር ትርጉም የለውም::

ሐዋርያው ጳውሎስ በተደጋጋሚ ስለ ኢየሱስ መስቀል በቀጥታ ተናግሯል ለምን? ምክንያቱም ደሙ የደህንነታችን

የመጨረሻው ማረጋገጫ ስለሆነ ነው ኢየሱስ በጥምቀቱ ኃጢአታችንን በሙሉ ወስዶ ሲያበቃ በመስቀል ላይ ባይደማ ኖሮ ሙሉ በሙሉ ባልዳንም ነበር ኃጢአታችን በሙሉ አይከፈልም አሁንም ድረስ ኃጢአተኞች እንሆን ነበር ሐዋርያው ጳውሎስ በተደጋጋሚ ስለ መስቀሉ የተናገረው ለዚህ ነው መስቀሉ ለደህንነታችን የመጨረሻው ደረጃ ነው::

የደህንነቱ እውነት ያለ ምንም መሸቃቀጥ ለዚህ ትቅልድ ተላልፎ ቢሆን ኖሮ ብዙ ኃጢአት የሌለባቸው ሰዎች ይኖሩ ነበር ነገር ግን እንደ አለመታደል ሆኖ እውነቱ ከጊዜ በኋላ በመጥፋቱ ብዙ ሰዎች የኢየሱስን ጥምቀት እውነተኛ ትርጉም ሳይገነዘቡ እውቀታቸው ስለ መስቀሉ ብቻ ነው::

እነርሱ የሚያምኑት ባዶ በሆነው የወንጌል ቃል ብቻ ስለሆነ አጥብቀው ለብዙ አመታት በኢየሱስ ቢያምኑም ሐጢያተኞች ሆነው ይቀራሉ ከ10 ወይም ከ50 የኃይማኖታዊ ሕይወት በኋላም ኃጢአተኞች ናቸው::

## የእኔ ምስክርነት

*እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን ጻድቅ አድርጎ ይመለከታልን?*

*አይመለከትም እርሱ ፍፁም ነው ጻድቃን ኃጢአታቸውን በሙሉ በጥምቀት አማካኝነት ወደ ኢየሱስ ያስተላለፉት ናቸው::*

በኢየሱስ ማመን የጀመርኩት የ20 ዓመት ወጣት በነበርኩበት ጊዜ ነው፡ ከዚያን ጊዜ በፊት የእግዚአብሔርን ቃል የማላውቅ በመሆኔ የተነሳ ምን ያህል ኃጢአት እንደሰራሁ አላውቅም እስከዚያን ጊዜ ድረስም እኖር የነበረው እግዚአብሔርን ሳላውቅ በራሴ መንገድ በመመራት ነበር፡፡

አንድ ጊዜም ታመምኩኝ በጣም ከመታመሜ የተነሳም የምሞት መስሎኝ ነበር በመጨረሻም ግን ከመሞቴ በፊት ኃጢአቶቼን በሙሉ ማስወገድ እንዳለብኝ ተሰማኝ ኢየሱስ የሞተው እንደ እኔ ያሉ ኃጢኣተኞችን ለማዳን እንደሆነ እሰማ ስለነበር በእርሱ ለማመን ወሰንኩኝ መጀመሪያ ላይ በደስታና በምስጋና ተሞልቼ ነበር

ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ግን ስሜቱ መድከም ጀመረ ከተወሰነ ጊዜም በኋላ ኃጢኣትን በየቀኑ ከመስራት በስተቀር ሌላ ምንም ማድረግ አልቻልኩም ከ10 ዓመታትም በኋላ ቢሆን አሁንም ኃጢአ ተኛ ነበርሁ እንዲያውም ከበፊቱ የበለጠ እንጂ ያነሰ ኃጢአተኛ አልነበርሁም ለ10 ዓመታት በኢየሱስ አምኛለሁ ሐጢያተኛ የመሆኔ እውነትም በጭራሽ አልተለወጠም በዚህም የተነሳ የሚቀጥለውን የመዝሙር ሐረግ አዘወትር ነበር *«♪ማልቀስ ሊያድነኝም! ፊቴ በእንባ ቢታጠብም ፍርሃቴን ሊያስወግድም! የአመታት ኃጢኣትንም ሊያጥብም! ማልቀስ ሊያድነኝም!♪»* ሁሌም ኃጢአትን ባደረኩ ቁጥር አለቅስ ነበር፡፡

«ውድ አምላኬ ሆይ እባክህን ለሰራሁት ለዚህ ኃጢኣት ይቅር በለኝ፡ እባክህን አንድ ጊዜ ይቅር በለኝና ሁለተኛ አይደገመኝም» እያልሁ እፀልይ ነበር አንዴ ኃጢአት በሰራሁ ቁጥር ለሶስት ቀናት እፀልያለሁ ራሴንም በባዶ ክፍል ውስጥ ቆልፌ ሶስቱን ቀናት በፆምና በፀሎት አሳልፍ ነበር ሕሊናዬ በወቀሳ ስለተሞላ የእግዚአብሄርን ይቅርታ ለማግኘት እያለቀስሁ ልመናዬን አቀረብሁ በሦስተኛው ቀን ጥሩ ስሜት ስለሚሰማኝ

ወደፊቱ ለመቅረብ ዳግም እንደተፈቀደልኝ አስባለሁ::

«አሁንም በድጋሚ ኃጢአቴን አጸዳሁ ሃሌ ሉያ!» ከዚያም ወደ ውጭ ወጥቼ በእምነት መኖር እጀምራለሁ አሁንም በድጋሚ ኃጢኣትን ስለምሰራ ከእግዚብሔር መለየት እጀምራለሁ ይህን ጨፍጋጋ ሒደት በመደጋገም ቀጠልሁ መጀመሪያ ላይ በኢየሱስ በማመኔ ተደስቼ ነበር ነገር ግን ማመኔን በቀጠልሁ ቁጥር ሐጢያቶቼ ጥቅም በማይሰጥ ክፍል ውስጥ እንዳለ አቧራ ተከማቹ::

ከ10 ዓመት በኋላም ከማመኔ በፊት ከነበርኩት የበለጥኩ ኃጢኣተኞ ሆንኩኝ «በዚህ በወጣትነት እድሜዩ በኢየሱስ ያመንኩት ለምንድን ነው? ልክ ልሞት ስል 80 ምናምን ዓመት እስኪሆነኝ ድረስ ጠብቄ በኢየሱስ ባምን ይሻለኝ ነበር ያን ጊዜ ሐጢያት ስለማይታወቀኝ በየቀኑ ንስሐ መግባት ባላስፈለገኝ ነበር» በማለት ተውኩት ከእግዚአብሄር ፈቃድ ጋር ተስማምቼ መኖር እንዳለብኝ አሰብሁ ያ ግን የሚቻል አልነበረም የማብድ መሰለኝ::

እግዚአብሄርን እንደ አዲስ መፈለግ ጀመርሁ የስነ መለኮት ትምህርት በመማርም ብዙ ጊዜ አጠፋሁ ነገር ግን ከጥቂት አመታቶች በኋላ ልቤ ይበልጥ መካን ሆነ ኃይማኖታዊ መፅሐፍትን ማንበብ ከመጀመሬ በፊት በሚሞቅ አልጋ ላይ ተመችቶት እንደማይተኛው እንደ ቅዱስ ዳሚየን ለመኖር እፈልግ ነበር በምቾት ላልኖር ማልሁ በፈንታው ራሴን ሙሉ በሙሉ ችግረኞችን በመርዳት ስራ ለመሳተፍ ወሰንሁ::

ስለዚህ ቅዱስ ሰው ባነበብኩኝ ጊዜም እኔም አንዱ ለመኖር ወሰንኩኝ ለራሴ የምናኔን ሕይወት ለመኖር ሞከርሁ አንዳንድ ጊዜ በደረቅ የሲሚንቶ ወለሎች ላይ ተንበርክኬ ለሰአታት መፀለይን አዘወተርሁ ያን ጊዜ ፀሎቶቼ ትርጉም ያላቸው ሆነው ስለሚሰሙኝ በኋላ ጥሩ ስሜት ይሰማኝ ነበር::

ሆኖም ግን ከ10 ዓመት በኋላ ይህን ለመታገስ አልቻልኩም ለእግዚአብሔር ፀለይኩ «በሰማይ ያለኸው ውድ አምላኬ እባክህ አድነኝ በሙሉ ልቤ ምአንተ አምናለሁ ካራ በአንገቴ ላይ ቢሆን እንኳን ለአንተ ያለኝን ታማኝነት እንደማልቀይር ታውቃለህ ሆኖም በአንተ እያመንሁ ውስጤ ለምን ባዶ ሆኖ ይሰማኛል? ከዚህ በፊት ስለ ሐጢያት ብዙ አስቤ አላውቅም በአንተ አምናለሁ ለአመታት በአንተ አምኜ ሳለሁ እንደዚህ የተበላሸሁት ለምን እንደሆነ ግራ ገብቶኛል፡፡»

ምክንያቱን ወደ ማወቅ የደረስሁት በዚህ ጊዜ ነበር በእግዚአብሄር ያመንሁት ከሐጢያቶቼ ሳልድን ነበር በወቅቱ እውነቱን አላወቅሁም ይህ እኔን ለማሳበድ በቂ ነበር፡፡

በልቤ ውስጥ ኃጢኣት እያለ ስለ እግዚአብሔር ፀጋ ቤዛነት ለሌሎች መናገር ይቻለኛልን? የምህረትን ወንጌል ልነግራቸው የምችለው እንዴት ነው? ሌሎችንስ በኢየሱስ እንዲያምኑ ልነግራቸው የምችለው እንዴት ነው? በተደጋጋሚ ጸለይኩ «አምላኬ ሆይ! በቅርቡ ከአገልጋዮች ትምህርት ቤት ተመርቄ አገልጋይህ ልሆን ነው በሐጢያት የጎበጥሁ አገልጋይ ከሆንሁ ለሌሎች ሐጢያተኞች እንዴት ስለ ቤዛነት መናገር ይቻለኛል? እኔ ራሴ ሐጢያተኛ ነኝ የሐዋርያው ጳውሎስን መልዕክቶች ሳነብ ማንም ሰው የክርስቶስ መንፈስ ከሌለው የእግዚአብሄር ልጅ እንዳልሆነ ተረድቻለሁ ነገር ግን ምንም ያህል በጉጉት ብመራመርም መንፈስ በውስጤ ለም በመጀመሪያ እዚያ እንደነበር ተሰምቶኛል ነገር ግን ጠፍቷል ምን ተከሰተ? አቤቱ ለምን እንዲህ እንደሆነ እባክህ ንገረኝ?»

በእርግጥም በቀላሉ በኢየሱስ በማመን መዳን የምችል መስሎኝ ራሴን ሳታልል ነበር በዚህም ለረጅም ጊዜ ያህል ስሰቃይ ነበር፡፡

እግዚአብሔር በጉጉት ለሚሹት ራሱን እንደሚገልጥላቸው

ቃል ገብቷል በመጨረሻ በእውነቱ ተገናኘኝ በኢየሱስ ማመን ከጀመርሁ በኋላ ለ10 አመታት ሐጢያተኛ ነበርሁ ነገር ግን የኢየሱስን ጥምቀትና የደሙን ምስጢር በተማርሁና በብሉይ ኪዳን ያለውን ግርዘትና በአዲስ ኪዳን ያለውን መንፈሳዊ ግርዘት ትርጉም በተረዳሁ ጊዜ ምክርስቶስ ጥምቀት አማካይነትም የደህንነትን ምስጢር ተረድቼ ባመንሁ ጊዜ መከራዬ ሁሉ አበቃ ነፍሴም እንደ በረዶ ነጭ ሆነች፡፡

ይህ ለእናንተም ተመሳሳይ ሊሆን ይችላል በኢየሱስ የጥምቀትና የመንፈሱ ወንጌል የምታምኑ ከሆናችሁ ኃጢኣት የሌለባችሁ ትሆናላችሁ አሁንም ድረስ ፍፁማን ላትሆኑ ትችላላችሁ ነገር ግን ፃድቃን ናችሁ ይህንን እውነት ወደ ልባችሁ ስትወስዱና ለሌሎች ስታሳውቁ እነርሱም ድነው «ሐሌሉያ» በማለት እየጮሁ እግዚአብሄርን ያመሰግናሉ፡፡

ቤዛነትን ያገኙትን ወንድሞችና እህቶች በሙሉ እንኳን ደስ አላችሁ ማለት እፈልጋለሁ ኢየሱስ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ ስላዳነን አመሰግነዋለሁ ሐሌሉያ!እኛ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ በደስታ ተዋጅተናል፡፡

ይህ ታላቅ በረከት ስለሆነ ደስታችንን ሁሉ ተራ በሆኑ ቃሎች መግለጥ አይቻለንም በመቀበላችን የተሰማንን ደስታ ለመግለፅ ተመጣጣኝ ቃላት ማግኘቱ አስቸጋሪ ነው አብረን መዝሙርን እንዘምር፡- *«♪ስሙ ምስጢር ሆነ ምስጢራቱን ገና ለእያንዳንዱ ፍጥረት አላወጅንምና ልክ ግንበኞች እንደማይፈልጉት ድንጋይ ተወርውሮ ነበር ሆኖም ግን ስሙ በልቤ ውስጥ ያለ ከውድ ወርቅ የሚበልጥ ነው♪»*

# የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ ኃጢኣተኞችን ከኃጢኣታቸው ለማዳን ከበቂም በላይ ነው

*ኃጢአትን በሙሉ ከልባችን የሚያስወግደው ምንድን ነው?*

*የኢየሱስ ጥምቀት ነው::*

ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱና በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደሙ የዓለምን ኃጢኣት በሙለ አስወግዷል እኛንም በመንፈሳዊ ግርዘት ሕዝቦቹ አድርጎናል እርሱ ዳግም የተወለዱት አምላክ ነው::

ለኃጢኣት ሁልግዜም ፍርድ አለ ሆኖም ግን ኢየሱስ የተጠመቀውና በመስቀል ላይም ፍርድን የተቀበለው እኛን ለማዳን ነው በደሙም ሁላችንንም አድኖናል ከሞትም በሶስተኛ ው ቀን ተነስቶአል ኢየሱስን ከሞት ያነሳውም አብ እግዚብሔር ነው::

የኢየሱስ ህይወት የእኛ ህይወትና የእግዚብሔር ልጆች ሆነን የምንኖርበትም ምልክት ነው የእርሱ ጥምቀት ኃጢአቶቻችን በሙሉ ወደ እርሱ ሲያስተላልፉ በመስቀል ላይ የፈሰሰው ውድ ደሙም በእኛ ፈንታ እርሱ ፍርድን ለመቀበሉ ማረጋገጫ ነው::

ውድ ወዳጆች በልባችሁ ይህ የኢየሱስ ጥምቀትና የደሙ ምስክርነት አለን? በድጋሚ እጠይቃችኋለሁ ደህንነታችሁ የመጣው በኢየሱስ ደም ብቻ ነውን? አይደለም ደህንነት የሚመጣው በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ነው::

## መናፍቅ ማነው?

*መናፍቅ ማነው?*

*በኢየሱስ ጥምቀት ባለማመኑ ራሱን የሚወነጅል መናፍቅ ነው::*

ውድ ወዳጆች በየቀኑ በኢየሱስ ላይ ያላችሁን እምነት ብትናዘዙም አሁንም ድረስ ሐጢያተኞች ናችሁን? በኢየሱስ እያመናችሁም አሁንም ድረስ ኃጢአተኞች ከሆናችሁ እናንተ መናፍቃን ናችሁ መናፍቅነት በእግዚአብሔር ቃል አለማመን ነው ቲቶ 3:10 ስለ መናፍቅነት ይናገራል:- *«በራሱም ላይ ፈርዶ ኃጢአትን እንዲያደርግ አውቀህ አንድ ጊዜ ሁለት ጊዜም ከገሰፅኸው በኋላ እንዲህ ከሚመስል ሰው ራቅ::»*

በራሱ ላይ የፈረደ ሰው ውድ አምላኬ! እኔ ኃጢአተኛ ነኝ በአንተ አምናለሁ ሆኖም ግን ኃጢኣተኛ ነኝ ማንም የፈለገውን ቢል እኔ ኃጢአተኛ መሆኔን አምናለሁ ይህም እውነት ነው» ብሎ ይፀልያል::

እግዚአብሔርም «አሁንም ድረስ ኃጢኣተኛና ልጄም ያልሆንክ ነህን? እንዲያ ከሆነ አንተ መናፍቅ ነህ ስለሆነም ወደ ገሃነም እሳት መወርወር አለብህ» ይለዋል::

የኢየሱስን ጥምቀት ወንጌል በልባችሁ ሳታምኑ በኢየሱስ ካመናችሁ ራሳችሁንም ኃጢአተኛ አድርጋችሁ በራሳችሁ ላይ የምትፈርዱ ከሆናችሁ እናንተ በእግዚአብሔር ፊት መናፍቃን ናችሁ::

# እውነተኛ ምዕመናን እነማን ናቸው?

*በእግዚአብሔር ፊት ያለ የደህንነት ምስክር ምንድነው?*

*ውኃው፣ ደሙና መንፈሱ ናቸው::*

በኢየሱስ የጥምቀትና የደሙ ወንጌል የሚያምኑ ሁሉ እነዚያ የእግዚአብሔር ልጆች የሆኑት በሙሉ እንዲሁም ኃጢአታቸው የተወገደላቸው በሙሉ ጻድቃን ናቸው በኢየሱስ እያመናችሁ እንዴት ኃጢአተኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ? ኃጢአተኛ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት አይችልም::

በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን የፀደቁት የእግዚአብሔር ምስክርነት በልባቸው ውስጥ አለ ምስክሩም የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ ናቸው ይህ የምህረት ስራም ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ በነበረ ጊዜ የሰራው ነው::

ስለሆነም ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በወሰደበት የጥምቀት ወንጌል ለማመን እምቢተኛ የሆነ ማንኛውም ሰው ከእግዚአብሄር ይቆረጣል::

የእምነት ወንድሞችና እህቶች ሐጢያተኞች የሚድኑት በኢየሱስ ደም ብቻ ሳይሆን የኢየሱስ ጥምቀት በሆነው ውሃም ጭምር እንደሆነ የሚናገረውን ወንጌል በልባችሁ ተቀብላችኋልን?

ኢየሱስ በዚህ ምድር በሰራው ስራ የሚያምን ውሃውን ደሙንና መንፈሱን የተቀበለ ሁሉ ከሐጢያት ሁሉ ይድናል ይህ የውኃው የደሙና የመንፈሱ ወንጌል እውነትና ጥበብ ነው::

ኢየሱስ የሰው ልጅ በሙሉ በእርሱ ይድን ዘንድ እኛን በጥምቀቱ ሙሉ በሙሉ አንፅቶናል አሁንም እናንተ በኢየሱስ ሙሉ በሙሉ ብታምኑ ኃጢኣተኛ ልትሆኑ የምትችሉበት መንገድ የለም::

ኢየሱስ እኛን ከሞት አድኖናል ኢየሱስ በዲያብሎስ ተታልለው ከእግዚአብሔር መንገድ ወጥተውና ርቀው የነበሩ ነፍሶችን ወደ እግዚአብሔር መልሷል እግዚአብሄር በኢየሱስ በውኃው በደሙና በመንፈሱ ወንጌል አማካኝነት ይሰራል እርሱም ጠርቶናል እኛም በእርሱ በማመን ልንድን እንችላለን::

በዚህ እጅግ ጥልቅ እውነት ታምናላችሁን? ደህንነት የሚገኘው በደም ብቻ ሳይሆን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ እንደሆነ እነግራችኋለሁ እነዚያ በኢየሱስ ደም ብቻ በማመን ድነናል የሚሉት በልባቸው ውስጥ ኃጢአት መኖሩን ማመን አለባቸው::

ሁላችንም በኢየሱስ ደም ማመናችን ለደህንነታችን በቂ እንደሆነ ማሰብ እናዘወትራለን ቀድሞ እንደዚህ እናስብ ነበር አሁን ግን ይህ በቂ እንዳልሆነ መገንዘብ አለብን እኛ በውኃ በደምና በመንፈስ በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ድነን ዳግም ተወልደናል::

ኃጢአተኛ የሆነ ማንም ሰው በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ በማመን ዳግም ሊወለድ ይችላል:: **(1ኛ ዮሐንስ 5:5-10)**

እግዚአብሔርን እናመስግነው ሃሌ ሉያ! ✉

# ስብከት 4

# እውነተኛና ትክክለኛ

# የሐጢያት ኑዛዜ እንዴት

# እንደሚደረግ

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሬቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡



«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዷልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ፣ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና።» **(ዮሐንስ 3፡16-17)**

**ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር** (www.amazon.com) **በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።**

# እውነተኛና ትክክለኛ የሐጢያት ኑዛዜ እንዴት እንደሚደረግ

**« 1ኛ ዮሐንስ 1:9 »**

**«በኃጢያታችን ብንናዘዝ ኃጢአታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነጻን የታመነና ጻድቅ ነው።»**

## የደሙ ወንጌል ግማሽ ወንጌል ነው

*በደሙ ወንጌል ብቻ በማመን ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንገባለንን?*

*በፍፁም። በሙሉው ወንጌል (በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል) ማመን አለብን።*

**1ኛ ዮሐንስ 1:9 የሚመለከተው ፃድቃንን ብቻ ነው ደህንነት ያልተቀበለ ኃጢያተኛ ይህ አንቀፅ በሚያመለክተው መሰረት ኃጢያቱን በመናዘዝ ምህረትን ለማግኘት ቢሞክር ኃጢያቱ አይሰረይለትም እዚህ ጋር እያልኩ ያለውን ነገር ተመልክታችሁታልን? ይህ ምንባብ እንደገና ላልተወለዱት ኃጥአን አይሰራም።**

በዚህ አለም ላይ ገና ዳግም ያልተወለዱ ብዙዎች አሉ ነገር ግን ይህንን ምንባብ ከ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 1 ወስደው ይቅርታን ለማግኘት ተስፋ በማድረግ ይፀልያሉ ከሐጢያቶቻቸውም ንስሐ ይገባሉ::

ነገር ግን ዳግም ያልተወለደ ሰው የኑዛዜ ፀሎቶችን በማድረግ ሙሉ በሙሉ ከሐጢያቶቹ ሊድን ይችላልን? ይህ እኛ በጥልቅ ወደ ዝርዝሩ ከመግባታችን በፊት ግልፅ ማድረግ ያለብን ነጥብ ነው::

1ኛ ዮሐንስን ከማንበባችሁ በፊት ሐዋርያው ዮሐንስ ፃድቅ ሰው ይሁን ወይም ኃጢያተኛ ማወቅ አለባችሁ እስቲ እኔ ልጠይቃችሁ ሐዋርያው ዮሐንስ በትክክለኛው የውኃና የመንፈስ ወንጌል በማመን እንደገና የተወለደ ፃድቅ ነበር ወይስ ኃጢያተኛ ነበር?

ሐዋርያው ዮሐንስን ኃጢያተኛ ነው ካላችሁ በመፅሐፍ ቅዱስ መሰረት እምነታችሁ ትክክል አይደለም ሐዋርያው ዮሐንስ በኢየሱስ ሲያምን እንደገና የተወለደ ፃድቅ ነው ካላችሁ ደግሞ ይህ እምነቱ ከእናንተ እምነት የሚለይ ስለመሆኑ ግልፅ ይሆንላችኋል እናንተም ሐዋርያው ዮሐንስ የነበረውን አይነት እምነት ሊኖራችሁ ይገባችኋል::

ሌላም ጥያቄ ልጠይቃችሁ ሐዋርያው ዮሐንስ እነዚያን መልዕክቶች የፃፈው ለኃጥኣን ነው ወይስ ለፃድቃን? ሐዋርያው ዮሐንስ መልዕክቶቹን የፃፈው ለፃድቃን ነበር::

ስለዚህም እንደገና ያልተወለዱ ኃጢያተኞች ሐዋርያው ዮሐንስ በምዕራፍ 1:8-9 ላይ የፃፋቸውን ቃሎች በመውሰድ ቢፀልዩና በሕይወታቸውም ቢተገብሯቸው ይህ ስህተት ነው እናንተ ፃድቅ ለመሆን የምትፈልጉ ከሆነ በመጀመሪያ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለባችሁ በመቀጠልም በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያታችሁን በመናዘዝ ንስሐ ትገባላችሁ

በመቀጠልም ጌታ የዓለምን ኃጢያት በሙሉ ባፀዳልን በወንጌሉ ኃጢያታችንን ያስወግድልናል፡፡

የሐዋርያው ዮሐንስ እምነት የዚህ አይነት ነበር በ1ኛ ዮሐንስ ምዕራፍ 5 ላይ እርሱ «በውኃ በደሙና በመንፈሱ» እምነት እንዳለው ይናገራል በውኃ በደምና በመንፈስ በመጣው በኢየሱስ ክርስቶስ ታምናላችሁን? የምታምኑት በመስቀሉ አማካይነት በመጣው ኢየሱስ ብቻ ነው በጥምቀቱ በደሙና በመንፈሱ?

በደሙ ወንጌል ብቻ በማመን ወደ እግዚብሔር መንግስት ለመግባት የምትችሉ ይመስላችኋልን? እምነታችሁ የተመሰረተው በመስቀሉ ላይ ደም ብቻ ከሆነ የምታውቁት ግማሹን ወንጌል ነው ማለት ነው በደሙ ወንጌል ብቻ የምታምኑ ከሆነ ራሳችሁን በየዕለቱ ለምትሰሩት ኃጢያት በመፀለይ እንደምታገኙት እርግጥ ነው ለዚህም ምክንያቱ ሐጢያቶቻችሁ ሊወገዱ የሚችሉት የንስሐ ፀሎቶችን በመፀለይ ነው ብላችሁ ማመናችሁ ነው፡፡

በኢየሱስ የመስቀሉ ላይ ደም በማመንና በየቀኑም ለኃጢያታችሁ ምህረትን በመለመን ብቻ ኃጢያቶቻችሁ እንደሚሰረዩላችሁ ታምናላችሁን? እናንተ ከእነዚህ ሰዎች አንዱ ከሆናችሁ ማንም ሰው በመስቀሉ ላይ ደም ብቻ ባለው እምነት ኃጢያቱ ሊነፃ ስለማይችል ለዘላለም ኃጢያትን በልባችሁ ይዛችሁ ትቀራላችሁ እናንተ ከእነዚህ ሰዎች መካከል ከሆናችሁ አሁንም ድረስ ትክክለኛውን የውኃና የመንፈስ ወንጌል አታውቁትም ማለት ነው ይኼኛው መንገድ የትም አያደርሳችሁም፡፡

ሐዋርያው ዮሐንስ ዳግም ውልደትን ሊያገኝ የቻለው በትክክለኛው የውኃው የደሙና የመንፈሱ ወንጌል ስለሚያምን ነው እናንተ ግን እያመናችሁ ያላችሁት በደሙ ወንጌል ብቻ

ነው ስለ ወንጌሉ እናንተ ራሳችሁ ግልፅ የሆነ መረዳት ሳይኖራችሁ እንዴትስ ሌሎችን ወደ ድነት መንገድ ልትመሩ ትችላላችሁ? ራሳችሁ እንኳን እንደገና ሳትወለዱ ኃጢያታችሁን በንስሐ ፀሎት ለማስወገድ ታስባላችሁ ይህ መቼም ቢሆን ሊሰራ የሚችል ነገር አይደለም።

ምንም እንኳን አንድ ሰው በጥንካሬና በፅናት ቢፀልይም ኃጢያቶቹ ከልቡ ሙሉ በሙሉ ሊሰረዩለት አይችሉም አንዳንድ ጊዜ ኃጢያቶቻችሁ በሙሉ እንደተወገዱላችሁ የምታስቡ ከሆነ ይህ የእናንተ ምኞትና የፍላጎታችሁ ውጤት ብቻ ነው የምትፀልዩና ለንስሐ የምትተጉ ከሆነ ለአንድ ቀን በጣም የታደሳችሁ መስሎ ይሰማችኋል ሆኖም ግን መቼም ቢሆን በዚህ መንገድ ከኃጢያታችሁ ነፃ ልትሆኑ አትችሉም።

ኃጢያተኞች የሚፀልዩት ከኃጢያታቸው እንደሚነፁ ተስፋ በማድረግ ነው እነሱ በኢየሱስ ካመኑ ከረጅም ጊዜ በኋላም ኃጢያተኞች ናቸው የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል በትክክል ስያውቁትም በኢየሱስ የምታምኑ ከሆናችሁና አሁንም ድረስ ግን እንደገና ያልተወለዳችሁ ከሆናችሁ እናንተም ከእነዚህ ሰዎች መካከል ናችሁ ማለት ነው በየዕለቱ ለኃጢያታችሁ ስርየት የምትፀልዩ ከሆነና አሁንም ድረስ ኃጢያተኞች መሆናችሁን የምታስቡ ከሆናችሁ ይህ እንደገና ላለመወለዳችሁ ምስክር ነው ልክ ሐዋርያው ዮሐንስ እንዳደረገው በየውኃ በመንፈስ ወንጌል የምታምኑ ስለመሆናችሁ መወሰን ይኖርባችኋል አለበለዚያም እምነታችሁን በአስተሳሰቦቻችሁና በስሜቶቻችሁ ላይ አድርጉ አንዱ ግልፅ እውነት ሲሆን ሌላው ደግሞ እውነት አይደለም።

እውነተኛው ወንጌል በመፅሐፍ ቅዱስ መሠረት ኢየሱስ በጥምቀቱ የዓለምን ኃጢያት በሙሉ እንደወሰደና በመስቀል ላይ በመሞትም ፍርድን ለእነዚህ ኃጢያቶች በሙሉ መቀበሉን የሚናገረው ወንጌል ነው አንድ ሰው በኢየሱስ ጥምቀትና

በመስቀል ላይ በመሞቱ የሚያምን ከሆነ ኃጢያቱ በሙሉ ይሰረይለታል በሌላ በኩል አንድ ሰው መተላለፎቹን በንስሐ ፀሎቶች ለማስወገድ የሚሞክር ከሆነ ከሐጢያቶቹ በጭራሽ ነፃ ሊሆን አይችልም በፀሎትና በትጋቱ ብቻ ከኃጢያቱና ከስህተት ስራው ሙሉ በሙሉ ለመዳን የሚፈልግ ከሆነ እርሱ መቼም ቢሆን ከኃጢያቱ ሊነጻ አይችልም የየዕለቱን ኃጢያቶቻችሁን በሙሉ ለማስታወስ የምትችሉ ይመስላችኋልን? እግዚአብሔር ንስሐ ያልገባችሁባቸውን ሐጢያቶቻችሁን ይተውላችኋልን? የንስሐ ፀሎትን በየዕለቱ ኃጢያቶቻችን ብቸኛ መፍትሔዎች ናቸውን? በፍፁም አይደሉም::

## እውነተኛ ንስሐና የኑዛዜ አስፈላጊነት

*የጥሩ ምግባርና የኑዛዜ ገደቦች ምንድን ናቸው?*

*በእድሜያችን በሙሉ ኃጢያቶቻችንን መናዘዝ ቢኖርብንም፣ መተላለፋችንንና ኃጢያቶቻችንን በመናዘዝ እንዲሁም ጥሩ ነገሮችን በማድረግ ብቻ ልንድን አንችልም::*

በመፅሐፍ ቅዱስ መሠረት ንስሐ ማለት ከስህተት እምነት ወደ ትክክለኛ እምነት መመለስ ማለት ነው ለፃድቃን ደግሞ ስህተት ከሆነ ተግባር ወደ ትክክለኛ ተግባር በመመለስ ወደ ወንጌሉ ብርሃን መምጣት ማለት ነው::

በአሁን ሰዓት ኃጢያተኞች ከሆናችሁ የዚህን አይነት ንስሐ

መግባት አለባችሁ «ውድ እግዚአብሔር እኔ ኃጢያተኛ ነኝ መግባት የሚገባኝም ወደ ገሃነም መሄድ ነው ሆኖም ግን ከኃጢያቶቼ ለመዳን እፈልጋለሁ እባክህን ከኃጢያቶቼ በሙሉ አድነኝ አሁንም ድረስ እንደገና አልተወለድኩኝም ወደ ገሃነም እንደምገባም አምናለሁ» ይህ ትክክለኛው ንስሐ ነው፡፡

ዳግም የተወለደውስ ምን አይነት ኑዛዜ ማድረግ ይኖርበታል? «አቤቱ ስጋዬን የመከተል ሐጢያት ሰርቻለሁ ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ ሲጠመቅ ከሐጢያቶቼ አሁን ከፈፀምሁዋቸው ሐጢያቶቼ እንኳን ሳይቀር እንዳዳነኝ አምናለሁ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ በሐጢያቶቼ አማካይነት እሞት ነበር በውሃና በደም ስላዳነኝ ጌታን አመሰግናለሁ» ዳግም የተወለደ ሰው የሚያደርገው ኑዛዜና ዳግም ያልተወለደው የሚያደርገው ኑዛዜ የተለያዩ ናቸው፡፡

እኛ ሁላችን ልክ የሐዋርያውን የዮሐንስ አይነት እምነት ሊኖረን ይገባል ኃጢያቶቻችሁን ከፃድቁ ኑዛዜ ጀርባ ለመደበቅ የምትሞክሩ ከሆነ የሐጢያት ደመወዝ ከሆነው ሞት በጭራሽ አትድኑም፡፡

ዳግም ውልደትን ያላገኙ ኃጢያተኞች በሙሉ ኃጢያታቸውን በንስሐ ፀሎት ከመደበቅ በመውጣት በእውነተኛው የውኃውና የመንፈሱ ወንጌል ማመን አለባቸው የሐዋርያውን የዮሐንስን ወንጌል በማመን ድነትን ማግኘት አለባቸው፡፡

ኃጢያተኞች ለሐጢያታቸው የሚፈረድባቸው ፍርድ ምን ያህል አስከፊ እንደሚሆን አያውቁም በእግዚአብሔር ፊት በጣም ከባዱ ኃጢያት እንደገና በመወለጃው በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል አለማመን ነው፡፡

በኢየሱስ የሚያምኑ ነገር ግን ገና ዳግም ያልተወለዱ ሁሉ በእግዚአብሄር ፊት መናዘዝ የሚኖርባቸው «አቤቱ እኔ ወደ

ሲያል እሳት መወርወር የሚገባኝ ሐጢያተኛ ነኝ» ብለው ነው «አቤቱ እባክህ ሐጢያቶቼን አስወግድልኝ» ከማለት መታቀብ ይኖርባቸዋል አንድ ኃጢያተኛ ኢየሱስ በዮርዳኖስ በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመሞት ከኃጢያቱ በሙሉ ነፃ እንዳወጣው የሚያምን ከሆነ ከኃጢያቱ በሙሉ ነፃ ሊወጣ ይችላል ይህ አንድ ኃጢያተኛ ከኃጢያቱ ሁሉ ለመንፃት በእግዚአብሔር ፊት መግባት ያለበት ንስሐ ነው::

አንድ ኃጢያተኛ ያለበት ዳግም እንዳልተወለደና በትክክለኛ ው የውኃና የመንፈስ ወንጌል እንደማያምን መናዘዝ አለበት ከዚያም በአንድ ጊዜ ሊድን ይችላልበውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሐጢያተኞች ደህንነት ሁሉ ይፈፀማል *«መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋርያት ሥራ 4:12)* እግዚአብሔር ልጁ ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ እንዲጠመቅና በመስቀል ላይ እንዲሞት በማድረግ ሐጢያተኞችን ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው አድኖዋቸዋል::

ጌታ የሰው ልጆች በስጋቸውም ሆነ በልባቸው ከተወለዱ አንስቶ እስከሚሞቱ ድረስ የሚሰሩትን ኃጢያት አፅድቶላቸዋል ለመዳንም በትክክለኛው ወንጌል ማመን አለብን ይህ ከኃጢያታችን የምንድንበትና በእውነት የምንፀድቅበት መንገድ ነው በትክክለኛው የውኃና የመንፈስ ወንጌል በማመን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ልንድን እንችላለን::

ኢየሱስ የተጠመቀው የሰው ልጆችን ኃጢያት በሙሉ ለመውሰድ ነው እንዲሁም ለእነዚህ ሐጢያቶች በመስቀል ላይ ሕይወቱን ከፍሎዋል ከሞትም በሶስተኛው ቀን በመነሳት በአሁኑ ሰዓት ከእግዚአብሄር ቀኝ ተቀምጦ ይገኛል ይህ አቻ የሌለው እውነታ ነው::

ሁላችንም ይህንን ኑዛዜ ማቅረብ ይገባናል «ጌታ ሆይ እስከ

ዕለተ ሞቴ ድረስ ሐጢያትን እሰራለሁ ከእናነ ማሕጸን ስወለድ ጀምሮ ሐጢያተኛ ሆኜተወልጃለሁ ለሰራሁዋቸው ሐጢያቶች በሙሉም ዕዳ አለብ ወደ ሲዖል እሳት መወርወር ይገባኛል በዚህ ምክንያት በውሃ በደምና በመንፈስ በመጣው በኢየሱስ ማመንና አዳኜ እንዲሆንም እፈልጋለሁ፡፡»

በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ 3 ላይ እንደተፃፈውም ኢየሱስ የሰው ልጆችን ኃጢቶች በሙሉ እስከምንሞትበት ቀን ድረስ የምንሰራውንም ኃጢያት ጭምር በዮርዳኖስ ወንዝ ሲጠመቅ አስወግዶልናል *«እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው፡፡» (ዮሐንስ 8:32)*

ኢየሱስ ያዳነን ከመሰረታዊ ኃጢያቶቻችን ብቻ ቢሆንና በየዕለቱ የምንሰራውን ኃጢያቶች በራሳችን እንድንፈታ ቢነግረን ኖሮ በከፍተኛ ችግር ውስጥ እንሆን ነበር ሆኖም ግን ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከኃጢያቶቻችን በሙሉ አድኖናል ስለምን መጨነቅ ይኖርብናል? በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ደሙ ስናምና ስናመሰግነው፣ መንፈስ ቅዱስ በልባችን ውስጥ ይሰርጋል፡፡

በኢየሱስ ታምናላችሁን? በውስጣችሁ መንፈስ ቅዱስ እንዳደረባችሁ ታምናላችሁን? ኃጢያቶቻሁ በሙሉ ኢየሱስ በዮርዳኖስ ወንዝ በዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ወደ እርሱ ከዓለም ኃጢያቶች ጋር አብረው ተላልፈዋል በኋላ ላይም እኛን ከዘላለም ጥፋት ያድነን ዘንድ በመስቀል ላይ ፍርድን ተቀብሏል ይህ ትክክለኛው ወንጌል ነው፡፡

## የጻድቃን ኑዛዜ

*የጻድቃን እውነተኛ ኑዛዜ ምንድን ነው?*

*በየዕለቱ ኃጢያትን እንደሚሰሩና ከ2000 ዓመታት በፊት ኢየሱስ ኃጢያታቸውን እንዳፀዳላቸው መናዘዝ ነው።*

1ኛ ዮሐንስ 1:9 ላይ *«በኃጢያታችን ብንናዘዝ ኃጢያታችን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው»* ይህ ማለት በትክክለኛው በውኃና በመንፈስ ወንጌል ለማመን የወሰነ ሰው ኃጢያቱን «ጌታ ሆይ! በህይወቴ ኃጢያትን ከመስራት ውጭ ሌላ ምንም እንደማልፈይድ አውቀዋለሁ እንዲሁም በፀሎት ከኃጢያት እንደማልድንም አውቃለሁ የኃጢያት ደሞዝ ሞት መሆኑንና ከኢየሱስ ጥምቀትና ስቅለት በስተቀር ከዚህ ኃጢያት የሚያነፃኝ እንደሌለ አምናለሁ ዛሬ ኃጢያት መስራቴን እናዘዛለሁ እንዲሁም ደግሞ ዛሬም ለሰራሁት ኃጢያት ኢየሱስ ከ2000 ዓመት በፊት በዮርዳኖስ ወንዝ ኃጢያቴን እንዳፀዳልኝ አምናለሁ» በማለት ይናዘዛል በዚህ መንገድ የሚፀልይ ከሆነም በአእምሮው ውስጥ ያለው የኃጢያት ችግር በአንዴ ይቃለልለታል።

ዳግም የተወለዱት ማድረግ የሚጠበቅባቸው ኃጢያታቸውን መናዘዝ ብቻ ነው ሁልጊዜም ኢየሱስ ኃጢያታቸውን በሙሉ እንዳስወገደላቸው ይመሰክራሉ ምክንያቱም ኢየሱስ ከ2000 አመታት በፊት ተጠምቆ

ለሐጢያተኞች በመሞቱ ምክንያት ምንም ያህል ደካሞች ቢሆኑም ሐጢያቶቻቸው በሙሉ ፈፅመው ተወግደዋልና::

ዛሬ ያነበብነው ነገር ለቅዱሳን በጣም ጠቃሚ የሆነ ነገር ነው ሆኖም ግን አንድ ኃጢያተኛ ይህን ጥቅስ በመውሰድ በስህተት መንገድ ከተጠቀመበት መጨረሻው የሚሆነው ገሃነም ነው የሆኖ ሆኖ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ በስህተት ጥቅም ላይ ከሚውሉት ምንባቦች አንዱ ይህ ነው ይህ ለረጅም ጊዜ በክርስትያኖች መካከል ትልቅ አለመግባባትን የፈጠረ ነገር ነው::

ብቃት የሌለው ሐኪም ህመምተኞቹን ይገድላል የሚል አባባል አለ ብቃት የሌለው ሐኪም ከሚችለው በላይ ለማድረግ ቢሞክር ህመምተኛውን ሊገድለው ይችላል::

አንድ ሰው ስራውን በትክክል ለማከናወን ይችል ዘንድ ብቃቱ እስከሚረጋገጥ ድረስ መሰልጠን እንዳለበት የሚናገረው የህይወት ህግ ነው ይህ ከዓለም ኃይማኖት ጋር ተመሳሳይ ነው የእግዚአብሔርን ቃል የሚያስተምሩ እውነቱን ልክ እንደተፃፈው በትክክልና በግልጥ ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል ከእነዚህ የሚማሩትም በተማሩት ነገር ላይ እምነት ሊኖራቸው ይገባል::

ሰባኪዎች ለተከታዮቻቸው የተሳሳቱ ትምህርቶችን ካስተማሩ ወይም ምዕመናን መፅሐፍ ቅዱስን በተሳሳተ መንገድ ከተማሩ የሁለቱም መጨረሻ ፍርድና ሲዖል ይሆናል መፅሐፍ ቅዱስን በትክክል ለማስተማር የሚችሉት ዳግም ውልደትን ያገኙት ብቻ ናቸው ጥሩ መድሃኒትም በትክክል ካልተወሰደ ይገድላል የእግዚአብሔር ቃልም እንዲሁ ነው ይህ ልክ እንደ እሳት ሁሉ ለህይወታችን አስፈላጊ ነው ልክ እሳትም በህፃናት እጅ ከገባ የሚያደርሰው አደጋም ያንኑ ያህል የከፋ ነው የእግዚብሔርም ቃል ትክክል ባልሆነ ሰው እጅ ከገባ

የሚያደርሰው ጥፋት እጅጉን የላቀ ነው።

የፃድቃንንና የኃጢያተኞችን ኑዛዜ ልዩነቱን በትክክል መረዳት አለብን 1ኛ ዮሐንስ 1:9 የተፃፈው ለፃድቃን ነው ፃድቅ ሰው በጌታ ፊት ኃጢያቱን ሲናዘዝ ኢየሱስ ከ2000 ዓመት በፊት ኃጢያቱን በሙሉ ስላስወገደለት ከኃጢያቱ በሙሉ የነፃ ይሆናል።

ኃጢያተኞች ሐጢያቶቻቸው የሚነፁት በየጊዜው ይቅርታን ለማግኘት በሚፀልዩት ፀሎት መሆኑን የሚያምኑ ከሆነ ስህተት ነው ሰው ዳግም ካልተወለደ ሐጢያቶቹ በኑዛዜ ብቻ ሊነፁ ይችላሉን?

እግዚአብሔር ፃድቅ ነው አንድያ ልጁንም ወደዚህ አለም ልኮ በጥምቀቱ አማካይነት የአለምን ሐጢያቶች እንዲወስድ በማድረግ በጥምቀቱ ውሃና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ የሚያምኑትን ሁሉ አድኖዋል ስለዚህ ፃድቅ የሆነ ሰው ሐጢያቶቹን ሲናዘዝ እግዚአብሄር ኢየሱስ ከ2000 አመታት በፊት ሐጢያቱን በሙሉ እንደወሰደ ይነግረዋል እንዲህ ያለው ግለሰብ ምንም እንኳን ስጋው አሁንም ድረስ ሐጢያት ቢሰራም በልቡ ውስጥ ሐጢያት እንደሌለ ያረጋግጣል። 🖂


# ስብከት 5

# አስቀድሞ በመወሰንና

# በመለኮት ምርጫ ፅንሰ ሐሳብ

# ውስጥ ያለው ስህተት

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡




«እውነትን በዓመፃ በሚከለክሉ ሰዎች በኃጢአተኝነታቸውና በዓመፃቸው ሁሉ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ከላይ ከሰማይ ይገለጣልና፡፡» (ሮሜ 1:18)

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡

# አስቀድሞ በመወሰንና በመለኮት ምርጫ ፅንሰ ሐሳብ ውስጥ ያለው ስህተት

**« ሮሜ 8:28-30 »**

**«እግዚአብሔር ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና አስቀድሞ የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ አጸደቃቸው ያጸደቃቸውንም እነዚህን ደግሞ አከበራቸው።»**




የክርስትናን ትምህርት ካዋቀሩት መሠረታዊ የነገረ መለኮት ትምህርቶች አንዱ የሆነው አስቀድሞ የመወሰንና የመለኮት ምርጫ ነገረ መለኮታዊ ፅንሰ ሐሳብ በኢየሱስ ማመን የሚፈልጉ ብዙዎችን ቃለ እግዚአብሄርን በተሳሳተ መንገድ እንዲያስተውሉ

መርቶዋቸዋል ይህ የተዛባ ፅንሰ ሐሳብ ብዙ ግራ መጋባትን ፈጥሮዋል፡፡

ይህ እውነት ያልሆነውና በእግዚአብሔር አስቀድሞ ስለ መወሰን የሚያብራራው የነገረ መለኮት ትምህርት እግዚአብሔር የሚወዳቸውን እንደመረጠና የሚጠላቸውን ደግሞ እንደሚያወግዝ ይናገራል ይህም ማለት ደግሞ እነዚያ አስቀድመው የተመረጡት ትክክለኛውን የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል በማግኘት እንደገና የተወለዱና ወደመንግስተ ሰማያት የሚገቡት ሲሆኑ ሌሎቹ ያልተመረጡት ደግሞ መጨረሻቸው የሚሆነው ገሃነም ነው፡፡

በእርግጥም እግዚአብሔር የተወሰንነውን ብቻ የመረጠን ቢሆን ኖሮ ራሳችንን «እኔ ተመርጬ ይሆን?» በሚል ጥያቄ ራሳችንን ከመወጠር በቀር ምንም የምንፈይደው ነገር አይኖረንም ነበር እኛ ያልተመረጥን ከሆንን በኢየሱስ ማመናችንም ምንም የሚጠቅመን ነገር አይኖርም ማለት ነው ስለዚህም እንደገና የመወሰንና የመለኮት ምርጫን ቃለ እግዚአብሄራዊ እሳቤ መመርመር ይኖርብናል፡፡

በዚህ የምናምን ከሆነንን እንዴት ከችግሮች ነፃ ሆነን በእግዚአብሔር ብቻ ለማመን እንችላለን? እግዚአብሔርስ በትክክል እኛን እንደመረጠን በምን ልናረጋግጥ እንችላለን? እንደዚያ ከሆነ ደግሞ እርሱ እግዚአብሔርነቱ ለተመረጡት ብቻ ይሆን ነበር ማለት ነው *«ወይስ እግዚአብሔር የአይሁድ ብቻአምላክ ነውን? የአህዛብስ አምላክ አይደለምን? አዎን ለተረገዘን ሁሉ አምላክ ነው፡፡» (ሮሜ 3:29)*

ብዙ ሰዎች የመታጨትንና በመንፈስ የመመረጥን ትክክለኛ ትርጉም ስለማይረዱት በኢየሱስ የሚያምኑ ቢሆንም እንኳን እንጠፋለን ብለው የሚያስቡ አሉ፡፡

ኤፌሶን 1:3-5 እንዲህ ይላል *«ለእግዚአብሔር ለአባታችን*

*ከጌታችንም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጸጋና ሰላም ለእናንተ ይሁን ክፉ ከሆነ ከአሁኑ ዓለም ያድነን ዘንድ እንደ አምላካችንና እንደ አባታችን ፈቃድ ስለ ኃጢአታችን ራሱን ሰጠ ለአብ ከዘላለም እስከ ዘላለም ክብር ይሁን አሜን፡፡»*

ስለዚህም አስቀድሞ ስለመወሰንና ስለ መለኮታዊ ምርጫ ያለንን ቃለ እግዚአብሄራዊ እሳቤ መመርመር ይኖርብናል በመቀጠልም በኢየሱስ ውኃና በመንፈሱ ያለንን እምነት ማጠንከር አለብን፡፡

ሮሜ የሚነግረን ምንድን ነው? አንዳንድ የቃለ እግዚአብሄር ምሁራን መሠረት የሌለውን «በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ምርጫ»ን ፈጠሩ ታዲያ ነገረ መለኮት እግዚአብሄር ነውን? ነገረ መለኮት እግዚአብሄር አይደለም፡፡

ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እንኳን እግዚአብሔር የሰው ዘር ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ መርጦ ፃድቃን በማድረግ ሁላችንንም አድኖናል አላማኒዎች በራሳቸው አስተሳሰቦች ያምናሉ ምዕመናን ግን የእምነታቸውን መሠረት በተፃፈው የእግዚአብሄር ቃል ላይ ያደርጋሉ፡፡

## መንፈሳዊ ምርጫ በብሉይ ኪዳን ዘመን

*የመንፈሳዊ ምርጫ ጽንሰ ሐሳብ እውነት ነውን?*

*አይደለም፡፡ ጌታችን ጠባብ አስተሳሰብ ያለው አምላክ አይደለም እግዚአብሔር የመረጠው በኢየሱስ ያሉን ኃጢያተኞችን በሙሉ ነው፡፡*

**በዘፍጥረት 25፡ 21-26 ስለ ሁለቱ የይስሐቅ ልጆች ስለ ኤሳው እና ስለ ያዕቆብ እናነባለን ሁለቱም ልጆች ገና በእናታቸው ማህፀን እያሉ እግዚአብሔር ያዕቆብን መረጠው::**

**የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ያልተረዱት ይህንን በሁኔታ ላይ ላልተመሰረተ የምርጫ ፅንሰ ሐሳብ እንደ መሠረት ይወስዱታል ይህ ደግሞ የዕድልን አምላክ ከክርስትና ጋር እንደ መቀላቀል ነው::**

**እግዚአብሔር የመረጠን በኢየሱስ ክርስቶስ ሳይሆን «በሁኔታ ላይ ባልተመሰረተ ምርጫ» መሆኑን የምናምን ከሆነ እምነታችን የዕድል አምላክንና ጣዖታትን ከማምለክ ጋር የሚመሳሰል ነው እግዚአብሄር የዕድል አምላክ አይደለም በዕድል አምላክ የምናምን ከሆንን እግዚአብሄር ለእኛ ያለውን ዕቅድ እየካድንና በሰይጣን ወጥመድ ውስጥ እየወደቅን ነው::**

**ሰዎች ለእግዚአብሔር ፈቃድ የማይታዘዙ ከሆኑ እንደሚጠፉ እንስሶች ከመምሰል በምንም አይለዩም እኛ ምዕመናን እንስሶች ስላልሆንን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፈውን እውነት የሚያነቡና የሚያምኑ እውነተኛ ምዕመናን መሆን ይገባናል በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን እውነት አስቀድሞ አለማሰብ ራስን ለሰይጣን አሳልፎ መስጠት ነው::**

**እውነተኛ እምነት ይኖረን ዘንድ በመጀመሪያ በመፅሐፍ ቅዱስ የተፃፈውን እውነት መከተልና በክርስቶስ ዳግም የተወለዱትን የእነዚያን እምነት መከተል ነው::**

**የካልቪን እምነት ውሱን በሆነው ቤዛነት ላይ ያተኩራል ይህም የእግዚአብሄር ፍቅርና የጌታ ቤዛነት አንዳንዶችን እንደማይመለከት የሚጠቁም ነው ይህ እውነት ሊሆን ይችላልን?**

**መፅሐፍ ቅዱስ *«ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ እግዚአብሔር ደስ ይለዋል»* ይላል *(1ኛ ጢሞቲዎስ 2:4)* የንስሐ በረከት**

የሚደርሳቸው ጥቂቶች ብቻ ከሆኑ ብዙ አማኞች በኢየሱስ ማመናቸውን ይተዉ ነበር እንዲሁም ደግሞ በእንደዚህ አይነቱ ጠባብ-አምላክ ማመን የሚፈልግስ ማነው?

አምላካችን ጠባብ-አስተሳሰብ ያለው ላለመሆኑ ሙሉ በሙሉ እርግጠኞች ልንሆን ይገባናል እርሱ የፍቅር የእውነትና የፍትህ አምላክ ነው በኢየሱስ በማመን የውኃውና የመንፈሱ ወንጌል ከኃጢያታችን በሙሉ እንደሚያድነን ማመን አለብን ኢየሱስ ከውኃና ከመንፈሱ እንደገና የተወለዱትን ሁሉ የሚያድን አምላክ ነው፡፡

በካልቪን ትምህርት መሰረት አሥር ሰዎች ቢኖሩ የተወሰኑት በእግዚአብሔር ይድኑና የተቀሩት ደግሞ ወደ ገሃነም እሳት ይወረወራሉ ይህ ውሸት ነው፡፡


እግዚአብሔር የተወሰኑትን ወድዶ የተቀሩትን ይጠላል ማለት ሊሆን የማይችል ነገር ነው እስቲ እግዚአብሔርን ዛሬ ከመካከላችን በአካል እንደተገኘ አድርገን እናስብ በስተቀኝ በኩል የተቀመጡትን በሙሉ መርጦ በስተግራ የተቀመጡትን በሙሉ ወደ ገሃነም ቢያስገባቸው እኛ እርሱን በትክክል አምላክ ነው ብለን እንቀበለዋለን?

እነዚያ ወደ ገሃነም የተጣሉትስ አቤቱታቸውን ኣያሰሙምን? ሁሉም ፍጥረታት «እግዚአብሔር እንዴት እንደዚህ ያዳላል?» በማለት ይጮሁ ነበር እግዚአብሔር የሰውን ዘር ሁሉ በክርስቶስ ኢየሱስ ስለመረጠ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ ምርጫ ውሸት ነው፡፡

ስለሆነም ማንም በኢየሱስ ክርስቶስ ስም በእግዚአብሔር የሚጠራ ሁሉ የተመረጠ ነው በመቀጠልስ እግዚአብሔር እነማንን ነው የሚጠራው? እርሱ የሚጠራው ፃድቃንን ሳይሆን ኃጥኣንን ነው እግዚአብሔር ራሳቸውን ቅዱስ አድርገው የሚወስዱትን አይጠራም፡፡

የእግዚአብሔር የቤዛነት ረከት ለሐጢያተኞችና ለሲዖል ለተኮነኑት የተሰጠ ነው ምርጫ ማለት እግዚአብሔር ኃጥኣንን በሙሉ የእርሱ ቅዱሳን ልጆች ለማድረግ መጥራቱ ነው።

## እግዚአብሔር ፍፁም ነው




እግዚአብሔር ፍጹም ነው እርሱ የተመረጡትን ብቻ የሚወድ አምላክ አይደለም እርሱ ኃጢያተኞችን በክርስቶስ ስም ይጠራቸዋል በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና እርሱ በሚሰጠው የሐጢያቶች ይቅርታ አማካይነት ከሚገኘው ደህንነት ውጪ የእግዚአብሄርን ፍቅርና ደህንነት እንዴት እናውቃለን? እርሱን ቅንነት የጎደለው አምላክ አታድርጉት።

ኤፌሶን 1:3-5ን በማንበብ እስቲ ያልተረዳችሁትን ነገር ለመገንዘብ ሞክሩ- *«በክርስቶስ በሰማያዊ ስፍራ በመንፈሳዊ በረከት ሁሉ የባረከን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አማላክና አባት ይባረክ ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን»* የተሳተው ነገር ምንድን ነው? የተሳሳተው ቃል

«በኢየሱስ ክርስቶስ» የሚለው ነው በካልቪኒዝም ትምህርት ውስጥ ያለው በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተው ምርጫ ከመፅሐፍ ቅዱስ ቃሎች ጋር አይጣጣምም መፅሐፍ ቅዱስ *«ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን»* ይለናል፡፡

እግዚአብሔር የሰውን ዘር በሙሉ ከመንፈስና ከእውነት ይወለዱ በክርስቶስ መርጦዋቸዋል እነዚያ ኃጢያተኞች ሆነው የተወለዱትና ኃጢያትን ከማድረግ ውጭ ሌላ ምንም ማድረግ የማይችሉት የእርሱ ልጆች ይሆኑ ዘንድ መርጦኣቸዋል የሰውን ዘር በሙሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በዳኑትና በተመረጡት ዝርዝር ውስጥ አካቷል፡፡

በሁኔታ ላይ ባልተመሰረተ ምርጫ ላይ ሙጭጭ ያሉ በርካታ የቃለ እግዚአብሄር ምሁራን የተመረጡት አንዳንዶች ብቻ ናቸው በማለታቸው ብዙ ሰዎች በተሳሳቱ ትምህርቶች የተዛባ እምነት ውስጥ ተጠምደዋል እነዚህ ሐሰተኛ የቃለ እግዚአብሄር ምሁራን እግዚአብሄር አንዳንዶችን መርጦ ሌሎችን በሁኔታ ላይ ባልተመሰረተ ምርጫ አማካይነት አስወግዶዋቸዋል ይላሉ የቃሉ እውነት ግን እግዚአብሄር ሐጢያተኛን ሁሉ በኢየሱስ እንደመረጠ ይናገራል ብዙ ሰዎች አፈ ታሪክን በማመናቸው ለሐሰት ትምህርቶች ተጋልጠዋል፡፡

ሆኖም ግን እኛ እግዚአብሔር የሰውን ዘር በሙሉ ለማዳን መወሰኑንና የሐጢያት ስርየትም በኢየሱስ ለሚያን ለእያንዳንዱ ሰው መሰጠቱን መገንዘባችንን ማወቅ አለብን ይህንን በማድረግ ከሐጢያቶቻችን ሁሉ መዳን እንችላለን የእግዚአብሄር ሕዝብ ፃድቅ ሕዝብ እንሆናለን የዘላለም ሕይወትም ይኖረናል እግዚአብሄርም ፃድቅ ለመሆኑ እርግጠኞች እንሆናለን፡፡

# በያዕቆብና በኤሳው ታሪክ ውስጥ ያለው መንፈሳዊ ምርጫ

*እግዚአብሔር የመረጠው ማንን ነው? የተመረጡትን ብቻ ነውን?*

*አይደለም እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በሙሉ በክርስቶስ መርጧል ማንም በኢየሱስ የሚምንን በጥምቀቱም የተነሳ ኃጢያት የሌለበት ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተመረጠ ነው::*

በዘፍጥረት 25፡19-28 ላይ ኤሳውና ያዕቆብ በእናታቸው ማህፀን ውስጥ ሆነውም ይታገሉ ነበር እግዚአብሔር በዘፍጥረት 25፡23 ላይ እንደሚናገረውም *«ሁለት ወገኖች በማህፀንሽ ናቸው ሁለቱም ሕዝብ ከሆድሽ ይከፈላሉ ሕዝቡም ከሕዝቡ ይበረታል ታላቁም ለታናሹ ይገዛል::»*

ኃጢያተኞች እነዚህን ቃሎች በነገረ መለኮታዊ አስቀድሞ የመወሰንና የመለኮት ምርጫ ፅንሰ ሐሳብ በመለወጥ በኢየሱስ የሚያምኑ ብዙዎች መመረጥ አለመመረጣቸውን በሚመለከት ግራ እንዲያጋቡ አድርገዋቸዋል! የተመረጥን ነን ብለው ሲያስቡ እንደዳኑ ስለሚያስቡ ከውና ከመንፈስ ዳግም የመወለድ ፍላጎት አይኖራቸውም::

ይህ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የምርጫ ሃሳብ በኢየሱስ የሚያምኑ ብዙ ሰዎችን ከምህረት ጎዳና አስወጥቶአቸው ለሲዖል

እንዲኮነኑ አድርጓቸዋል ይህ እግዚአብሔርን ጨካኝ መስሎ እንዲታይ ማድረግም ነው::

በርካታ የነገረ መለኮት ምሁራን ከራሳቸው አስተሳሰቦች የመነጨ የሐሰት ትምህርት ስለሚያስተምሩ በኢየሱስ የሚያምኑ ብዙዎች የተመረጡ ስለመሆናቸው ወይም ቤዛነታቸው አስቀድሞ የተወሰነ ስለመሆኑ ግራ ተጋብተው ተቅበዝብዘዋል ምክንያቱም ስለመመረጣቸው እርግጠኞች አይደሉምና ነው::

ከያዕቆብና ከኤሳው እግዚአብሔር የመረጠው ማንን ነው? እርሱ ያዕቆብን በኢየሱስ ክርስቶስ መርጦታል በሮሜ 9:10-11 ላይ ገና ሳይወለዱ በአንድ ሰው ቢፀነሱም መልካም ወይም ክፉ ሳያደርጉ እግዚአብሄር ከወንድሙ ይልቅ ያዕቆብን እንደመረጠ ተነግሮዋል::

የእግዚአብሔር ተግባር ያዕቆብን መምረጥ ብቻ ነበር ይህ የሆነውም ከሠራው ስራ አንፃር ሳይሆን ከምርጫው ነው መፅሐፍ ቅዱስም ኢየሱስ የመጣው ህይወትን በቅድስና የሚመሩትን ሳይሆን ኃጢያተኞችን ለማዳን መሆኑን ይነግረናል::

ሰዎች በሙሉ የአዳም ዘሮች እስከሆኑ ድረስ ኃጥኣን ናቸው ዳዊት በእናቱ ማህፀን ከነበረበት ጊዜ አንስቶ ኃጢያተኛ ነበር በአመፃም ተወልዶዋል *«እነሆ በዓመፃ ተፀነስሁ እናቴም በኃጢያት ወለደችኝ::» (መዝሙር 51:5)*

ሰዎች ሁሉ ዘሮቻቸው ከሰሩዋቸው ሐጢያቶች የተነሳ ሐጢያተኞች ሆነው ይወለዳሉ ስለዚህ በዚህ አለም የተወለደ እያንዳንዱ ሰው ሐጢያተኛ ይሆናል እንደ ሐጢያተኛ ይንቀሳቀሳል የሐጢያትን ፍሬዎችም ያፈራል::

ገና ምንም ኃጢያት ያልሰራ ህፃን ቀድሞውኑ ሐጢያተኛ ነው የሐጢያትን ዘር ይዞ ተወልዶዋልና በልቡ ውስጥ ክፉ አሳቦች ዝሙት አመንዝራነትና ወንጀለኝነት አለበት የቅድመ

አያቶቹን ሐጢያቶች ይዞ ተወልዶዋል ሰዎች ሁሉ ገና ከመወለዳቸው በፊት እንኳን ሐጢያተኞች ናቸው::

እግዚአብሔር እኛን ደካሞች አድርጎ የፈጠረን ምክንያቱ ከዚህ እንደሚከተለው ነው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር ፍጥረት ነው ሆኖም ግን ጌታ እኛን ከኃጢያት በማዳን የእርሱ ልጆች ሊያደርገን እቅድ ነበረው አዳምንም ኃጢያት እንዲሰራ የፈቀደለት ለዚህ ነው::

ኃጢያተኞች በሆንን ጊዜ እግዚአብሄር ኢየሱስን ወደዚህ አለም በመላክ አንድያ ልጁን በጥምቀቱ አማካይነት የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ እንዲወስድ ፈቀደ::

የእግዚአብሔር ፍላጎት የሰው ልጆችን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ደሙ እንዲያምኑና በእምነታቸው ኃይልም የእርሱ ልጆች እንዲሆኑ ለማስቻል ነው ሐጢያትን በሙሉ በክርስቶስ እንደሚያስወግድ ተስፋ በመስጠት አዳም ኃጢያት እንዲሰራ ፈቅዶዋል::

ስህተት በሆነው ሃይማኖት የሚያምኑት «ያዕቆብና ኤሳውን ተመልከቱ አንዱን መርጦ አንዱን ደግሞ ትቶታል» ሲሉ ይደመጣሉ እግዚአብሔር ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አልመረጠኝም እርሱ የመረጠን በክርስቶስ ኢየሱስ ነው መመልከት ያለብን በመፅሐፍ ቅዱስ የተፃፈውን እውነት ብቻ ነው ሮሜ 9:10-12 ላይ እንዲህ ይላል *«ይህ ብቻ አይደለም ነገር ግን ርብቃ ደግሞ ከአንዱ ከአባታችን ከይስሐቅ በፀነሰች ጊዜ ልጆቹ ገና ሳይወለዱ በጎ ወይም ክፉ ምንም ሳያደርጉ ከጠሪው እንጂ ከሥራ ሳይሆን በምርጫ የሚሆን የእግዚአብሔር አሳብ ይጸና ዘንድ ለእርስዋ ለታናሹ ታላቁ ይገዛል ተባለለት::»*


እግዚአብሔር ያዕቆብን በኢየሱስ መርጦታል ያዕቆብ የኃጢያተኞችና ራሳቸውን እንደ ፃድቃን የማይቆጥሩ ሰዎች ምሳሌ ነበር በኤፌሶን 1:4 ላይ እግዚአብሔር በእርሱ

እንደመረጠን ይናገራል፡፡

እግዚአብሔር የጠራው ማንን ነው? እግዚብሔር ያዕቆብን የጠራው እርሱ በእግዚብሔር ፊት ኃጢያተኛና ፃድቅ ያልሆነ ነገር ግን በእግዚአብሔር የሚተማመን መሆኑን ያውቅ ስለነበር ነው እግዚአብሔር ያዕቆብን በልጁ በክርስቶስ ስም ከጠራው በኋላ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል በማመን አድኖት ልጁ አድርጎታል ስለሆነም እግዚአብሔር ያዕቆብን ጠርቶ በምህረቱ ባረከው፡፡

እርሱ ኃጢያተኞችን በኢየሱስ ምህረት ለመባረክና ለመቀደስ ይጠራቸዋል ይህ የእግዚአብሔር እቅድ ነው፡፡

## ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ የመመረጥ ሐሰተኛ ትምህርት




በቅርቡ አንድ በሁኔታ ላይ ባልተመሰረተ ምርጫ ላይ የተመረኮዘ ታሪክ ያለውን መፅሐፍ አንብቤአለሁ አንድ ወጣት ሰው ህልም ያልማል በሕልሙም አንድ ሴት ተገልጣለት ወደ አንድ ቦታ እንዲከተላት ትጠይቀዋለች እርሱም ይከተላታል በመቀጠልም ይህች አሮጊት ሴትዮ ወጣቱ በእግዚአብሔር እንደተመረጠ ትነግረዋለች፡፡

በእግዚአብሔር እንኳን ሳያምን እንዴት እግዚአብሔር

ሊመርጠው እንደቻለ አሮጊቷን ይጠይቃታል አሮጊቷም ታማኝ ባይሆንም እግዚአብሄር ያለ ምንም ቅድመ ሁኔታ እንደመረጠው ትነግረዋለች::

ይህ እውነት አይደለም እግዚብሔር እንዴት ሆነ ብሎ አንዳንድ ሰዎችን ለሲዖል ሲኮንን ሌሎችን ለደህንነት ይመርጣል? እግዚአብሄር እያንዳንዱን ሰው በኢየሱስ በኩል መርጦታል::

ኢየሱስን የሚያገልል የነገረ መለኮት የምርጫ ፅንሰ ሐሳብ ውሸት ነው እውነት አይደለም ነገር ግን አንዳንድ የነገረ መለኮት ምሁራን እግዚአብሄር የመረጠው አንዳንዶቻችንን ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ ያ እውነት አይደለም እግዚአብሄር በኢየሱስ በኩል እንዳንዱን ሰው ማዳን ይፈልጋል የማይድኑት በኢየሱስ በኩል በሆነው የውሃና የመንፈስ ቤዛነት የማያምኑት ብቻ ናቸው::

እግዚአብሔር የሰው ዘር በሙሉ በልጁ በኢየሱስ በኩል ለደህንነት ወስኖታል አለምን ከመፍጠሩም በፊት ልጆቹ ሊያድርገን አቅዶዋል እርሱ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት በኩል የሰውን ዘር ከአለም ሐጢያቶች ሁሉ ለማዳን አቅዶዋል ይህ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተፃፈ እውነት ነው::

በክርስቶስ ዳግም የተወለዱ ፃድቃን ምርጦች ናቸው ነገር ግን የነገረ መለኮት ምሁራን እግዚአብሄር የመረጠው አንዳንዶቻችንን ብቻ ነው በማለት ሙጭጭ ይላሉ ለምሳሌ የቡዲስት መነኮሳት እግዚአብሄር ካልመረጣቸው መካከል ናቸው ይላሉ ነገር ግን እግዚአብሄር እነርሱንም ደግሞ በኢየሱስ በኩል መርጦዋቸዋል::

እግዚአብሔር የሚመርጠው ያለምንም መስፈርት ማንንም ከሆነ እኛም ወንጌልን መስበክ ባላስፈለገን ነበር እግዚአብሔር ማንንም ያለ ክርስቶስ የሆነውንም እንኳን የሚመርጥ ከሆነ

ኃጢያተኞችም በክርስቶስ ማመን አያስፈልጋቸውም ነበር ታዲያ የፍቅር፣ የእውነትና የደህንነት ቃሎች እንዴት ሊፈፀሙ ይችላሉ?

የእግዚአብሔር አገልጋዮችስ ወንጌልን በዚህ ምድር ላይ ለመስበክ የሚያስፈልጋቸው አንዳች ምክንያት ይኖራቸው ነበርን? እግዚአብሔርስ በኢየሱስ የማያምኑትንም ጭምር የሚመርጥ ከሆነ፣ ይህ ወንጌል ትርጉም የለሽ አይሆንምን?

እግዚአብሔር ያዕቆብን በኢየሱስ የመረጠበት ምክንያትና ያዕቆብን ወድዶ ኤሳውን የጠላበት ምክንያት ከመፈጠራቸው በፊት ሲወለዱ ያዕቆብ በኢየሱስ እንደሚያምንና ኤሳው ግን በኢየሱስ እንደማያምን ያውቅ ስለነበር ነው::

እግዚአብሔር ያዕቆብን የወደደው ለምንድን ነው? ያዕቆብ ኃጢያተኛ ስለነበርና ከንቱነቱን ስላወቀ ነው ስለዚህ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያተኛ መሆኑን አምኖ የአምላክን ፀጋ ለመነ እግዚአብሄር ያዕቆብን ያዳነው ለዚህ ነው::

ኤሳው ግን በጌታ ከመደገፍ ይልቅ ይበልጥ በራሱ ተደገፈ የእግዚአብሄርንም ጸጋ አልተራበም ስለዚህ እግዚአብሄር ያዕቆብን እንደወደደና ኤሳውን እንደጠላ ተናገረ ይህ የእውነት ቃል ነው::

እግዚአብሔር ሁላችንንም በኢየሱስ ደህንነትን እናገኝ ዘንድመርጦናል ኃጢያተኞች በሙሉ ማድረግ የሚጠበቅባቸው በኢየሱስ ማመን ብቻ ነው በዚህም የእግዚአብሔር እውነትና ፍትህ በልባቸው ይሰፍናል እኛ ኃጢያተኞችም ማድረግ የምንችለው ብቸኛ ነገር ቢኖር በኢየሱስ ማመንና መዳን ብቻ ነው ማድረግ ያለብን ነገር ቢኖር በኢየሱስ በኩል በመዳናችን ማመን ነው::

# ሐሰተኛው ደረጃ በደረጃ የመቀደስ ፅንሰ ሐሳብ

*ኃጢያተኛ ቀስ በቀስ ቅዱስ ሊሆን መቻሉ እውነት ነውን?*

*አይደለም ይህ አይቻልም እግዚአብሔር ኃጢያተኞችን በሙሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በኢየሱስ ጥምቀትና መንፈስ ከኃጢያት ነፃ አድርጓቸዋል፡፡*

ሰይጣን ሐጢያተኞች ከሐጢያቶቻቸው መዳን እንዳይችሉ ደረጃ በደረጃ በመቀደስ ፅንሰ ሐሳብ አታሎዋቸዋል ደረጃ በደረጃ መቀደስ ማለት ሐጢያተኞች በኢየሱስ ካመኑ በኋላ ቅዱስ የሚሆኑት ቀስ በቀስ ነው ማለት ነው፡፡

ፅንሰ ሐሳቡ እንደሚከተለው ነው ሐጢያተኞች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፃድቅ አይሆኑም ነገር ግን በኢየሱስ ሲያምኑ የሚድኑት ከአዳም ሐጢያት ብቻ ነው በተግባር የተሰሩ ሐጢያቶች የሚገዱት በየቀኑ የንስሐ ፀሎትን በማድረግ ነው ሰዎችም ቀስ በቀስ ይቀደሳሉ፡፡

የዚህ ፅንሰ ሐሳብ ፋይዳ ደረጃ በደረጃ የመቀደስ ጉዳይ ነው አንድ ሰው በኢየሱስ ማመኑና ቀስ በቀስ ቅዱስ ክርስቲያን መሆኑ ትልቅ ነገር ይመስላል ይህ ፅንሰ ሐሳብ በርካታ ክርስቲያኖችን ለአመታት በማሳት አዘናግቶዋቸዋል በክርስትና ውስጥ ከአንተ ይበልጥ ቅዱስ ነኝ የሚሉ ክርስቲያኖች የበዙት ለዚህ ነው፡፡

አንድ ቀን እንደሚለወጡና ሐጢያት መስራት

እንደሚያቆሙ ያስባሉ ነገር ግን ሕይወታቸውን ሐጢያተኞች ሆነው ይኖሩታል ከሞቱ በኋላም በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች ሆነው ይፈረድባቸዋል።

በሮሜ 8:30 ላይ ያለውን የእግዚአብሔርን እውነተኛ ቃል እናንብብ *«አስቀድሞም የወሰናቸውን እነዚህን ደግሞ ጠራቸው የጠራቸውን እነዚህን ደግሞ አፀደቃቸው ያፀደቃቸውን እነዚህን ደግሞ አከበራቸው»*

እንዲሁም ቁጥር 29 ደግሞ *«ልጁ በብዙ ወንድሞች መካከል በኩር ይሆን ዘንድ አስቀድሞ ያወቃቸው የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ደግሞ ወስኖአልና»* ይላል በመጀመሪያ እይታ ፃድቅ ለመሆን ደረጃዎች ያሉ ይመስላል ነገር ግን ቃሉ ለአንዴና ለመጨረሻ እንደተሰጠ ይነግረናል።

*«የጠራቸውን ደግሞ አፀደቃቸው»* ኢየሱስ ኃጢያተኞችን ጠርቶ በዮርዳኖስ ባደረገው ጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ አፅድቆዋቸዋል።

ስለዚህ ቤዛነት ያመነ ሰው የከበረ የእግዚአብሄር ልጅ ይሆናል ሐጢያተኞችን መቤዠትና በዚህ ስም እነርሱን ማክበር የእግዚአብሄር ጸጋ ሥራ ነው።

ይህ እግዚአብሔር የሚነግረን ነገር ነው ሆኖም ግን አንዳንድ ክርስቲያኖች ሮሜ 8:30ን እንድንመለከት ይነግሩናል «ለመቀደስ ደረጃዎች አሉ ያ ማለት ቀስ በቀስ እንለወጣለንማለት አይደለምን? የተታለሉት በዚህ መንገድ ነው ሐጢያተኛ በጊዜ ሂደት ውስጥ ፃድቅ እንደሚሆን ለሰዎች በወደፊት የግስ ጊዜ ይነግሩዋቸዋል።

ሆኖም ግን መፅሐፍ ቅዱስ የሚነገረን በሐላፊ ጊዜ ነው እኛ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፀድቀናል ይህ ደረጃ በደረጃ ከመቀደስ ፅንሰ ሐሳብ ፈፅሞ የተለየ ነው።


ደረጃ በደረጃ የመቀደሱ ፅንሰ ሐሳብ በኢየሱስ ስናምን

ይቅር የተባልነው የአዳምን ሐጢያት ብቻ ነው ይላል ይህ የሚጠቁመው በእግዚአብሄር ፊት ስንቆም ፃድቅ እንሆን ዘንድ ሐይማኖታዊ ሕይወትን መኖርና በየቀኑም ከሐጢያቶቻችን ንስሐ መግባት ያለብን መሆኑን ነው::

ብዙ ሰዎችም በዚህ ፅንሰ ሐሳብ ስለሚያምኑ በኢየሱስ ካመኑ በኋላም አሁንም ድረስ ኃጢያተኞች ናቸው ደረጃ በደረጃ የመቀደስ ፅንሰ ሐሳብ እውነት ያልሆነው ለዚህ ነው::

መፅሐፍ ቅዱስ ቅዱሳንና የእግዚአብሔር ልጆች ልንሆን የምንችለው በእምነት መሆኑን ይነግረናል ልክ ሕፃናት ወደዚህች ምድር በሚመጡበት አኳኋን የእግዚአብሔር ልጆችም በኢየሱስ ምህረት ሲያምኑና ምህረትን ሲያገኙ ቅዱሳን ይሆናሉ ሐሰተኛው ደረጃ በደረጃ የመቀደስ ፅንሰ ሐሳብ ከውሸት ፈለቀ ነው::

## ከኃጢያቶች ሁሉ የተሟላ መዳን



ሮሜ 8:1-2 እንዲህ ይናገራል *«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና»* ይህ እግዚአብሔር ኃጢያተኞችን በሙሉ ቅዱስ እንዳደረጋቸውና ወደ ኢየሱስ የመጡትንም ከሐጢትና ከሞት እንዳዳናቸው ይነግረናል፡፡

መፅሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን 9:12 ላይ ስለ ሙሉ ምህረት ይነግረናል *«የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስነት በገዛ ደሙ ገባ እንጂ በፍየሎችና በጥጆች ደም አይደለም» ይህ ማለት እኛ በኢየሱስ ያመንን ቤዛነትን አግኝተን ሰማይ ለመግባት ተፈቅዶልናል ማለት ነው፡፡*

እኛ በክርስቶስ ኢየሱስ የውኃና የመንፈስ ቤዛነት ወንጌልን ሰምተን ያመንን ለሐጢያቶቻችን ሁሉ ይቅርታን አግኝተናል ነገር ግን ይቅርታን ያገኙት ለአዳም ሐጢያት ብቻ መሆኑን የሚያምኑ ሐጢያተኞች በሙሉ ሊድኑ አይችሉም በኢየሱስ ካመኑ በኋላ ከፈፀሙዋቸው ሐጢያቶች ለመቀደስ ሲሉ በየቀኑ ንስሐ መግባት እንዳለባቸው ይሰማቸዋል፡፡

የተዛባው እምነታቸው ወደ ሲዖል ይነዳቸዋል የተሳሳቱት አመኔታዎቻቸውም ራሳቸውን ከበደሎቻቸው ሁሉ ነፃ ለማውጣት በየቀኑ ንስሐ እንዲገቡ ያደርጋቸዋል ከሲዖል የሚያድነን እውነተኛ እምነት ይህ አይደለም፡፡

በኢየሱስ አምነው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ቤዛነትን አግኝተው ቢሆን ኖሮ ፃድቃንና የእግዚአብሄር ልጆች ይሆኑ ነበር እወነተኛ ቤዛነት ምዕመናንን ፃድቃን በማድረግ ለአንዴና ለመጨረሻ ወደ እግዚአብሄር ልጅነት ይለውጣቸዋል፡፡

ምንም እንኳን አማኞች ከኃጢያቶቻቸው ለዘላለም የነፁ ቢሆኑም ስጋቸው ግን እስከሚሞቱበት ቀን ድረስ ኃጢያትን ከመስራት አይታቀብም ሆኖም ግን ልባቸው በእግዚአብሔር

ቅድስና የተሞላ ነው ይህንን እውነት መቼም ቢሆን ልናዛበው አይገባንም፡፡

መፅሐፍ ቅዱስ በወንጌል ስናምን እንደተቀደስንና እንደፀደቅን ይነግረናል፡፡

እውነተኛውን ወንጌል ለማወቅ ዕብራውያን 10:9-14ን እንመልከት *«ቀጥሎ እነሆ አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ ሁለተኛውንም ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል ሊቀ ካህናትም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢያትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መስዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሟል እርሱ ግን ስለ ኃጢኣት አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደ ፊት ይጠብቃል አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጎአቸዋልና፡፡»*

*«በዚህም ፍቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ ፈፅሞ በማቅረብ ተቀድሰናል»* ይህ የተፃፈው የአሁን ጊዜን አመልካች በሆነ ግስ እንጂ የወደፊት ጊዜን አመልካች በሆነ ግስ አለመሆኑን ልብ በሉ፡፡

ሙሉ በሙሉ ለመቀደስ አንድ ሰው ኢየሱስ በሰጠን የውኃና የመንፈስ ወንጌል ማመን አለበት፡፡

# ኢየሱስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘላለማዊ ቤዛነትን ሰጥቷል

*ሰው ሁልጊዜ እንዲደሰት የተነገረው ለምንድነው? (1ኛ ሰሎንቄ 5:16)*

*ምክንያቱም ኢየሱስ ኃጢያቱን በሙሉ ስላስወገደለት በእርሱ ፊት ከመደሰትና ከማመስገን በስተቀር ምንም ሌላ ነገር ማድረግ ስለማይችል ነው::*

በኢየሱስ ዘላለማዊ ምህረት የምናምን ከሆነ ሁላችንም በአንድ ጊዜ ቅዱሳን እንሆናለን መፅሐፍ ቅዱስ እንደሚለውም *«በሁሉ አመስግኑ ይህ የእግዚአብሔር ፍቃድ በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ እናንተ ነውና::» (1ኛ ተሰሎንቄ 5:16-18)*

ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ ሁልጊዜ መደሰት የምንችለው እንዴት ነው? እነዚያ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ዘላለማዊ ቤዛነትን ያገኙ ያለ ልክ ሊደሰቱ ይችላሉ ምክንያቱም ከሐጢያት ነፃ ሆነዋል ኢየሱስ በዮርዳኖስ ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ እንደወሰደ በማወቃቸው ሰላም አግኝተዋል በእርሱ ፊትም ትሁታን ሆነዋል ለፀጋውም አመስጋኞች ናቸው ከዚህ የተነሳ ያለ ማቋረጥ ይደሰታሉ::

*«ዓመፃቸው የተሰረየላቸው ኃጢአታቸውም የተከደነላቸው ብፁኣን ናቸው ጌታ ኃጢአቱን የማይቁርጥበት ሰው ብፁዕ ነው» (ሮሜ 4:7)* ይህ ማለት ሐጢያቶቻችን ገናም በልባችን ውስጥ እያሉ ተሸፈነዋል ማለት አይደለም ልባችን ነፅቷል ኢየሱስ

ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ፈፅሞ አስወግዶ ለአንዴና ለመጨረሻ አድኖናል::

ይህ ዘላለማዊ ቤዛነት በአዲስ ኪዳንም ተጠቅሷል ኢየሱስ በሚጠመቅበት ጊዜ *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና»* አለ:: *(ማቴዎስ 3:15)*

በብሉይ ኪዳን ጊዜ በጎች ወይም ደግሞ ፍየሎች የሰውን ኃጢያት በእጆች መጫን አማካይነት ይወስዱ እንደነበረ ሁሉ ኢየሱስም የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ የሰውን ዘር እጅግ ተገቢና ገጣሚ በሆነ መንገድ አንፅቶታል::

ኢየሱስ እንዲህ ብሏል *«ፅድቅን መፈጸም ይገባናል»* ኢየሱስ እጅግ ተገቢ በሆነ መንገድ ተጠምቆ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ በመውሰድ አድኖናል::

በማቴዎስ 3:15 ላይ ኢየሱስ የዓለምን ኃጢያቶች በሙሉ መውሰዱ በግልፅ ተቀምጦኣል የእግዚአብሔር ፍትህ ተጠናቀቀ ይህንን ዘላለማዊ ቤዛነት ለማስተዋል መሞከር አይኖርብንም የእርሱ የደህንነት ቃል አድርገን ልንወስደው ይገባናል *«መተላለፉ የቀረችለት ኃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው::» (መዝሙር 32:1)*

ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ በዮርዳኖስ ወንዝ በተጠመቀ ጊዜ የሰው ልጅን የልብና የስጋ ኃጢያት በሙሉ አንጽቷል በዚህ በተበላሸና በዘቀጠ አለም ውስጥ የምንሰራውንም ኃጢያት ጭምር አፅድቶልናል ኃጢያቶቻችንንም በሙሉ ከወሰደልን በኋላ በመስቀል ላይ በመሞት ነፃ አውጥቶናል::


በዚህ የኃጢያት ቤዛነት የሚያምን ማንኛውም ሰው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ፃድቅና ያለ ነቀፋ ሊሆን ይችላል ኢየሱስ ለዘላለም ስለሚኖር በክርስቶስ ቤዛነት የሚያምን ማንኛ ውም ሰው በፃድቅነቱ ይኖራል::

አሁን እኛም በእግዚአብሔር ፊት ቆመን በሙሉ ልብ

«እንደምን ነህ ጌታዬ? በአንተ አንድያ ልጅ በክርስቶስ ኢየሱስ አምናለሁ እኔም ያንተ ልጅ ነኝ ይህን ያገኘሁት በስራዬ ሳይሆን በኢየሱስ የውኃና የመንፈስ ወንጌል ላይ ባለኝ እምነትና ዳግም ውልደት ነው ከዓለም ኃጢያት በሙሉ አድነኸኛል *«ፅድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናል» (ማቴዎስ 3፡15)* ባልከውም አምናለሁ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉም እኔ ልጅህ ለመሆን በቅቻለሁ ለዚህም በጣም አመሰግንሃለሁ፡፡»

ኢየሱስ ሐጢያቶቻችሁን ሁሉ አስወግዶዋልን? ለኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ለሆነው ሞቱ ምስጋና ይድረሰውና ሐጢያተኞች በዚህ በማመን ብቻ ሐጢያተኞች ሊቀደሱ ይችላሉ፡፡

## በኢየሱስ ጥምቀትና በቤዛነት መካከል ያለው ግንኙነት




በኢየሱስ እያመነና በቤተክርስቲያን ውስጥም «አቤቱ ባለፈው ሳምንት የሰራኋቸውን ሐጢያቶች እባክህ ይቅር በለኝ ባለፉት ሦስት ቀናቶች የሰራኋቸውን ሐጢያቶች ይቅር በለኝ

ጌታ ሆይ ዛሬ የሰራኋቸውንም ሐጢያቶች ይቅር በለኝ በኢየሱስ አምናለሁ» ብሎ እየፀለየ ሐጢያተኛ ሆኖ የሚኖር ሰውን አስቡ::

ይህ ሰው በየቀኑ በሚያደርገው ፀሎት ኃጢያቱ ሁሉ ይቅር ተባለለት ብለን እናስብ በኋላ ግን ወደ ቀን ተቀን ህይወቱ ተመልሶ እንደገና ሐጢያትን ይሰራል እንደገናም ሐጢያተኛ ይሆናል:: ሲመለስ አሁንም ሌላ ኃጢያትን ወደ መስራት ይመለሳል::

ኢየሱስ የእግዚብሔር በግ ሆኖ በመምጣት የዓለምን ኃጢያት በሙሉ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ በመሰቀሉ አስወግዷል ለመዳንም ኃጢያተኞች ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ማመን አለባቸው::

ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያትን በሙሉ አስወግዶ የእግዚአብሄርን ፅድቅ ፈፅሞዋል የአለም ሐጢያቶች በሙሉ ተወግደዋል በዚህ እውነት ያመነ ሁሉ ነፃ ወጥቷል በማቴዎስ 3:13-17 ላይ እንደተፃፈው ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ የተጠመቀውና የምዕመናን ሁሉ መድህን የሆነው «ለዚህ» ነው::

እውነተኛው ወንጌል ኢየሱስ የዓለምን ኃጢያት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ማስወገዱን ይናገራል በተቃራኒው የውሸት ኃይማኖቶች ደግሞ የምንድነው በየቀኑ በምናደርገው ፀሎት መሆኑን ይነግሩናል ማመን ያለብን የትኛውን ነው? የዳንነው ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ነው፣ ወይስ በየቀኑ ነው የምንድነው?

ኢየሱስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዳዳነን ግልፅ ነው እውነተኛው አመኔታ ለአንዴና ለመጨረሻ በተሰጠው የውኃና የመንፈስ ቤዛነት ማመን ነው በየቀኑ መዳን እንዳለብን የሚያምኑት መቼም ቢሆን ሊድኑ አይችሉም::

እውነተኛ ቤዛነት ሊመጣ የሚችለው ኢየሱስ በጥምቀቱና

በመስቀል ላይ ሞቱ ለአንዴና ለመጨረሻ እንዳዳነን ከማመን መሆኑን ማወቅ አለባቸው ከእኛ የሚጠበቀው ነገር እግዚአብሄርን ማመስገንና በዚህ በእውነተኛው ወንጌል ማመን ነው::

ሆኖም ግን በእምነታቸው ትክክለኛውን ምሪት ያልያዙት ሰዎች የዳኑት ከአዳም ሐጢያትብቻ እንደሆነ ያምናሉ በዚህም እኛ ሁልጊዜ መዳን እንዳለብንና በየቀኑም «ደረጃ በደረጃ» ቅዱስ እንደምንሆን ይሰብካሉ ይህ ሙሉ በሙሉ ስህተት ነው::

የኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ መሞቱ ለሰው ልጆች ዘላለማዊ ደህምነትንና ይቅርታን አስገኟል ይህ እውነት ነው እኛ ከኃጢያት እንድን ዘንድ ኃጢያቶቻችን በሙሉ በጥምቀቱ አማካኝነት ወደ ኢየሱስ መተላለፍና እርሱም ደግሞ በመስቀል ላይ ስለኛ ኃጢያት ፍርድን በመቀበል መሞት ነበረበት::

ሐጢያት ከሰራን በኋላ «ይቅር በለኝ» ማለት ከእግዚአብሄር ፍትህ ጋር አይጣጣምም የእግዚብሔር ሕግ የኃጢያት ደመወዝ ሞት መሆኑን ይናገራል እግዚብሄርም ደግሞ ፍፁምና ቅዱስ መሆኑን በትክክል መገንዘብ አለብን::

ኃጢያት ከሰሩ በኋላ «አዝናለሁ እባክህ ይቅር በለኝ» ብለው ወደ እግዚአብሄር የሚፀልዩ የእግዚአብሄርን ፍትህ አያውቁም እነርሱ ይቅርታን ለማግኘት ቢጸልዩም አላማቸው ግን ሕሊናቸውን ማረጋጋት ነው አንድ ሰው በየቀኑ ለሚሰራው ጥፋት በተደጋጋሚ ይቅርታ መጠየቁ ትክክል ነውን? ብቸኛው የመዳኛው መንገድ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ደም ማመን ነው ይህንን ከልባችን ልናምነው ይገባናል የእግዚአብሔርን ፍርድ ማስወገድ የምንችልበት ብቸኛው መንገድ ይህ ነው::

ከኃጢያት ነፃ ስለ መውጣት አብዝተን እናስብ በዕብራውያን 9:22 ላይ እንዲህ ተፅፎዋል *«እንደ ሕጉም*

*ከጥቂቶች በስተቀር ሁሉም በደም ይነፃል ደምም ሳይፈስ ስርየት የለም::»*

በእግዚአብሔር ፍፁም ሕግ መሰረትም፣ ኃጢያት መንፃት ያለበት በደም ነው ደም ሳይፈስስ ስርየት የለም ይህ የእግዚአብሔር ፍፁም ሕግ ነው የኃጢያት ደሞዝ ሳይከፈል ፈፅሞ ስርየት ሊኖር አይችልም::

የእግዚአብሔር ሕግ ፍፁም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ በመጥምቁ ዮሐንስ የተጠመቀውና በመስቀል ላይም ደሙን ያፈሰሰልን እኛን ኃጢያተኞቹን ሊያነፃን ነው መተላለፋችንን በሙሉ በጥምቀቱ ከወሰደ በኋላ ለእነርሱም ፍርድን ለመቀበል በመስቀል ላይ ደምቶልናል የኃጢያቶቻችንን ደሞዝ በእኛ ፈንታ እርሱ ከፍሎልናል::

*ቤዛነት ለአንዴና ለመጨረሻ ተሰጥቷል ወይስ በየቀኑ ይሰጣል?*

*ለአንዴና ለመጨረሻ ነው ኢየሱስ የዓለምን ኃጢያተኞች ኃጢያት በሙሉ በጥምቀቱ ወስዷል::*

በማቴዎስ 3:15 ላይ ኢየሱስ በጣም ትክክል በሆነው ሥርዓት ሲጠመቅ የዓለምን ኃጢያቶች በሙሉ አንጽቷል እንዲሁም ደግሞ በመስቀል ላይ በመሞት እኛን ከዓለም ኃጢያቶች በሙሉ አንፅቶናል::

በየቀኑ ይቅርታን መጠየቅ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶ እንደገና እንዲሞት መጠየቅ ነው የእግዚአብሄርን ፃድቅ ሕግ

በትክክል መረዳት ይኖርብናል ኢየሱስ እኛን ከኃጢያት ለማንፃት በተደጋጋሚ መሞት የለበትም።

እግዚአብሔር በኢየሱስ አምነው ለሰሩዋቸው ሐጢያቶች ደጋግመው ይቅርታ የሚጠይቁትን እጅግ ስዶች እንደሆኑ አድርጎ ይቆጥራቸዋል «እነዚህ ስድ ሞኞች! ልጄ ኢየሱስ ለሁለተኛ ጊዜ እንዲጠመቅና እንደገና በመስቀል ላይ እንዲሞት እየጠየቁ ነው! ምኢየሱስ ቤዛነት እያመኑ ገናም ራሳቸውን ሐጢያተኞች ብለው ይጠራሉ! ፃድቅ በሆነው ሕጌ እፈርድባቸውና ሁሉንም ወደሚነደው የሲዖል ጉድጓድ እልካቸዋለሁ ብቸኛ ልጃችሁን ዳግም ለመግደል ፍቃደኞች ትሆናላችሁን? እናንተም በራሳችሁ ኃጢያት የተነሳ ልጄን ለሁለተኛ ጊዜ እንድገድለው እየጠየቃችሁኝ ነው የምትሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በተደጋጋሚ ይቅር እንድል በመጠየቅ ቁጣዬን አትቀቀስቅሱብኝ በውሃውና በመንፈሱ የቤዛነት ወንጌል ብቻ እመኑ።»

ኢየሱስ ኃጢያተኛ ሆነው ለቀሩት ሲነግራቸው እውነተኛ ወንጌል ወደሚሰበክበት ቤተክርስቲያን መሄድና የሐሰት እምነትን ትተው ሐሰትን በእምነት በማሸነፍ ቤዛነትን መቀበል እንደሚገባቸው ነግሮዋቸዋል።

አሁን እናንተም ከልባችሁ በማመን የምትድኑበት ጊዜ ነው ታምናላችሁን?

# በእውነት ላይ ሳይሆን በሥራዎች ላይ የተመሰረተ እምነት ውጤቱ

*ብዙ ክርስትያኖች አንድ ወጥ የሆነ የታመነ ሕይወት መምራት ለምን ተሳናቸው?*

*ምክንያቱም በሥራቸው ስለሚተማመኑ ነው::*

በኢየሱስ የሚያምኑ ነገር ግን ነፃ ያልወጡ ሐጢያተኞች እንኳን ከ3-5 አመታቶች ብሩህ ሆነው ሊያበሩ ይችላሉ በመጀመሪያ ግለት ይታይባቸዋል ነገር ግን እምነታቸው ከጊዜ ጋር ይደበዝዛል በኢየሱስ የምታምኑት በስራዎቻችሁ አማካይነት ከሆነ ግለታችሁ ፈጥኖ ይጠፋል።

የታወረ ሊያይ አይችልም ስለዚህ በሌሎች ስሜቶቻቸው ላይ ይደገፉና በዚህ መንገድ እውቀትን ያከማቻሉ አይኖቻቸው እንባን ሲያቀሩ ይህን የኃጢያታቸው ማስተሰረያ አድርገው በስህተት ይወስዱታል እውነተኛ ስርየት ስሜት አይደለም።

በመንፈስ የታወሩት የተለያዩ ታላላቅ መንፈሳዊ ጉባኤዎችን በመካፈል የመጀመሪያውን ፍቅራቸውን ለመመለስ ያስባሉ ሆኖም ግን ስሜታቸውን ሊመልሱት አይችሉም የኃጢያትን ስርየት ማግኘት እንዲሁ የሚቻል ነገር አይደለም ከመጀመሪያው ጀምሮ በትክክል አምነው ከነበረ ቀናት በተቆጠሩ ጊዜ በረከቱ ይበልጥ ፊታቸውን ባበራው ነበር።

ነገር ግን የውሸት ስርየት በመጀመሪያው ላይ ደምቆ

ከቆይታ ጋር የሚደበዝዝ ነው የግለቱ ምዳድ ፈፅሞ ይበርዳል ምክንያቱም በመንፈሳዊ ሁኔታቸው የታወሩ ከመጀመሪያውም እውነተኛ የሆነውን ወንጌል መስማት ተስኖዋቸዋልና፡፡

ግብዝ የሆኑ ፀሐፍትና ፈሪሳውያን ቅዱሳት መፃህፍቶችን በእጆቻቸው ይይዛሉ የጌታን ፀሎትና የሐዋርያትን የእምነት ስርአተ ደንብ ያነበንባሉ ሁልጊዜም ይጸልያሉ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሹመትን ያገኛሉ በስሜትም ይሞላሉ ነገር ግን ሐጢያቶቻቸው ይከማቻሉ በመጨረሻ እግዚአብሄር ያባርራቸዋል በስተ ውጭ በሐይማኖታዊ ግለት ኖራ ተለስነዋል በስተ ውስጥ ግን ልቦናቸው በሐጢያት በስብሶዋል ይህ በእውነት ላይ የተመሰረተ እምነት ውጤት ሳይሆን በስራዎች ላይ የተመሠረተ ሐይማኖት ውጤት ነው፡፡

## በእምነት ፃድቃን እንሆናለን

*ለዚህ አለም ኃጢያት ሁሉ የሆነው ቤዛነት አስቀድሞ ተፈፅሞዋልን?*

*አዎን፡፡ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ሞቱ የኃጢያት ቤዛነት ተፈፅሞዋል፡፡*

ዕብራውያን 10:16-18ን እናንብብ *«ከዚያ ወራት በኋላ ከእርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እፅፈዋለሁ ብሎ ከተናገረ በኋላ*

*ኃጢያታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል። የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለኃጢያት ማቅረብ የለም።»*

አሁን እኛ በኢየሱስ የጥምቀት ውኃና በመስቀሉ ላይ ደሙ ከኃጢያታችን በሙሉ ነፅተናል ከዚህ በኋላም ለኃጢያት ስርየት የምንለምነው ነገር የለም በመጀመሪያ ላይ ስትሰሙት የሚታመን ነገር ላይመስላችሁ ይችላል ሆኖም ግን ይህ ከመፅሐፍ ቅዱስ ቃሎች ጋር የሚስማማ ነው እነዚህ የሰው ቃሎች ናቸውን? መፅሐፍ ቅዱስ ሁሉም ነገር የሚለካበት መለኪያና ቱምቢ ነው።

*«ከዚያ ወራት በኋላ ከእርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ፤ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እፅፈዋለሁ»* ምህረትን ካገኛችሁ በኋላ የሚሰማችሁ ምንድን ነው? አሁን ልባችሁ ከኃጢያት የፀዳ ነው ስለዚህም የመታደስ ስሜት ይሰማችኋል አሁን እናንተ ቅዱሳን ሆናችኋል ስለሆነም በብርሃን ለመኖር ትችላላችሁ።

እንዲሁም በዕብራውያን 10:17 ላይ ጌታ እንዲህ ይላል *«ኃጢያታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል»* እርሱ ቤዛነትን ያገኙትን ሐጢያቶችና አመፃች እንደማያስታውስ ነግሮናል ለምን? ምክንያቱም ኢየሱስ እጅግ ተስማሚ በሆነ መንገድ «ለዚሁ» ተጠምቋልና ኢየሱስ ሐጢያትን በሙሉ ከወሰደ በኋላ በእርሱ በሚያምኑት ምትክ ተኮነነ።

አሁን እርሱ ለኃጢያቶቻችን በሙሉ ዋጋ ስለከፈለ ሐጢያቶቻችንን ልናስታውስ ብንችልም ስለ እነርሱ የጥፋተኝነት ስሜት አይሰማንም ዳግመኛ ለሐጢያቶቻችን አንሞትም ምክንያቱም ኢየሱስ ሐጢያትን ሁሉ አስወግዶዋል ስለ እኛም በመስቀል ላይ ደምቷል።

*ዕብራውያን 10:18 ላይ እንዲህ ይላል «የእነዚህም ስርየት*

*ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢያት ማቅረብ የለም»* ይህም ማለት እርሱ የአለምን ኃጢያቶች በሙሉ ደምስሶዋል ማለት ነው በኢየሱስ ዳግም የተወለዱትም ዳግመኛ ምንም አይነት የሐጢያት ቁርባን ማቅረብ አያስፈልጋቸውም ማለትም ጭምር ነው::

«ኦ አምላኬ! እባክህን ይቅር በለኝ በኢየሱስ ባምንም አሁንም ድረስ የምኖረው በምስቅልቅል ውስጥ ነው ምክንያቱም ገና አልተዋጀሁም ክርስትያን ነኝ አእምሮዬ ግን ሙሉ በሙሉ በኃጢያት በስብሶዋል» እንዲህ ብለን መፀለይ የለብንም::

ኃጢያተኞች ኃጢያትን የሚሰሩት እያወቁ አይደለም የእግዚአብሔርን እውነተኛ ሕግም ስላልተረዱት ኃጢያት ማለት ምን እንደሆነ እንኳን በትክክል አያውቁትም የሚያውቁት ነገር ቢኖር በአእምሮኣቸው ውስጥ ኃጢያትን ማድረግ እንደሌለባቸው እንጂ በእግዚአብሔር ፊት በትክክል ኃጢያት የሚባለው ምን እንደሆነ በትክክል አልተገነዘቡትም እግዚአብሔር በኢየሱስ አለማመን ትልቅ ኃጢያት መሆኑን ያስገነዝበናል::

ዮሐንስ 16:9 በእግዚአብሔር ፊት ኃጢያት ማለት ምን እንደሆነ ይነግረናል *«ስለ ኃጢአት በእኔ ስለማያምኑ ነው»* በእርሱ አለማመን በእግዚብሔር ፊት ኃጢአት ነው ዮሐንስ 16:10 ላይ ደግሞ ስለ ቅድስና ሲናገር *«ስለፅድቅም ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህ በኋላ ስለማታዩኝ ነው»* ይላል በሌላ አነጋገር ኢየሱስ ይህን አለም ከሐጢያት ሁሉ ነፃ ስላወጣ ለሁለተኛ ጊዜ በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመሞት ዳግመኛ ነፃ ሊያወጣን አያስፈልግም::


በቤዛነት ያመኑትን ሊቀድሳቸውና ሊያፀድቃቸው ጠርቶዋቸዋል በዚህ አለም ላይ ቤዛነት በእርሱ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ሞቱ አማካይነት ተጠናቋል ሐጢያተኞችን ነፃ

ለማውጣት ሌላ ቤዛነት አያስፈልግም፡፡

*«መዳም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋርያት ሥራ 4:12)* ኢየሱስ የሰው ልጆችን ኃጢያት ሙሉ በሙሉ ሊያነፃ ወደዚህ ምድር መጥቶ በዮርዳኖስ ወንዝ በመጥምቁ ዮሐንስ ከተጠመቀ በኋላ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ሞቶልናል ከልባችሁ እመኑና ትድናላችሁ ኢየሱስ በውኃውና በመንፈሱ ቀድሷችኋል፡፡

ኢየሱስ ኃጢያቶቻችንን በሙሉ በውኃውና በመንፈሱ ከስጋችን አጽድቶልናል በእምነታችንም ድነናል በእውነታው የምናምን ከሆነ በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የምናምን ከሆነን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የተቀደስን እንሆናለን የኢየሱስ ጥምቀትና የመስቀሉ ላይ ደሙ እነዚህ ሁለቱ መሰረታዊ እውነታዎች ናቸው፡፡

## ኃጢያተኞች እንደ መከለያ የሚጠቀሙባቸው ጥቅሶች



1ኛ ዮሐንስ 1፡9 እንደሚለው *«በኃጢያታችን ብንናዘዝ ኃጢያታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው፡፡»*

እኛ የሚጠበቅብን ኃጢያታችንን መናዘዝ ብቻ ከሆነ በጣም ጥሩ ነበር ይህንን በአእምሮዋችን እንያዝ አንዳንድ የቃለ እግዚአብሄር ምሁራን አዲስ ትምህርት ይዘው ቀርበዋል አንድ ሰው ሐጢያቶቹን በሚናዘዝበት ጊዜ ሁሉ ይቅርታን ሊያገኝ ይችላል ብለው ሙጭጭ ይላሉ ይህ ምቹ አይደለምን? ሆኖም ግን ኢየሱስ ኃጢያታችን የሚሰረየው ስንጸልይ ነው አላለም፡፡

ሐጢያቶቻችንን በመናዘዝ ብቻ በእርግጥ ይቅርታን ልናገኝ እንችላለን ወይስ አስቀድሞ ቤዛነትን አግኝተናል? የምታምኑትስ የትኛውን ነው? ይህን የውሸት ሃይማኖት የሚሰብኩት ሰዎች ኃጢያታቸው የሚሰረይላቸው በኑዛዜ መሆኑን ያምናሉ ነገር ግን እንዲያውም የቤዛነትን እውነተኛ ቃሎች ስለማያውቁ ሐጢያት በልቦቻቸው ውስጥ ይቆያል በኢየሱስ የሚያምኑ ሐጢያተኞች ለሰሩዋቸው ሐጢያቶች ይቅርታን ለማግኘት በሚፀልዩበት ጊዜ ሁሉ ይቅርታን የሚያገኙ መሆናቸው ትርጉም አይሰጥም፡፡

ከዚህ የተነሳ በመቤዠት ላይ የተናገራቸውን የእርሱን ቃሎች መቀበልና ምንም ነገር ቢነገርም በእውነትና በሐሰት መካከል መለየት ይኖርብናል፡፡

ኃጢያተኞች 1ኛ ዮሐንስ 1፡9ን በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል ጥቅሱ የሚመለከተው በየቀኑ ለሚሰሩ ሐጢያቶች የሚሰጠውን ይቅርታ እንደሆነ በተሳሳተ መንገድ ያስባሉ አስተምህሮቶቹን በጥንቃቄ እናንብባቸው *«በኃጢያታችን ብንናዘዝ ኃጢያታችንን ይቅር ሊለን ከዓመፃም ሁሉ ሊያነፃን የታመነና ጻድቅ ነው»* የዳንነው ከአዳም ሐጢያት ብቻ ስለሆነ የታመነና ፃድቅ ሆኖ ይቅር ይለን ዘንድ የሰራናቸውን

ሐጢያቶች መናዘዝ አለብን ብላችሁ ታስባላችሁን? እነዚህ ከስጋችን ድካም የመነጨ የተዛቡ አስተሳሰቦች ናቸው::

በኢየሱስ ጥምቀትና ደም በምናምንበት ወቅት ይህ እውነት እንዳልሆነ እንረዳለን ኃጢያት በሙሉ ከብዙ ከብዙ ጊዜ በፊት በጥምቀቱና በመስቀሉ ላይ ደሙ አማካኝነት ተወግዷል::

በመንፈሱ መሰረት ማመንና በተዛቡ አስተሳሰቦች መሠረት ማመን ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው በራሳቸው አስተሳሰቦች መሠረት የሚያምኑ በየቀኑ ስለ ሐጢያቶቻቸው መታጠብ እንደሚያስፈልጋቸው ይሰማቸዋል ነገር ግን በውሃውና በደሙ ቤዛነት የሚያምኑ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና ደም አማካይነት ለአንዴና ለመጨረሻ ነፃ ወጥተዋል::

እንደገና ለመዋጀት በየቀኑ መናዘዝ እንዳለባቸው የሚያምኑ በኢየሱስ ጥምቀትና ደም አማካይነት የተገኘውን ቤዛነት ያለ ማመን ሐጢያት እየሰሩ ነው::

በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ለአንዴና ለዘላለሙ ነፅታችኋልን? ቤዛነትን ያላገኙ ሐጢያቶቻቸውን በየቀኑ በመናዘዝ ደህንነትን ለማግኘት ይሞክራሉ ይህ ወደፊት የሚሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሚመለከት ያለውን ችግር አያቃልልም::

ወደፊት ለሚሰሩዋቸው ኃጢያቶች አስቀድመው ለመናዘዝ ይሞክሩ ይሆናል ነገር ግን እንደዚህ ማድረጋቸው በኢየሱስ ላይ ያላቸው እምነት ጎዶሎ መሆኑን ያሳያል ኢየሱስ በጥምቀቱና በደሙ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሐጢያት ነፃ አውጥቶን ኩነኔውን በራሱ ላይ ወስደዋል እኛ በእርሱ በማመናችን ብቻ ነፃ ወጥተናል::

ለመዳን የወደፊት ሐጢያቶቻችሁን እንኳን መናዘዝ እንዳለባችሁ የምታስቡ ከሆነ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም ስለ መወለድ አንዳች ነገር ከማያውቁት አላማኒዎች የተለያችሁ


አትሆኑም ሐጢያተኛ በኑዛዜ አማካይነት ቤዛነትን ሊያገኙ አይችሉም::

ስለዚህ «እኔ ገና ቤዛነትን ያላገኘሁ ሐጢያተኛ ነኝ» ብላችሁ ከልባችሁ ተናዛችሁ የእርሱን ጥምቀትና የመስቀል ላይ ሞት ወንጌል አድምጣችሁ ካመናችሁ እግዚአብሄር ከሐጢያታችሁ ሁሉ ነፃ ያወጣችኋል::

ነገር ግን በቤዛነቱ ወንጌል ካላመናችሁና በንስሐ ፀሎት ውስጥ ብቻ የምትደበቁ ከሆናችሁ ኢየሱስ ፃድቅ ፈራጅ ሆኖ ዳግመኛ ወደዚህ አለም በሚመጣበት ጊዜ አስከፊ ፍርድ ይጠብቃችኋል::

በውሃውና በመንፈሱ የቤዛነት ወንጌል የማያምኑ ይፈረድባቸዋል ከኑዛዜዎቻቸው ጀርባ ቢደበቁም ፍርድ ይገጥማቸዋል ስለዚህ የፍርዱን ቀን አትጠብቁ አሁኑኑ በተባረከው የውሃና የመንፈስ ወንጌል እመኑ::

## ትክክለኛው ኑዛዜና እውነተኛው እምነት



## 235 አስቀድሞ በመወሰንና በመለኮት ምርጫ ፅንሰ ሐሳብ ውስጥ ያለው ስህተት

እግዚአብሔር ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አድኖናል እዚህ ላይ እኔ እያልኩት ያለውን ለማብራራት አንድ እውነተኛ የሕይወት ምሳሌን እንጠቀም የሰሜን ኮርያ ሰላይ ወደ ደቡብ ኮርያ መጣ እንበል በዚህንም ጊዜ እኛ ምን ያህል እንደበለፀግን ሲመለከት መታለሉን ስለተረዳ ራሱን ለማጋለጥ ወሰነ፡፡

በአቅራቢያው ወደሚገኝ የፖሊስ ጣቢያ ከሄደ በኋላም «እኔ ከሰሜን የመጣሁ ሰላይ ነኝ» ወይም «ወደ ሰሜን የመጣሁት እከሌን ለመግደልና ያንንና ይህንን ለማፈንዳት ነው ቀደም ብዬ ይህንን አፈንድቻለሁ አሁን ግን እጄን እሰጣለሁ ስለዚህ ከእንግዲህ ሰላይ አይደለሁም» በማለት ሊናዘዝ ይችላል፡፡

ይህ ትክክለኛ ኑዛዜ ነውን? ለመናዘዝ ከፈለገ ማለት ያለበት ነገር ቢኖር «እኔ ሰላይ ነኝ» ብቻ ነው ይህ ቀላል ዓረፍተ ነገር ግለሰቡ መጥፎ ሰው እንደሆነና ሊፈረድበት እንደሚገባ ሁሉን ነገር ይጠቁማል ከዚህ ቀላል አረፍተ ነገር አንፃር እርሱ የተሰጠው ተልዕኮ ምንም ቢሆን ይቅርታን ያገኛል፡፡

ልክ እንደዚህ ሁሉ አንድ ኃጢያተኛ በእግዚአብሔር ፊት «እኔ ያልዳንኩኝ ኃጢኣተኛ ነኝ ወደ ገሃነም ልገባና ፍርድም ሊፈረድብኝ የሚገባኝ ነኝ እባክህን አድነኝ» ቢልና በኢየሱስ ቢያምን ቤዛነትን ያገኛል ኢየሱስ ስለ እኛ ተጠመቀ ደሙን አፍስሶዋል እኛ ማድረግ ያለብን ለመዳን በእርሱ አማካይነት በደህንነት ማመን ነው፡፡

ራዕይ 2፡17 እንዲህ ይላል *«ነጭ ድንጋዩንም እሰጠዋለሁ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል»* መፅሐፍ ቅዱስ የኢየሱስን ስም የሚያውቀው እውነተኛውን ወንጌል ያገኘ ብቻ መሆኑን ይነግረናል ፃድቅ የመሆንን ምስጢር የሚያውቀው ለአንዴና ለመጨረሻ ቤዛነትን ያገኘ ብቻ ነው፡፡

ይህንን የማያውቁ በየቀኑ የንስሐ ፀሎቶችን ቢፀልዩም አሁንም ሐጢያተኛ ይሆናሉ መናዘዝ ማለት በየቀኑ ለይቅርታ መፀለይ ማለት አይደለም ምንም እንኳን አንድ ሰው ለ10 ዓመታት ክርስትያን የሆነ ቢሆንም በየቀኑ እግዚአብሔርን ለይቅርታ የሚጠይቅ ከሆነ አሁንም ድረስ ኃጢኣተኛ ነው አሁንም ድረስ የእግዚአብሔር ልጅ አልሆነም::

ለመዳን ኃጢያተኞች መናዘዝና በኢየሱስ ቤዛነት ማመን ይኖርባቸዋል እውነተኛው እምነት ነው::

## በ1ኛ ዮሐንስ 1:9 ስለ ኑዛዜ የሚነግረን የአንድን ሰው ሐጢያቶች ስለ መዘርዘር አይደለም

*ለመዳን ኃጢያታችንን መናዘዝ ያለብን አንድ ጊዜ ነው ወይስ በየዕለቱ?*

*አንድ ጊዜ ብቻ ነው::*

አንድ ሌባ ወይም ወንጀለኛ ወንጀሎቹን በመናዘዙ ብቻ ሊድን ይችላልን? ኃጢአተኞች ኃጢአታቸውን በመናዘዛቸው ብቻ ሊድኑ አይችሉም ኃጢአተኞች በሙሉ ሊድኑ የሚችሉት በተባረከው የኢየሱስ የውኃና የመንፈስ ወንጌል በማመን ብቻ ነው አንዳንድ በስህተት የሚሄዱ ክርስትያኖች እንዲህ በማለት ይናዘዛሉ::

«ውድ እግዚአብሔር! ዛሬም ከአንድ ሰው ጋር ተጣልቻለሁ

ኃጢአትንም ሰርቻለሁ አንድን ሰው አታልያለሁ እንዲሁም ደግሞ ሰርቄያለሁ::»

እንዲህ ብሎም ፀሎቱን ቢቀጥል እግዚአብሔር «ዝም በል አንተ ኃጢአተኛ! እና ምን ይደረግ?» ይለዋል::

«እባክህ አድምጠኝ እግዚአብሔር ኃጢአቶቻችንን እንድናዘዝ ነግረኸናል ምህረትህንም እለምንሃለሁ::»

የዚህን አይነት ፀሎት እግዚአብሔር ሊሰማው የሚፈልገው አይነት አይደለም እርሱ ለማድመጥ የሚፈልገው በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑትን ሰዎች ፀሎት ነው ኃጢያታቸውን አምነው በዳግም ውልደት ወንጌል ያመኑትን ነው::

አውግስጦስ የእናቱን ጡት ከሚጠባበት ጊዜ ጀምሮ ይፀልይ እንደነበር ተናግሯል የዚህን አይነት ፀሎትም ወደ እግዚአብሔር መንግስት የሚያስገባው መስሎት ነበር በዚህ ከመሳቅ ሌላ ምንም አናደርግም የአንድን ሰው ኃጢያት መናዘዝ ምንም አይፈይድም::

እግዚአብሔር «ዝም በል! ኃጢያተኛ መሆንህን ብቻ ንገረኝ ኃጢያተኛ ከሆንክ ስለዚያ መናገርህን አቁም እስካሁን ድረስ የምታምነው በስህተት ነው ስለዚህ እውነተኛው ወንጌል ወደሚሰበክበት ቤተ ክርስትያን ሂድ በመዳኛው ወንጌል እመንና ዳን ካልሆነ መጥቼ እፈርድብሃለሁ» ይለዋል::

የሐጢያት ይቅርታን ለማግኘት የሚፀለዩ የንስሐ ፀሎቶችና በኑዛዜ አማካይነት ለመዳን የሚደረጉ ማናቸውም ሌሎች ሙከራዎች የተዛባና እውነተኛ ያልሆነ እምነት ይጠቁማል::

ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስናምን የውሃውና የደሙ ወንጌል ከሐጢያታችን ሁሉ ነፃ እንደሚያወጣን በ1ኛ ዮሐንስ 1:9 ላይ ተፅፎዋል::

## *«ከእኔ ራቁ»*

*አመፅን መተግበር ማለት ምን ማለት ነው?*

*ይህ ማለት በውስጣችን ኃጢአት እያለ በኢየሱስ ማመን ማለት ነው::*

ክርስቲያን የሆኑ ኃጢአተኞች የተዛባ እምነት ስላላቸው በኢየሱስ ፊት አመፅን ያደርጋሉ *«በዚያን ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን በስምህስ አጋንንትን አላወጣንምን በስምህስ ተኣምራት አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ::» (ማቴዎስ 7:22-23)*

አንድ በስህተት እምነት የሚያምን ሰው ቢሞትና በእግዚአብሔር ፊት ቢቆም የሚለውን አስቡት «ጌታ ሆይ! እንደምን ሰንብተሃል? ከምድር ላይ ሆኜ ከማስብህ በላይ ውብ ነህ አመሰግንሃለሁ ጌታዬ:: አድነሽኛል ምንም እንኳን በልቤ ኃጢአትን የማደርግ ብሆንም እንደኃጢኣተኛ እንደማትመለከተኝ አምናለሁ ወደዚህ የመጣሁትም አንተ ወደ መንግስትህ እንደምታስገባኝ ቃል ስለገባህልኝ ነው አሁን አበቦች ሁሌም ወደሚፈኩበት እሄዳለሁ:: በል ቻዎ እንገናኛለን» በእግዚአብሔር ፊት ይህን ይናገራል::

ወደ አትክልቱ ስፍራ መንቀሳቀስ ሲጀምር ኢየሱስ ያስቆመዋል «ቆይ! እስቲ ይህ ሰው በልቡ ኃጢአት እንዳለበት እንይ ብሎ ኃጢአተኛ ነህን?» ብሎ ይጠይቀዋል::

«በእርግጥ ኃጢአት አለብኝ ሆኖም ግን እኔ ባንተ አምን የለም እንዴ?» ይላል።

«በእኔ ብታምንም ኃጢኣት አለብህን?» ብሎ ይጠይቀዋል።

«አዎን በእርግጥ ኃጢአት አለብኝ።»

«ምን? ኃጢአት አለብህ? የሕይወትን መፅሐፍ አምጡልኝ እንዲሁም ደግሞ የሥራ መፅሐፍንም አምጡልኝ ስሙንም ተመልከቱ ስሙም የትኛው መፅሐፍ ላይ እንደተጻፈ ተመልከቱ።»

እርግጠኛ ለመሆንም ስሙ በሥራ መፅሐፍ ላይ ተመዝግቧል።

«አሁን በምድር ላይ የሰራኸውን ኃጢአት በሙሉ ተናዘዝ።»

ሰውየው ያንን ለማድረግ ባይሞክርም እግዚአብሄር አፉን ከፍቶ ሐጢያቶቹን እንዲናዘዝ አስገደደው።

«አዎ እንዲህና እንዲህ ያሉትን ሐጢያቶች ፈፅሜያለሁ...ሰርቻለሁ።»

በጣም ግራ ከመጋባቱ የተነሳም አፉን ለመክደን አልቻለም።

«እሺ አሁን ይበቃል! እርሱ ገሃነም ለመግባት የሚያስፈልገውን ያህል ኃጢኣት ሰርቷል ከዚያም በላይ ነው! ስለዚህም ወደመቃጠያው ስፍራ ላኩት!» ተብሎ ይፈረድበታል።


ይህ ሰውም አበቦች ወደሚፈኩበት የእርሻ ቦታ ሳይሆን የተላከው ቀን ከሌት በእሳት ወደሚለበለብበት ቦታ ነው ወደ ገሃነም በሚወሰድበት ጊዜ ጥርሱን በንዴት ያፋጭ ነበር።

«እኔ በአንተ አምኛለሁ በስምህም ተንብያለሁ በስምህም ሰብኬኣለሁ አንተን ለማገልገልም እቤቴን ሸጫለሁ ባንተ ስምንም የተቸገሩትን ረድቻለሁ ብዙ መከራን ተቀብያለሁ ፀልዬኣለሁ ህመምተኛንም ፈውሻለሁ...ስለዚህም መሄድ የሚገባኝ ወደ

መንግስተ ሰማያት ነው» በማለት ቅሬታውን ያቀርባል።

ጥርሶቹን ከመጠን በላይ ስላፋጫቸው ከጥቅም ውጭ አደረጋቸው ወደ ገሃነም በደረሰ ጊዜ ስለ ኢየሱስ ምህረት ትክክለኛ ትርጉም የማያውቁ ክርስትያኖችን ያገኛል የወንጌሉን ትክክለኛ ትርጉም የሚተዉ ሁሉ በእርሱ ዘንድ ተቀባይነትን አያገኙም።

## የሐሳዊ ምዕመናን ሐጢያቶች በስራዎች መፅሐፍ ውስጥ ተመዝግበዋል




በኢየሱስ ብናምንም ባናምንም እግዚአብሔር በልባቸው ኃጢአት ያለባቸውን በሙሉ ያጠፋቸዋል በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ቅንጣት ታህል ኃጢኣትን እንኳ ቢገኝ በፍርድ ቀን ይህ ሰው የሚገባው ወደ ገሃነም ነው እግዚአብሔር ገና ቤዛነትን ያላገኙ ሐጢያተኞች ቤዛነትን ማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ ነፃ ያልወጡ መሆናቸውን እንዲናዘዙ ይነግራቸዋል።

የኃጢአተኛ ኃጢአቶች የሚመዘገቡት በልቡ ውስጥ ነው ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል እንደገና የተወለዱት ኃጢአታቸውን ቢያስታውሱም እንኳን ከልባቸው ግን

ይሰረዝላቸዋል እነርሱ ፃድቃን ናቸው።

ሆኖም ግን እነዚያ ዳግም ውልደትን ያላገኙት በልባቸው ኃጢአት አለባቸው እነርሱ ለዚህም ለዚያም ይፀልያሉ ሐጢያቶቻቸው ግን አሁንም እዚያው ናቸው ከ10 አመታት በፊት ከ11 አመታት በፊት ከ20 አመታት በፊት ሳይቀር ለፈፀሙዋቸው በደሎች ንስሐ በመግባት ሐጢያቶቻቸውን በመናዘዝ ዕድሜያቸውን ይፈጃሉ።

በፀሎታቸው በተደጋጋሚ ንስሐ መግባት አለባቸውን? ይህንን የሚያደርጉትስ ለምንድነው? ይህንን ማድረግ አይደፈልጉም ነገር ግን መፀለይ ሲጀምሩ በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኞች መሆናቸውን ያስታውሳሉ ከዚህ የተነሳ ከልባቸው ከመፀለያቸው በፊት ለሐጢያቶቻቸው ስርየት ማግኘት እንደሚኖርባቸው ይሰማቸዋል።

እግዚአብሔር ኃጢአቶቻቸውን በልቦቻቸው ገበታዎች ላይ በብረት ብዕር ስለፃፈው ሐጢያቶቻቸው በጭራሽ ሊፋቁ አይችሉም ከዚህ የተነሳ ወደ እግዚአብሄር በሚቀርቡበት ጊዜ ሁሉ ሐጢያቶቻቸውን መናዘዝ እንደሚኖርባቸው ይሰማቸዋል ስለዚህ ምሉዕ ከሆነው የኢየሱስ ወንጌል ገሚሱን ብቻ የሚያምኑ ሐጢያተኞች ሆነው በጉስቁልና ይኖሩና ፍፃሜያቸው ሲያል ይሆናል።

በኤርሚያስ 17:1 ላይ እንደተፃፈውም *«የይሁዳ ኃጢኣት በብረት ብዕርና በተሾለ ዕብነ አልማዝ ተፅፎኣል በልባቸው ጽላትና በመሠዊቸው ቀንዶች ተቀርጾኣል።»*

ይሁዳ የእስራኤል ሕዝብ ንጉሳዊ ነገድ ስም ነው መፅሐፍ ቅዱስ ይሁዳ የሰውን ዘር ሁሉ እንዲወክል ስላስቀመጠው ይሁዳ ማለት ሁሉም ሕዝብ ማለት ነው።

የይሁዳ ኃጢአት የተፃፈው በብረት ብዕርና በዕብነ አልማዝ ብረትን በሚቆርጥ ቁስ ነው አልማዝ በምድር ላይ ጠንካራው

ቁስ ነው ኃጢአቶቻችን በብረት ብዕርና በሾለ ዕብነ አልማዝ ተመዝግቦዋል፡፡

አንዴ ከተከተቡ በኋላ መቼም ቢሆን አይጠፉም በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል እስካላመንን ድረስ ሊጠፉ አይችሉም፡፡

በአስተሳሰቦቻቸው ቤዛነትን ማግኘት በክርስትና ትምህርቶች ማመን ቃለ እግዚአብሄርን ማሰታወስና ራሳቸውን ለቤተክርስቲያን አገልግሎት መስጠት ሐጢያት በልቦቻቸው ውስጥ እስካለ ድረስ ፋይዳ የለውም፡፡

ሐጢያቶቻቸው ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ፈፅሞ ስለማይፋቁ ሐጢያተኞች ሐጢያቶቻቸውን በማስታወስ በሚፀልዩበት ጊዜ ሁሉ «አቤቱ እኔ ሐጢያተኛ ነኝ» ይላሉ ምንም ያህል ከእግዚአብሄር ጋር አብዝተው ሕብረት ለማድረግ ቢሞክሩ በቤተክርስቲያን ውስጥም ብዙ ሐላፊነትን ቢሸከሙ የስነ መለኮት ትምህርትን ቢማሩ በልቦቻቸው ውስጥ አሁንም ሐጢያት አለ፡፡


ከዚህ የተነሳ ወደ ተራሮች ይወጣሉ በልሳን ለመናገርም ከንቱ ሙከራ ያደርጋሉ የሚንቀለቀል የእሳት ነበልባል ራዕዮችንም ማየት ይሻሉ ነገር ግን ሁሉም ፋይዳ የለውም ሐጢያት በልባቸው ውስጥ እስካለ ድረስ ፈፅሞ ሰላም አይኖራችሁም፡፡

በኤርሚያስ 17:1 ላይ እንደተጻፈው ከሆነ ኃጢአቶቻችን በመሠዊያቸውን ቀንዶች ላይ ተፅፈዋል በመንግስተ ሰማያት የሕይወትና የስራ መፅሐፍ አለ ሰዎችም በነዚህ ውስጥ ይመዘገባሉ እግዚአብሔርም ኃጢአቶቻችንን በነዚህ መዛግብት ላይና በልባችንም ውስጥ ይከትባቸዋል በሕጉም ያሳየናል፡፡

በኢየሱስ ጥምቀትና እርሱ ለኛ ሲል በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም በማመንም በእነዚህ መፅሐፍት ላይ የተመዘገቡትን ኃጢአቶቻችንን ሰርዘን መዳን አለብን ከዚህ በኋላ

ዘላለማዊ ህይወትን ለመኖርና ስማችንንም በሕይወት መፅሐፍ ላይ ለማስመዝገብ ዝግጁዎች እንሆናለን፡፡

## ስማችሁ በሕይወት መፅሐፍ ውስጥ አለን?




በህይወት መፅሐፍ ላይ ስማችሁ መመዝገቡ በጣም አስፈላጊ ነገር ነው ስማችሁ በዚያ መጽሐፍ ላይ ከሌለ በኢየሱስ የማመናችሁ ትርጉም ምንድን ነው? ቤዛነትን በተጨባጭ ለማግኘ ት ከውሃና ከመንፈስ ዳግም በመወለድ ማመን አለባችሁ፡፡

ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ ልክ 30 ዓመት እንደሆነው የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ለመውሰድ ተጠመቀ እኛንም ከኃጢአት ያድነን ዘንድ በመስቀል ላይ ተሰቅሏል በማቴዎስ 3፡15 ላይ እንደተጻፈውም ኢየሱስ «ለእኛ» ሲል ተጠምቆ በመስቀል ላይ ሞቶልናል ስማችን በሕይወት መፅሐፍ ላይ እንዲመዘገብ በዚህ ማመን አለብን፡፡

ሰዎች ሞተው በእግዚአብሔር ፊት ሲቆሙ እግዚአብሔር እንዲህ ይላቸዋል «የዚህ ሰው ስም በሕይወት መፅሐፍ ውስጥ እንዳለ ይታይ፡፡»

«አዎን ጌታ» ከተባለ፡-

«አዎን በምድር ላይ ስለ እኔ ብዙ ተሰቃይተሃል ከዚህ በኋላ ግን ይህ መቼም እንዲደርስብህ አልፈቅድም» ከዚያም እግዚአብሔር በዚህ ሰው አናት ላይ የቅድስናን ዘውድ ይጭንለታል፡፡

«አመሰግንሃለሁ ጌታዬ፡፡ ለዘላለምም ሳወድስህ እኖራለሁ፡፡»

«መላዕከት በዚህ ሰው ራስ ላይ ዘውድን ጫኑ» ብሎ ያዛቸዋል፡፡

«ጌታ፣ አንተ እኔን ማዳንህ ከበቂም በላይ ነው ዘውዱም ደግሞ ከሚገባኝ በላይ ነው አመሰግንሃለሁ ስላዳንከኝም ለዘላለም አወድስሃለሁ አንተ ባለህበት ለመኖር በመቻሌም ደስታዬ ወሰን የለሽ ነው፡፡»

«መላዕክት ተንበርከኩና 10,000ኛ ልጄን በጀርባችሁ ተሸከሙት፡፡»

መላዕክቱም «እሺ ጌታ» ብለው

«እባክህ ጀርባዬ ላይ ታዘል» ይሉታል፡፡

«በጣም የሚመች ነው ይህንን በትክክል እያደረኩት ነውን? እንሂድ» ይላቸዋል፡፡

መላዕክቱም በጥንቃቄ ይዘውት «ለመዝናናት ትፈልጋለህን?» ብለው ይጠይቁታል፡፡

እርሱም «ይህ ቦታ በጣም ያምራል እንዴትስ ትልቅ ነው፡፡» ይላቸዋል፡፡

«ለብዙ ቢሊየን ዓመታት የተንቀሳቀስኩበት ቢሆንም አሁንም ድረስ አልጨረስኩትም» ይለዋል መልዓኩ ለሰውየው፡፡

«እውነትህን ነው? መቼም ሳልከብድህ አልቀረሁም አሁን መውረድ እችላለሁ፡፡»

«በዚህ መቼም ቢሆን አይደክመንም» ሲል ይመልስለታል መልዓኩ፡፡

«አመሰግናለሁ መንግስተ ሰማይ መሬት ላይ መቆም እፈልጋለሁ ከእኔ በፊት እዚህ የደረሱት ፃድቃን ሁሉ የታሉ?» ብሎ ይጠይቀዋል::

«በዚያ በኩል ናቸው» ሲለው፣

«ወደዚያ እንሂድ» ይለዋል::

ሃሌሉያ! እርስ በርሳቸው ተቃቀፉ ፈገግም አሉ ለዘላለምም በደስታ መኖር ቀጠሉ::

ሸኢየሱስ አምኖ ነገር ግን ገናም ሐጢያተኛ ሆኖ ስለሞተና በእግዚአብሄር ፊት ስለቆመ ሰው አስቡ እርሱም ደግሞ በኢየሱስ እንደሚያምንና ሐጢያተኛ እንደሆነ ያምናል::

እግዚብሔር እንዲህ ይላል «የዚህ ሰው ስም በሕይወት መፅሐፍ ተፅፎ እንደሆነ ይታይ::»

መላዕክቱም ሲመልሱ «ጌታ ሆይ! ስሙ በዚያ የለም» ይሉታል::

«ቀጥላችሁ ደግሞ በሥራ መፅሐፍ ላይ ተመልከቱት::»

«ስሙና ኃጢአቱ ደግሞ በዚያ መፅሐፍ ላይ ነበሩ::»

«ይህን ሰው ስለ ነዳጅ ዋጋና ስለሌላ ነገር ወደማያስብበት ቦታ ላኩት በዚያም ለዘላለም ይኑር» ይላል::


«ኦ! ጌታዬ ይህ ትክክል አይደለም...» ይላል::

ይህ ትክክል አይደለም ነው የሚለው! አዎን በኢየሱስ አብዝቶ እያመነ ሳለ ለምን ወደ ሲዖል ይላካል?»

ምክንያቱ በሰይጣን መታለሉና የወንጌሉን ከፊል እውነት ብቻ ማድመጡ ነው የኢየሱስን ቤዛነት እውነተኛ ትርጉም በተሳሳተ መንገድ ከተረዳነው መጨረሻችን ሲዖል ይሆናል::

ይህ ሰው በኢየሱስ አመነ ሆኖም በሰይጣን ስለተታለለ ሐጢያተኛ እንደሆነ አሰበ እውነተኛውን ወንጌል ሰምቶ ቢሆን ኑሮ እምነቱ ልክ አለመሆኑን ይገነዘብ ነበር ሆኖም ግን በራሱ የተሳሳተ እምነት ላይ ካለው አስተሳሰብ የተነሳ ይህ ሊሆንለት አልቻለም::

ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመሄድ የምትፈልጉ ከሆነ ከውኃና ከመንፈሱ እንደገና ስለመወለድ በደንብ ማመን አለባችሁ በማቴዎስ 3:15 ላይ እንደተጻፈው ኢየሱስ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ የወሰደው «ለዚህ ነው» በውሃውና በደሙ ደህንነት ማመን ይገባችኋል::




የሌላውን ጥያቄ በጭራሽ እምቢ እንደማይል ጥሩ አይነት ሰው ማንኛውንም ነገር ማመን የምትመርጡ ከሆነ ፍፃሜያችሁ ሲዖል ይሆናል በገሃነምም በጣም ብዙ ጥሩ ሰዎች አሉ በመንግስተ ሰማያት ያሉት ግን ለሚያምኑት ነገር ሲታገሉ የነበሩ ታጋዮች ናቸው::

በሰማይ ያሉ ኃጢአተኞች መድረሻቸው ሲዖል እንደነበረ ያወቁ ነገር ግን ሐጢያቶቻቸው በኢየሱስ ጥምቀትና ደም አማካይነት መታጠቡን በምስጋና ያመኑ ናቸው::

በሰማይ የጆሮዎችና የአፎች ክምር አለ ይባላል ምክንያቱም ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ቤዛነት የሚያምኑት በአፋቸው ወይም በጆሮዎቻቸው ብቻ ስለሆነ እግዚአብሄር ቀሪ አካሎቻቸው ይጣላሉ::

አንድ በኢየሱስ የሚያምንና በልቡ ውስጥ ግን አሁንም ድረስ ኃጢአት ያለበት ሰው በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ «ጌታ ሆይ! በልቤ ውስጥ ምንም እንኳን ኃጢአት ቢኖርብኝም ሰዎች

በኢየሱስ የማምን ስለሆነ ፃድቅ ብለው ይጠሩኛል አንተም እኔን ኃጢያት እንደሌለብኝ አድርገህ እንደምትመለከተኝ አምናለሁ የተማርኩትና ሳምነው የነበረው ይህንን ነው ብዙ ሰዎች ያደርጉ እንደነበረውም ነው የማምነው፡፡ ሳምነው የነበረውም በጣም ብዙ ሰዎች ያምኑት የነበረውን ነገር ነው፡፡»

እግዚአብሔርም ሲመልስ «በልባቸው ውስጥ ኃጢኣት ያለባቸውን ሰዎች ይቅር ልላቸው አልችልም እንደገና ከመንፈስና ከውኃ በሆነው ዳግም የመወለድ በረከት ሐጢያቶቻችሁን ሁሉ አጥቤያለሁ እናንተ ግን በዚያ ለማመን እምቢተኞች ሆናችሁ መላዕክቶች! ይህንን የማይረባ ሰው ወደ ሲዖል እሳት ወርውሩት» ይላል፡፡

በኢየሱስ አምናለሁ እያለ በልቡ ውስጥ ሐጢያት እንዳለ የሚያስብ ማንኛውም ሰው መጨረሻው ሲዖል ይሆናል እውነተኛውን የቤዛነት ወንጌል አድምጣችሁ ከሐጢያት ሁሉ ነፃ ውጡ አለበለዚያ በሲዖል ትቃጠላላችሁ፡፡

በልባችሁ ውስጥ ኃጢአት እያለ ከኃጢአት ውጭ ነኝ ማለት እግዚብሔርን ማታለል ነው በስተመጨረሻ ላይ በኃጢአተኛና በቅዱሳን መካከል ምን ያህል ልዩነት እንዳለ ለመመልከት እንችላለን እኔ እናንተ ትድኑ ዘንድ ለምን እንደምመሰክርም ትረዱታላችሁ፡፡

ወደ ገሃነምና ወደ መንግስተ ሰማያት በሚወስዱት መንታ መንገዶች ላይ በቆማችሁ ጊዜም በሙሉው ወንጌል (በኢየሱስ ጥምቀትና ሞት) በሚያምኑትና በሌሎቹ መካከል ያለውን ልዩነት ትረዱታላችሁ ይህ ትልቅ ልዩነትን ይፈጥራል የተወሰኑት የእግዚብሔርን መንግስት ሲወርሱ የተቀሩት ደግሞ ወደ ገሃነም ይገባሉ፡፡

በኢየሱስ አምናችሁ አሁንም ግን ኃጢአተኞች ናችሁን? እንዲህ ከሆነ እንደገና ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል መወለድ

እንዳለባችሁ ማወቅ አለባችሁ እግዚአብሔር በልባቸው ኃጢኣት ያለባቸውን የሚልከው ወደ ገሃነም ነው መንግስተ ሰማያት መግባት የሚችሉት ምሉዕ በሆነው የሐጢያት ይቅርታ የሚያምኑ ብቻ ናቸው::

ይህን አሁኑኑ አድርጉት ችላ ካላችሁት በጣም ሊረፍድ ይችላል አስቀድማችሁ ተዘጋጁ መጨረሻችሁ ሲያል ከመሆኑ በፊት በውሃውና በመንፈሱ ቤዛነት አምናችሁ ተቀደሱ::

ለጌታችን ለኢየሱስ ምስጋና ይግባው! እኛን ሐጢያተኞቹን ፃድቅ በማድረጉ ረገድ ላደረገልን ቸርነቱ እናመሰግነዋለን ሃሌሉያ!

## ኢየሱስ፡ የፃድቃን ጠበቃ

*ሐጢያቶቻችን በንስሐ ፀሎት ሊደመሰሱ ይችላሉን?*

*በፍፁም! ይህ የማይቻል ነው ሰይጣን እኛን ከሚያታልልባቸው መንገዶች አንዱ ይህ ነው::*

1ኛ ዮሐንስ 2:1-2ን እናንብብ *«ልጆቼ ሆይ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እፅፍላችኋለሁ ምንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው እርሱም የኃጢኣታችን ማስተሰረያ ነው*

*ለኃጢአታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለም ሁሉ ኃጢአት እንጂ።»*

እዚህ ላይ የተፃፈውን ማት ትችላላችሁን? አሁንም ድረስ በኢየሱስ እያመነ በውስጡ ኃጢአት ያለበት አለን? በልባችሁ ውስጥ ኃጢአት እያለ ለእግዚአብሔር እንደሌለባችሁ የምትናገሩ ከሆነ እናንተ እርሱን እያታለላችሁ ነው ማለት ነው እንዲሁም ደግሞ ራሳችሁንም ጭምር ታታልላላችሁ።

ሆኖም ግን ኢየሱስን በትክክል ከተረዳችሁትና ኃጢአትን በሙሉ በዮርዳኖስ በመጠመቅ እንዳነፃላችሁ የምታምኑ ከሆነ ከኃጢአት ሙሉ በሙሉ ነፃ ልትሆኑ ትችላላችሁ በመቀጠልም «ጌታ ሆይ! በአንተ ዳግም ከውኃና ከመንፈስ ለመወለድ ችያለሁ። ኃጢኣት የለብኝም በፊትህም ያለምንም ኃፍረት ልቆም እችላለሁ» ማለት ትችላላችሁ።

እግዚአብሄርም መልስ ይሰጣል «አዎ ትክክል ነህ አብርሃም ፃድቅ ስለመሆኑ በእኔና በራሱ ስላመነ አንተም ደግሞ ፃድቅ ነህ ምክንያቱም ሐጢያቶችህን ሁሉ አስወግጄአለሁና።»

ሆኖም ግን እስቲ በኢየሱስ እያመነ አሁንም ድረስ በልቡ ውስጥ ኃጢአት ያለበትን ሰው ተመልከቱት «በኢየሱስ የማምን ስለሆነ ምንም እንኳን በልቤ ኃጢአት ቢኖርም ወደ መንግስተ ሰማያት እገባለሁ» ይላል።

ሰማይ ለመግባት አብዝቶ ከመሻቱ የተነሳ በፍርዱ ወንበር ቆሞ ሳለ ሊከራከር ይሞክራል ነገር ግን መጨረሻው ሲዖል ነው ለምን? ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን የተባረከ ወንጌል አላወቀም።

ማንም ሰው በምድር ላይ በሚኖርበት ጊዜ ኃጢአተኛ መሆኑን መናዘዝ አለበት «እኔ ኃጢአተኛ ነኝ መድረሻዬም ገሃነም ነው እባክህ አድነኝ» በማለትም መፀለይ ይኖርበታል በምህረት ፀሎት ብቻ የሚድን ኃጢአተኛ የለም ከዚህም ሌላ

ኃጢኣተኛ መሆኑን አምኖ ነፃ ለመውጣት የውኃውና የመንፈሱን ወንጌል መቀበል ይኖርበታል ፃድቅ ሊሆን የሚችለው በውሃውና በመንፈሱ ቤዛነት አማካይነት ብቻ ነው፡፡

በኢየሱስ ይቅርታን የሚያገኘው የአዳም ሐጢያት ብቻ ነው እኛም ደህንነትን ለማግኘት ከእውነተኛ ሐጢያቶቻችን ንስሐ መግባት ይኖርብናል ብሎ ሙጭጭ የሚለው ሐሰተኛ ወንጌል ነው ይህ በቀጥታ የሚመራን ወደ ሲዖል ነው እጅግ በርካታ ምዕመናን ይህንን የሐሰት ወንጌል በማመን ራሳቸውን ለሲዖል ዳርገዋል ይህ ዝንባሌ በዘመናችን የበለጠ ገኖ ወጥቷል፡፡

ሐሰተኛ ወንጌል ውስጥ ብትወድቁ መውደቃችሁን ታውቁታላችሁን?ስር መሆናችሁን ታውቃላችሁን? ዕዳችሁን በሙሉ ከከፈላችሁ በኋላም ባለ ዕዳዎች ትሆናላችሁን? አስቡት እስቲ! በኢየሱስ እያመናችሁም አሁንም ድረስ ራሳችሁን እንደ ኃጢአተኛ የምትቆጥሩ ከሆናችሁ በእርሱ በትክክል ታምናላችሁ ማለት ይቻላልን? እናንተ አማኞችና ኃጢአተኞች ናችሁ ወይስ አማኝና ፃድቅ ሰው?

ለራሳችሁ መምረጥ ትችላላችሁ ወይ ኃጢአቶቻችሁ በሙሉ ይቅር መባላችሁን ልታምኑ ትችላላችሁ አለበለዚያም በየቀኑ ለመተላለፎቻችሁ ንስሐ ልትገቡ ትችላላችሁ ምርጫችሁ ወደ ሰማይ ወይም ወደ ሲዖል የምትሄዱ ለመሆናችሁ ይወስናል እውነተኛውን ወንጌል የነገራችሁን ወንጌላዊ ልትሰሙት ይገባል፡፡

በሐሰተኛ ወንጌል የሚያምኑ በእያንዳንዱ የማለዳ የፀሎት ስብሰባ ላይ በእያንዳንዱ የረቡዕ አገልግሎት ላይ በየአርቡ የሙሉ ሌሊት ፀሎት ላይ ገናም ለሐጢያቶቻቸው ይቅርታን ለማግኘት ይፀልያሉ፡፡

«ጌታ ሆይ! ኃጢአትን ሰርቻለሁ በዚህ ሳምንት ኃጢኣትን አድርጌአለሁ» ይላሉ ከዚያም ከዓመታት በፊት የሰሩትንም ኃጢአት በማስታወስ ለእነዚያም ይፀልያሉ ይህ የውኃውንና

የመንፈሱን የተባረከ ወንጌል መፃረር ነው::

ኃጢኣቶቻችን በሙሉ መከፈል ያለባቸው በደም ነው ዕብራውያን 9:22 ላይ *«ደም ሳይፈስስ ስርየት የለም»* ይላል ኃጢአት እንዳለባችሁ የምታስቡ ከሆነ እንደገና ስለእናንተ እንዲደማላችሁ እየጠየቃችሁት ነውን? ምሉዕ በሆነው ቤዛነት የማያምኑ የኢየሱስን ቤዛነት ወደ ውሸት በመለወጣቸው ተጠያቂዎች ናቸው እንዲያውም ኢየሱስ ለአንዴና ለመጨረሻ እንዳላዳነንና ውሸታም እንደሆነ ያውጃሉ::

በኢየሱስ ቤዛነትን ለማግኘት እናንተ በእውነተኛው የቤዛነት ወንጌል፣ በእውነተኛው የውኃና የመንፈስ ወንጌል ማመን አለባችሁ በብዙ መቶዎች ሺዎችና ሚሊዮን ፀሎቶች ከኃጢኣት ልትድኑ ትችላላችሁን? እውነተኛው ወንጌል ለአንዴና ለዘላለሙ ያድነናል ፃድቃን ሁኑ ወደ እግዚብሔርም መንግስት ግቡ ለዘላለምም ፃድቅ ሕይወት ኑሩ::

*♪በኢየሱስ አዲስ ህይወትን እኖራለሁ ያለፈው አልፎ አዲስ ፍጡር ሆኛለሁ የጠፋው ጊዜም አልፏል ኦ! ኢየሱስ የእውነት ኑሮዬ ነው በኢየሱስ አዲስ ህይወትን እኖራለሁ::♪*

በኢየሱስ አዲስ ህይወትን ትኖራላችሁ እንደምትፈልጉት ውብ መስላችሁ ባትታዩም በጣም አጭር ወይም ወፍራም ብትሆኑም ከውሃና ከመንፈስ ዳግም በመወለድ ወንጌል የተባረኩ የደስታ ኑሮ ይኖራሉ አፍንጫችሁ ጥሩ ቅርፅ ባይኖረው ወይም አጭር ብትሆኑ ምን ፋይዳ አለው? ፍፁማን ስላልሆንን በኢየሱስ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም በመወለድ ድነናል ነገር ግን ትዕቢተኞች ፍፃሜያቸው ሲያል ይሆናል::

ጌታ ሆይ! አመሰግንሃለሁ ለጌታዬ ሁልግዜም ምስጋናን አቀርባለሁ በውኃና በመንፈሱ ወንጌል በማመን ዳግም በመወለድ የምናምን ስለሆነ ወደ እግዚብሔር መንግስት እንገባለን::

# ሐሰት ወደ ገሃነም ይመራናል

*በመጨረሻ ላይ የጽድቅናን ዘውድ የሚደፋው ማነው?*

*ውሸትን ያሸነፈው ነው፡፡*

የሐሰት ወንጌል ይቅርታን ለማግኘት በየቀኑ ንስሐ መግባት እንዳለብን ይነግረናል የውሃውና የመንፈሱ ወንጌል ግን ቀደም ብሎ ሙሉ በሙሉ ይቅርታ እንዳገኘንና ማድረግ የሚያስፈልገንም ይህንን ማመን ብቻ እንደሆነ ይነግረናል፡፡

እውነቱ የቱ ነው? በየቀኑ ንስሐ መግባት አለብን? ወይስ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ለማስወገድ እጅግ ተስማሚ በሆነ መንገድ በተጠመቀ ጊዜ እንዳዳነን ማመን ትክክል ነው? እውነቱ ለአንዴና ለመጨረሻ ሐጢያቶቻችንን መውሰዱና በዚህ ትክክለኛ መንገድ ደህንነት የሰጠን መሆኑ ነው፡፡

በመንፈሳዊው ጦርነት ውስጥ ውሸትን ማሸነፍ ይኖርብናል ብዙ ሰዎች ይህን ውሸት በመከተል ላይ ናቸው *«በጴርጋሞን ወዳለው ቤተ ክርስትያን መልዓክ እንዲህ ብለህ ፃፍ፡- በሁለት ወገን የተሳለ ስለታም ሰይፍ ያለው እንዲህ ይላል- የሰይጣን ዙፋን ባለበት የምትኖርበትን አውቃለሁ ስሜንም ትጠብቃለህ ሰይጣንም በሚኖርበት በእናንተ ዘንድ የተገደለው የታመነው ምስክሬ አንቲጳስ እንኳ ሃይማኖቴን አልካድህም፡፡» (ራዕይ 2:12-13)*

*«መንፈስ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚለውን ጆሮ ያለው ይስማ ድል ለነሳው ከተሰወረ መና እሰጠዋለሁ ነጭ ድንጋይንም*

*እሰጠዋለሁ በድንጋዩም ላይ ከተቀበለው በቀር አንድ ስንኳ የሚያውቀው የሌለ አዲስ ስም ተጽፎአል፡፡» (ራዕይ 2:17)*

በርካታ ክፉ መናፍስቶች በሚኖሩበትና ሐሰትም እውነት ስለመሆኑ በሚያስመስልበት ቦታ ሰይጣን የብርሃን መልአክ መስሎ ይገለጣል እግዚአብሄር ከውሃና ከመንፈስ የሆነውን የደህንነት እውነት ሰምቶ የተረዳን ነገር ግን በዚያ የማያምንን ማንኛውንም ሰው ሊረዳው አይችልም እንደዚህ ያለ ሰው በእርግጥም ፍፃሜው ሲዖል ይሆናል፡፡

በኢየሱስ ደህንነት ያምን እንደሆነ እያንዳንዱ ሰው ለራሱ መወሰን ይኖርበታል ማንም ከእግራችሁ ስር ተንበርክኮ ታምኑና ትድኑ ዘንድ የሚለምናችሁ አይኖርም፡፡

ከኃጢአት ለመዳን የምትፈልጉ ከሆነ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል እመኑ በማዳን ፍቅሩና እኛን ባዳነበት ፀጋው ምስጋናን ተሞልታችሁ ከሆነ እመኑት ወደ ገሃነም ለመግባት የተዘጋጃችሁ ኃጢአተኞች መሆናችሁን የምታውቁም በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ደም አምናችሁ ዳኑ ያን ጊዜ ፃድቃን ትሆናላችሁ፡፡

ኃጢአተኞች እንዳልሆናችሁ የምታስቡ ከሆነ በኢየሱስ በማመን ቤዛነት ማግኘት አያስፈልጋችሁም ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድ ወንጌል ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ነፃ የሚወጡት ሐጢያተኞች ብቻ ናቸው ኢየሱስ የሐጢያተኞች መድህንና የችግረኞች አፅናኝ ነው እርሱ ፈጣሪ ነው እርሱ የፍቅር መምህር ነው፡፡

በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል አምናችሁ እንደገና ትወለዱ ዘንድ አሁንም እጠይቃችኋለሁ እመኑ በዚህም ኢየሱስ የእናንተ አዳኝ፣ ወዳጅ፣ እረኛና አምላክ እንደሚሆን እርግጠኞች ልትሆኑ ትችላላችሁ ሐጢያተኞች በኢየሱስ ማመን አለባቸው ፍፃሜያችሁ ሲዖል እንዲሆን ካልፈለጋችሁ ይህንን ልታምኑ

ይገባል እግዚአብሄር የደህንነትን ወንጌል እንድናምን አይለምነንም::

ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት ትፈልጋላችሁን? የምትፈልጉ ከሆነ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል እመኑ ኢየሱስ «እኔ መንገድም፣ እውነትም ህይወትም ነኝ እመኑኝ» ይላል ወደ ገሃነም መጣል የሚፈልግ አለን? እንደዚህ ከሆነ በዚህ አትመኑ ይህ ከሆነ ለእናንተም በገሃነም ቦታ አዘጋጅቶላችኋል::

እግዚብሔር አይለምንም ነጋዴ ደንበኞቹን የሚያባብለው እቃዎቹን ለመሸጥ ነው እግዚአብሔር ግን መንግስተ ሰማያትን በነፃ የሚሰጠው ቤዛነትን ላገኙ ብቻ ነው እግዚአብሄር ፃድቅ ነው::

ሰዎች የዓለም ፍፃሜ እንደቀረበ ይናገራሉ አዎን፣ እኔም የማስበው እንደዚያ ነው በእውነተኛው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድ ወንጌል አለማመን ሞኝነት ነው::

ከውኃና ከመንፈስ ዳግም በመወለድ የተባረከ ወንጌል እመኑ ወደ እግዚአብሔር መንግስት አብረን እንግባ ኢየሱስ በሚኖርበት ቦታ ከእኔ ጋር መሄድ አትፈልጉምን?

*እናንተ ፃድቃን ናችሁ*
*ወይስ ኃጢያተኞች?*

*በልባችን ኃጢአት የሌለብን*
*ፃድቃን ነን::*

ሮሜ 8:1-2ን እናንብብ *«እንግዲህ በክርስቶስ ኢየሱስ ላሉት አሁን ኩነኔ የለባቸውም በክርስቶስ ኢየሱስ ያለው የሕይወት መንፈስ ሕግ ከኃጢአትና ከሞት ሕግ አርነት አውጥቶኛልና::»*

ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ አማካይነት ኃጢአቶቻችንን በሙሉ አስወግዶዋል ለኃጢኣታቸው ፍርድን መቀበል የነበረባቸውን ኃጢአተኞች በሙሉም አድኖአል።

የእግዚአብሔር ደህንነት ሁለት ነገሮችን ይዞዋል አንደኛው ሕጉ ሲሆን ሌላው ደግሞ ፍቅሩ ነው ሕጉ ኃጢአተኞች መሆናችንን ያስተምረናል በሕጉ መሰረትም የኃጢኣት ደሞዝ ሞት ነው በሕጉ መዳን አንችልም ሕጉ የኛን ኃጢአተኛ ተፈጥሮና እጣችንን ያስተምረናል እኛ ኃጢኣተኞች መሆናችንን ለማወቅ ያስችለናል።

የኃጢአትን ደሞዝ ለመክፈል ኢየሱስ ወደዚህ ምድር በመምጣትና የእኛን ኃጢኣት በሙሉ በመውሰድ በእኛ ፈንታ የራሱን ህይወት በመሰዋት ፍርድን ተቀበለልን እኛን ሁላችንን ከኃጢኣት ያዳነን የእግዚአብሔር ፍቅር ይህ ነው።

ውሸትን ማሸነፍ አለብን እግዚአብሄር ውሸትን ለሚያሸንፍ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን በረከት ይሰጠዋል።

በኢየሱስ በማመንም እንድናለን የእርሱን ቃሎች በማመን ወደ ፅድቅና እውነትን ወደ መረዳት እንደርሳለን በልቦቻችሁ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም በመወለድ እውነት እመኑ ትድኑማላችሁ። ✉

# ስብከት 6

# የተለወጠው ክህነት

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ..ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::



«እንግዲህ በሰማያት ያሉትን የሚመስለው ነገር በዚህ ሊነጻ እንጂ በሰማያት ያሉት ራሳቸው ከእርሱ ይልቅ በሚበልጥ መስዋዕት ሊነጹ የግድ ነበር።» (ዕብራውያን 9፡23)

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ።

# የተለወጠው ክህነት

« ዕብራውያን 7:1-28 »

«የሳሌም ንጉስና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ መልከ ፄዴቅ አብርሃም ነገስታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ካለው ሁሉ አሥራትን አካፈለው የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የፅድቅ ንጉስ ነው ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉስ ማለት የሰላም ንጉስ ማለት ነው:: አባትና እናት የትውልድም ቁጥር የሉትም ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍፃሜ የለውም ዳሩ ግን በእግዚብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አስራት የሰጠው ይህ ሰው እንዴት ትልቅ እንደነበር እስቲ ተመልከቱ ከሌላ ልጆችም ካህንነትን የሚቀበሉት ከህዝቡ ማለትም ከወንድሞቻቸው እነርሱ ምንም ከአብርሃም ወገብ ቢወጡም ከእነርሱ አሥራትን በህግ እንዲያስወጡ ትዕዛዝ አላቸው ከእነርሱ የማይቆጠረው ግን ከአብርሃም አስራትን አውጥቷል የተስፋ ቃል የነበረውንም ባርኳል ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው በዚህስ የሚሞቱ ሰዎች አሥራትን ያስወጣሉ በዚያ ግን የሚያስወጣ በሕይወት እንዲኖር የተመሰከረለት እርሱ ነው ይህንም ለማለት ሲፈቀድ አሥራትን የሚያስወጣ ሌዊ እንኳን በአብርሃም እጅ አሥራትን ሰጥቶአል መልከ ጻዴቅ በተገናኘው ጊዜ ገና በአባቱ ወገብ ነበረና::

እንግዲህ ሕዝቡ በሌዊ ክህነት ተመሠረተን ሕግ ተቀብለዋልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን እንደ አሮን ሹመት የማይቆጠር እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ

ካህን ሊነሳ ወደ ፊት ስለ ምን ያስፈልጋል? ክህነቱ ሲለወጥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና ይህ ነገር የተነገረለት እርሱ በሌላ ወገን ተከፍሎአልና በዚያ መሠዊያውን ያገለገለ ማንም የለም ጌታችን ከይሁዳ ነገድ እንደ ወጣ የተገለጠ ነውና ስለዚህም ነገድ ሙሴ ምንም እንኳ ስለ ክህነት አልተናገረም።

በማያልፍም ህይወት ኃይል እንጂ በሥጋ ትእዛዝ ሕግ ሳይሆን ሌላ ካህን በመልከ ጼዴቅ ምሳሌ ቢነሳ ይህ እጅግ አብልጦ የሚገለጥ ነው አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ይመሰክራልና ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል።

እነርሱም ያለ መሃላ ካህናት ሆነዋልና እርሱ ግን ጌታ፡- አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይጸጸትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖኣልና ያለ መሐላ ካህን እንዳልሆነ መጠን እንዲሁም ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኖኣል።

እነርሱም እንዳይኖሩ ሞት ስለከለከላቸው ካህናት የሆኑት ብዙ ናቸው እርሱ ግን ለዘላለም የሚኖር ስለ ሆነ የማይለወጥ ክህነት አለው ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በሕይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈፅሞ ሊያድናቸው ይችላል።

ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም ሌለበት ከኃጢኣተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ እንደዚህ ያለ ሊቀ ካህናት ይገባና፤ እርሱም እንደነዚያ ሊቀ ካህናት አስቀድሞ ስለ ራሱ ኃጢኣት በኋላም ስለ ህዝቡ ኃጢአት ዕለት ዕለት መስዋዕትን ሊያቀርብ አያስፈልገውም ራሱን ባቀረበ ጊዜ ይህን አንድ ጊዜ ፈፅሞ አድርጎአልና ሕጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት

**አድርጎ ይሾማልና ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘላለም ፍፁም የሆነውን ልጅ ይሾማል።»**

# ኢየሱስ ሰማያዊውን ክህነት አገለገለ

*የላቀው ማነው? ሊቀ ካህኑ መልከፄዴቅ ወይስ እንደ አሮን ስርአት የሆነው ምድራዊው ሊቀ ካህን?*

*ታላቁ ካህን መልከ ጼዲቅ ነው።*

**በብሉይ ኪዳን ጊዜ መልከ ጼዲቅ የሚባል ካህን ነበር በአብርሃም ዘመን ኮልዶጎሞርና ነገስታቶቹ ተባብረው የሰዶምንና የገሞራን ንብረቶች ሁሉ ዘረፉ አብርሃምም በቤቱ ያደጉትንና የሰለጠኑትን አገልጋዮች በማስታጠቅ ወደ ጦርነት መራቸው።**

**በዚያም የኤላምን ንጉስ ኮልዶጎሞርና ከእርሱ ጋር የተባበሩትን ነገስታት ሁሉ አሸንፎ የአጎቱን ልጅ ሎጥንና ንብረቶቹን ሁሉ አስመለሰ አብርሃም ጠላቶቹን አሸንፎ ከተመለሰ በኋላ የሳሌም ንጉስና የልዑል እግዚአብሄር ካህን መልከፄዴቅ ዳቦና የወይን ጠጅ ይዞ በመምጣት አብርሃምን ባረከው አብርሃምም ከሁሉም ነገር አስራትን ሰጠው። (ዘፍጥረት ምዕራፍ 14)**

**በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሊቀ ካህኑ መልከ ጼዲቅና በእርሱ ስርአት ውስጥ ያሉ ሊቀ ካህናት ታላቅነት በስፋት ተዘርዝሮዋል ሊቀ ካህን መልከ ጼዲቅ «የሰላም ንጉሥ»**

«የፅድቅ ንጉሥ» አባት እናትና የዘር ግንድ የሌለው ነበር ለዘመኑ መጀመሪያም መጨረሻም የለውም ነገር ግን በእግዚአብሄር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል።

መፅሐፍ ቅዱስ የአዲሱን ኪዳን የኢየሱስ ክህነት ከብሉይ ኪዳኑ ሊቀ ካህን ከአሮን ክህነት ጋር በማነፃፀር እንደ መልከፄዴቅ ስርአት ሊቀ ካህናት የነበረውን የኢየሱስ ክርስቶስን ታላቅነት በጥንቃቄ እንድንመለከት ይነግረናል።

የሌዊ ዝርያዎች ካህን በመሆን ከሕዝቡ አስራትን ይሰበስቡ ነበር የአብርሃም ዝርያዎች የሆኑ ቢሆኑም ይህ የእነርሱ ድርሻ ነው ነገር ግን አብርሃም ለሊቀ ካህኑ መልከ ጼዴቅ አስራትን በሰጠ ጊዜ ሌዊ ገናም በአባቱ ወገብ ውስጥ ነበር።

በብሉይ ኪዳን የነበሩት ካህናት ከኢየሱስ ይበልጡ ነበርን? ይህ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ተብራርቷል ኢየሱስ በምድር ላይ ከነበሩ ካህናት በሙሉ ይበልጥ ነበርን? ማንስ በማን መባረክ አለበት? የዕብራውያን መፅሐፍ የሚጀመርው ስለዚህ በመናገር ነው *«አሁን ከሁሉም ንፅፅር ትንሹ በሚሻለው ይባረካል»* አብርሐም በታላቁ ካህን በመልከፄዴቅ ተባርኮ ነበር።

መታመን ያለብን በብሉይ ኪዳን ቅዱስ ድንኳን መስዋዕታዊ ስርአት አማካይነት በእግዚአብሄር ትዕዛዛት ላይ ነውን? ወይስ መታመን ያለብን በውሃና በመንፈስ መስዋዕቱ አማካይነት ሰማያዊ ሊቀ ካህን ሆኖ በመጣልን በኢየሱስ ክርስቶስ?

በምንመርጠው አተረጓጎም ላይ በመመርኮዝ ወይ እንባረካለን አለበለዚያም እንኮነናለን? በእግዚአብሔር ቃል መሰረት በየቀኑ ለምንሰራው ኃጢያት መስዋዕትን እያቀረብን እንኖራለን? ወይስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ራሱን በመስቀል ላይ በመሰዋት ለኛ ዘላለማዊ ደህንነትን ባመጣልን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን? ከእነዚህ ከሁለቱ አንዱን በመምረጥ መኖር መቻል አለብን።

በብሉይ ኪዳን ጊዜ የእስራኤል ሕዝቦች የአሮንና የሌዊን ዝርያዎች ይመለከቱ ነበር በአዲስ ኪዳን ጊዜ ደግሞ ከሁለቱ ከኢየሱስና በአሮን ስር ካሉ ካህናት የትኛው ታላቅ እንደሆነ ብንጠየቅ ኢየሱስ ታላቅ እንደሆነ መናገር እንችላለን ነገረ ግን ሰዎች ይህንን ሐቅ በሚገባ ቢያውቁትም በእምነታቸው የሚከተሉት ጥቂቶች ናቸው፡፡

መፅሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ ግልፅ የሆነ መልስ ይሰጠናል በመሰዊያው ላይ አገልግሎ ከማያውቅ የተለየ ነገር የመጣው ኢየሱስ ሰማያዊውን ክህነት ወስዶ «ክህነቱ ሲለወጥ ሕጉም ደግሞ ይለወጥ ዘንድ ግድ ነው፡፡»

እግዚአብሔር በሙሴ አማካኝነት ለእስራኤል ሕዝቦች ትዕዛዛትንና 613 የሕጉን ዝርዝር ሰጥቶኣቸዋል ሙሴም ለሕዝቡ በትዕዛዛቱና በሕግጋቱ መሠረት መኖር እንዳለባቸው ተናግሮአል ሕዝቡም ያንኑ ለማድረግ ተስማምቷል፡፡

*እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ኪዳን በመተው ሁለተኛውን ኪዳን ያፀናው ለምድን ነው?*

*ምክንያቱም ሰው በመጀመሪያው ኪዳን መሠረት ለመኖር በጣም ደካማ ስለነበር ነው*

በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእስራኤል ሕዝቦች በፔንታቱክ ማለትም በዘፍጥረት፣ በዘፀዓት፣ በዘሌዋውያን፣ በዘኁልቁ ና በዘዳግም ውስጥ ባሉት የእግዚአብሄር ትዕዛዛት ለመኖር ቃል ገብተው ነበር እግዚአብሄር እያንዳንዱን ትዕዛዝ አወጀላቸው

እነርሱም ያለ ምንም ማመንታት እያንዳንዱን ትዕዛዝ ለመታዘዝ ተስማሙ::

ነገር ግን ከዘዳግም በኋላ ከኢያሱ ዘመን ጀምሮ በእግዚብሔር ትዕዛዛት መሠረት በጭራሽ መኖር እንዳልቻሉ እናያለን ከመሳፍንት ጀምሮ እስከ 1ኛ ነገስትና 2ኛ ነገስት ድረስ መሪዎቻቸውን ማሳጣት ጀመሩ በኋላም በተቀደሰው ድንኳን ውስጥ የሚከናወነውን የመስዋዕት ስርአት እስኪለውጡ ድረስ በሰበሱ::

በመጨረሻም በሚልክያስ ውስጥ ምንም እንኳን እግዚአብሔር ነውር የሌለበት ቁርባን እንዲያቀርቡ ያዘዛቸው ቢሆንም ሊቀርቡ ብቃት የሌላቸው እንስሶችን አቀረቡ ካህናቶቹንም «እባካችሁ እለፉትና ይህንን ተቀበሉ» በማለት ለመኑዋቸው በእግዚአብሄር ሕግ መሰረት መስዋዕቶችን በማቅረብ ፋንታ ሕጉን በማንአለብኝነት ለወጡት::

የእስራኤል ሕዝቦች በብሉይ ኪዳን ዘመን አንድ ጊዜም እንኳን የእግዚአብሄርን ሕግ ሙሉ በሙሉ ጠብቀውት አያውቁም በሰርአቱ ውስጥ የተገለጠውን ደህንነት ረሱት ቸልም አሉት ስለዚህ እግዚአብሄር የመስዋዕት ስርአቱን መለወጥ ነበረበት «ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት ጋር አዲስ ኪዳን አደርጋለሁ::»

ኤርምያስ 31:31-34ን እንመልከት *«እነሆ ከእስራኤል ቤትና ከይሁዳ ቤት አዲስ ቃል ኪዳን የምገባበት ወራት ይመጣል ይላል እግዚአብሔር ከግብፅ አገር አወጣቸው ዘንድ እጃቸውን በያዝኩበት ቀን ከአባቶቻቸው ጋር እንደገባሁት ያለ ቃል ኪዳን አይደለም እነርሱ በቃል ኪዳኔ አልፀኑምና እኔም ቸላ አልኩዋቸው ይላል እግዚአብሔር:: ከእነዚያም ቀናት በኋላ ከእስራኤል ቤት ጋር የምትገባው ቃል ኪዳን ይህ ነውና ይላል እግዚአብሔር:: ሕጌን በልቦናችሁ አኖራለሁ በልባችሁም*

*እፅፈዋለሁ እኔም አምላክ እሆናቸኋለሁ እነርሱም ሕዝቤ ይሆኑኛል እያንዳንዱ ሰው ባልንጀራውን እያንዳንዱም ወንድሙን እግዚአብሔርን እወቅ ብሎ አያስተምርም ከታናሽ እስከ ታላቅ ያውቁኛልና ይላል እግዚአብሔር። በደላቸውን እምራቸዋለሁና ኃጢአታቸውን ከእንግዲህ ወዲህ አላስብምና።»*

እግዚአብሔር አዲስ ኪዳን እንደሚያደርግ ተናግሯል አስቀድሞ ከእሰራኤል ሕዝብ ጋር ኪዳን ተጋብቶ ነበር ነገር ግን እነርሱ በእግዚአብሄር ቃል መኖር ተሳናቸው ከዚህ የተነሳ ከሕዝቡ ጋር አዲስ የደህንነት ኪዳን ለማድረግ ወሰነ።

በእግዚአብሔር ፊትም «የምናመልከው አንተን ብቻ ሲሆን ትዕዛዛትህንም እናከብራለን» ሲሉ ቃል ገብተዋል እግዚአብሔርም «ከእኔ በቀር ሌላ አምላክ የላችሁም» ብሏቸዋል የእስራኤል ሕዝቦችም ሲመልሱ «በእርግጥም ሌላ አምላክን አናመልክም አንተ የኛ ብቸኛ አምላካችን ነህ ከአንተ ሌላ አምላክም አይኖረንም» ብለው ቃል ገብተው ነበር ሆኖም ግን ይህን ቃል ለመጠበቅ አልቻሉም።

የሕጉ መሠረት የሆኑት አስርቱ ትዕዛዛት ናቸው «ከእኔ ሌላ አምላክ የለም ወይም የማንኛውንም ነገር አምሳያ አታድርጉ አትስገዱላቸው አታምልኩዋቸውምም ሰንበትን አስታውሳችሁ ቀድሱት የአምላካችሁን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ አትጥሩ እናታችሁንና አባታችሁን አክብሩ አትግደሉ አታመንዝሩ በባልንጀራችሁ ላይ በሐሰት አትመስክሩ የባለንጀራችሁን ቤት አትመኙ።» (ዘፀዓት ምዕራፍ 20)

ሕጉ በ613 ዝርዝር አንቀፆች በንዑስ ተከፋፍሎ በዘመናቸው ሁሉ እንዲጠብቁዋቸው ተሰጥተዋቸው ነበር «በሴቶች ላይ ማድረግ የማይገባቸውን በወንድ ልጆች ላይ ማድረግ የማይገባቸውን በእንጀራ እናቶች ላይ ማድረግ የማይገባቸውን...» የእግዚአብሄር ሕግ መልካም ነገሮችን ሁሉ

እንዲያደርጉና ክፉ ነገሮችንም እንዳያደርጉ አዞዋቸዋል አስርቱ ትዕዛዛትና 613 ዝርዝር አንቀፆች እነዚህ ናቸው።


ሆኖም ግን በሰው ልጆች መካከል አንድም እንኳን እነዚህን ህግጋት ለማክበር የሚችል የለም ስለዚህ እግዚአብሄር ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ይድኑ ዘንድ ሌላ መንገድን ማዘጋጀት ነበረበት።

ክህነቱ የተለወጠው መቼ ነው? ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ከመጣ በኋላ የክህነት ሥርዓቱ ተለውጧል ኢየሱስ ክህነቱን ከአሮን ዘር ከነበሩት ካህናት በሙሉ ተቀበለ እርሱ በሌዊ ስርአት ውስጥ ላሉት ካህናት የውርስ መብት የነበረውን የድንኳኑን መስዋዕት ለየ ሰማያዊውን ሊቀ ክህነት ማገልገል የሚችለው እርሱ ብቻ ነው።

እርሱ ወደዚህ አለም የመጣው የአሮን ዘር ሆኖ ሳይሆን የነገስታት ቤት የሆነው የይሁዳ ዝርያ ሆኖ ነው በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ አማካይነት መስዋዕት ሆኖ ራሱን በማቅረብ የሰውን ዘር ሁሉ ከሐጢያቶቻቸው አዳነ።

ራሱን በማቅረብም የኃጢኣትን ችግር መፍታት እንድንችል አስችሎናል የሰው ዘርን ኃጢኣት በሙሉም በጥምቀቱና በደሙ ስርየት አንፅቷል እርሱ ለሐጢያት ሁሉ አንድ የዘላለም መስዋዕጥ አቀረበ።

## ከክህነት ሥርዓቱ መለወጥ ጋር ተያይዞም የሕግ ለውጥ ነበረ




ውድ ጓደኞቼ በብሉይ ኪዳን የነበረው የክህነት ሥርዓት በአዲስ ኪዳን ላይ ተለውጧል በብሉይ ኪዳን ዘመን ከሌዊ ቤት ከሆኑት የአሮን ዝርያዎች መካከል የሆነው ሊቀ ካህን ባለፈው አመት እስራኤሎች ለሰሩዋቸው ሐጢያቶች የማስተሰርያ መስዋዕት ያቀርባል ሊቀ ካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል መስዋዕት የሆነውን እንስሳ ደም ይዞ ወደ ስርየት መክደኛው ይቀርባል ከመጋረጃው በስተ ጀርባ ወዳለው ቅድስተ ቅዱሳን መግባት የሚችለው ሊቀ ካህኑ ብቻ ነበር፡፡

ሆኖም ግን ከኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት በኋላ የአሮን ክህነት ወደ እርሱ ተላልፏል ኢየሱስ ዘላለማዊውን ክህነት ተቀብሏል ከዚያም ኢየሱስ የሰው ዘር በሙሉ ከሐጢያቶቹ ይድን ዘንድ ራሱን በማቅረብ ዘላለማዊውን ክህነት አገለገለ፡፡

በብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህኑ ለራሱ ሕዝብ ማገልገል ከመቻሉ በፊት እጆቹን በወይፈኑ ራስ ላይ በመጫን የራሱን ሐጢያቶች ማስተሰረይ ነበረበት እጆቹን ጭኖ «አቤቱ ሐጢያት ሰርቻለሁ» በማለት ሐጢያቶቹን ያሻግራል ከዚያም እንስሳውን በማረድ ደሙን በስርየት መክደኛው ላይና ፊት ለፊት ሰባት ጊዜ ይረጨዋል፡፡

ሊቀ ካህኑ አሮን ራሱ ብቁ ካልሆነ ሕዝቡም ምን ያህል ደካማ እንደሚሆን ማሰብ ትችላላችሁ የሌዊ ልጅ የሆነው ሊቀ ካህኑ አሮን ራሱ ሐጢያተኛ ስለነበር የራሱንና የቤተሰቡን ሐጢያቶች ለማስተሰረይ ኮርማ ማቅረብ ነበረበት፡፡

ጌታ በኤርምያስ ምዕራፍ 31 ላይ ሲናገር እንዲህ ይላል «ኪዳኑን አፈርሳለሁ ኪዳንን ከእናንተ ጋር ገብቻለሁ እናንተ ግን አልጠበቃችሁትም የመጀመሪያው ኪዳንም ስለማይቀድሳችሁ ይህንን ትቼ ሌላ አዲስ ኪዳንን እሰጣችኋለሁ ከዚህም በኋላ የማድናችሁ በሕግጋቶቼ ሳይሆን በምሰጣችሁ የውኃና የመንፈስ ወንጌል ነው፡፡»

እግዚአብሔር አዲስ ኪዳንን ገብቶልናል ጊዜው ሲደርስ ኢየሱስ በሰው አምሳል ወደዚህ አለም መጥቶ የአለምን ሐጢያቶች ለመውሰድ ራሱን አቀረበ በእርሱ የምናምነውንም ለማዳን በመስቀል ላይ ደሙን አፈሰሰ በጥምቀቱ አማካይነትም የሰውን ዘር ሁሉ ሐጢያቶች አስወገደ፡፡

የእግዚአብሔርም ሕግ ተወግዶ በሌላ ተተክቷል የእስራኤል ልጆች በእግዚአብሄር ሕግ መሠረት ኖረው ቢሆን ኖሮ መዳን ይችሉ ነበር ነገር ግን እንደዚያ አላደረጉም *«ኃጢኣት በሕግ ይታወቃልና፡፡» (ሮሜ 3:20)*

እስራኤሎች ሐጢያተኞች መሆናቸውንና ሕጉም ሊያድናቸው እንዳልቻለ ይገነዘቡ ዘንድ የእግዚአብሄር ፍላጎት ነበር እርሱ ያዳናቸው በውኃውና በመንፈሱ የደህንነት ወንጌል እንጂ በሥራቸው አይደለም ከእርሱ ወሰን የለሽ ፍቅር የተነሳም እኛን የዓለምን ሕዝቦች በሙሉ ለማዳን አዲስ ኪዳንን ሰጥቶናል ይህም የኢየሱስ የጥምቀትና የመንፈስ ወንጌል ነው፡፡

የጥምቀቱንና የደሙን ትርጉም ሳታውቁ በኢየሱስ የምታምኑ ከሆነ እምነታችሁ ሁሉ ከንቱ ነው ያንን ስታደርጉ ልክ በኢየሱስ ጨርሾ እንዳላመናችሁ ሁሉ ይበልጥ ትታወካላችሁ፡፡

እግዚአብሔር የሰውን ዘር ከሐጢያቶቹ ለማዳን አዲስ ኪዳን እንዳደረገ ተናግሮዋል በውጤቱም እኛ በሕግ ስራዎች ሳይሆን በውሃና በደም አማካይነት ፃድቅ በሆነው የደህንነት ሕግ ድነናል::

ይህ ዘላለማዊ ተስፋው ነው በኢየሱስ ለምናምነው ለእኛም ተስፋውን ፈፅሞልናል ስለ ኢየሱስ ታላቅነትም ነግሮናል በብሉይ ኪዳን ውስጥ ካሉት የአሮን ስርአተ ካህናቶች ጋር በማነፃፀርም እንዴት ታላቅ እንደሆነ ነግሮናል::

በኢየሱስ ውኃና ደም በማመን እኛ ከሌሎች የተለየን ሆነናል እስቲ አስቡት የእናንተ ፓስተር ምንም ያህል ንግግር አዋቂ ቢሆን እንዴት ከኢየሱስ ሊበልጥ ይችላል? ይህ ሊሆን የሚችልበት ምንም አይነት መንገድ የለም እኛ ልንድን የምንችለው በእውነተኛ ው የውኃና የደሙ ወንጌል ብቻ ነው እንጂ የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት በመቀበል ብቻ አይደለም የክህነት ስርዓቱ እንደተቀየረ ሁሉ የደህንነት ህጉም እንዲሁ ተለውጧል::

## የእግዚአብሔር ፍቅር ታላቅነት

*ከእግዚአብሔር*
*ህግና ከፍቅሩ የሚበልጠው*
*የትኛው ነው?*

*ፍቅሩ ነው::*

እኛ ልንድን የምንችለው በኢየሱስ ስናምን ብቻ ነው ኢየሱስ እንዴት እንዳዳነን ማወቃችን እግዚብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ ያሳየናል ታዲያ በትዕዛዛቶቹ

በማመንና በእግዚአብሄር ፍቅር ታላቅነት በማመን መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?

ሕግ አክባሪዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ በቤተክርስቲያን ትምህርቶችና በግል ልምምዶች ላይ የበለጠ ያተኩራሉ ነገር ግን በኢየሱስ ከልብና ሙሉ በሙሉ ማመን የሚመጣው በውሃና በመንፈስ አማካይነት በተፈፀመው ታላቅ ደህንነት ማመን ነው::

ዛሬም እንኳን ብዙ የአዳም ኃጢያት ይቅር ተብሎዋል ይላሉ ነገር ግን በየቀኑ ለሚሰሩዋቸው ሐጢያቶች ንስሐ መግባት እንዳለባቸው ያምናሉ ብዙ ሰዎች ይህንን አምነው በብሉይ ኪዳን ትዕዛዛቶች መሠረት ለመኖር ይሞክራሉ እነርሱ በውሃና በመንፈስ የመጣውን የኢየሱስን ታላቅ ደህንነት አሁንም አልተረዱትም::

በብሉይ ኪዳን እስራኤሎች ከሐጢያቶቻቸው ለመዳን በእግዚአብሄር ሕግ መኖር ነበረባቸው ነገር ግን መዳን አልቻሉም እግዚአብሄር ድካማችንንና ብቁ አለመሆናችንን ስለሚያውቅ ትዕዛዛቱን አስወገዳቸው በስራዎቻችን ብቻ ፈፅሞ መዳን አንችልም ኢየሱስ የሚያድነን በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል አማካይነት እንደሆነ ተናግሮዋል እርሱ «እኔ ራሴ ሁላችሁንም ከሐጢያቶቻችሁ ሁሉ አድናችኋለሁ» ብሎዋል እግዚአብሄርም በዘፍጥረት ውስጥ የተነበየው ይህንኑ ነው::

*«እርሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኰናውን ትቀጠቅጣለህ» (ዘፍጥረት 3:15)* አዳምና ሔዋን ኃጢኣትን ከሰሩና ከወደቁ በኋላ ኃጢአታቸውን ከእግዚአብሔር ለመሰወር ቅጠልን አገልድመው ነበር እግዚአብሔር ግን ጠርቷቸው የደህንነት ምሳሌ ይሆናቸው ዘንድ ቆዳ አለበሳቸው ዘፍጥረት ስለ ሁለት አይነት የደህንነት ልብስ ይናገራል አንዱ የተሰራው ከበለስ ቅጠሎች ሲሆን ሌላው የተሰራው ከቆዳዎች ነበር የትኛ ው የበለጠ ጥሩ እንደሆነ ታስባላችሁ? በእርግጥም እንስሳ የሰው

ልጅን ለመጠበቅ የተሰጠ በመሆኑ የቆዳው ልብስ የበለጠ ተመራጭ ነው።

የበለስ ቅጠል ልብስ በቶሎ ያረጃል እንዲሁም ደግሞ እንደምታውቁት የበለስ ቅጠል የሰው አምስት ጣቶችን ይመስላል ስለሆነም እነዚህን የበለስ ቅጠሎች መልበስ ማለት የአንድን ሰው ኃጢአት ከመልካም ስራ ጀርባ መደበቅ ማለት ነው ይህን ቅጠል ለብሳችሁ ብትቀመጡ ወዲያውኑ ይቀደዳል ልጅ እያለሁ በተመሳሳይ ቅጠሎች የወታደር ልብስ እየሰራን እንጫወት ነበር ምንም ያህል ብጠነቀቅላቸውም እንኳን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ መቀደዳቸው የግድ ነበር በተመሳሳይ መንገድም የሰው ልጅ ስጋ ቅድስናን የማይቻል ያደርገዋል።

ሆኖም ግን የውኃውና የደሙ ደህንነት የኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ ኃጢአተኞችን በሙሉ ማዳኑ የእግዚአብሔርን ፍቅር ታላቅነት ለመመስከር ከበቂም በላይ ነው የእግዚአብሔር ፍቅር ይህንን ያህል ታላቅ ነው።

## አሁንም ድረስ በሕገ - በእግዚአብሔር የሚያምኑ ሰዎች

*ሕግ አክባሪዎች በስራዎቻቸው*
*በየቀኑ አዳዲስ መኀናፀፊያዎችን*
*የሚሠሩት ለምንድነው?*

*ሥራቸው ቅዱስ ሊያደርጋቸው*
*እንደማይችል ስለማያውቁ ነው።*

መጎናፀፊያዎቻቸውን ከበለስ ቅጠል የሚሰሩ በሕግ ላይ የተመሠረተ ሕይወትን ይመራሉ እነዚህ የተደናበሩ ምዕመናን በየጊዜው መጎናፀፊያዎቻቸውን መቀየር ይኖርባቸዋል ወደ ቤተክርስቲያን ሲሄዱ አዳዲስ መጎናፀፊያዎችን ማዘጋጀት አለባቸው «ውድ እግዚአብሔር! ባለፈው ሳምንት ብዙ ኃጢኣት ሰርቻለሁ ሆኖም ጌታ አንተ በመስቀል ላይ እንዳዳንከኝ አምናለሁ አቤቱ እባክህ ሐጢያቶቼን በመስቀሉ ደም እጠብልኝ» በዚያው ጊዜም አዲስ መጎናፀፊያ ይሰፋሉ «ኦ! እግዚአብሄር ይመስገን ሃሌሉያ!» ባለው ደምህ አድነኝ፡፡»

ነገር ግን ወዲያውኑ ቤታቸው ሲደርሱ አዲስ መጎናፀፊያ መስፋት ይኖርባቸዋል ለምን? አሮጌው አርጅቷልና «አቤቱ ባለፉት ሶስት ቀናት እንደገና ሐጢያት ሰርቻለሁ እባክህ ይቅር በለኝ» በተደጋጋሚ አዳዲስ የንስሐ መጎናፀፊያዎችን ሰርተው ይለብሳሉ፡፡

በመጀመሪያ ልብሶቹ ለተወሰኑ ቀናት ያህል ሊያገለግሉ ይችሉ ይሆናሉ ነገር ግን ከጥቂት ጊዜ ምኋላ በየቀኑ አዳዲስ መጎናፀፊያዎች ያስፈልጉዋቸዋል በእግዚአብሔር ሕግ ለመኖር ስለማይችሉ ሁልጊዜም በራሳቸው የሚያፍሩ ይሆናሉ «ኦ! ይህ በጣም የሚያሳፍረኝ ነው ጌታዬ! ኦ ጌታ! አሁንም ኃጢአትን አድርጌኣለሁ!» በዚህም የተነሳ በድጋሚ የምህረትን ልብስ መስፋት ይኖርባቸዋል «ኦ ጌታዬ! በየቀኑ ከበለስ ቅጠል ልብስን መስራት በጣም አስቸጋሪ ነው» ሁልጊዜ አዳዲስ መጎናፀፊያዎችን በመስፋት ይለፋሉ፡፡

እንደዚህ አይነት ሰዎች ሁልጊዜም ወደ ጌታ የሚጮሁት ኃጢአታቸውን ለመናዘዝ ነው ከናፍርቶቻቸውንም በመንከስ ወደ እግዚአብሔር ይጮኃሉ ይህን ማድረግ ሲሰለቻቸውስ ምን ያደርጋሉ?

በዓመት አንዴ ወይም ሁለት ጊዜ ወደ ተራሮች በመሄድ

ይፀልያሉ ይጾማሉ በዚህም ጠንካራና በቀላሉ የማያረጁ መጎናፀፊያዎችን ለመስራት ይሞክራሉ «አቤቱ ኃጢአቶቼን ሁሉ አንጻልኝ አድሰኝ አቤቱ አምናለሁ» እያሉም ይጸልያሉ በሌሊት መጸለይም የተሻለ ስለሚመስላቸው ቀኑ አልፎ ጨለማ እስከሚመጣ ድረስ ዕረፍት ያደርጋሉ አለዚያም ደግሞ ወደ ጨለማ ዋሻዎች በመሄድ ወደ እግዚአብሔር ይጮሃሉ *«♪ጌታ ሆይ ባንተ አምናለሁ!» «በተመስጦ አእምሮ እፀልያለሁ! ንስሐ እገባና ልቤን በተደቆሰ ሐሳብ እሞላዋለሁ♪»* ድምፃቸውንም ከፍ አድርገው «አምናለሁ» ብለው ይጮኃሉ በዚህ መንገድ ለረጅም ጊዜ እንደሚቆይ ተስፋ የሚያደርጉትን የተለየ መጎናፀፊያ ይሰራሉ ነገር ግን ማርጀቱ አይቀርም::

ኦ! ከዚህ አይነቱ የፀሎት ተራራ መመለስ ምን አይነትን ስሜት ይፈጥር ይሆን! ህይወትን እንደሚያድስ እስትንፋስ ወይም ደግሞ በፀደይ እንደሚፈነዳ አበባ፣ ልባቸው በሐሴትና በምስጋና የተሞላ ይሆናል ከተራራው መንፈስ ይበልጥ ንፁህ የመሆን ስሜት እየተሰማቸው ልዩና አዳዲስ የሆኑትን መጎናፀፊያዎቻቸውን ለብሰው አለምን ይጋፈጣሉ::

ወደ ቤታቸው ተመልሰው እንደበፊቱ ኑሮአቸውን ሲጀምሩ ግን እነዚህ ልብሶቻቸው መቆሸሸና ማርጀት ይጀምራሉ::

ጓደኞቻቸውም «የት ነበራችሁ?» ብለው ሲጠይቋቸው:-

«ራቅ ወዳለ ቦታ ሄጄ ነበር» ይላሉ::

«የተወሰነ ክብደታችሁን የቀነሳችሁ ትመስላላችሁ» ሲሏቸውም

«አዎን ሆኖም ግን ያ ሌላ ታሪክ ነው» ይላሉ::

በጭራህ ስለመፆማቸው አይናገሩም ወደ ቤተ ክርስቲያን እየሄዱም በዚያ ይፀልያሉ «በሴቶች ፍትወት አልያዝም አልዋሽም የባለንጀራዬን ንብረት አልመኝም ሰውን ሁሉ አፍቅራለሁ» ብለውም ቃል ይገባሉ::

ሆኖም ግን በጣም የተዋበችን ሴት በሚመለከቱበት ጊዜ በልባቸው የነበረው ቅድስና በሙሉ ወደ አመንዝራነት ይቀየራል «ተመልከቱ ቀሚሷ ምን ያህል አጭር እንደሆነ ቀሚሶች ይበልጥኑ እያጠሩ ነው! እነዚህን ውብ እግሮች ደግሜ ማየትን እሻለሁ!» ወዲያውኑ ደግሞ «ኦ! ጌታ! እንደገና ኃጢኣትን ሰርቻለሁ!» ይላሉ::

ሕግ አክባሪዎች ፃድቃን ይመስላሉ ነገር ግን እነረሱ በየቀኑ አዳዲስ መጎናፀፊያዎችን እንደሚሰሩ ማወቅ አለባችሁ ሕግ አጥባቂነት በበለስ ቅጠሎች ማመን ነው ይህ ደግሞ የተሳሳተ እምነት ነው ብዙ ሰዎች በእግዚአብሄር ሕግ መሠረት ፃድቅ ሆነው ለመኖር አጥብቀው ይሞክራሉ በተራራ ላይ ቆመው ላንቃቸው እስኪበጠስ ድረስ ይጮኻሉ::

ሕግ አክባሪዎች በቤተ ክርስቲያን ፀሎትን ሲመሩ የተለዩና መስህብ ያላቸው ይመስላሉ «በሰማይ ያለኸው ቅዱስ አባታችን! ያለፈውን ሳምንት በሙሉ በኃጢአት አሳልፈናል እባክህን ይቅር በለን...» በማለት በእንባ እየታጠቡ ይፀልያሉ ብዙዎቹም ፀሎት የሚመሩትን ሰዎች «ይህ ሰው በተራሮች ላይ በመፆምና በመፀለይ ረጅም ጊዜ ያሳለፈ መሆን አለበት» ብለው ያስባሉ ሆኖም ግን የዚህ ሰው እምነቱ በሕግ ላይ የተመሰረተ ስለሆነ የፀሎቱ ጊዜ እንኳን በአግባቡ ሳያበቃ የሕግ አክባሪው ልብ በዕብሪትና በሐጢያት መሞላት ይጀምራል::

ሰዎች ከበለስ ቅጠል አንድ የተለየ ልብስን ቢሰሩ ምናልባትም ለሁለት ሦስት ወራት ድረስ ሊቆዩ ይችሉ ይሆናሉ ሆኖም ግን ከተወሰነ ጊዜ በኋላ እነዚህ ልብሶች እያረጁና የአገልግሎት ዘመናቸውም እያለቀ ይመጣል አዲስ መጎናፀፊያ በመስራትም ግብዝ የሆነውን ሕይወታቸውን መኖር ይቀጥላሉ ሕግ አክባሪዎች ለመዳን ሲሉ የሚኖሩት ሕይወት ይህ ነው ያለ ማቋረጥ ከበለስ ቅጠሎች አዳዲስ መጎማፀፊያዎችን ይሰራሉ::

ሕግ አጥባቂነት በበለስ ቅጠሎች የተመሰለ እምነት ነው ሕግ አክባሪዎች «ሁላችሁም ባለፈው ሳምንት ሐጢያት ሰርታችኋል አልሰራችሁም? እንግዲያውስ ንስሐ ግቡ» ብለው ይነግሩዋችኋል::

ሕግ አክባሪ ድምፁን እንዴት ቅዱስ እንደሚያስመስል ያውቅበታል «አቤቱ! አዝናለሁ በሕጉ አልኖርሁም ትዕዛዛቶችህን አልጠበቅሁም አቤቱ ይቅር በለኝ አንድ ጊዜ ብቻ ይቅር በለኝ::»

ምንም እንኳን በሕጉ መሠረት በጥብቅ ለመኖር የሚፈልጉ ቢሆንም እንደዚያ ሊኖሩ ግን ፈፅሞ አይችሉም በእርግጥም እንደዚህ በማድረጋቸው እነርሱ የእግዚአብሔርን ሕግና እግዚአብሔርን ራሱንም እየተፈታተኑት ነው እነርሱ በእግዚአብሔር ፊት ዕብሪተኞች ናቸው::

## የቹዳል ቤይ ፍላጎቶች

*እግዚአብሔር ሕጉን ወደ ጎን*
*የተወው ለምንድን ነው?*

*እኛን ከሐጢያት ለማዳን*
*ጥቅም ስላለው ነው::*

በአንድ ወቅት ቹዳል ቤይ ተብሎ የሚጠራ ወጣት ነበር በ1950ው የኮሪያውያን ጦርነት ወቅት የኮሚዩኒስት ወታደሮች መጥተው ፅኑ የሆነውን ሐይማኖታዊ እምነቱን አስጥለው ኮሙዩኒስት ሊያደርጉት በሰንበት ቀን ግቢያቸውን ያፀዳ ዘንድ

ጠየቁት ይህ ሰው ግን ኃይማኖቱ በሰንበት ቀን እንዲሰራ ስለማይፈቅድለት እሺ አላለም ወታደሮቹ በተደጋጋሚ ቢጠይቁትም ይህ ሰው ግን አሻፈረኝ አለ፡፡

በመጨረሻም ወታደሮቹ ይህን ሰው ከዛፍ ጋር አስረውት መሳሪያ በመደገን «የምትመርጠው የትኛውን ነው? ግቢውን መጥረግ ወይስ መሞት?» ብለው ጠየቁት፡፡

ውሳኔ እንዲወስን ባስገደዱት ጊዜ እንዲህ አላቸው «በተቀደሰው የሰንበት ቀን ከምሰራ መሞት ይሻለኛል፡፡»

«አንተ ራስህ ምርጫህን ስለወሰንህ እኛም እናስወግድሃለን» በማለት ገደሉት በኋላም ያልተናወጠውን ሐይማኖታዊ እምነቱን ለማስታወስ የቤተክርስቲያን መሪዎች ዲያቆን አድርገው ሾሙት፡፡

ፅናቱ ጠንካራ ቢሆንም ሐይማኖታዊ እምነቱ ፈሩን የለቀቀ ነበር ግቢውን ያልጠረገውና ወንጌልን ለእነዚያ ወታደሮች ያልሰበከው ለምንድነው? ለምን እልኸኛ ሆኖ ሞተ? እግዚአብሄር በሰንበት ቀን ስራ ስላልሰራ ያመሰግነዋልን? አያመሰግነውም፡፡

እኛ መንፈሳዊ ህይወትን መምራት አለብን በእግዚአብሄር ፊት አስፈላጊው ነገር እምነታችን እንጂ ሥራዎቻችን አይደሉም የቤተክርስቲያን መሪዎች እንደ ቱዳል ቤይ ያለን ሰው ማወደስ ይሻሉ ምክንያቱም የቤተክርስቲያናቸውን የበላይነትና ትክክለኛ ነት ማሳየት ይፈልጋሉና ነገሩ ኢየሱስን ከተገዳደሩት ግብዝ ፈሪሳውያን ጋር ይመሳሰላል፡፡

ከህግ አክባሪዎች ልንማር የምንችለው ምንም ነገር የለም መማር ያለብን ስለ መንፈሳዊ እምነት ነው ኢየሱስ ለምን እንደተጠመቀና በመስቀል ላይ ደሙን እንዳፈሰሰ ማወቅና በትክክለኛው የውኃና የመንፈስ ወንጌል ማመን አለብን፡፡

በመጀመሪያ ለጥያቄዎቻችን መልስ ማግኘት አለብን

ከዚያም ዳግም ይወለዱ ዘንድ ለአለም ሕዝቦች ሁሉ ወንጌልን ለማሰራጨት መሞከር አለብን ራሳችንን ለመንፈሳዊ ስራዎች ማነሳሳት አለብን።

አንድ ሰባኪ «እንደ ወጣቱ ቹዳል ቤይ ሁኑ ሰንበትንም አክብሩ!» ቢላችሁ ይህ ሰው ያለምንም ጥርጥር የሚፈልገው እናንተ እሁድ እሁድ ቤተ ክርስትያን እንድትሄዱለት ብቻ ነው።

ሌላ ታሪክ ደግሞ ልንገራችሁ በየእሁዱ ቤተክርስቲያን ለመሄድ ስትል በብዙ መከራዎች ውስጥ ያለፈች አንዲት ሴት ነበረች አማቶችዋ ክርስቲያኖች ስላልነበሩ ወደ ቤተክርስቲያን እንዳትሄድ ለመከልከል አብዝተው ይሞክሩ ነበር በእለተ እሁድ ስራ እንድትሰራ ይነግሩዋታል ነገር ግን በየቅዳሜዎቹ ምሽት ወደ እርሻ ሄዳ በጨረቃ ብርሃን በመስራት ቤተሰቡ በዕለተ እሁድ ወደ ቤተክርስቲያን ከመሄድ ለመከልከል ማማኻኛዎች እንዳይኖራቸው አደረገች።

በእርግጥም ወደ ቤተክርስቲያን መሄድ በጣም ጥሩ ነው ነገር ግን በየእሁዱ ምን ያህል ታማኞች እንደሆንን ለማሳየት ስንል ብቻ ወደ አምልኮ መምጣት በቂ ነውን? እውነተኛው እምነት ከውኃውና ከመንፈስ ወንጌል እንደገና መወለድ ነው እውነተኛ እምነት የሚጀምረው በዳግም ውልደት ነው።

በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት በመኖር ልትድኑ ትችላላችሁን? በፍፁም። እኔ እየነገርኳችሁ ያለሁት ህጉን እንድተዉት አይደለም ነገር ግን የሕጉን አንቀፆች በሙሉ መጠበቅ የማይቻል መሆኑን ሁላችንም እናውቃለን።

በያዕቆብ መልዕክት 2:10 ላይ እንዲህ ይላል *«ሕግን ሁሉ የሚጠብቅ ነገር ግን በአንዱ የሚሰናከል ማንም ቢኖር በሁሉ በደለኛ ይሆናል»* ስለሆነም በመጀመሪያ እንዴት ከውኃና ከመንፈስ ለመወለድ እንደምትችሉ አስቡ በመቀጠልም ይህን ወንጌል ወደምትሰሙበት ቤተ ክርስቲያን ሂዱ ዳግም

ከተወለዳችሁ በኋላም በእምነት ልትኖሩ ትችላላችሁ በመጨረሻም ጌታ በሚጠራችሁ ጊዜ በፊቱ በደስታ ልትመላለሱ ትችላላችሁ::

ወደ ሐሰተኛ ቤተ ክርስቲያኖች በመሄድ ጊዜያችሁንና ገንዘባችሁን በማይገባ ምፅዋት አታባክኑ የውሸት ካህናት እናንተን ገሃነም ከመግባት ሊያድኗችሁ አይችሉም በመጀመሪያ እንደገና ለመወለድ የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል እወቁት::

ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣበትን ምክንያት እስቲ አስቡት በሕጉ መሰረት በመኖር የእግዚአብሔርን መንግስት ለመውረስ የምንችል ቢሆን ኑሮ እርሱ ወደዚህ ምድር መምጣት አያስፈልገውም ነበር ከመጣ በኋላ የክህነቱ ሥርዓት ተለውጧል ሕግን ማክበር ያለፈ ጊዜ ትውስታ ሆኖዋል ከመዳናችን በፊት በሕጉ መሠረት በመኖር መዳን እንደምንችል እናስብ ነበር ነገር ግን ይህ የእውነተኛ እምነት ምልክት አይደለም::


ኢየሱስ ከፍቅር የተነሳ በጥምቀቱ ውኃ በደሙና በመንፈሱ ከዓለም ኃጢአቶች በሙሉ አድኖናል በዮርዳኖስ በመጠመቁ በመስቀል ላይ ደሙን በማፍሰሱና በትንሳኤው ደህንነታችንን ፈፅሞታል::

እግዚአብሔር የመጀመሪያዎቹን ስርአቶች ያስወገዳቸው ደካማና ረብ የለሽ በመሆናቸው ነው *«ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶኣል እነርሱም ያለ መሃላ ካህናት ሆነዋልና» (ዕብራውያን 7:19-20)* ኢየሱስ መሃላ ገብቶ በጥምቀቱና በደሙ ከኃጢኣት ሁሉ አንፅቶናል ከሕግ አክባሪነት የመነጨ ሰማዕትነት ፍሬ አልባ ሞት ነው እንዲሁም ደግሞ ትክክለኛው እምነት በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን ነው::

ፍሬያማ እምነት ሊኖረን ይገባል ለነፍሳችሁ ጥሩ የሚመስላችሁ የትኛው ነው? በየጊዜው ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድና ሕጉን በመጠበቅ መኖር ይሻላል ወይስ የውኃውና የመንፈሱ ወንጌል ወደሚሰበክበት ትክክለኛው የእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ዳግም መወለድ? የትኛው ቤተ ክርስቲያን ወይም ሰባኪ ነው ለነፍሳችሁ የሚበጀው? በደንብ አስባችሁበት ለነፍሳችሁ ጥሩ ይሆናል የምትሉትን ምረጡ፡፡

እግዚአብሔር ነፍሳችሁን የሚያድነው የውሃውንና የመንፈሱን ወንጌለ ቃላቶች በያዘ ሰባኪ አማካይነት ነው ሁሉም ሰው ለራሱ ነፍስ ኃላፊነቱን መውሰድ አለበት እውነተኛ አማኝ ነፍሱን ለእግዚአብሔር የሚሰጥ ነው፡፡

## ኢየሱስ ካህን የሆነው በመሐላው መሠረት ነው




በዕብራውያን 7:20-21 ላይ እንዲህ ይላል *«እነርሱም ያለ መሐላ ካህናት ሆነዋልና እርሱ ግን ጌታ አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ማለ አይፀፀትም ብሎ በተናገረለት ከመሐላ ጋር ካህን ሆኖአልና ያለ መሐላ ለሚሻል*

*ኪዳን ዋስ ሆኖአል::»*

እንዲሁም በመዝሙረ ዳዊት 110:4 ላይ እንዲህ ይላል *«አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ እግዚአብሔር ማለ አይፀፀትም»* ጌታ መሐላ አድርጓል ከእኛም ጋር ቃል ኪዳን በመጋባት ኪዳኑን በተፃፈው ቃሉ አማካይነት አሳይቶናል «እኔ በመልከጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ሊቀ ካህን እሆናለሁ መልከ ጼዴቅ የፅድቅና የሰላም ንጉስ ለዘላለምም ሊቀ ካህን ነው ለደህንነታችሁ በመልከ ጼዴቅ ሥርዓት መሠረት ለዘላለም ሊቀ ካህን እሆናለሁ::»

ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ ለተሻለው ኪዳን ዋስ ሆነ (ዕብራውያን 7:22) በኮርማዎችና በፍየሎች ደም ፈንታ ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ለማስወገድ በመጠመቅና በመስቀል ላይ በመድማት መስዋዕት አድርጎ ራሱን አቀረበ::

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሊቀ ካህኑ ሲሞት ልጁ 30 ዓመት ሲሆነው ካህነቱን ይረከባል እርሱ አርጅቶ ልጁ 30 አመት ሲሆነው ደግሞ ክህነቱን ለልጁ ያስረክባል::

በዚህም ብዙ የካህናት ዝርያዎች ነበሩ ስለሆነም ዳዊት ሁሉም በየተራ የራሳቸውን ሚና የሚጫወቱበትን ዘዴ ቀየሰ ሁሉም የአሮን ዘሮች በሙሉ በክህነት ለማገልገል ቃል ስለተገባላቸው ሁሉም በክህነት የማገልገል መብቱ አላቸው ሉቃስ እንዳለው *«ከአቢያ ክፍል የሆነ ዘካርያስ የሚባል አንድ ካህን ነበረ...እርሱም በክፍሉ ተራ በእግዚአብሔር ፊት ሲያገለግል...»*

ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ ክህነቱን ለዘላለም ለማገልገል ወሰደ ሊመጣ ላለው በጎ ነገር ካህን ሆኖ መጣ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን ደህንነትም ፈጸመ::

የአሮን ዘሮች ደካሞችና በስጋቸውም ምሉአን የነበሩ አልነበሩም አንድ ሊቀ ካህን ሲሞት የሚሆነው ምንድን ነው?

ልጁ በተራው ክህነቱን ይቀበለዋል ነገር ግን እንደዚህ ያሉ መስዋዕቶች የሰውን ዘር ደህንነት ለማረጋገጥ በጭራሽ በቂ አልነበሩም በሰው ዘር ማመን እውነተኛና ሙሉ እምነት ሊሆን አይችልም እንዲሁም ደግሞ መስዋዕት ብቻውን የሰው ልጆችን ሊያድን አይችልም በሰው ያለ እምነት ሙሉ ሊሆን አይችልም።

በአዲስ ኪዳን ዘመን ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም መጣ እርሱ ለዘላለም የሚኖር በመሆኑ በየጊዜው መስዋዕትን ማቅረብ አላስፈለገውም በጥምቀቱም ኃጢአቶቻችንን በሙሉ ለዘላለም ወስዷል በእርሱ የሚያምኑትን በሙሉ ከኃጢኣት ነፃ ለማድረግ ራሱን በመስዋዕትነት አቅርቧል።

አሁን እርሱ ሕያው ሆኖ ስለ እኛ ሊመሰክር በእግዚብሔር ቀኝ ተቀምጦዋል «ውድ አባት እነርሱ አሁንም ምሉእን ላይሆኑ ይችላሉ ነገር ግን በእኔ አምነዋል ሐጢያቶቻቸውን ከረጅም ጊዜ ምፊት አላስወገድሁላቸውምን?» ኢየሱስ ለደህንነታችን የዘላለም ሊቀ ካህን ነው።

በምድር የነበሩት ካህናት ሙሉ ሆነው አያውቁም በሚሞቱበት ጊዜም ልጆቻቸው ክህነቱን ይወርሳሉ ጌታችን ለዘላለም ይኖራል ወደዚህ ምድር በመምጣት በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በዮርዳኖስ በመጠመቅና ለኛ ኃጢአትም ሲል በመስቀል ላይ በመድማት ዘላለማዊ ደህንነትን አረጋግጦልናል።

*«የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢኣት ማቅረብ የለም» (ዕብራውያን 10:18)* ኢየሱስ እስከመጨረሻው ሰዓት ድረስ ስለኛ ደህንነት ይመሰክራል ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል ተወልዳችኋልን?

*«ቅዱስና ያለ ተንኮል ነውርም የሌለበት ከኃጢአተኞችም የተለየ ከሰማያትም ከፍ ከፍ ያለ» (ዕብራውያን 7:26) «ሕጉ ድካም ያላቸውን ሰዎች ሊቀ ካህናት አድርጎ ይሾማልና ከሕግ በኋላ የመጣ የመሐላው ቃል ግን ለዘላለም ፍጹም የሆነውን*


*ልጅ ይሾማል፡፡» (ዕብራውያን 7:28)*

**ልነግራችሁ የምወደው ነገር ቢኖር ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ ውኃና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ከኃጢአት ሁሉ እንዳዳነን ነው እርሱ እኛን ከኃጢአት ሁሉ ነፃ ያደረገን በሕጉ ስለኖርን ሳይሆን ነገር ግን ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶ ለዘላለም ስለተፈረደበት ነው፡፡**

**በዘላለማዊ ደህንነት አማካኝነት እኛን ለዘላለም ከኃጢኣት ሁሉ እንዳዳነን ታምናላችሁን? ካመናችሁ ድናችኋል ካላመናችሁ ደግሞ ስለ ኢየሱስ ዘላለማዊ ምህረት ብዙ የምትማሩት ነገር ይቀራችኋል ማለት ነው፡፡**

**እውነተኛ እምነት ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል ይመጣል ይህም ሙሉ በሙሉ በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሰረተ ነው ዘላለማዊና ሰማያዊ ሊቀ ካህን የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ አማካይነት ዘላለማዊ አዳኛችን ሆንዋል፡፡**

## እምነታችንን ሙሉ በሙሉ መረዳት አለብን



በትክክለኛው መንገድ እንዴት በኢየሱስ ማመን እንደምንችልና እምነታችን እንደምናቀና ማሰብ ይኖርብናል ተገቢና ትክክለኛ በሆነ መንገድ በኢየሱስ ማመን የምንችለው እንዴት ነው? ይህንን ማድረግ የምንችለው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ወንጌል በማመን ነው::

ትክክለኛው እምነት የራሳችንን የተሳሳቱ አስተሳሰቦች ሳንጨምር በኢየሱስ ስራ በጥምቀቱና በደሙ ማመን ነው ይህ እውነት እንደሆነ ታምናላችሁን? መንፈሳዊ ሁኔታችሁ እንዴት ነው? በራሳችሁ ስራዎችና ጥረቶች ላይ አብዝታችሁ ትደገፋላችሁን?

በኢየሱስ ማመን ከጀመርኩ ብዙ ጊዜ ባይሆነኝም ከሕግ አጥባቂነት የተነሳ ለ10 ዓመታት ያህል ተሰቃይቻለሁ ውሎ አድሮም በእንደዚያ አይነቱ ሕይወት ተሰላቸሁ ስለዚያ ጊዜ ማስታወስ እንኳን አልፈልግም ባለቤቴ እዚሁ ተቀምጣለች ነገሩ ለእኛ ምን ያህል አስከፊ እንደነበር ታውቃለች እሁድ እሁድ ባለቤቴን «የኔ ማር፣ ዛሬ እንዝናና እስቲ!» እላታለሁ::

«ሆኖም ግን ዛሬ እሁድ ነው!»

በእሁድ ልብስ እንኳን አታጥብም አንድ እሁድ ቀን የውስጥ ሱሪዬ ተቀደደብኝ እስከ ሰኞ መጠበቅ እንደሚኖርብኝ ነገረችኝ እንዲያውም ሰንበትን በትክክል መጠበቅ እንዳለብን ስሟዘዝ የነበርሁት እኔ ነኝ ነገር ግን አስቸጋሪ ነበር በእሁድ ቀናቶች በጭራሽ አርፈን አናውቅም ምክንያቱም ሰንበትን በትክክል መጠበቅ አስቸጋሪ ነበር እነዚያን ቀናት አሁንም አስታውሳቸዋለሁ::

ውድ ጓደኞቼ በኢየሱስ በትክክል ለማመን በጥምቀቱና በደሙ ኃጢአቶቻችን በሙሉ መታጠባቸውን ማመን አለብን እውነተኛ እምነት በኢየሱስ መለኮታዊነትና ሰብአዊነት እንደዚሁም በዚህ አለም ላይ ባከናወናቸው ነገሮች ሁሉ ማመን

ነው እውነተኛው ምዕመን በኢየሱስ ቃሎች ሁሉ ያምናል::

«በኢየሱስ ማመን» ማለት ምን ማለት ነው? ይህ በኢየሱስ ጥምቀትና ደም ማመን ማለት ነው ይህን ያህል ቀላል ነው ማድረግ የሚጠበቅብን መፅሐፍ ቅዱስን በማንበብ እውነተኛውን ወንጌል ማመን ነው እኛ ሁላችንም በትክክለኛው መንገድ ማመን አለብን::

«ጌታ ሆይ! አመሰግንሃለሁ አሁን በእኔ ጥረት እንዳልሆነ አውቃለሁ! ሐጢያት በሕግ ይታወቃል (ሮሜ 3:20) አሁን ሁሉንም ነገር ተረድቻለሁ እኔ እንደዚያ ያሰብኩት ሕጉ ጥሩ ስለነበር የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ስለሆነና በእሱ መኖር እንዳለብኝ ስላሰብኩ ነው አሁንም ድረስ በዚያ ለመኖር ብዙ እጥር ነበር ሆኖም ግን በሕጉ ለመኖር መሞከሬ ስህተት መሆኑን አሁን ተገነዘብኩ አሁን የእግዚአብሔርን ትዕዛዛት ለመጠበቅ የማልችል መሆኔን ተረዳሁ ሆኖም ግን በእግዚብሔር ሕግ መሰረት ልቤ በኃጢአት የተሞላችና ክፋት ያለባት መሆኗን ተገንዝቤኣለሁ አሁን ሕጉ የተሰጠን በልባችን ኃጢአተኞች መሆናችንን እንድናውቅ መሆኑን አምናለሁ ኦ! ጌታዬ ያንተን ፍላጎት ሳልረዳ ሕጉን ለመጠበቅ ታገልኩ ይህን መሞከር እንኳን በጣም ትምክህተኝነት ነው አሁን እፀልያለሁ አሁን ኢየሱስ የተጠመቀውና የደማው ለኔ ደህንነት መሆኑን አውቃለሁ አምናለሁ!»

እናንተ ማመን ያለባችሁ በእውነትና በግልፅ ነው ማመን ያለባችሁ በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተፃፉት ቃሎች ብቻ ነው ሙሉ በሙሉ ልትወለዱ የምትችሉበት ብቸኛው መንገድም ይህ ነው::

በኢየሱስ ማመን ማለት ምን ማለት ነው? በተወሰነ ጊዜ ልናሟላው የምንችለው ነገር ነውን? እምነታችን ልንሰራለት የሚገባ ኃይማኖት ነውን? ሰዎች አንዳንዴ አማልክትን ይሰራሉ

በመቀጠልም ለእነዚህ አማልክት የሚመጥን ኃይማኖትን ይፈጥራሉ ኃይማኖት ሰው የሚሰራበት ሂደት ሲሆን መዳረሻውም የሰው መልካምነት ነው።

እምነት ምንድን ነው? እምነት በእግዚአብሔር ማመንና እሱን ማምለክ ማለት ነው የኢየሱስን ደህንነትና ምህረት ስላየን ለዚህም እናመሰግነዋለን ይህ እውነተኛ እምነት ነው በእምነትና በኃይማኖት መካከል ያለው ልዩነት ይህ ነው በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ካወቃችሁ ስለ እምነት በመረዳታችሁ 100 ማርክ ታገኛላችሁ።

ዳግም ውልደትና ያላገኙ የቃለ እግዚአብሄር ምሁራን በኢየሱስ ማመን እንዳለብንና በቅድስና መኖር እንደሚገባን ይነግሩናል በሕጉ በመኖር ብቻ አማኞች ልንሆን እንችላለን? በእርግጥ ጥሩዎች መሆን አለብን ከእኛ ዳግም ከተወለድነው የበለጠ ጥሩ የሆነስ አለን?

ዋነኛ ጉዳዩም ደግሞ እነርሱ ይህን የሚናገሩት ለኃጢኣተኞ መሆኑ ነው በአንድ ሐጢያተኛ ውስጥ 12 አይነት ሐጢያቶች አሉ እንዴት በቅድስና ሊኖር ይችላል? ምናልባትም ይህንን በአእምሮው ቢያምንበትም በልቡ ግን አይቀበለውም አንድ ኃጢአተኛ ከቤተ ክርስቲያን ሲወጣ በቅድስና መኖር ከፅንሰ ሐሳብ የዘለለ አይሆንም ደመ ነፍሱ ወደ ሐጢያት ይነዳዋል።

ስለዚህ በሰማይ መንግስት የዘላለም ሊቀ ካህን በሆነው አምነን በሕጉ ለመኖር ወይም በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ለማመን በልባችን መወሰን ይኖርብናል።

ኢየሱስ ለሚያምኑበት እውነተኛ ሊቀ ካህን መሆኑን አስታውሱ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደሙ አማካይነት የተገኘውን እውነተኛ ደህንነት ለማወቅና በማመን ሁላችንም እንዳን።

# ዳግም የተወለዱት ስለ ዓለም መጨረሻ አይሰጉም

*ዳግም የተወለዱት ስለ ዓለም መጨረሻ የማይሰጉት ለምንድን ነው?*

*ምክንያቱ፣ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ያላቸው እምነት ነፃ ስላወጣቸው ነው፡፡*

ዳግም የተወለዳችሁ ከሆነ የዓለም መጨረሻ ቢቃረብ ምንም የሚያሰጋችሁ ነገር አይኖርም ብዙ በኮርያ የሚኖሩ ክርስቲያኖች ዓለም በጥቅምት 28:1992 ዓ.ም ትጠፋለች ብለው ያምኑ ነበር እንዲሁም ደግሞ ቀኑ በጣም አስፈሪና አስጊ እንደሚሆን ያወሩ ነበር ነገር ግን የተናገሩት ሁሉ ውሸት ሆነ በተጨባጭ ዳግም የተወለዱ እስከ መጨረሻዋ ቅፅበት ድረስ ወንጌልን እያሰራጩ በቅድስና ይኖራሉ የዚህ ምድር መጨረሻ እስከሚመጣ ድረስ ማድረግ ያለብን አንድ ነገር የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል መስበክ ነው፡፡

ሙሽራው ሲመጣ በተጨባጭ ከውሃና ከመንፈስ የተወለዱት ሙሽሮች «ኦ! በመጨረሻ መጣህ! ስጋዬ አሁንም ድረስ ጎዶሎ ነው አንተ ግን ወደኸኝ ከሐጢያቶቼ ሁሉ አዳንኸኝ ስለዚህ በልቤ ውስጥ ሐጢያት የለም አቤቱ አመሰግንሃለሁ አንተ አዳኜ ነህ!» በማለት በታላቅ ደስታ ይገናኙታል፡፡

ኢየሱስ ለፃድቃን ሁሉ መንፈሳዊ ሙሽራ ነው ሠርጉ የሚከናወነው ሙሽራው ሙሽራይቱን ስለወደዳት እንጂ ሙሽራይቱ ስለወደደችው አይደለም አንዳንድ ጊዜ ምዚህ አለም ላይ እንደዚህ እንደሚሆን አውቃለሁ በሰማይ ግን ሠርጉ ስለ

መከናወኑ የሚወሰነው ሙሽራው ነው ሙሽሮቹ ማንም ይሁኑ በፍቅርና በደህንነት ስጦታው ላይ ተመስርቶ ማግባት የመረጠው ሙሽራው ነው ሠርጉ በሰማይ የሚከናወነው እንደዚህ ነው፡፡

ሙሽራው ስለሙሽሮቹ በሙሉ ያውቃል ምክንያቱም የሚወዳቸው ሙሽሮች በሙሉ ኃጢአተኞች ስለሆኑና እርሱም ራርቶላቸው ኃጢአታቸውን በሙሉ በጥምቀት ወደ እርሱ ካስተላለፈ በኋላ በመስቀል ላይ በመድማት ፍርድን ስለተቀበለላቸው ነው፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ወደ ምድር የመጣው ከአሮን ወገን ሆኖ አይደለም፡ ወደዚህ ምድር የመጣው ምድራዊ መስዋዕትን ለማቅረብ አይደለም ይህን የሚሰሩ ብዙ ከሌዊ ወገን የሆኑ የአሮን ዝርያዎች ነበሩ፡፡

በእርግጥም የብሉይ ኪዳን መስዋዕቶች ዋናው ተዋናይ ራሱ ኢየሱስ ነበር ስለዚህ እውነተኛው ነገር ወደዚህ አለም ሲመጣ ጥላው ምን ሆነ? ጥላው ተወገደ፡፡

ኢየሱስ ወደዚህ አለም ሲመጣ አሮን እንዳደረገው ፈፅሞ መስዋዕቶችን አላቀረበም ሐጢያተኞችን ለማዳን በመጠመቅና ደሙን በማፍሰስ ራሱን ለሰው ዘር አቀረበ ደህንነትንም በመስቀል ላይ ፈፀመ፡፡

በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደም የሚያምኑ ደህንነት ተረጋግጦላቸዋል ኢየሱስ ኃጢአቶቻችንን በሙሉ ያነፃልን ግልፅ ባልሆነ መንገድ አይደለም እርሱ ይህን ያደረገው በጣም ግልፅ በሆነ መንገድ ነው *«እኔ መንገድም፣ እውነትም፣ ህይወትም ነኝ» (ዮሐንስ 14፡6)* ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ በጥምቀቱ በሞቱና በትንሳኤው አድኖናል፡፡

# ብሉይ ኪዳን የኢየሱስ ምሳሌ ነው

*ሌላ ኪዳን ለመግባት ያስፈለገበት ምክንያት ምንድን ነው?*

*ምክንያቱም የመጀመሪያው ኪዳን ደካማና ጥቅም የለሽ ስለነበረ ነው፡፡*

ብሉይ ኪዳን የአዲስ ኪዳን ጥላ ነው ምንም እንኳን ኢየሱስ ልክ እንደ ብሉይ ኪዳን ሊቀ ካህናት ፈፅሞ መስዋዕቶችን ባያቀርብም ዘላለማዊና ሰማያዊ የሆነውን የተሻለ ክህነት አገልግሎዋል በዚህ አለም ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሲወለዱ ጀምሮ በሐጢያት የተሞሉ ስለሆኑ ሐጢያተኞች ሆነዋል በእግዚአብሄር ሕግ አማካይነት በጭራሽ ፃድቃን ሊሆኑ አይችሉም ስለዚህ እግዚአብሄር ሌላ ኪዳንን አፀና፡፡


በሰማይ ያለው አባታችን አንድያ ልጁን ወደዚህ ምድር በመላክ እኛም በእርሱ ጥምቀት፣ ሞትና ትንሳኤ አምነን ዘላለማዊ ህይወትን እንድንቀዳጅ ቃል ገብቶልናል ይህ የእግዚአብሔር ሁለተኛው ኪዳን ነው ሁለተኛው ኪዳን እኛ በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል እንድናምን ይጠይቀናል፡፡

ጌታ ከዚህ በኋላ ስለምናደርገው መልካም ስራ አይጠይቀንም እንዲሁም ደግሞ ለመዳን እንዴት መኖር እንዳለብን አያዘንም እርሱ የሚጠይቀን፣ በልጁ ደህንነት እንድናምን ብቻ ነው ጌታ ከሁሉም በላይ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ እንድናምን ይጠይቀናል እኛም እሺ ማለት አለብን፡፡

በመፅሐፍ ቅዱስ፣ የይሁዳ ነገድ የነገስታት ዘር ነበር፡፡ እስከ ንጉስ ሠለሞን ድረስ ያሉት የእስራኤል ነገስታት በሙሉ የሚወለዱት ከይሁዳ ዘር ነበር፡፡ እንዲሁም ደግሞ የይሁዳ ነገድ እስከ 586 ዓ.ዓ. ድረስ የእስራኤልን ደቡባዊ ግዛት በንጉስነት ይገዛ ነበር በዚህም የይሁዳ ሕዝቦች የእስራኤል መለያዎች ሆነው ይወሰዳሉ፡፡ የሌዊ ዝርዎች ደግሞ ካህናት ነበሩ የእስራኤል እያንዳንዱ ነገድ የራሱ ሚና ነበረው እግዚአብሔርም ለይሁዳ ነገድ ኢየሱስ ከእነሱ እንደሚነሳ ቃል ገብቶላቸው ነበር፡፡

ከይሁዳ ነገድ ጋር ኪዳን መግባት ያስፈለገው ለምንድን ነው? ይህን ኪዳን መግባት ኪዳኑን ከመላው የዓለም ሕዝብ ጋር እንደመግባት ነበር ምክንያቱም በዚህ መንገድ የይሁዳ ሕዝብ እስራኤሎችን ይወክላል እስራኤላውያን የዓለም ሕዝብ ሁሉ ተምሳሌት ስለሆኑ ነው እያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ የራሱ ሚና ነበረው እግዚአብሄርም ኢየሱስ ከይሁዳ ነገድ እንደሚወጣ ተስፋ ሰጥቷል ይህም የሰው ልጆች ሁሉ በጥምቀቱ በመስቀሉ ላይ ሞቱና በትንሳኤው የሚያገኙት ደህንነት ነው፡፡

## የሰው ልጆች ኃጢአት በንሰሐ ፀሎት ሊወገድ አይችልም



በኤርምያስ 17:1 ላይ የሰው ልጆች ኃጢኣት በሁለት ቦታዎች ላይ መመዝገቡ ተፅፏል *«የይሁዳ ኃጢኣት በብረት ብዕርና በተሾለ ዕብነ አልማዝ ተጽፎኣል በልባቸው ጽላትና በመሠዊያቸው ቀንዶች ተቀርጾኣል::»*

ኃጢአቶቻችን በልባችን ውስጥ ተቀርፀዋል ኃጢአተኞች መሆናችንንም የምናውቀው በዚህ ነው አንድ ሰው በኢየሱስ ከማመኑ በፊት ኃጢአተኛ መሆኑን አያውቅም ለምን? ለዚህ ምክንያቱም የእግዚአብሔር ሕግ በልቡ ውስጥ የለም ስለዚህ አንድ ሰው አንድ ጊዜ በኢየሱስ ሲያምን በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኛ መሆኑን ይገነዘባል::

አንዳንዶች ሐጢያተኞች መሆናቸውን የሚገነዘቡት በኢየሱስ ካመኑ ከ10 አመታት በኂላ ነው «አቤቱ! እኔ ሐጢያተኛ ነኝ! ድኛለሁ ብዬ አስቤ ነበር ነገር ግን አሁንም ድረስ ሐጢያተኛ ነኝ!» ግንዛቤው የሚመጣው መጨረሻ ላይ እውነተኛ ማንነታችንን ስናይ ነው እነርሱ ለአስር አመታት ደስተኞች ነበሩ ነገር ግን ድንገት እውነቱን ተረዱ ለምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ይህ ግንዛቤ የመጣው ሐጢያቶቻቸውና መተላለፎቻቸው በመጨረሻ በእግዚአብሄር ሕግ አማካይነት ግልፅ ስለሆኑ ነው እንደዚህ ያለ ግለሰብ ዳግም ሳይወለድ ለ10 አመታት በኢየሱስ አምኖዋል::

ሐጢያተኛው ኃጢያቶቹን ከልቡ መፋቅ ስለማይችል በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያተኛ ሆኖ ይኖራል አንዳንዶች ወደዚህ ግንዛቤ ለመድረስ 5 አመታት ሲወስድባቸው ሌሎች ደግሞ 10 አመታት ይወስድባቸዋል አንዳንዶች ወደ ግንዛቤ የሚደርሱት ከ30 አመታቶች በኂላ ሲሆን አንዳንዶች ደግሞ ከ50 አመታት በኂላ ነው አንዳንዶች እስከነአካቴው እውነቱን ፈፅመው አይገነዘቡትም «አቤቱ አምላኬ ትዕዛዛቶቹ በልቦናዬ ውስጥ ከመሆናቸው በፊት ጥሩ ነበርሁ ሕጉን በሚገባ እየጠበቅሁ

እንደነበር እርግጠኛ ነበርሁ አሁን ግን በየቀኑ ሐጢያት እንደምሰራ ተረድቻለሁ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው *«እኔ ያለ ሕግ ሕያው ነበርሁ ትዕዛዝ በመጣች ጊዜ ግን ሐጢያት ሕያው ሆነ እኔም ሞትሁ» (ሮሜ 7:9)* በክርስቶስ ባምንም ኃጢአተኛ ነኝ፡፡

በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት እንዳትኖሩ የሚከለክላችሁ የእናንተው ኃጢአት ነው ኃጢአቶቻችሁ በልቦቻችሁ ተፅፈዋል እግዚአብሔር ኃጢአቶቻችሁን በዚያ ስለሚመዘግባቸው አንገታችሁን ለፀሎት በምታጎነብሱበት ወቅት ኃጢአቶቻችሁ በሙሉ ይታያሉ «ይደንቃል! እኔ እናንተ የሰራችሁኝ ኃጢአት ነኝ» ይሏችኋል፡፡

«እንዴ! እኔ ከሁለት ዓመት በፊት አላንፃሁህምን? ለምን እንደገና በድንገት ትከሰታለህ? ለምን አልጠፋህም?» ብላችሁ ትመልሳላችሁ፡፡

«ኦ! አስጠሊታ አትሁን! እኔ በልብህ ውስጥ ተመዝግቤአለሁ ምንም የምታስብ ብትሆን አሁንም ድረስ ኃጢአተኛ ነህ፡፡»

«አይደለሁም! አይደለሁም» ትሉ ይሆናል፡፡

ስለዚህም ሐጢያተኛው ከ2 ዓመት በፊት ለሰራቸው ሐጢያቶች እንደገና ንስሐ ይገባል «ጌታዬ ሆይ! እባክህ አድነኝ በፊት በሰራሁት ኃጢአት አሁንም ድረስ እየተሰቃየሁ ነው በፊት ለኃጢአቶቼ ንስሐን የገባሁ ብሆንም አሁንም ድረስ ግን በውስጤ ናቸው እባክህን ኃጢአትን ስለሰራሁ ይቅር በለኝ» ብላችሁ ትፀልያላችሁ፡፡

ነገር ግን እነዚያ ኃጢአቶች በንስሐ ይወገዳሉን? ምክንያቱም የሰዎች ሐጢያቶች በልቦቻቸው ውስጥ ስለተፃፉ ያለ ውሃውና ያለ መንፈሱ ወንጌል በጭራሽ ሊፋቁ አይችሉም እውነተኛ ስርየት ሊገኝ የሚችለው በውሃውና በመንፈሱ

ወንጌል አማካይነት ብቻ ነው ልንድን የምንችለው በእውነተኛው የኢየሱስ ወንጌል ስናምን ብቻ ነው።

## አዳኛችሁ እሆናለሁ

*ለአዲሱ ኪዳን ምላሽ መስጠት ያለብን እንዴት ነው?*

*አዲሱን ኪዳን በልባችን አምነን ለአለም በመስበክ ነው*

በሰማይ ያለው አምላካችን ከኛ ጋር አዲስ ኪዳንን ገብቷል «አዳኛችሁ እሆናለሁ በውኃውና በደሙ አማካይነት ሙሉ በሙሉ ከዓለም ኃጢአቶች ሁሉ ነፃ አደርጋችኋለሁ በእኔ የሚያምኑትንም ሁሉ በእርግጠኝነት እባርካቸዋለሁ።»

እግዚአብሔር በሰጠን አዲስ ኪዳን ታምናላችሁን? በኪዳኑ እውነትና በውሃውና በደሙ ደህንነት በማመን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ መዳንና ዳግም መወለድ እንችላለን።

አንድን ሐኪም በትክክል ካልመረመረን አናምነውም አንድ ሐኪም በመጀመሪያ በሽተኛውን በደንብ መመርመርና አስፈላጊውን ሕክምና ማዘዝ አለበት ብዙ አይነት መድሃኒቶች አሉ ነገር ግን የሚጠቅመው የትኛው መድሃኒት እንደሆነ ሐኪሙ ማወቅ አለበት ሐኪሙ በሽተኞቹን ከመረመረ በኋላ ሊፈውሱዋችሁ የሚችሉ በርካታ መድሃኒቶች አሉ ምርመራው የተሳሳተ ከሆነ ግን እነዚያ ጥሩ መድሃኒቶች በሽተኛውን ከመጉዳት በቀር ለውጥ አያመጡም።

እንዲሁም ደግሞ በኢየሱስ በምታምኑበት ጊዜ በእግዚአብሔር ቃል በመመርኮዝ የመንፈሳችሁን ሁኔታ ማወቅና መረዳት አለባችሁ መንፈሳችሁን በእግዚአብሔር ቃል ስትመረምሩት የመንፈሳችሁን ሁኔታና ደረጃ በትክክል ልትገነዘቡ ትችላላችሁ የመንፈስ ሐኪም ህመምተኞቹን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ይፈውሳቸዋል ሁሉም ዳግም ውልደትን ያገኛሉ፡፡

«እኔ መዳን ወይም አለመዳኔን አላውቅም» የምትሉ ከሆነ አልዳናችሁም ማለት ነው አንድ መጋቢ በትክክል የኢየሱስ ተከታይ ከሆነ የተከታዮቹን ችግር መፍታት መቻል አለበት ከዚያም የእምነታቸውን ችግር በመፍታት ወደ መንፈሳዊነት ሊመራቸው ይችላል የተከታዮቹን ትክክለኛ መንፈሳዊ ሁናቴ መረዳት መቻል አለበት፡፡

ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው የዓለምን ኃጢኣት በሙሉ ለማስወገድ ነው እርሱ ወደዚህ ምድር መጥቶ ከተጠመቀ በኋላ በመስቀል ላይ በመሰቀል ሞቷል የሐጢያት ስርየት ሲያደርግ ሐጢያቶቻችሁን አላስወገደምን? የውኃውና የመንፈሱ ቃል የምዕመናንን ሐጢያት በሙሉ ደምስሶዋል፡፡

ወንጌል እንደ ድማሚት ነው ከረጃጅም ሕንፃዎች አንስቶ ተራሮችንም ጭምር ይንዳል የኢየሱስም ስራ እንዲሁ ነው በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑትን በሙሉ ከኃጢአታቸው ያነፃቸዋል አሁን በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተብራራውን የውኃና የመንፈስ ወንጌል እንመልከት፡፡

# በብለይ ኪዳን የነበረው እጆችን የመጫን ወንጌል

*በብሉይ ኪዳን ጊዜ እጆችን*
*የመጫን ጠቀሜታው*
*ምንድን ነበር?*

*ጥቅሙ ኃጢአትን ወደ መሥዋዕቱ*
*ለማስተላለፍ ነበር፡፡*

በዘሌዋውያን 1:3-4 የተፃፈውን የስርየት ወንጌል እውነት እንመልከት *«መባውም የሚቃጠል መስዋዕት ከላሞች መንጋ ቢሆን፣ ነውር የሌለበትን ተባቱን ያቀርባል በእግዚአብሔር ፊት እንዲሰምር በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ያቀርበዋል እጁንም በሚቃጠለው መሥዋዕት ራስ ላይ ይጭናል ያተሰርይለትም ዘንድ የሠመረ ይሆናል፡፡»*

ይህ ምንባብ የሚቃጠለው መሥዋዕት በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ከመታረዱ በፊት እጁን በመሥዋዕቱ ራስ ላይ በመጫን ኃጢአቱን በሙሉ ነውር ወደሌለበትና ሕያው ወደሆነው መሥዋዕት ማስተላለፍ እንዳለበት ይናገራል፡፡

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሐጢያተኛው በየቀኑ ለሰራቸው ሐጢያቶች ስርየትን ለማድረግ እጆቹን በመስዋዕቱ ላይ ይጭናል የሐጢያቱን መስዋዕት በእግዚአብሄር ፊት ያርደዋል ካህኑም ከደሙ የተወሰነውን ወስዶ በሚቃጠለው መስዋዕት መሠውያ ቀንዶች ላይ ይቀባዋል ከዚያም የቀረውን ደም ከመሰውያው በታች ያፈስሰዋል ሐጢያተኛውም በየቀኑ ከሰራው ሐጢያት ይቅርታን ያፈኛል፡፡

አመቱን ሙሉ ስለተሰራው ሐጢያትም በዘሌዋውያን 16:6-10 እንዲህ ተፅፎዋል *«አሮንም ለእርሱ ያለውን የኃጢአቱን መሥዋዕት ወይፈን ያቀርባል ለራሱም ለቤተሰቡም ያስተሰርያል ሁለቱንም አውራ ፍየሎች ወስዶ በመገናኛው ድንኳን አጠገብ በእግዚአብሔር ፊት ያቆማቸዋል አሮንም በሁለቱ ፍሎች ላይ ዕጣ ይጥልባቸዋል አንዱን ዕጣ ለእግዚአብሔር ሌላውንም ለሚለቀቅ። አሮንም በየእግዚአብሔር ዕጣ የሆነበትን ፍየል ያቀርባል ስለ ኃጢኣትም መሥዋዕት ያደርገዋል የመለቀቅም ዕጣ ሆነበትን ፍየል ያስተሰርይበት ዘንድ ለመለቀቅም ወደ ምድረ በዳ ይሰድደው ዘንድ በሕይወቱ በእግዚአብሔር ፊት ያቆመዋል»* በመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተብራራው አዛዜል ማለት «ማስወገድ» ማለት ነው ስለዚህ አመቱን ሙሉ የተሰራው ሐጢያት በሰባተኛው ወር በአስረኛው ቀን ይወገዳል።

በዘሌዋውያን 16:29-30 ላይም እንዲህ ተፅፎዋል *«ይህ የዘላለም ሥርዓት ይሁንላችሁ በዚህ ቀን ትነጹ ዘንድ ማስተሰረያ ሆንላችኋልና በሰባተኛው ወር ከወሩም በአሥረኛው ቀን ራሳችሁን አስጨንቋት የአገር ልጅም በእናንተ መካከል የተቀመጠም እንግዳ ሥራን ሁሉ አትሥሩበት በእግዚብሔርም ፊት ከኃጢአታችሁ ሁሉ ትነፃላችሁ።»*

ይህ እስራኤላውያን ለአንድ አመት የሠሩትን ኃጢአት የሚያስተሰርዩበት ቀን ነው ይህ የሚሆነው እንዴት ነው? በመጀመሪያ ሊቀ ካህኑ አሮን መሥዋዕቱን ማቅረብ አለበት የእስራኤልን ሕዝብ የሚወክለው ማነው? አሮን ነው እግዚአብሔር አሮንንና የእርሱን ዝርያዎች በሙሉ ካህናት ይሆኑ ዘንድ መርቋቸዋል።

አሮን ወይፈኑን በመስዋዕትነት ያቀረበው የራሱንና የቤተሰቡን ኃጢአት ለማስተሰረይ ነው መስዋዕቱን በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ካረደው በኋላ ከደሙ የተወሰነውን በስርየት

መክደኛው ላይ ሰባት ጊዜ ይረጨዋል በመጀመሪያ ለራሱና ለቤተሰቡ ማስተሰረይ ነበረበት፡፡

ሥርየት ማለት የአንድን ሰው ኃጢኣት ወደ መስዋዕቱ በማስተላለፍ በዚያ ሰው ፈንታ መስዋዕቱን እንዲሞት ማድረግ ማለት ነው በኃጢያቱ የተነሳ መሞት የነበረበት ኃጢአተኛ ራሱ ቢሆንም ኃጢአቱን በሙሉ ወደ መስዋዕቱ ያስተላለፈ ከሆነ በእርሱ ፈንታ የሚሞተው መስዋዕቱ ይሆናል ማለት ነው፡፡

የራሱንና የቤተሰቡን ኃጢአት በሙሉ ካስወገደም በኋላ የእስራኤልን ሕዝብ ኃጢአት በሙሉ የተሸከሙትን ፍየሎች አንዱን አውራ ፍየል ለእግዚአብሔር አንዱን ደግሞ ወደ ምድረ በዳ ለመስደድ ያቀርባል፡፡

አንዱ ፍየል የሐጢያት መስዋዕት ሆኖ ይቀርባል አሮንም እጆቹን በዚህ ፍየል ራስ ላይ በመጫን «ኦ እግዚአብሔር! ሕዝቦችህ እስራኤላውያን 12ቱን ትዕዛዛትና 613ቱን ሕግጋቶችህን አፍርሰዋል እስራኤላውያንም ኃጢአተኞች ሆነዋል አሁንም እኔ የእስራኤሎችን አመታዊ ኃጢአት በሙሉ ለማስተላለፍ እጆቼን በዚህ አውራ ፍየል ራስ ላይ እጭናለሁ» ይላል፡፡

ከዚያም የፍየሉን ጉሮሮ በመቁረጥ ደሙን ይዞ ወደ መገናኛው ድንኳን ቅድስተ ቅዱሳን ይገባል በስርየት መክደኛው ላይም ደሙን ሰባት ጊዜ ይረጨዋል፡፡

በዘሌዋውያን 16:14-15 እንዲህ ተፅፎዋል *«ከወይፈኑም ደም ወስዶ በስርየቱ መክደኛ ላይ ወደ ምሥራቅ በጣቱ ይረጨዋል ከደሙም በመክደኛው ፊት በጣቱ ሰባት ጊዜ ይረጫል ስለ ሕዝቡም ኃጢኣት የሚሠዋውን መሥዋዕት ፍየል ያርዳል ደሙንም ወደ መጋረጃው ውስጥ ያመጣዋል በወይፈኑም ደም እንዳደረገ በፍየሉ ደም ያደርጋል በመክደኛ ውም ላይና በመክደኛውም ፊት ይረጨዋል፡፡»*

የፍየሉንም ደም በመሰዊያው ላይ በረጨው ቁጥር ከልብሱ ጋር የተያያዘው ደውል ድምፅ ይሰጣል በዚህም ከውጭ ተቀምጠው የሚጠብቁት እስራኤላውያን ድምፁን ይሰሙታል ለኃጢአታቸው የሚደረገው ስርየት የሚከናወነው በሊቀ ካህኑ በመሆኑ የቃጭሎቹ ድምፃች ሐጢያቶቻቸው ይቅር መባላቸውን የሚያበስሩ ናቸው ይህ ለእስራኤል ሕዝቦች የበረከት ድምፅ ነው፡፡

ደውሎቹም ለሰባት ጊዜ ያህል ከጮኹ «አሁን ቀልሎልኛል በዓመቱ ውስጥ ለሰራሁት ኃጢአት ስፀፀት ነበር አሁን ግን ነፃ ነኝ» ይላሉ ከዚህም በኋላ ከፀፀት ነፃ ሆነው ሰዎቹ ወደ ቤቶቻቸው ይመለሳሉ በዚያን ጊዜ ይሰሙ የነበሩት የደውሉ ድምፅ በአሁን ጊዜ ካለው የውኃውና የመንፈሱ ወንጌል ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡

የውኃውንና የመንፈሱን የቤዛነት ወንጌል ስንሰማ ከልባችን ስናምንበትና በአፋችን ስንመሰክር ይህ በትክክል በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል የማመን ትርጉም ነው ደውሉ ለሰባት ጊዜ ያህል ሲጮህ የእስራኤል ልጆች ኃጢኣት በሙሉ ይወገዳል ኃጢአቶቻቸውም በሙሉ በእግዚአብሔር ፊት ይወገዳሉ፡፡

ሊቀ ካህኑ አንደኛውን ፍየል ለእግዚአብሔር መስዋዕት ካቀረበ በኋላ የቀረውን ፍየል ደግሞ ከድንኳኑ ውጭ ለተሰበሰቡት ሰዎች ይዞላቸው ይወጣል ሰዎቹ እየተመለከቱት እንዳለም ሊቀ ካህኑ አሮን እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ ይጭናል፡፡

በዘሌዋውያን 16:21-22 ላይ እንዲህ ተፅፎዋል *«አሮንም ሁለቱን እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ ይጭናል በላዩም የእስራኤልን ልጆች በደል ሁሉ መተላለፋቸውንም ሁሉ ኃጢአታቸውንም ሁሉ ይናዘዛል በፍየሉም ራስ ላይ ያሸክመዋል በተዘጋጀው ሰውም እጅ ወደ ምድረ በዳ ይሰድደዋል ፍየሉም ኃጢአታቸውን ሁሉ ወደ በረሀ ይሸከማል ፍየሉንም በምድረ በዳ*

*ውስጥ ይለቅቀዋል::»*

ሊቀ ካህኑ አሮን በሌላው ፍየል (አዛዜል) ላይ እጆቹን ጭኖ እስራኤሎች አመቱን በሙሉ የሠዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ይናዘዛል «ኦ እግዚአብሔር! እስራኤላውያን በፊትህ ኃጢአትን ሰርተዋል 10ቱን ትዕዛዛትህንና 613ቱን ሕግጋትህን አፍርሰዋል አቤቱ እስራኤሎች አመቱን በሙሉ የሰሩዋቸውን ሐጢያቶች በሙሉ ወደዚህ ፍየል ራስ ላይ አሻግራለሁ::»

በኤርምያስ 17:1 መሠረት ኃጢአቶች የሚፃፉት ሁለት ቦታዎች ላይ ነው አንዱ በስራዎች መፅሐፍ ላይ ሲሆን ሌላው በልቦቻችሁ ፅላቶች ላይ ነው::

ስለዚህ ሰዎች ለኃጢአቶቻቸው ስርየትን የሚያገኙ ከሆነ ሐጢያቶቻቸው ከስራዎች መፅሐፍና ከልቦቻቸው ፅላቶች ላይ መፋቅ አለባቸው በስርየት ቀን አንዱ ፍየል በፍርድ መፅሐፍ ላይ ለተፃፉት ሐጢያቶች ሲሆን ሌላው ፍየል ደግሞ በልቦቻቸው ፅላቶች ላይ ለተፃፉት ሐጢያቶች ነበር::

*እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ላይ ባለው የመስዋዕት ሥርዓት ለእስራኤላውያን ያሳየው ምንድን ነው?*

*አዳኝ መጥቶ ሐጢያቶቻቸውን እጅግ ተገቢ በሆነ መንገድ ለአንዴና ለመጨረሻ የሚደመስስ መሆኑ ነው::*

ሊቀ ካህኑ እጆቹን በፍየሉ ራስ ላይ በመጫን አመቱን ሙሉ የሰሩዋቸው ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ፍየሉ መተላለፋቸውን አሳይቷቸዋል ኃጢአቶቻቸውም ወደ ፍየሉ ራስ ላይ ከተላለፉ በኋላ በተገቢው ሰው ወደ ምድረ በዳ እንዲሰደድ ይደረጋል::

ፍልስጤም ምድረ በዳ ነበረች እስራኤሎች አመቱን ሙሉ የሰሩዋቸውን ሐጢያቶች የተሸከመው ፍየል ለዚህ ስራ በተመደበው ሰው አማካይነት ውሃም ሆነ ሳር ወደማይኖርበት ምድረ በዳ ይወሰዳል ሰዎቹም ይህ ፍየል ወደ ምድረ በዳው ሲሰደድ ቆመው ይመለከቱታል::

እነርሱም ለራሳቸው እንዲህ ይላሉ «እኔ መሞት ሲገባኝ በእኔ ፈንታ ይህ ፍየል ይሞታል የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው ሆኖም ግን በእኔ ፈንታ ፍየሉ ሞቷል አንተ ፍየል አመሰግንሃለሁ ያንተ መሞት ማለት ለእኔ መኖር ነው» ፍየሉ ወደ ምድረ በዳ ርቆ ከተወሰደ በኋላ እስራኤሎች አመቱን ሙሉ የሰሩት ሐጢያት ይቅርታን ያገኛል::

በልባችሁ ውስጥ ያለው ኃጢአት ወደ መስዋዕቱ ከተላለፈ እናንተ ከኃጢአት ነፅታችኋል ማለት ነው ይህንን ያህል ቀላል ነው:: እውነትን አንድ ጊዜ ካስተዋልነው ሁልጊዜም ቀላል ነው::

ፍየሉ ከአድማሱ ባሻገር ይሰወራል እስራኤሎች አመቱን ሙሉ የሠሩዋቸው ሐጢያቶች በሙሉ ተወግደዋል ፍየሉ ውሃና ሳር በሌለበት ምድረ በዳ ይቅበዘበዛል ውሎ አድሮም እስራኤሎች አመቱን ሙሉ የሠሩዋቸውን ሐጢያቶች ይዞ ይሞታል::

የኃጢኣት ደሞዝ ሞት ነው የእግዚአብሔርም ፍትህ ተፈፃሚ ሆንዋል እስራኤሎች በሕይወት ይኖሩ ዘንድ እግዚአብሄር ፍየሉን መስዋዕት አደረገው እስራኤሎችም

አመቱን በሙሉ የፈፀሙዋቸው መተላለፎች በሙሉ ነፅተዋል::

በብሉይ ኪዳን በየቀኑ የሚሠራው ሐጢያትና አመቱን በሙሉ የተሰራው ሐጢያት ይቅርታን እንዳገኘ ሁሉ የእኛም ሐጢያቶች እንደዚሁ ለአንዴና ለሁሌም ይቅርታን ያገኘ ዘንድ የእግዚአብሄር ኪዳን ነው መሲሁን ልኮ ከዕድሜ ልክ ሐጢያቶቻችን ያድነን ዘንድ ኪዳን ገብቷል ኪዳኑም በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት ተግባራዊ ሆንዋል::

## በአዲስ ኪዳን ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል እንደገና መወለድ

*ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ የተጠመቀው ለምንድን ነው?*

*የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ በመውሰድ ፅድቅን ለመፈፀም ነው በአዲስ ኪዳን ያለው የኢየሱስ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን ካለው እጆችን መጫን ጋር ተመሳሳይ ነው::*

ማቴዎስ 3:13-15ን እናንብብ *«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት::»*

ኢየሱስ ወደ ዮርዳኖስ ወንዝ በመሄድ በመጥምቁ ዮሐንስ

እጅ ተጠመቀ በዚህም ፅድቅን ሁሉ ፈፀመ የተጠመቀው በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ ነው ዮሐንስ ደግሞ ከሴት ከተወለዱ ሁሉ ታላቁ ሰው ነው::

ማቴዎስ 11:11-12 እንዲህ ይላል *«እውነት እላችኋለሁ ከሴቶች ከተወለዱት መካከል ከመጥምቁ ዮሐንስ የሚበልጥ አልተነሳም በመንግሥተ ሰማያት ግን ከሁሉ የሚያንሰው ይበልጠዋል ከመጥምቁም ከዮሐንስ ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ መንግሥተ ሰማያት ትገፋለች ግፈኞችም ይናጠቋታል::»*

አጥማቂው ዮሐንስ የሰው ዘር ወኪል ይሆን ዘንድ በእግዚአብሔር ተመርጦ ከክርስቶስ 6 ወራቶች በፊት ተላከ እርሱም ከአሮን ዝርያ የሆነና የመጨረሻው ሊቀ ካህን ነበር::

አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ፣ *«እኔ ባንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተ ወደ እኔ ትመጣለህን?»* ብሎ ጠይቆታል::

*«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና»* የእርሱ አላማ የሰው ልጆችን ሁሉ ከኃጢአት ነፃ በማድረግ የእግዚአብሔር ልጆች እንዲሆኑ ማድረግ ነው ኢየሱስ ለዮሐንስ ሲናገር «ከውኃውና ከመንፈሱ ዳግም የመወለድን ወንጌል መፈፀም አለብን ስለዚህ አሁን አጥምቀኝ» አለው::

ዮሐንስ ኢየሱስን አጠመቀው የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ ለማስወገድ ኢየሱስ መጠመቁ ተገቢ ነበር ሁሉ ለመውሰድ መጠመቅ ለኢየሱስ ጽድቅን መፈፀም ነበር ኢየሱስም እጅግ ተገቢ በሆነ መንገድ ስለተጠመቀ እኛ ከኃጢአቶቻችን በሙሉ ድነናል ኢየሱስ የተጠመቀው ኃጢአቶቻችን በሙሉ ወደ እርሱ ይተላለፉ ዘንድ ነው::

ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ 30 ዓመት ሲሞላው ተጠመቀ ይህ የእርሱ የመጀመሪያው ግልጋሎቱም ይህ ነበር

ኢየሱስ ጽድቅን በሙሉ ኃጢአቶቻችንን በማስወገድና የሰው ልጆችን ሁሉ በማፅደቅ የዓለምን ሕዝብ በሙሉ ከኃጢአት የነጻ እንዲሆን አድርጓል፡፡

ኢየሱስ ወደዚህ አለም መጥቶ ከሐጢያቶቻችን በሙሉ ለማዳን እጅግ ተገቢ በሆነ መንገድ ተጠመቀ «በዚህም» ጽድቅ ሁሉ ተፈጸመ፡፡

እግዚአብሔር *«በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ ይህ ነው» (ማቴዎስ 3:17)* አለ ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጆች ሁሉ ኃጢአት ሁሉ እንደሚወስድና በመስቀል ላይ እንደሚደማም ያውቅ ነበር ሆኖም *«አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወድ አይሁን» (ማቴዎስ 26:39)* በማለት የአባቱን ፈቃድ ታዘዘ የሰውን ዘር ሐጢያቶች በሙሉ ማስወገድና ለአለም ሕዝብ ደህንነትን መስጠት ነበር፡፡

ስለዚህ ኢየሱስ የአባቱን ፈቃድ ለመፈፀም በአጥማቂው ዮሐንስ ተጠመቀ፡፡

*«በቀጣዩ ቀን ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚስወግድ የእግዚአብሔር በግ!» (ዮሐንስ 1:29)* ብሎ መስክሮለታል ኢየሱስ ኃጢአትን በሙሉ ተቀብሎ በጎልጎልታ በመስቀል ላይ ደምቷል *«እነሆ! የዓለምን ኃጢአት የሚስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»* በማለት መሠከረ ይህ የአጥማቂው ዮሐንስ ምስክርነት ነው፡፡

ኃጢአት አለባችሁ ወይስ የለባችሁም? እናንተ ፃድቃን ናችሁ ወይስ ኃጢያተኞች? እውነቱ ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ወስዶ ለእኛም በመስቀል ላይ የተሰቀለልን መሆኑ ነው፡፡

*የኃጢአተኞች ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ የተላለፉት መቼ ነበር?*

*ኢየሱስ በዮርዳኖስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ሐጢያቶቻችንን ሁሉ ወስዶዋል፡፡*

**እኛ በዚህ ምድር ከተወለድንበት ጊዜ አንስቶ ከ1-10 ዓመት ድረስ ባለው እድሜያችንም እንኳን ኃጢአትን እንሰራ ነበር ኢየሱስ እነዚህን ኃጢአቶችም ጭምር ወስዷል እንዲሁም በ11 እና 20 አመታችን መካከልም ሐጢያት እንሰራለን በልቦቻችንና በምግባሮቻችን የሰራናቸውን ሐጢያቶች በሙሉ እርሱ ወስዶዋቸዋል፡፡**

**በ21 እና 45 አመታችን መካከልም እንደዚሁ ሐጢያት እንሰራለን እነዚህን ሁሉ ወስዶዋቸዋል እርሱ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶ በመስቀል ላይ ተሰቀለ ከተወለድንበት ቀን አንስቶ እስከምንሞትበት ቀን ድረስ ኃጢአትን እንሰራለን ሆኖም ግን ሁሉንም ኃጢአቶቻችንን እርሱ ወስዷቸዋል፡፡**

***«እነሆ! የዓለምን ኃጢአት ሁሉ የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»* ከመጀመሪያው ሰው ከአዳም አንስቶ በዚህ ዓለም ላይ እስከሚወለደው የመጨረሻ ሰው ድረስ ያለውን ሐጢያት በሙሉ አስወግዶዋል የማንን ኃጢት መውሰድ እንዳለበት ሳያማርጥ የሁሉንም ሰዎች ኃጢአት ወስዷል፡፡**

**እርሱ እያንዳንዳችንን ብቻ ለመውደድ አልወሰነም እርሱ ስጋን ለብሶ ወደዚህ ምድር በመምጣት የአለምን ኃጢአት**

በሙሉ ከወሰደ በኋላ በመስቀል ላይ ተሰቅሏል በሁላችን ፈንታም ፍርድን ከተቀበለ በኋላ የዚህን ዓለም ኃጢአቶች ለዘላለም ደምስሶዋቸዋል፡፡

ከእርሱ ደህንነት የተገለለ ሰው የለም *«የዓለም ኃጢአት ሁሉ»* የኛንም ኃጢአት ያጠቃልላል ኢየሱስ ሁሉንም አስወግዶአል፡፡

በጥምቀቱና በደሙ አማካኝነትም የዓለምን ኃጢአት በሙሉ አንፅቷል በጥምቀቱ አማካይነት ሁሉንም አስወግዶ ለሐጢያቶቻችን በመስቀል ላይ ተፈርዶበታል ኢየሱስ በመስቀል ላይ ከመሞቱ በፊት *«ተፈፀመ» (ዮሐንስ 19፡30)* አለ ይህ ማለት የሰው ዘር ደህንነት ተጠናቋል ማለት ነው፡፡

ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተሰቀለው ለምንድን ነው? የስጋ ሕይወት ያለው በደም ውስጥ ስለሆነና ለአንድ ሰው ህይወትም ደሙ የሕይወት ስርየት ስለሆነ ነው (ዘሌዋውያን 17፡11) ኢየሱስ መጠመቅ ያስፈለገው ለምንድን ነው? ለዚህ ደግሞ ምክንያቱ እርሱ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ለመውሰድ ስለፈለገ ነው፡፡

*«ከዚህ በኋላ ኢየሱስ ሁሉ እንደ ተፈጸመ አውቆ የመጽሐፉ ቃል ይፈጸም ዘንድ «ተጠማሁ» አለ» (ዮሐንስ 19፡28)* ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያሉት የእግዚአብሄር ኪዳናት በሙሉ በዮርዳኖስ ባደረገው ጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ መፈፀማቸውን በማወቅ ሞተ፡፡

ኢየሱስ የቤዛነቱ ቃል ኪዳን በእርሱ እንደተፈጸመ ካወቀ በኋላ *«ተፈፀመ!»* ብሎ ተናገረ ከዚያም በመስቀል ላይ ሞተ እኛ ን ቀደሰን በሶስተኛው ቀንም ከሞት ተነስቶ አሁን በእግዚአብሄር ቀኝ ወደተቀመጠበት ወደ ሰማይ አረገ፡፡

ሐጢያቶች በሙሉ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ሞቱ አማካይነት መወገዳቸው ከውሃና ከመንፈስ ዳግም

የመወለድ ወንጌል ውጤት ነበር ይህንን እመኑት ለሐጢያቶቻችሁ ሁሉ ይቅርታን ታገኛላችሁ::


በየቀኑ ስለ ንስሐ በመፀለይ ከሐጢያቶቻችን መንፃት አንችልም ቤዛነት ለአንዴና ለሁሌም የተለገሰው በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ሞቱ ብቻ ነው *«የእነዚህም ሥርየት ባለበት ዘንድ ከእንግዲህ ወዲህ ስለ ኃጢኣት ማቅረብ የለም::» (ዕብራውያን 10:18)*

አሁን እኛ ሁላችን ማድረግ ያለብን በኢየሱስ ጥምቀትና ስቅለት ማመን ነው በዚህ እመኑና ትድናላችሁ::

ሮሜ 5:1-2 እንዲህ ይላል *«እንግዲህ በእምነት ከፀደቅን በእግዚአብሔር ዘንድ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሰላምን እንያዝ በእርሱም ደግሞ ወደቆምንበት ወደዚህ ጸጋ በእምነት መግባትን አግኝተናል በእግዚአብሔር ክብርም ተስፋ እንመካለን::»*

ለመፅደቅ ከውኃና ከመንፈስ የሆነውን ዳግም የመወለድ የተባረከ ወንጌል ከማመን ውጪ ሌላ መንገድ የለም::

## የእግዚአብሔር ሕግ አላማ



በዕብራውያን 10:9 ላይ እንዲህ ተፅፎዋል *«ቀጥሎ እነሆ! አምላኬ ሆይ ፈቃድህን ላደርግ መጥቼአለሁ ብሎአል ሁለተኛ ውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል»* በሕጉ አማካይነት ልንቀደስ አንችልም ሕጉ የሚያደርገን ኃጢአተኞች ብቻ ነው ሕጉን እንታዘዝ ዘንድ የእግዚአብሔር አላማ አይደለም፡፡

በሮሜ 3:20 ላይ እንዲህ ይላል *«ይህም የሕግን ሥራ በመስራት ሥጋ የለበሰ ሁሉ በእርሱ ፊት ስለማይጸድቅ ነው ኃጢኣት በሕግ ይታወቃልና»* እግዚአብሔር አብርሃም ኪዳኑን ከተቀበለ ከ430 አመታት በኋላ በሙሴ በኩል ሕጉን ለእስራኤሎች ሰጠ ሕጉን የሰጣቸው በእግዚአብሄር ፊት ሐጢያት መስራት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያውቁ አንድ ነበር፡፡

የሕጉ አላማ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኞች መሆናችንን ለማሳወቅ ነው በዚህ ዕውቀት አማካይነት በተባረከው የውሃና የመንፈስ ዳግም የመወለድ የተባረከ ወንጌል በማመን ወደ ኢየሱስ እንድንጠጋ ይጠበቅብናል እግዚአብሄር የሰጠን ሕግ አላማው ይህ ነው፡፡

## ጌታ የመጣው የእግዚአብሔርን ፍቃድ ለመፈፀም ነው

*በእግዚአብሔር ፊት ማድረግ ያለብን ምንድን ነው?*

*በኢየሱስ በኩል በሆነው የእግዚአብሔር ቤዛነት ማመን ይኖርብናል፡፡*

*«እነሆ አምላኬ ፈቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ ብሎአል ሁለተኛውን ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል» (ዕብራውያን 10:9)* እኛ በሕጉ ልንቀደስ ስለማንችል እግዚብሔርም በሕጉ አልቀደሰንም እግዚአብሄር ያዳነን ምሉዕ በሆነው ቤዛነቱ እንጂ በሕጉ አይደለም እግዚአብሄር በፍቅሩና በምህረቱ አዳነን፡፡

*«በዚህም ፈቃድ የኢየሱስ ክርስቶስን ስጋ አንድ ጊዜ ፈጽሞ በማቅረብ ተቀድሰናል ሊቀ ካህናቱም ሁሉ ዕለት ዕለት እያገለገለ ኃጢአትን ሊያስወግዱ ከቶ የማይችሉትን እነዚያን መሥዋዕቶች ብዙ ጊዜ እያቀረበ ቆሞኣል እርሱ ግን ስለ ኃጢአት አንድን መስዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ፡፡» (ዕብራውያን 10:10-12)*

የቤዛነት ሰራው ስለተጠናቀቀና ሌላ የሚሠራው ነገር ስላልነበረው በእግዚአብሄር ቀኝ ተቀመጠ ከዚህ በኋላም እኛን ለማዳን ዳግም መጠመቅ አሊያም መሰቀል አያስፈልገውም፡፡

አሁን የዓለም ኃጢኣት በሙሉ ተወግዷል ከዚህ በኋላ እርሱ የሚያደርገው ነገር ቢኖር በእርሱ ለሚያምኑት ዘላለማዊ ሕይወትን መስጠት ብቻ ነው አሁን እርሱ በውሃውና በመንፈሱ ደህንነት ያመኑትን በመንፈሱ አትሞዋቸዋል፡፡

ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ አስቀገደ በመስቀል ላይ በመሞትም ስራውን አጠናቀቀ አሁን የጌታ ስራ የተጠናቀቀ በመሆኑም በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል፡፡

ኢየሱስ ለዘላለም ከሐጢያት እንዳዳነን ማመን አለብን በጥምቀቱና በደሙ ለዘላለም ፍፁማን አድርጎናል፡፡

# የእግዚአብሔር ጠላቶች የሚሆኑ

*የእግዚአብሔር ጠላቶች*
*እነማን ናቸው?*

*በኢየሱስ እያመኑ ግን*
*በውስጣቸው ኃጢአት ያለባቸው*
*ናቸው፡፡*

በዕብራውያን 10:12-13 ላይ ጌታ እንዲህ ይላል *«እርሱ ግን ስለ ኃጢኣት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ ጠላቶቹም የእግሩ መረገጫ እስኪደረጉ ድረስ ወደፊት ይጠብቃል አንድ ጊዜ በማቅረብ የሚቀደሱትን የዘላለም ፍጹማን አድርጓቸዋልና»* የመጨረሻው ፍርድ እጣ ፈንታቸውን እስከሚወስን ድረስም እንደሚጠብቃቸው ተናግሯል፡፡

የእርሱ ጠላቶች አሁንም ድረስ «እግዚአብሔር ሆይ! ኃጢአቴን ይቅር በለኝ!» ይላሉ ሰይጣንና ተከታዮቹም በእርሱ የውኃና የመንፈስ ወንጌል አያምኑም ስለዚህ የእርሱን ይቅርታ መለመናቸውን ይቀጥላሉ፡፡

ጌታችን ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወስዶ በእርሱ ለምናምነው ሞተልን ኢየሱስ በእርሱ የሚያምኑትን ሁሉ ለማዳን አንድ ቀን ለሁለተኛ ጊዜ ይገለጣል «አቤቱ ፈጥነህ ወደ እኛ ና» ሐጢያት አልባ የሆኑት በመንግስተ ሰማይ ለዘላለም አብረውት ይኖሩ ዘንድ ሊወስዳቸው ዳግም ይመጣል፡፡

ሐጢያተኞች ነን ብለው ድርቅ የሚሉ ጌታ በሚመለስበት

ጊዜ በሰማይ ቦታ አያገኙም በመጨረሻው ቀንም ተፈርዶባቸው ወደ ገሃነም እሳት ይወረወራሉ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም መወለድን ለማመን እምበተኞች የሚሆኑ የሚጠብቃቸው ቅጣት ይህ ነው::

ጌታችን ኢየሱስ እውነት ባልሆነ ነገር የሚያምኑትን እንደ ጠላቶቹ አድርጎ ይመለከታቸዋል ይህንን እውነት ያልሆነ ነገር መዋጋት ያለብን ለዚህ ነው በተባረከው ዳግም ከውሃና ከመንፈስ የመወለድ ወንጌል ማመን ያለብን ለዚህ ነው::

## በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለብን

*ዕዳዎቻችን (ኃጢአቶቻችን)*
*በሙሉ ተከፍለው ሳሉ ለሐጢያቶቻችን*
*ስርየት ማግኘት ያስፈልገናልን?*

*በፍፁም አይገባንም::*

*ዕብራውያን* **10:15-16** ላይ እንዲህ ተፅፎዋል *«መንፈስ ቅዱስም ደግሞ ስለዚህ ይመሰክርልናል ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እፅፈዋለሁ::»*

ኃጢአቶቻችንን በሙሉ ካስወገደልንም በኋላ *«ይህ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ነው»* ብሏል ይህ ኪዳን ምንድን ነው? *«ሕጌን በልባቸው አኖራለሁ በልቡናቸውም እፅፈዋለሁ»* በመጀመሪያ እኛም በሕጉ መሠረት ለመኖር ሞክረን ነበር ነገር

ግን በእውነት በሕጉ መዳን አንችልም፡፡

በኋላም ኢየሱስ ከውኃና ከመንፈሱ ዳግም የመወለድን የተባረከ ወንጌል በልቦቻቸው ያመኑትን እንዳዳናቸው አወቅን ማንም በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ የሚያምን ሁሉ ይድናል፡፡

ኢየሱስ የደህንነት ጌታ ነው *«መዳንም በሌላ በማንም የለም እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና» (የሐዋርያት ሥራ 4:12)* ኢየሱስ ወደዚህ ምድር የመጣው አዳኛችን ሆኖ ነው እኛ በስራዎቻችን መዳን ስለማንችል ኢየሱስ አዳነን በፍቅርና በደህንነት ሕጉ እንዳዳነንም በልባችን ፅላቶች ላይ ፃፈልን ለእኛ ባለው ፍቅር የተነሳም እርሱ በልባችን ከተፃፈው ኃጢአት አድኖናል፡፡

*«ኃጢአታቸውንና ዓመፃቸውንም ደግሜ አላስብም ይላል የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም፡፡» (ዕብራውያን 10:17-18)*

አሁን ሕግ አልባ ምግባሮቻችንን ዳግመኛ አያስታውስም አሁን ሐጢያታችንን በሙሉ በማስወገዱ እኛ ምዕመናን ይቅር የሚባሉ ሐጢያቶች የሉብንም ዕዳዎቻችን ሙሉ በሙሉ ተከፍለዋል ሳይከፈል የቀረ ምንም ነገር የለም ሰዎች በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ አማካይነት ባዳነን የኢየሱስ አገልግሎት በእምነት ድነዋል፡፡

አሁን እኛ ሁላችን ማድረግ ያለብን ብቸኛ ነገር በኢየሱስ የጥምቀቱና የደሙ ወንጌል ማመን ነው *«እውነትን ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐንስ 8:32)* በኢየሱስ በኩል በተገኘው ደህንነት እመኑ ቤዛነትን ማግኘት ከመተንፈስም ይቀልላል እናንተ ማድረግ የሚኖርባችሁ ነገሮችን እንዳሉ ማመን ነው መዳን ማለት በእግዚአብሔር ቃል ማመን ማለት ነው፡፡


ኢየሱስ (በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው

ደም) አዳኛችን እንደሆነ እመኑ ደህንነት የእናንተ እንደሆነ እመኑ እንዲሁም ደግሞ እርሱ እንዳዳናችሁ ሙሉ እምነት ይኑራችሁ ሃሳቦቻችሁን በሙሉ ትታችሁ በኢየሱስ ደህንነት እመኑ በኢየሱስ በተጨባጭ እንድታምኑና ከእርሱ ጋር ወደ ዘላለም ሕይወት ለመግባት እንድትዘጋጁ እፀልያለሁ፡፡ ✉

# ስብከት 7

# የኢየሱስ ጥምቀት ለቤዛነት አስፈላጊ የሆነ ሒደት ነው

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡



«በዚህ ላይ፡- «መሥዋዕትንና መባን በሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕትንም ስለ ኃጢአትም የሚሠዋ መሥዋዕትን አልወደድህም በእርሱም ደስ አላለህም ብሎ፣ እነዚህም እንደ ሕግ የሚቀርቡት ናቸው፣ ቀጥሎ፡- እነሆ አምላኬ ሆይ፣ ፈቃድህን ላደርግ መጥቻለሁ፣ ብሏል ሁለተኛውንም ሊያቆም የፊተኛውን ይሽራል፡፡» (ዕብራውያን 10፡8-9)

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡

# የኢየሱስ ጥምቀት ለቤዛነት አስፈላጊ የሆነ ሒደት ነው

**« ማቴዎስ 3:13-17 »**

**«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ እንዲህ መፈፀም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ከውኃው ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው አለ።»**

## የመጥምቁ ዮሐንስ ጥምቀት

*ንስሐ ምንድን ነው?*

*በኃጢኣት ከተሞላ ህይወት መመለስና ለመቀደስም በኢየሱስ ማመን ማለት ነው።*

በአለም ላይ የሚኖሩ ብዙዎቹ ሰዎች ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም ለምን እንደመጣና በአጥማቂው ዮሐንስ ለምን

እንደተጠመቀ አያውቁም ስለዚህ ስለ ኢየሱስ ጥምቀትና ኢየሱስን ስላጠመቀው አጥማቂው ዮሐንስ አላማ እንመርምር፡፡

በመጀመርያ አጥማቂው ዮሐንስ ሕዝቡ ሐጢያቶቻቸውን እንዲናዘዙ በማድረግ ከሐጢያቶቻቸው ወደ እግዚአብሄር ለመመለስ እንዳጠመቃቸው በማቴዎስ 3፡1-12 ላይ ተብራርቷል፡፡

*«እኔ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ» (ቁጥር 11)* እንዲሁም *«የጌታን መንገድ አዘጋጁ ጥርጊያውንም አቅኑ እያለ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ» (ቁጥር 3)* መጥምቁ ዮሐንስ የግመል ፀጉርን ለብሶ አንበጣን ይመገብ ነበር ስለ ኃጢአት የንስሐ ጥምቀትን ይሰብክ ነበር፡፡

ለሕዝቡም «ንስሐ ግቡ! የሰው ልጆች አዳኝ እየመጣ ነው ጥርጊያውንም አቅኑ መንገዱንም አዘጋጁ ጣዖታትን ማምለክ ትታችሁ ጌታን በልባችሁ ተቀበሉ» እያለ ይሰብክ ነበር፡፡

ከምን መመለስ? በሐጢያት የተሞላው ሕይወት ከሚሰራቸው ሌሎች ክፉ ድርጊቶች ስለዚህ እኛ ማድረግ ያለብን ነገር ምንድን ነው? ለመቀደስ በኢየሱስ መጠመቅ አለብን መጥምቁ ዮሐንስ በምድረ በዳ ሲጮህ «ኑና በእኔ ተጠመቁ ኃጢታችሁንም አንጹ አዳኛችሁ መሲሁ እየመጣ ነው በብሉይ ኪዳን እንዳለው የመስዋዕት በግ በመሆንም ኃጢአታቸሁን በሙሉ ለዘላለሙ ያስወግድላችኋል» እያለ ያስተምር ነበር፡፡

በብሉይ ኪዳን የየቀኑ ኃጢአቶች ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ የሚሻገሩት በመጫን ነው የእስራኤሎች አመቱን ሙሉ የሠሩዋቸው ሐጢያቶችም በየአመቱ በሰባተኛው ወር በአስረኛ ው ቀን በሚውለው የስርየት ቀን በሊቀ ካህኑ አማካይነት ወደ ፍየሉ ይሻገራሉ፡፡ (ዘሌዋውያን 16፡29-31)

በተመሳሳይ መንገድ የሰው ዘር ሐጢያቶች በእርሱ በኩል ይደመሰሱ ዘንድ በጥምቀቱ አማካይነት በአንድ ጊዜ ወደ

ኢየሱስ መሻገር ነበረባቸው ስለዚህ ኢየሱስ ዮሐንስ ሕዝቡን ወደ ኢየሱስ ተመልሰው እንዲጠመቁ አደፋፈራቸው::

በአጥማቂው ዮሐንስ የሚደረገው ጥምቀት የመጀመሪያ ጥቅሙ ለንስሐ ነው ይህም በኋላ ላይ ወደ ኢየሱስ ይመጡ የነበሩትን ሰዎች ወደ እርሱ አስቀድሞ መመለስ ነው ንስሐ ማለት ከኃጢአት ህይወት መመለስና የሐጢያቶች ይቅርታን ለማግኘትም በመሲሁ ማመን ማለት ነው::

የእስራኤል ሕዝቦች በሚመጣው መሲህ ከኃጢኣታቸው እንደሚድኑ ተስፋ ነበራቸው ልክ እንደዚሁ እኛም ከ2000 አመታት በፊት በወረደውና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ለማስወገድ በመጣው በኢየሱስ ቤዛነትን አግኝተናል ነገር ግን በብሉይ ኪዳን የነበሩት እስራኤሎች የእግዚአብሄርን ሕግ ትተው የተሳሳቱ መስዋዕቶችን በማቅረብ መሲሁን ረሱት::

አጥማቂው ዮሐንስ የእግዚአብሔርን ሕግና በኋላ የሚመጣውን መሲህ ሊያስታውሳቸው ስለሚያስፈልግ ሰዎችን ማጥመቅ ጀመረ ውሎ አድሮም ኢየሱስን በዮርዳኖስ አጠመቀው::

ብዙ ሰዎችም ለጣዖት አምልኮዋቸውና የእግዚአብሄርን ሕግ ከመተዋቸው ንስሐ እየገቡ ወደ ዮሐንስ በመምጣት ተጠመቁ በአንድ ተገቢ መስዋዕት ውስጥ ሦስት አስፈላጊ ፍሬ ነገሮች - በሕይወት ያለ እንስሳ እጆችን መጫንና ደሙ ናቸው የአለም ሕዝብ በሙሉ በኢየሱስ በማመን ይድናል::

እነዚህ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን የፖለቲከኞች ቡድኖችና ጣዖት አምላኪዎች የእግዚአብሄርን ቃል ባያምኑም የእግዚአብሄር ሕዝቦች እንደሆኑ አሰቡ በሌሎች አማልክቶችና በራሳቸው አስተሳሰቦች አመኑ ለመጠመቅ ሲመጡ *«እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ*

*በልባችሁም:- አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ እላችኋለሁና» (ማቴዎስ 3:7-9)* ተብሎ ተነገራቸው፡፡


እነዚህ ፈሪሳውያንና ሰዱቃውያን ምንም እንኳን በእግዚአብሔር የማያምኑና ጣዖት አምላኪዎች ቢሆኑም የእግዚአብሔር ልጆች ነን ብለው ያስቡ የነበሩ ናቸው ያመኑ የነበሩትም በሐሳባቸው በፈጠሩዋቸው አማልክት ነው፡፡

ለመጠመቅ ወደ አጥማቂው ዮሐንስ በመጡ ጊዜ «የተሳሳቱ መስዋዕቶችን ማቅረብ አይገባችሁም ነገር ግን ከሐጢያት ተመልሳችሁ መሲሁ መጥቶ ከሐጢያቶቻችሁ እንደሚያነፃችሁ ከልባችሁ እመኑ ይህንን በልባችሁ ማመን ያስፈልጋችኋል» እያለ ይመክራቸው ነበር፡፡

ንስሐ መግባት ማለት ከስህተት መንገድ መመለስ ማለት ነው እውነተኛ ንስሐም ከሐሰት እምነትና ከኃጢአት ወደ ኢየሱስ መመለስ ነው ይህም በጥምቀቱ ቤዛነትና በመስቀል ላይ ፍርዱ ማመንን ይጠይቃል፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ ወደ እግዚአብሄር እንዲመለሱ ለማሳመን የእግዚአብሄርን ሕግና የመስዋዕት ስርአት ቸል ላሉት የእስራኤል ሕዝቦች ተማህፅኖውን አቀረበ በእርሱ አምነው ከሐጢያቶቻቸው ሁሉ ይድኑ ዘንድ ሕዝቡን ወደ ኢየሱስ ማቅረብ የአጥማቂው ዮሐንስ ሚና ነበር፡፡

# በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት በሆነው ቤዛነት ታምናላችሁን?




ኢየሱስ በይፋ በጀመረው አገልግሎቱ ያደረገው የመጀመሪያው ነገር በአጥማቂው ዮሐንስ መጠመቅ ነበር የአለም ሐጢያቶችም በሙሉ በዚህ መንገድ ወደ እርሱ ተሻግረዋል::

የኢየሱስ ጥምቀት እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ከኃጢአት ለማንፃት የጀመረው የመጀመሪያው ተግባር ሲሆን ይህም የዓለምን ኃጢአት ያስወገደበት የኢየሱስ የፅድቅ ተግባር ነው ኢየሱስ በጥምቀቱ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ እንዳስወገደ የሚያምኑትን በሙሉ ያድናቸዋል::

ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ በኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ የመንግሰተ ሰማያት ወንጌል ተጀመረ ኢየሱስ በዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ሰማያት ተከፈቱ በማቴዎስ 3:15 ላይ እንደተገለጠውም ይህ በብሉይ ኪዳን በዘሌዋውያን 1:1-5፤4:27-31 ላይ እንደተብራራው በትክክል የስርየት መስዋዕትን ይመስላል::

በብሉይ ኪዳን ውስጥ ያለው እያንዳንዱ ነገር በአዲስ ኪዳን

ውስጥ ባልንጀራ አለው በአዲስ ኪዳን ያለው እያንዳንዱ ነገርም በብሉይ ኪዳን ውስጥ ባልንጀራ አለ *«በእግዚአብሔር መፅሐፍ ፈልጉ አንብቡም አፌ አዝዞኣልና መንፈሱም ሰብስቦኣቸዋልና ከእነዚህ አንዲት አትጠፋም በልንጀራውንም የሚያጣ የለም።» (ኢሳያስ 34:16)*

## ብሉይና አዲስ ኪዳናት ስርየትን ስላገኙት የሕዝቡ ሐጢያቶች በሙሉ ይናገራሉ

*በየዕለቱ ለምንሰራቸው ኃጢአቶች ንስሐ መግባት ያስፈልገናል?*

*አያስፈልገንም። እውነተኛ ንስሐ ሐጢያትን በሙሉ አምኖ ቤዛነትን ለማግኘት ልቡናን ወደ ኢየሱስ ጥምቀት መመለስ ነው።*

በብሉይ ኪዳን በየቀኑ የሚሰራው ኃጢአት በእጆች መጫን አማካይነት ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ ይሻገራል ከዚያም መስዋዕቱ በሐጢያተኛው ምትክ ይደማና ይደፈረድበታል አመቱን ሙሉ የተከማቹት ሐጢያቶችም እጆችን በመጫን ወደ ሐጢያት መስዋዕቱ ይሻገራል በዚህም ሕዝቡ አመቱን ሙሉ የሰራው ሐጢያት ይቅርታን ያገኛል።

በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ወደ ምድር መጥቶ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ለማስወገድ የተጠመቀበት ስርዓት ከዚህ ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው በብሉይ ኪዳን የተተነበየው

የእግዚአብሔር ቃልም ተፈፀመ::

ኢየሱስን ያጠመቀው አጥማቂው ዮሐንስ ከኢየሱስ 6 ወር አስቀድሞ የመጣ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር በዮሐንስ 1:29 ላይ በተናገረው መሠረትም *«እነሆ የዓለምን ኃጢኣት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»* በማለት መስክሮኣል::

አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስን በዮርዳኖስ ወንዝ ባጠመቀው ጊዜ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ አስተላልፎታል በዚህ መንገድ ጌታ ለሰው ልጆች ኃጢአት በሙሉ ስርየትን አድርጓል አሁን እኛ ማድረግ የሚጠበቅብን ነገር በዚህ ማመን ነው::

የዓለም ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተላልፈዋል የኢየሱስ ደቀመዛሙርት በሐዋርያት ስራ 3:19 ላይ እንዲህ አሉ *«እንግዲህ ከጌታ ፊት የመፅናናት ዘመን እንድትመጣላችሁ አስቀድሞም ለእናንተ የመረጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲልክላችሁ ኃጢኣታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንሰሐ ግቡ ተመለሱም::»*

ሐዋርያቱ ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ የተጠመቀበትን ምክንያት እንድንገነዘብና ሰዎችን ለምን እንዲከተሉት እንደጠየቃቸውም እንድንረዳ እየነገሩን ነው በኢየሱስ የጥምቀት ቤዛነት እመኑ ከሐጢያቶቻችሁም ታጠቡ::

መሲሁ በተጠመቀ ጊዜ የአለምን ኃጢአት በሙሉ አስወግዷል የዓለም ኃጢአት በሙሉ ወደ ኢየሱስ የተላለፈውም በዚህ መንገድ ነበር በዚህም በማቴዎስ 3:13-17 ላይ እንደተመዘገበው የእግዚአብሄር ኪዳን በኢየሱስ ጥምቀት ተፈፀመ::

*«ያን ጊዜ ኢየሱስ በዮሐንስ ሊጠመቅ ከገሊላ ወደ ዮርዳኖስ መጣ ዮሐንስ ግን እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን? ብሎ ይከለክለው ነበር ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ እንዲህ መፈፀም*

*ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ከውኃው ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው አለ፡፡»*

የእግዚአብሔርን የደህንነት ቃል ለመፈፀም ኢየሱስ ወደ ዮሐንስ በመሄድ ተጠመቀ አጥማቂው ዮሐንስ የእግዚአብሔር ልዩ አገልጋይ ነበር ሉቃስ ምዕራፍ 1 ላይ ዮሐንስ የመጀመሪያው ሊቀ ካህን የአሮን ዘር መሆኑን ይናገራል እግዚአብሔርም ከአሮን ዘር የሖነውን ዮሐንስን መረጠው ምክንያቱም የሰው ዘር ሁሉ ወኪል የሆነው ፅድቅን ሁሉ ይፈፅም ዘንድ ፈልጓልና፡፡

ስለዚህ እግዚአብሔር ዮሐንስ ኢየሱስ ከመወለዱ ከ6 ወራቶች በፊት በሊቀ ካህን ቤት እንዲወለድ አደረገ አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስ ከመምጣቱ አስቀድሞ በምድረ በዳ *«እናንተ የእፉኝት ልጆች ከሚመጣው ቁጣ እንድትሸሹ ማን አመለከታችሁ? እንግዲህ ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ በልባችሁም- አብርሃም አባት አለን እንደምትሉ አይምሰላችሁ እላችኋለሁና»* ብሎ እየጮኸ ለኢየሱስ መንገድን ሲጠርግ ነበር፡፡

የቤዛነት ወንጌል በሐዋርያት *ሥራ 3:19* ላይ በግልፅ ተብራርቷል አጥማቂው ዮሐንስ ስለ ሰው ልጆች ኃጢአት በተናገረና በጮኸ ጊዜ ብዙዎች አምነው ተለወጡ፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ኢየሱስ በማሻገሩ የሰው ዘር ሐጢያቶች በሙሉ በአንድ ጊዜ ተደምስሰዋል አጥማቂው ዮሐንስ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ እንዳስወገደ ስለመሰከረ የውሃና የመንፈስ ወንጌል በሆነው የቤዛነት ወንጌል በማመን መዳን እንደምንችል እናውቃለን፡፡

# መጥምቁ ዮሐንስ ከኢየሱስ በፊት የመጣበት ምክንያት

*«እንዲህ» ለሚለው ቃል ያሉት ትርጉሞች ምንድናቸው?*

*1. በጣም ተገቢ*
*2. በጣም ተስማሚ*
*3. የግድ በዚህ መንገድ ብቻ (ሌላ መንገድ የለም)*

በአዳኙ ኢየሱስ በማመን ሐጢያቶቻቸው የተወገዱላቸው ደህንነታቸውን ማቴዎስ ለኢየሱስ ጥምቀተ ወንጌል በሰጠው ምስክርነት አማካይነት ማረጋገጥ ይችላሉ በማቴዎስ 3:15-16 ላይ ኢየሱስ ወደ ዮሐንስ መጥቶ፣ «አጥምቀኝ» ብሎታል ዮሐንስም *«እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን?»* ብሎ ይከለክለው ነበር::


ኢየሱስን ያጠመቀው አጥማቂው ዮሐንስ ነበር ማን እንደሆነ ግን ያውቅ ነበር አጥማቂው ዮሐንስ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ወደ ኢየሱስ እንዲያስተላልፍ የተላከ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነበር ኢየሱስ የብሉይ ኪዳንን ትንቢት ለመፈፀም አዳኝ ሆኖ ስለመጣ የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ በራሱ ላይ ይሸከም ዘንድ አጥማቂው ዮሐንስ እንዲያጠናቅቀው አዘዘው::

ለምን? ምክንያቱም ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ፣ ፈጣሪና አዳኝ ነው ወደ እኛ የመጣውም እኛን ከኃጢአቶቻችን በሙሉ ሊያነፃን ነው ስለሆነም የዓለምን ሰዎች በሙሉ ለማዳን መጠመቅ ያስፈልገው ነበር::

*«እንዲህ»* ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ በመጠመቅ ኃጢአቶቻችንን በሙሉ አስወግዶዋል በመስቀል ላይም በእኛ ምትክ ተኮነነ የኢየሱስ ጥምቀት ለደህንነታችን ምስክርነበር ኢየሱስ በብሉይ ኪዳን ሐጢያቶች በሙሉ መስዋዕጥ ሆኖ ወደቀረበው በግ እንደሚሻገር ቃል እንደገባ ሁሉ የሰው ልጅም በግ ሆኖ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወሰደ::

ስለዚህ በብሉይ ኪዳን የሚደረገው እጆችን መጫንና በአዲስ ኪዳን የሆነው የኢየሱስ ጥምቀት ሐጢያቶች የሚሻገሩበትና በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል ለሚያምኑት ደህንነትና የዘላለም ሕይወት የሚሰጥባቸው ናቸው::

## የኢየሱስ ጥምቀት ኃጢአቶቻችንን በሙሉ አጥቦልናል




ኢየሱስ መጠመቅ በፈለገ ጊዜ አጥማቂው ዮሐንስ *«እኔ በአንተ ልጠመቅ ያስፈልገኛል አንተም ወደ እኔ ትመጣለህን?»* ብሎ ሊከለክለው ሞክሮ ነበር::

ኢየሱስም ግን እንዲህ ብሎ መለሰ *«አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ እንዲህ መፈፀም ይገባናልና አለው»* አሁንስ ፍቀድልኝ ፍቀድልኝ ለዮሐንስ ሲናገርም «በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑትን እንዳድናቸውና ወደ እኔ

እንድመልሳቸው አንተ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ወደ እኔ ማስተላለፍ አለብህ በእኔ ጥምቀትና ደም ለሚያምኑት በሙሉ ለኃጢአታቸው ፍርድን እቀበልላቸዋለሁ ስለዚህ አሁን ፍቀድልኝ::»

ኢየሱስ የተጠመቀው በአጥማቂው ዮሐንስ ሲሆን ይህም የኢየሱስ ጥምቀት ፃድቅ ከሆነው የእግዚአብሄር የቤዛነት ሕግ ጋር የተስማማ ነበር ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ የዓለም ኃጢአት በሙሉ ወደ እርሱ በመተላለፋቸው የተነሳ እኛም በኢየሱስ አምነን ስንጠመቅ ለአንዴና ለሁሌ ቤዛነትን ልናገኝ እንችላለን እጆችን በመጫን ስርዓትም ኃጢአቶቻችንን በሙሉ ስለወሰደ በእኛ ፈንታም በመስቀል ላይ ስለሞተልንና አሁንም በእግዚአብሔር ቀኝ ስለተቀመጠ በውሃውና በመንፈሱ ቤዛነት በማመን ልንድን እንችላለን::

ሁላችንንም ከዓለም ኃጢአት በሙሉ ያዳነን ኢየሱስ ነው ኢየሱስ ኃጢአታችንን በሙሉ በጥምቀቱ እንደወሰደና ለእነዚህ ኃጢአቶችም በእኛ ፈንታ በመስቀል ላይ በመሞት ፍርድን እንደተቀበለ በማመን ልንድን እንችላለን የኢየሱስ ጥምቀት የቤዛነት ወንጌል መጀመሪያው ነው::

ቤዛነትን የሚያስገኘው ጥምቀት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተደጋጋሚ ተገልጧል ሐዋርያው ጳውሎስም ለገላትያ በላከው መልዕክቱ እንደፃፈው ከክርስቶስ ጋር መሞቱን ተናግሯል በክርስቶስ ስለተጠመቀና ክርስቶስን ስለለበሰከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎዋል ሐዋርያው ጳውሎስ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ሞቱ አማካይነት በተሰጠው ቤዛነት ያለውን እምነቱን ይናገራል::

## *«አሁንስ ፍቀድልኝ»*

*የመጥምቁ ዮሐንስ ሚና ምንድን ነበር?*

*የእርሱ ሚና የነበረው የሰው ልጆች ሁሉ ሊቀ ካህን በመሆን የሰው ልጆችን ኃጢአት በሙሉ ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍ ነበር፡፡*

ኢየሱስ ለዮሐንስ ሲናገር *«እንግዲህ ጽድቅን ሁሉ እንዲህ መፈፀም ይገባናልና አለው»* አለው ጽድቅን ሁሉ ማለቱም ኃጢአትን በሙሉ በጥምቀቱ ማስወገድና የሰው ልጆችን በሙሉ በልባቸው ኃጢአት የሌለባቸው ማድረግ ነው *«ከዚያም ፈቀደለት»* ኢየሱስ በዮርዳኖስ ተጠመቀ፡፡

ሊቀ ካህኑ እጆቹን በሕያው ፍየል ራስ ላይ እንደጫነ ሁሉ አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ በመጫን የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ወደ እርሱ አስተላልፏል ኢየሱስን ባጠመቀ ጊዜ የአጥማቂው ዮሐንስ ሚና የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ወደ ኢየሱስ ማስተላለፍ ነበር «አቤቱ እኔ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ወደ በግህ ወደ ኢየሱስ አስተላልፋለሁ» በዚህም የዓለም ኃጢኣት በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተላልፏል፡፡

አጥማቂው ዮሐንስ እጆቹን በኢየሱስ ራስ ላይ በመጫን ወደ ውሃው ውስጥ አጠለመው ኢየሱስ ከውኃው ሲወጣ ዮሐንስ እጆቹን አነሳ የኢየሱስ ጥምቀት የፅድቅ ደህንነትን አምጥቷል በዚህም በጥምቀቱ የሚያምነውን የሰው ዘር በሙሉ አድኖዋል፡፡

# ሰማይ ተከፍቶ ድምፅ ከሰማይ መጣ

*መንግስተ ሰማያት የተከፈተው ከመቼ ጊዜ ጀምሮ ነበር?*

*ከመጥምቁ ዮሐንስ ጊዜ ጀምሮ ነበር፡፡ (ማቴዎስ 11:12)*

*«ኢየሱስም ከተጠመቀ በኋላ ወዲያውኑ ከውኃው ወጣ እነሆም ሰማያት ተከፈቱ የእግዚአብሔርም መንፈስ እንደ ርግብ ሲወርድ በእርሱ ላይም ሲመጣ አየ እነሆም ድምፅ ከሰማያት መጥቶ በእርሱ ደስ የሚለኝ ልጄ ይህ ነው አለ፡፡» (ማቴዎስ 3:16-17)*

ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ በጥምቀቱ በወሰደ ጊዜ ሰማያት ተከፈቱ በዚህም እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት የገባው ቃል ኪዳን በኢየሱስ ጥምቀት ተፈፀመ፡፡

በዚህም የእግዚአብሔር በግ የሆነውኢየሱስ የዓለምን ሰዎች በሙሉ ከኃጢአታቸው አድኖኣቸዋል፡፡

ይህም በዮሐንስ 1:29 ላይ ተመስክሮአል *«እነሆ! የዓለምን ኃጢኣት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»* የዓለም ኃጢአቶች በሙሉ የእግዚአብሄር በግ ወደሆነው ኢየሱስ በመሻገራቸው ከሦስት አመታት በኋላ ሸክሙን በጫንቃው ተሸክሞ በጎልጎታ ወዳለው መስቀል ሄደ ሐጢያቶቻቸውን በሙሉ በጥምቀቱ ከወሰደ በኋላ በሄደበት ቦታ ሁሉ እርሱን በእምነት ለተቀበሉት ሐጢያቶቻቸው በሙሉ ይቅርታን ማግኘታቸውን ነገራቸው፡፡

በዮሐንስ 8:11 ላይ በዝሙት ተግባር ላይ የተገኘችን ሴት

*«እኔም አልፈርድብሽም!»* ብሏታል ምክንያቱም የእግዚአብሄር ልጅ የሆነው እርሱ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ስለወሰደ በአለም ላይ ያለ እያንዳንዱ ምዕመን መቀደስ ይችላል እርሱ በተጠመቀ ጊዜ ሰማያት ተከፈቱ የመንግስተ ሰማያት በሮችም ተከፍተው በኢየሱስ ጥምቀት ያመነ ሁሉ በነፃነት ሊገባ ይችላል፡፡

## ኢየሱስ የተሰቀለው የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ በጥምቀቱ ከወሰደ በኋላ ነው

*ኢየሱስ የሰይጣንን ራስ የቀጠቀጠው እንዴት ነበር?*

*ለኃጢአቶቻችን በሙሉ ፍርድን ከተቀበለ በኋላ ከሞት በመነሳት ነው፡፡*

የዓለም ኃጢአቶች በሙሉ ወደ ራሱ ስለተሻገሩ ኢየሱስ በመስቀል ላይ የሚቀበለውን ስቃይ ባሰበ ጊዜ በጣሙን ተሸብሮ ታወከ ላቡ እንደ ደም ነጠብጣቦች እስኪሆን ድረስ ጸለየ ከደቀመዛሙርቱ ጋር ጌቴሴማኔ ወደተባለ ስፍራ ሄደ እንዲህ ሲልም ጮኸ *«አባቴ ቢቻልስ ይህች ፅዋ ትለፍ፡፡» (ማቴዎስ 26፡39)* «እኔ በጥምቀት የዓለምን ኃጢአት በሙሉ ወስጃለሁ *ለዚህ ግን አልሙት*» እግዚአብሔርግን ምላሽ አልሰጠም፡፡

በብሉይ ኪዳን በነበረው የስርየት ቀን ደሙ በሊቀ ካህኑ አማካኝነት በስርየት መክደኛው ላይ ይረጭ ዘንድ የሐጢያቱ መስዋዕት መታረድ ነበረበት በተመሳሳይ መንገድ ኢየሱስ

መስቀል ነበረበት እግዚአብሄርም ይህንን በሌላ መንገድ ሊያደርገው እንደማይችል ወስኖዋል፡፡

መሰዊያው የእግዚአብሔር ፍርድን የሚያመለክት ሲሆን የመስዋዕቱ ደም ደግሞ ህይወትን ያመለክታል በስርየት መክደኛ ው ላይ ደምን ሰባት ጊዜ መርጨት ማለት ፍርዱ ሁሉ ተሻግሮዋል ማለት ነው፡፡ (ዘሌዋውያን 16፡1-22)

ኢየሱስ ይህች ፅዋ ታልፈው ዘንድ ፀልዩአል በሰማይ ያለው አባቱ ግን አልፈቀደለትም በመጨረሻም ኢየሱስ እንዲህ አለ- *«አንተ እንደምትወድ ይሁን እንጂ እኔ እንደምወደው አይሁን» (ማቴዎስ 26፡39)* ወደ እግዚአብሔር ሲፀልይ እርሱ እንደወደደው እንዲሆን ተናገረ ፀሎቱንም ከጨረሰ በኋላ የአባቱን ፈቃድ ተከተለ፡፡

ኢየሱስ የራሱን ፍላጎት ሳይሆን የአባቱን ፈቃድ ተቀበለ ለምን? ምክንያቱም እርሱ ከእኛ ለወሰደው ኃጢአት ፍርድን ባይቀበል ኖሮ ደህንነት አይጠናቀቅም ነበር *«የኃጢአት ደምዝ ሞት ነው የእግዚብሔር ስጦታ ግን በጌታ በኢየሱ ክርስቶስ ዘላለማዊ ህይወት ነው፡፡» (ሮሜ 6፡23)*

እግዚአብሔር መድህን ልኮ በእጆች መጫንና በኢየሱስ ጥምቀት አማካኝነት የሰውን ዘር እንደሚያድን የሚናገረውን ኪዳን ታዞዋል ኢየሱስም የአባቱን ፍቃድ በመቀበል ለኛ ሲል ፍርድን ተቀብሎልናል፡፡

ፍፃሜውን ያገኘው በዘፍጥረት 3፡15 ላይ የተተነበየው ነው *«በአንተና በሴቲቱ መካከል በዘርህና በዘሯም መካከል ጠላትነትን አደርጋለሁ ራሱ ራስህን ይቀጠቅጣል አንተም ሰኮናውን ትቀጠቅጣለህ»* እግዚአብሔር የሔዋን ዘር የሆነውን መሲህ እንደሚልክ ለአዳም ነገረው እርሱም የሰውን ዘር ሐጢያተኛ እንዲሆንና ወደ ሲዖል እንዲወርድ ያደረገውን ሰይጣንን የሸንፈዋል፡፡

የኢየሱስን ጥምቀትና በመስቀል ላይ ያፈሰሰውን ደም ስናውቅና ስናምን ኃጢአቶቻችን በሙሉ ይወገዳሉ እኛም ከፍርድ እንድናለን፡፡

የኢየሱስን ጥምቀትና በመስቀል ላይ ያፈሰሰውን ደም በምናስብበት ጊዜ በልባችን ውስጥ አሳማኝ የሆነ እምነት ሊኖረን ይገባናል ይህንን በልባችሁ እመኑት ያን ጊዜ ትድናላችሁ፡፡

## የኢየሱስ ጥምቀት የሰማያዊው ወንጌል መጀመሪያ ነው

*ጌታ ወደ ሰማይ*
*ከመሄዱ በፊት የመጨረሻው*
*ትዕዛዙ ምንድን ነበር?*

*ደቀመዛሙርቱን አህዛብን ሁሉ በአብ*
*በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቋቸው*
*ደቀ መዛሙርቱ እንዲያደርጓቸው*
*አዘዛቸው፡፡*

የኢየሱስ ጥምቀት የወንጌል መጀመሪያ ነው ይህም የዓለምን ኃጢአተኞች በሙሉ በጥምቀቱና በደሙ አድኖአቸዋል በማቴዎስ 28:19 ላይ እንደተፃፈውም *«እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁን ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው»* ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ አብን ወልድንና መንፈስ ቅዱስን

እንዲመሰክሩና የሰው ልጆችንም የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ ከኃጢኣት በሙሉ እንዳነፃቸው እንዲያስተምሩ አዘዝዞአቸዋል፡፡

ኢየሱስ ከአህዛብ ሁሉ ደቀመዛሙርት እንዲያደርጉ ስለ ኢየሱስ ስለ ቤዛነትና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ስላስወገደው ጥምቀት እንዲያስተምሩዋቸው ስልጣንን ሰጥቶዋቸዋል ይህም የኢየሱስ ጥምቀት የሰው ልጆችን በሙሉ ከኃጢኣታቸው እንዳነፃ የሚያስተምረው ወንጌል ነው፡፡

ከ2,000 ዓመታት በፊት ኢየሱስ ስጋን ለብሶ ወደ ምድር በመምጣት በአጥማቂው ዮሐንስ እጅ ተጠመቀ በኢየሱስ ጥምቀትም የእኛን ሐጢያቶች በሙሉ ጨምሮ የአለም ኃጢአቶች በሙሉ ወደ እርሱ ተሻግሮዋል፡፡

ወደ እርሱ የተላለፈው ኃጢአት ምን ያህል ነው? የነገዎቹ ኃጢአቶችስ? ቃሉ ወደፊት የምንሰራቸው ኃጢአቶች ወደ እርሱ መተላለፋቸውን ይነግረናል የልጆቻችን፣ የትውልዶቻችን፣ የአሁንና የወደፊት፣ እንዲሁም ከአዳምና ከሔዋን ጊዜ ጀምሮ የነበረው ኃጢአት በሙሉ ወደ ኢየሱስ መተላለፋቸውን ይነግረናል፡፡

እንዴት ኃጢአት ላይኖርን ይችላል? እኛስ እንዴት ኃጢአት አልባ ልንሆን እንችላለን? ምዕመናን በሙሉ ራሳቸውን ከሐጢያት ነፃ አድርገው ወደ እግዚአብሄር መንግስት ይገቡ ዘንድ ኢየሱስ በጥምቀቱ የእኛን ሐጢያቶችና የአለምን ሐጢያቶች በሙሉ ወስዶዋል፡፡

*«እውነትን የሚያደርግ ግን ስራው በእግዚአብሔር ተደርጎ እንደሆነ ይገለጥ ዘንድ፣ ወደ ብርሃን ይመጣል፡፡» (ዮሐንስ 3፡21)*

ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱ፣ በመስቀል ላይ ሞቱና በትንሳኤው ኃጢአቶቻችንን በሙሉ አጥቦልናል ስለዚህ በእርሱ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባለፈው ሕይወቱ ማመን ማለት

ከኃጢአት በሙሉ መዳን ማለት ነው ይህ የቤዛነት እምነት ነው።

በኢየሱስ ጥምቀትና በክርስቶስ ደም ስናምን እንድናለን በኢየሱስ ክርስቶስ በትክክል የምናምን ከሆንን ፃድቃን ነን ወይስ ሐጢያተኞች? ፃድቃን ነን ደካማ ፍጥረታት ብንሆን እንኳን ሐጢያት አልባ ነንን? አዎ ሐጢያት አልባ ነን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ፍርዱ ማመን ምሉዕና ተገቢ እምነት መያዝ ነው።

## በኢየሱስ ስም ማጥመቅና መጠመቅ

*የሰማያዊው ወንጌል መጀመሪያ ምንድን ነው?*

*የኢየሱስ ጥምቀት ነው።*

ሰዎች ደካማ ፍጥረታት ስለሆኑ አገልጋዮች በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ የሚያምኑትን እምነታቸውን ያፀኑ ዘንድ ያጠምቁዋቸዋል ዳግም የተወለዱት የእምነት ማረጋገጫ አድርገው ኢየሱስ በተጠመቀበት ተመሳሳይ መንገድ በመጠመቃቸው መዳናቸውን ያረጋግጣሉ።

በመጀመርያ አገልጋዩ ዳግም በሚወለደው ግለሰብ ራስ ላይ እጆቹን በመጫን ግለሰቡ እስከ ዕድሜው ፍፃሜ ድረስ እግዚአብሄርን ያመልክ ዘንድ የአምላክን በረከት ይለምንለታል ከዚያም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ያጠምቀዋል።

እኛ በመጀመሪያ በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ባለን እምነት ተጠምቀናል ይህ ጥምቀት አላማው ሐጢያት በሙሉ ወደ ኢየሱስ መሻገሩን የተጠመቀው ግለሰብም ከኢየሱስ ጋር መሞቱንና ከእርሱም ጋር መነሳቱን ማሳየት ነው::

መጠመቅ የአንድ ሰው ኃጢአቶች በሙሉ በጥምቀት ወደ ኢየሱስ መተላለፋቸውንና እርሱም ለእኛ ኃጢአት ፍርድን መቀበሉን ብሎም ሞትን ድል አድርጎ መነሳቱን ማመኑን የሚገልፅበት ድርጊት ነው እንዲሁም የአንድን ሰው እምነትም በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ በሰይጣንና በወንድሞችና በእህቶች ፊት ማወጅ ነው ከውሃና ከመንፈስ መወለዱን መናዘዝ ነው::

እነዚያ የኢየሱስን ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ያፈሰሰውን ደም ትክክለኛ ትርጉም የሚያውቁና የሚያምኑ በሙሉ ከዓለም ኃጢአቶች ሙሉ በሙሉ ድነዋል ስለሆነም፣ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም ይጠመቃሉ::

*«አሮጌው ነገር አልፏል እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኗል» (2ኛ ቆሮንቶስ 5:17)* አሮጌ ነገሮቻችን በሙሉ አልፈዋል እኛም የእምነት ሰዎች ሆነን ዳግም ተወልደናል ይህንንም በልባችን ለማረጋገጥ እንጠመቃለን በኢየሱስ ጥምቀት በማመንም በኢየሱስ እንጠመቃለን::

# በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ደም ዳግም ከተወለዱ በኋላ የሚኖረው ሕይወት

*ዳግም የተወለዱት የሚኖሩት ለምንድን ነው?*

*እነርሱ ወንጌልን በዓለም በመስበክ ለእግዚአብሔር መንግስትና ለፅድቁ ይኖራሉ*

ቤዛነትና ዳግም ውልደት ከተገኘ በኋላ ያለው ሕይወት በእግዚአብሄር ቃል ማመንን ማካተት አለበት የሚኖሩት ኑሮም አንድ ሰው በየቀኑ ለሚሰራው ኃጢአት እየፀለየ እንደሚኖረው አይነት ስሜታዊ ኑሮ መሆን የለበትም በፈንታው በየቀኑ ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ የወሰደልን ለመሆኑ እርግጠኛ በመሆን የታመነ ሕይወት መሆን ይኖርበታል።

ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ኃጢአቶቻችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ተሻግረዋል ከዚያም ለሐጢያቶቻችን በሙሉ ፍርድን ተከትሎ እስኪሰቀል ድረስ ለሦስት አመታት ይህንን ሸክም ተሸከመ።

ስለዚህ እኛ አማኞች እምነት ሊኖረን የሚገባው በውስጥ ፍላጎታችንና ተራ በሆኑ ስሜቶቻችን ሳይሆን በተፃፈው የእግዚአብሔር ቃል መሆን አለበት ይህን ለማድረግ ካልቻልን ግን ዳግም ውልደትን ካገኘን በኋላም በየዕለቱ ለምንሰራቸው ኃጢአቶች ከመጨነቅ በቀር የምንፈይደው አንዳች ነገር የለም።

ከግል ስሜት ጋር የተያያዘውን የኃጢአት ምልከታ አስወግደን በውሃውና በደሙ ወንጌል ብቻ ማመን ይኖርብናል

ቤዛነትን ያገኘ ግለሰብ ሊመራው የሚገባው ሕይወት ይህ ነው፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የተናገረው ነገር ምንድን ነው? *«እነሆ! የዓለምን ኃጢኣት የሚያስወግደው የእግዚአብሔር በግ!» (ዮሐንስ 1:29)* እርሱም ኢየሱስ የዛሬውን፣ የነገውንና የትላንቱንም ኃጢአት ጭምር አስወግዷል ነው ያለው፡፡

እነዚያን ኃጢአቶች በሙሉ አላስወገደምን? ኃጢአት በሙሉስ ወደ ኢየሱስ አልተላለፈምን? የዓለም ኃጢአት ያለፉትን የአሁኖቹንና የወደፊቱን ሐጢአቶቻችንን በሙሉ ይጨምራል በኢየሱስ ጥምቀት አማካይነት የቤዛነትን ወንጌል ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡

በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ የሚያምኑ ይድናሉ በኢየሱስ ጥምቀት ያመነ ሁሉ በልቡ ኃጢአት የለበትም፡፡

ሆኖም ብዙ ሰዎች ሐጢያቶቻቸው በሙሉ በጥምቀቱ አማካይነት አስቀድሞ ወደ ኢየሱስ መሻገሩን ባለማወቃቸው ገናም ሐጢአት እንዳለባቸው ያስባሉ በሰይጣን ተታለዋል ሰይጣን በሥጋዊ አስተሳሰቦቻቸው «በየቀኑ ሐጢያት ትሰራለህ እንዴት ሐጢያት አልባ ልትሆን ትችላለህን?» ሲል ያንሾካሹክላቸዋል፡፡

እነርሱ ማድረግ የሚጠበቅባቸው ሐጢያት አልባ ለመሆን በእግዚአብሄር ማመን ነው ነገር ግን አሁንም ስለሚሠሩ ሐጢያተኞች መሆናቸውን እንዲያስቡ አታለዋቸዋል በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ያመነ ሐጢያት የለበትም፡፡

ብቁ ያልሆንና ደካሞች ሆነን በዚህ ዓለም ላይ እየኖርን በመሆናችን ምክንያት በስራዎቻችንና በምግባሮቻችን ብቻ ፃድቃን ነን ማለት በጭራሽ አንችልም ነገር ግን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ እውነት መዳናችንን በእምነት መናገር እንችላለን በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ማመናችንን አንድ ጊዜ ከተረዳን ልባችን ስለሚቀደስ ሐጢያት እንደሌለብን በእርግጠኝነት እናውቃለን፡፡

*«♫ተዋጅቻለሁ አንተም ተዋጅተሃል ሁላችንም ተዋጅተናል ♫»* በመንፈስ እንደምንመራ ማወቅና ወንጌልን ለመስበክ ባለን ፍላጎታችን የምንኖር መሆናችንን ማወቅ ትልቅ ደስታን ያጎናፅፋል፡፡

በእርግጥ አማኞች ብንሆንም በየቀኑ ሐጢያትን እንሰራለን ነገር ግን ሐጢያት የለብንም በልባችን ውስጥ የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ አለን ልባችን በሐጢያት መሞላት ልማዱ ነው ነገር ግን አሁን በኢየሱስ ጥምቀት ስላመንን እንዴት ሐጢያተኞች ሆነን ልንቀር እንችላለን፡፡

*«ከዚያ ወራት በኋላ ከእነርሱ ጋር የምገባው ኪዳን ይህ ነው ይላል ጌታ በልባቸው ሕጌን አኖራለሁ በልቡናቸውም እፅፈዋለሁ፡፡» (ዕብራውያን 10:16)*

ልባችን ከኃጢአት የነፃ ነው ኢየሱስ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ አማካኝነት ከኃጢአት በሙሉ እንድንድን አስችሎናል ከኃጢአት መዳን የሚመነጨው በእግዚአብሔር ቃል ከማመን ነው፡፡

## ማንም በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደም የሚያምን ሁሉ ዳግም ኃጢኣተኛ ሊሆን አይችልም

*ኃጢአትን በሰራን ቁጥር ኃጢአተኞች እንሆናለን?*

*አንሆንም፡፡ መቼም ቢሆን ኃጢአተኞች አንሆንም፡፡*

በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ካላመንን ይቅርታን ለማግኘት ደጋግመን ብንፀልይም ሐጢያት በልቦቻችን ውስጥ ይኖራል ነገር ግን በእውነተኛው ወንጌል ባመንን ጊዜ ኃጢአቶቻችን በሙሉ ይወገዳሉ::

«ሃይ! ምእነዚህ ቀናት ብሩህና ደስተኛና የሆነው እንዴት ነው?»

«አየህ ከእንግዲህ ወዲያ በልቤ ኃጢአት የለብኝም ለዚያ ነው::»

«እውነትህን ነው? እንደዚያ ከሆነ አሁን እንደፈለክ ኃጢአት መስራት ትችላለህ ማለት ነዋ?»

«ታውቃለህ የሰው ልጅ ኃጢአትን ከመስራት ውጭ ምንም ሊያደርግ አይቻለውም ይህ የሰው ልጅ ተፈጥሮ ነው ሆኖም ግን ኢየሱስ ኃጢአቶቻችንን በሙሉ ወስዶ በመስቀል ላይም ፍርድን ተቀብሎልናል በዚህም የተነሳ አሁን እኔ ይህን ወንጌል በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እያገለገልኩኝ ነው በሮሜ ምዕራፍ 6 ላይ በተጻፈው መሰረትም ሁላችንም መኖር ያለብን እንደዚህ ነው በልቤም ምንም ኃጢአት የሌለብኝ ከመሆኔ የተነሳም ሁልግዜም ፅድቅ የሆነውን ነገር አደርጋለሁ ወንጌልን በመላው ዓለም ለመስበክም በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ማመንና ወንጌልን በመላው አለም መስበክ አለብን! የቤዛነታችን አለቃ በሆነው በኢየሱስ ስናምን ዳግመኛ በጭራህ ሐጢያተኞች አንሆንም በኢየሱስ ጥምቀት በተገኘው የዘላለም ደምና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ማመን ይኖርብናል በምስጋና ተሞልቻለሁ!»

# መንፈስ ቅዱስን የሚቀበለው ማነው?

*መጥምቁ ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ የመሰከረው ምንድን ነው?*

*እርሱ የዓለምን ኃጢአቶች ማለትም ያለፉትን፣ አሁን ያሉትንና ወደፊት የሚፈፀሙትን ሐጢያቶችና የአዳምንም ሐጢያት ሳይቀር የወሰደው የእግዚአብሄር በግ ኢየሱስ እንደሆነ መስክሯል፡፡*

በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ የሚያምን በሙሉ ደህንነትን ያገኛል መንፈስን ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው? የሐዋርያት ሥራ 2:38-39 መልሱን ይነግረናል *«ጴጥሮስም ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ የተስፋው ቃልም ለእናንተና ለልጆቻችሁ ጌታ አምላካችንም ወደ እርሱ ለሚጠራቸው በሩቅ ላሉ ሁሉ ነውና አላቸው፡፡»*

በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ማለት በኢየሱስ ጥምቀት ማመንና ቤዛነትን ማግኘት ማለት ነው ያን ጊዜ መንፈስ የእግዚአብሄር ስጦታ ሆኖ ይሰጣል፡፡


በኢየሱስ ክርስቶስ ስም መጠመቅ ማለት በክርስቶስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደም በማመን መቀደስ ማለትም ጭምር ነው ይህን እምነት ስንቀበል ቤዛነትን እናገኝና ፃድቃን እንሆናለን አማኞች በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀሉ ላይ

ባፈሰሰው ደሙ በሚያምኑ ጊዜ እንደ በረዶ የነጡ ይሆናሉ፡፡

*«የመንፈስ ቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ»* ኃጢአቶቻችን በሙሉ ወደ ኢየሱስ ክርስቶስ መተላለፋቸውንና ለእነዚህ ኃጢአቶችም ሲል በመስቀል ላይ ፍርድን እንደተቀበለልን ስናምን ልባችን ይፀዳል በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ስናምን አዲስ ህይወትን እንጀምራለን በዚህም የመንፈስ ቅዱስ ስጦታን ተቀብለን የእግዚአብሔር ቅዱሳን ልጆች እንሆናለን፡፡

*«እውነትንም ታውቃላችሁ፣ እውነትም አርነት ያወጣችኋል» (ዮሐንስ 8:32)* የጌታን የመስቀል ላይ ፍርድ ትክክለኛ ትርጉም ልናውቅ ይገባናል እውነቱ ኢየሱስ ክርስቶስ በጥምቀቱና በመስቀሉ ላይ ባፈሰሰው ደም ኃጢአታችንን መደምሰሱ ነው ቤዛነት የሚሰጠን እውነቱን ስናምን ነው፡፡

## የኢየሱስ ጥምቀት ያድነናል




በብሉይ ኪዳን የመስዋዕት ስርአት አማካይነት የሚከናወነው የሐጢያት ስርየት በአዲስ ኪዳን የኢየሱስን ጥምቀት ያመላክታል የኢየሱስ ጥምቀት በብሉይ ኪዳን ላሉ ትንቢቶች በሙሉ መሰረት ነው በብሉይ ኪዳን እጆችን የመጫኑ

እኩያ በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ጥምቀት ውስጥ ሊገኝ ይችላል፡፡

የእስራኤሎች ሐጢያቶች በእጆች መጫን አማካይነት ወደ አዛዜሉ ፍየል እንደተሸገረ ሁሉ የአለም ሐጢያቶች በሙሉም በጥምቀቱ አማካይነት ወደ ኢየሱስ ተሻግረዋል፡፡

ከኃጢአቶቻችን በሙሉ ለመዳን በኢየሱስ ጥምቀት ማመን አለብን? አዎን! በዚህ ማመን አለብን! ኢየሱስ በጥምቀቱ ኃጢአቶቶቻችንን በሙሉ የመውሰዱን እውነት መቀበል አለብን በኢየሱስ ጥምቀት የማናምን ከሆንን ኃጢአቶቻችን ወደ እርሱ ሊተላለፉ አይችሉም ደህንነነታችንን ሙሉ ለማድረግ በዚህ ማመን አለብን ከዚህ ውጭ ግን መቼም ቢሆን ፃድቃን ልንሆን አንችልም፡፡

ኢየሱስ በጥምቀቱ የአለምን ሐጢያተኞች በሙሉ እጅግ ተስማሚና ፃድቅ በሆነ መንገድ አድኖዋቸዋል ከዚህ ሌላ ምንም መንገድ የለም የኢየሱስ ጥምቀት ኃጢአቶች ሁሉ ወደ እርሱ የተሻገሩበት ሒደት በመሆኑ ልቦቻችን ለዘለቄታው ከሐጢያት ይፀዱ ዘንድ ልናምንበት ይገባናል፡፡

የኢየሱስ ደም ለኃጢአቶቻችን ሁሉ የተሰጠ ፍርድ እንደነበርም ማመን ይገባናል ስለዚህ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም የሚያምኑ በሙሉ ከኃጢአት ድነዋል፡፡

ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት በኢየሱስ ጥምቀት ማመን ይገባናል ይህ ትክክለኛ ቅጣትን የምናልፍበትና ከኃጢአቶቻችንም በሙሉ የምንነፃበት ብቸኛው መንገድ ነው፡፡

በአዲስ ኪዳን ያለው የኢየሱስ ጥምቀትና በብሉይ ኪዳን ያለው እጆችን መጫን አንዳቸው ለሌላቸው መስተዋት ናቸው እነዚህም በብሉይ ኪዳንና በአዲስ ኪዳን መካከል ያሉ ማያያዣ ቀለበቶች ናቸው፡፡

በአዲስ ኪዳን አጥማቂው ዮሐንስ ወደ ምድር የመጣው

ከኢየሱስ 6 ወር አስቀድሞ ነበር ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ *«የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ» (ማርቆስ 1:1)* ወንጌሉ የሚጀምረው በጥምቀቱ ኢየሱስ የዓለምን ኃጢአት በሙሉ በወሰደ ጊዜ ነው፡፡

ለሰው ዘር ደህንነት የተደረገው አገልግሎት እንደ ሰንሰለት በተያያዙ ክስተቶች አማካይነት ተግባራዊ ተደርጓል ይህም የኢየሱስ መወለድ የእርሱ ጥምቀት የመስቀል ላይ ሞቱና ትንሳኤው እንዲሁም ወደ ሰማይ ያደረገው ዕርገቱ ናቸው በእነዚህ የክስተቶች ሰንሰለት ውስጥ ያለውን የደህንነት ሒደት አውቀን በመረዳት ስናምን ከሐጢያቶቻችን ሁሉ እንድናለን የኢየሱስ ጥምቀት የወንጌል መጀመሪያው ሲሆን በመስቀል ላይ ያፈሰሰው ደሙ ደግሞ መደምደሚያው ነው፡፡

*«የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል መጀመሪያ» (ማርቆስ 1:1)* የጽድቅ ምግባሮቹን -ጥምቀቱን በመስቀል ላይ ያፈሰሰውን ደሙን ትንሳኤውን ዕርገቱንና ዳግም ምፅአቱን - አንዳቸውንም ከእግዚአብሄር ልጅ ወንጌል መግደፍ አንችልም፡፡

ኢየሱስ ስጋን ለብሶ ወደዚህ ምድር በመምጣት የሰው ዘር ኃጢአቶች በሙሉ በጥምቀቱ አስወገደ የሰማያዊው ወንጌል ጅማሬ ይህ ነው ከእነዚህ አንዱ እንኳን ቢጎድል ሰማያዊው ወንጌል የተሟላ ባልሆነም ነበር፡፡

ስለዚህ አንድ ሰው ዳግም ለመወለድ ቢፈልግ በክርስቶስ ጥምቀትና በደሙ እውነት አያምኑም ብዙዎችም የኢየሱስ ጥምቀት ኃይማኖታዊ ስርዓት ብቻ እንደሆነ ያስባሉ ይህ አደገኛና የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው ማንም በኢየሱስ የሚያምን ሁሉ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙም ጭምር ማመን አለበት፡፡

ለይቅርታ በመፀለይ ብቻ ኃጢአቶቻችን እንዴት ሊነፁልን ይችላሉ? ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ ሲጠመቅ ሐጢያቶቻችን

በሙሉ ወደ እርሱ ተሻገሩ ከዚህ ሌላ የሰው ዘርን ኃጢአት ሊወስድ የሚችልበት ምንም ሌላ መንገድ አልነበረውም::

*መንግስተ ሰማያት ለመግባት ከውኃና ከመንፈስ ዳግም መወለድ ይኖርብናል ያለ ውኃ ጥምቀት ያለ መስቀሉ ደሙና ያለ መንፈስ ቤዛነት ሊኖር አይችልም ኢየሱስ በዮሐንስ 3:5 ላይ ለኒቆዲሞስ እንደነገረው እግዚአብሄርን ማየት የሚችለው ዳግም የተወለደ ሰው ብቻ ነው እውነተኛ ደህንነት የምናገኘው በኢየሱስ ጥምቅትና በደሙ ስናምን ነው::*

## ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ልንድን እንችላለን?

*ኢየሱስ አዳኛችን የሆነው እንዴት ነው?*

*በጥምቀቱ ኃጢኣቶቻችንን በሙሉ በመውሰዱ ነው::*

ኢየሱስ ወደዚህ ምድር መጥቶ በጥምቀቱ አማካይነት ሐጢያቶቻችንን በሙሉ የመውሰዱን እምነት ከይፋ አገልግሎቱ ከገደፍን ወይም ከድንግል ማርያም የተወለደውን የኢየሱስን ቅድስና ቸል ካልን ወይም በክርስቶስ መስቀል ለማመን ግድ የለሾች ከሆንን ክርስትና ልክ እንደ ቡዲስቶች በመቅደሶቻቸው ውስጥ እንደሚያደርጉት ምዕመናን «ይቅር በለኝ! ይቅር በለኝ! ይቅር በለኝ!» ብለው እንዲጮሁ የሚመራ ተራ የሆነ ወግ አጥባቂ ሐይማኖት ይሆናል::

የኢየሱስን ጥምቀት መተው ማለት ኃጢአቶቻችን ወደ

እርሱ አልተላለፉም ማለት ነው እምነታችን ከንቱ ይሆናል በተጨባጭ ምንም የከፈለው ነገር ሳይኖር እዳዎቹን ሁሉ እንደከፈለ ከሚናገረው ባለ ዕዳም የተለየን አንሆንም ዋሾዎች ያደርገናል ባለዕዳው በተጨባጭ ምንም የከፈለው ነገር ሳይሆን እዳዎቹን ሁሉ መክፈሉን ከተናገረ በተግባርም በሕሊናም ገና ባለ ዕዳ ነው።

ኢየሱስ በጥምቀቱ ውሃ ምዕመናንን አንፅቶ የእግዚአብሄር ልጆች አድርጎዋቸዋል በእርሱ የሚያምኑት በሙሉ ይጸድቁ ዘንድም ኢየሱስ ክርስቶስ በመጥምቁ ዮሐንስ እጅ በመጠመቅ ኃጢአታቸውን በሙሉ ወስዷል ይህንን ስናውቅና ስንገነዘብ ኃጢአቶቻችን በሙሉ ይወገዱልናል።

ለፀጋው እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ሉቃስ 2:14 እንዲህ ይናገራል *«እግዚአብሔርንም እያመሰገኑ ክብር ለእግዚአብሔር በአርያም ይሁን ሰላምም በምድር ለሰውም በጎ ፍቃድ አሉ»* በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ያለን እምነት ደህንነትን አምጥቶልን የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን አድርጎናል የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ አድኖናል በእነዚህ ሁለት ነገሮች ያመነ ሁሉ ይድናል።

ከስራዎቹ ምንም የሚተው ነገር የለም አንዳንዶች ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ መስቀሉ እንጂ በሌላ አልተመካም በመስቀሉ ብቻ ሲያምኑ ይታያሉ ሆኖም ግን የኢየሱስም ጥምቀት ከመስቀሉ ጋር የተገናኘ ነው።

በሮሜ ምዕራፍ 4 ላይ ጳውሎስ በክርስቶስ መጠመቁንና ከክርስቶስ ጋር መሞቱንም እናያለን በተጨማሪም በገላትያ 2:20 ላይ *«ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኜየ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው»* ተፅፎዋል።

እንዲሁም በገላትያ 3:27-29 ላይ እንዲህ ተፅፎዋል *«ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም ባርያ ወይም ጨዋ ሰው የለም ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁም በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ እናንተም የክርስቶስ ከሆናችሁ እንኪያስ የአብርሃም ዘር እንደ ተስፋውም ቃል ወራሾች ናችሁ::»*

በኢየሱስ ክርስቶስ መጠመቅ ማለት ኢየሱስ በዚህ ምድር ላይ እያለ በሰራቸው ነገሮች በጥምቀቱና በደሙ ማመን ማለት ነው በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ማመን ማለት ደግሞ ኢየሱስ ከ2000 ዓመታት በፊት ኃጢአታችንን ደመሰሰልን በሚለው እውነት ማመን ነው ደህንነትን የሚያስገኝልን ሌላ ምንም አይነት መንገድ የለም::

## በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደም ስናምን በእግዚአብሔር ዘንድ ድነናል::

*ለይቅርታ በመፀለይ ብቻ ኃጢአቶቻችን ሊነጹ ይችላሉን?*

*አይችሉም:: ለኃጢአቶቻችን ይቅርታ የምናገኘው ኃጢአቶቻችን በሙሉ ኢየሱስ በመጥምቁ ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ ወደ እርሱ መተላለፋቸውን ስናምን ብቻ ነው::*

*«ሰው በልቡ አምኖ ይጸድቃልና በአፉም መስክሮም ይድናልና።» (ሮሜ 10:10)*

*«ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ፤ ክርስቶስን ለብሳችኋልና» (ገላትያ 3:27)* እምነታችን በክርስቶስ እንድንጠመቅ ክርስቶስን እንድንለብስና የእግዚአብሔር ልጆች እንድንሆን ያደርገናል ኢየሱስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ በተጠመቀ ጊዜ የኛ ኃጢአትና የዓለም ኃጢአቶች በሙሉ ወደ እርሱ ተላልፈዋል።

እምነታችን ከክርስቶስ ጋር ህብረትን እንመሰረት ዘንድ መርቶናል እርሱ በሞተ ጊዜ እኛም ሞተናል እርሱ በተሰቀለም ጊዜ እኛም ተሰቅለናል አሁንም እኛ በኢየሱስ ክርስቶስ፣ በጥምቀቱ፣ በሞቱ፣ በትንሳኤውና በዕርገቱ ስለምናምን ወደ እግዚአብሔር መንግስት ገብተን ለዘላለም እንኖራለን።

ሰዎች በኢየሱስ ደም ብቻ የሚያምኑ ከሆነ በልባቸው ውስጥ በተሞላው ኃጢአት ከመሰቃየት ውጭ ምንም ሊያደርጉ የሚችሉት ነገር የለም ለምን? ምክንያቱም እነሱ የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ የወሰደውንና በሐጢያት የተሞሉትን ልቦች አንፅቶ ለዘላለም እንደ በረዶ ነጭ ያደረጋቸውን የኢየሱስን ጥምቀት ትርጉም አያውቁትም አይቀበሉትምም።

ከኃጢአታችሁ በሙሉ ለዘላለሙ ባዳናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትና ደም ታምናላችሁን? እባካችሁ በዚህ በማይለወጥ እውነት እመኑ በኢየሱስ ጥምቀት የማታምኑ ከሆናችሁ እምነታችሁ ከንቱ ነው በኢየሱስ ጥምቀት እምነት የሌላችሁ ከሆናችሁ ለኃጢአቶቻችሁ ቤዛነትን ልታገኙ አትችሉም ምላሽ በሌለው ፍቅር ውስጥም ተጠምዳችኋል።

እነዚያ በመስቀሉ ብቻ የሚያምኑ ሰዎች «ኢየሱስ ጌታዬ በመስቀል ላይ ለእኔ የሞተልኝ አዳኜ ነው እንደገናም ለትንሳኤው ምስክርነት ተነስቶ ለ40 ቀናት ያህል ቆይቶ ወደ

ሰማይ አርጓል አሁንም በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀምጧል እኛን ሊፈርድ ለሁለተኛ ጊዜ እንደሚመጣ አምናለሁ ኢየሱስን ልገናኘው እንድችል ሙሉ በሙሉ እንዲለውጠኝ እፀልያለሁ ኦ! ወዳጄና ጌታዬ ኢየሱስ!» አዳኜ መጥቶ ሙሉ በሙሉ እንደሚቀይረኝና እርሱን ማግኘት የምችል እንደሚያደርገኝም አምናለሁ ኦ ጌታዬ! ኢየሱስ ሆይ!» ሲሉ ይደመጣሉ::

ለኃጢአታቸው ይቅርታን ይጠይቃሉ በዚህም ከኃጢአት ነፃ የሚሆኑ ይመስላቸዋል ነገር ግን በልባቸወ ኃጢአት አለ «በኢየሱስ አምናለሁ ሆኖም ግን በልቤ ኃጢአት አለ ኢየሱስን ብወደውም በውስጤ ኃጢአት አለ «ሙሽራዬ ወደ እኔ ና» ልለው ግን አልችልም ምክንያቱም በልቤ ውስጥ ኃጢአት አለብኝና ኃጢአት በልቤ ስላለም ስለ መዳኔ እርግጠኛ አይደለሁም ስለሆነም ኢየሱስ የሚመጣው እኔ በደንብ ስዘጋጅና በደንብ ስፀልይ እንደሆነ ተስፋ አደርጋለሁ ኢየሱስን በጣም በሙሉ ልቤ የምወደው ብሆንም በልቤ ውስጥ ኃጢአት ስላለ ልጋፈጠው አልደፍርም::

ኢየሱስ እነዚህ ሰዎች «ሙሉ አይደለንም ብላችሁ ለምን ታስባላችሁ?» ብሎ ቢጠይቃቸው፤

መልሳቸው የሚሆነው «ጌታ ሆይ! በየዕለቱ ኃጢትን ስለምሰራ ፃድቅ አለመሆኔን አውቃለሁ ስለሆነም ኃጢአተኞችን በምትጠራ ጊዜ አስታውሰኝ» ይሆናል::

የሁሉም ነገር ፈጣሪና ፈራጅ የሆነው እግዚአብሔር ኃጢያተኞችን አይቀበልም ልጆቹም አያደርጋቸውም::

ሙሽራው መጥቶ የሙሽራይቱን የኃጢአት ችግር በሙሉ ያቀለላት ቢሆንም እርሷ ግን ይህን ባለማወቋ ጠፍታለች በስጋችን ኃጢአትን ስለሰራን ብቻ በእግዚአብሔር ፊት ኃጢአተኞች ነን ብለን የምናስብ ከሆነ በእግዚአብሔር እምነት የለንም ማለት ነው የእግዚአብሔርን የእውነት ቃልም

ባልተረዳንና ባላወቅን ጊዜም ኃጢአት በልባችን መራባቱን ይቀጥላል::

*ሰዎች በልባቸው ውስጥ በቀረ ኃጢአት የሚሰቃዩት ለምንድን ነው?*

*የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ ያስወገደውን የኢየሱስን ጥምቀት ትርጉም ባለማወቃቸው ወይም ባለመገንዘባቸው ነው::*

ሙሽራው የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ አስወግዷል የት? በዮርዳኖስ በተጠመቀ ጊዜ:: እነዚያ በዚህ የማያምኑት በሙሉ ኃጢአተኞች ናቸው እነዚህ ሰዎች የረከሱ ሙሽሮች ሆነው ይቀራሉ::

ሙሽራውም የሚያገባትን «የኔ ሙሽራ ሳትሆኚ እንዴት ልታፈቅሪኝ ትችያለሽ? እኔን ሙሽራዬ ብለሽ ከመጥራትሽ በፊት ከኃጢኣትሽ በሙሉ መንፃት አለብሽ::»

ያለ ኢየሱስ ጥምቀት ቤዛነትን ልናገኝ እንችላለን? አንችልም! እኛ የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አምሳል ነው ስለዚህ በልቦቻችን ፍትህን እንሻለን ሕሊናችንም ንፁህ ሊሆን ይሞክራል ነገር ግን ልባችን ከኃጢአት ሳይነፃ እኛ ራሳችንን ፃድቃን እንደሆንን አድርገን ማሰባችን ስህተት ነው በትክክል ኃጢአት አልባና ፃድቃን ነን ልንል የምንችለው በኢየሱስ ጥምቀት የምናምን ስንሆን ብቻ ነው::

በልቦቻችን ውስጥ በተጨባጭ ሐጢያት እያለ ረሳችንን ያለ ሐጢያት እንደሆንን አድርገን የምንመለከት ከሆንን ሕሊናችን

በጭራሽ ሊቀደስ አይችልም በዚህ አይነት ሁኔታም እግዚአብሔርም አይቀበለንም እግዚአብሔር መቼም አይዋሽም፡፡

እግዚአብሄር የእስራኤልን ልጆች እንዲቆጥርና ለሕይወታቸው ቤዛነትን እንዲከፍሉ ለሙሴ ነገረው ባለጠጋው ከግማሽ ሰቅል በላይ አይሰጥም ደሃውም ከዚያ ያነሰ አይሰጥም እያንዳንዱ ሰው ቤዛ ይከፍላል፡፡

ስለዚህ አንድ ሰው ለህይወቱ ቤዛነትን በከፈለለት በኢየሱስ ካላመነ እንዴት ሊቀደስ ይችላል? እንደዚህ ያለ ሰው በልቡ ውስጥ ኃጢአት መኖሩን ይቀጥላል፡፡

በኢየሱስ ደም ብቻ የምናምን ከሆነ በልባችን ውስጥ ኃጢአት እንዳለና ሐጢያተኞች መሆናችንንም መናዘዝ ይኖርብናል ነገር ግን በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ስናምን በትክክል ኃጢአት እንደሌለብን መናገር እንችላለን በዚህም ደህንነትና ዘላለማዊ ህይወት የእኛ ይሆናሉ፡፡

## መንፈስ ቅዱስን መሳደብ

*የሰውን ልጅ ወደ ገሃነም የሚልከው ምን አይነት ኃጢኣት ነው?*

*በመንፈስ ቅዱስ ላይ የሚሰራ ኃጢአት ማለትም በኢየሱስ ጥምቀት አለማመን ነው፡፡*

ሮሜ 1:17 እንዲህ ይላል *«የእግዚአብሔር ፅድቅ ከእምነት ወደ እምነት በእርሱ ይገለጣልና»* የእግዚአብሔር ፅድቅ በወንጌል ውስጥ ተገልጦዋል ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ አለም መጥቶ ሀጢያቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱና በመስቀል ላይ ሞቱ አስወገዳቸው የኢየሱስ ጥምቀትና ደሙ የወንጌል ሐይል ነው ኢየሱስ ሐጢያቶቻችንን ለአንዴና ለዘላለም አስወግዶዋቸዋል።

ማመን ማለት መዳን ሲሆን፣ አለማመን ደግሞ ዘላለማዊ ገሃነም ማለት ነው በሰማይ ያለው አባታችን አንድያ ልጁን ወደዚህ ምድር ልኮ ስለ እኛ ኃጢአት እንዲጠመቅ አደረገው ስለዚህ በእረሱ የሚያምን ከመተላለፎቹ ሁሉ መንፃት ይችላል።

በዚህ አለም ላይ የቀረው ብቸኛው ኃጢአት በእርሱ ጥምቀትና ደም የአለማመን ሐጢያት ነው አለማመን መንፈስ ቅዱስን መሳደብ ነው ይህም የማምነውን ሰው ለሲዖል የሚኮንነውና የእግዚአብሄርን ፍርድ የሚቀበልበት ሐጢያት ነው ይህ ከሐጢያቶች ሁሉ እጅግ አስከፊው ሐጢያት ነው ይህንን ሐጢያት ከሰራችሁ ንስሐ መግባትና በኢየሱስ ጥምቀት በማመን ቤዛነትን ማግኘት አለባችሁ እንደዚያ ካልሆነ ለዘላለም ትጠፋላችሁ።

በእርሱ ጥምቀትና በደሙ አማካይነት በሆነው የቤዛነት ምስክርነት ድናችኋልን? የዮሐንስን ምስክርነት በዮሐንስ 1:29 ላይ በተጻፈው መሰረት ተቀብላችሁታልን? *«እነሆ የዓለምን ኃጢኣት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!»* በዕብራውያን 10:18 ላይ በተጻፈው መሰረት በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ታምናላችሁን? *«የእነዚህም ስርየት ባለበት ዘንድ ከዚህ ወዲህ ስለ ኃጢአት ማቅረብ የለም።»*

እግዚአብሔር በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ለሚያምኑት በልቦቻቸው ውስጥ ማረጋገጫን ሰጥቶዋቸዋል እግዚአብሄር ልጆቹ አድርጎዋቸዋል በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ የሚያምኑ

ፃድቅ በሆነው የኢየሱስ ፍቅር ቤዛነትን አግኝተዋል፡፡

እግዚአብሔር የላከው የእግዚአብሔርን ቃል ይናገራል ከመሬት የሆነውና እግዚአብሔር ያልላከው ግን የሚሰብከው የራሱን አስተሳሰብ ነው በዚህ ምድር ላይ የእግዚአብሔርን ቃል የሚሰብኩ ብዙዎች ናቸው በእግዚአብሄር የተላኩ የኢየሱስን ጥምቀትና የደሙን ወንጌል ይሰብካሉ፡፡

ነገር ግን የራሳቸውን ቃሎች የሚሰብኩ የራሳቸውን አስተሳሰቦች ብቻ እያብራሩ ነው «ከአዳም ሐጢያት ድነናል ሆኖም ግን ሁላችንም በየዕለቱ የምንሰራቸውን ኃጢአቶቻች ለማስተሰረይ መፀለይ አለብን» ብለው ይሰብካሉ ቀስ በቀስም እንደምንቀደስ ይናገራሉ፡፡

ነገር ግን ሰው በራሱ ጥረት ሊቀደስ ይችላልን? በራሳችን ትሩፋቶች ብርታትና በጥረቶቻችን መቀደስ እንችላለንን? የተቀደስነው እግዚአብሄር ሐጢያቶቻችንን በሙሉ በማስወገዱ ነው ወይስ በገዛ ራሳችን ቤዛነትን ለማግኘት ስለሞከርን?

እውነተኛው እምነት ይቀድሰናል ከሰልን ለአንድ ሺህ ጊዜ በማጠብ ነጭ ልናደርገው ይቻለናልን? ጥቁር ቆዳንስ ነጭ ማድረግ ይቻለናልን? ምንም ያህል ሳሙና ወይም በረኪና ብንጠቀም ኃጢአታችንን ልናነፃው አንችልም ፅድቃችን የመርገም ጨርቅ ነው የምንፀድቀው በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ በማመን ነው ወይስ በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ በማመን ብቻ?

እውነተኛ እምነት የሚመጣው በኢየሱስ የጥምቀቱ ውኃና በመስቀል ላይ ካፈሰሰው ደም ነው ደህንነት ከራሳችን ጥረት ሊመጣ አይችልም ከኃጢኣት ሊያነፃንና ፃድቃን ሊያደርገን የሚችለው በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ያለን እምነት ብቻ ነው፡፡

እግዚአብሔር የሰው ልጆችን በሙሉ በልጁ እጅ አሳልፎ

ሰጥቷል በእርሱ የሚያምን ሁሉም ዘላለማዊ ህይወትን ያገኛል በልጁ ማመን ማለት በጥምቀቱና በደሙ በማመን በሚገኘው ደህንነት ማመን ማለት ነው በዚህ የሚያምን የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ዘላለማዊ ህይወትን ያገኛል የዳኑትም ለዘላለም በእግዚአብሄር ቀኝ ይኖራሉ፡፡

በኢየሱስ ጥምቀትና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው አንድነቱ ማመን በመንፈሱም ማመን ነው የእውነት ቃል ዳግም እንድንወለድ ይፈቅድልናል በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ በማመን ድነናል፡፡

እምነት ይኑራችሁ በኢየሱስ ጥምቀትና በደሙ ማመን ማለት ዘላለማዊ ቤዛነትን ማግኘት ማለት ነው በእውነተኛው ወንጌል በማመን የኃጢአት ይቅርታን አግኙ፡፡ ✉

# ስብከት 8

# የአብን ፈቃድ በእምነት

# እንፈፅም

ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ..ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡



«በነገው ዮሐንስ ኢየሱስን ወደ እርሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለው፡- «እነሆ! የዓለምን ኃጢኣት የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ!» (ዮሐንስ 1፡29)


ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር (www.amazon.com) በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ፡፡

# የአብን ፈቃድ በእምነት እንፈፅም

**« ማቴዎስ 7:21-23 »**

**«በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም በዚያን ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን በስምህ አጋንንትን አላወጣንምን በስምህ ብዙ ታምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላውቅኋችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ።»**

## ምናልባት እኔም አንዱ ነኝ




ኢየሱስ ክርስቶስ *«በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት አይገባም»* ብሎ ተናግሮዋል እነዚህ ቃሎች በበርካታ

ክርስቲያኖች ልቦች ውስጥ ፍርሃትን በመጫር የእግዚአብሄርን ፈቃድ ያደርጉ ዘንድ እንዲጥሩ አድርገዋቸዋል፡፡

በርካታ ክርስቲያኖች መንግስተ ሰማያት ለመግባት የሚያስፈልጋቸው ብቸኛው ነገር በኢየሱስ ማመን እንደሆነ ያስባሉ ነገር ግን «ጌታ ጌታ» የሚለው ሁሉ መንግስተ ሰማያት እንደማይገባ ማቴዎስ 7:21 ይነግረናል፡፡

ይህን ጥቅስ ያነበቡ ብዙዎች «አንዱ እኔ ሳልሆን አልቀርም» ይላሉ «አይደለም ኢየሱስ የተናገረው ስለማያምኑት ነው» በማለት ራሳቸውን ይሸነግላሉ አሳቡ ግን በአእምሮዋቸው ውስጥ ይቀርና ያውካቸዋል፡፡

ስለዚህ *«በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ»* በሚለው የጥቅሱ ቀጣይ ክፍል ላይ ይንጠለጠላሉ *«የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ»* በሚሉት ቃሎች ላይ በመንጠልጠል አስራትን በታማኝነት በመክፈል የንጋት ፀሎት በመፀለይ በመስበክ በጎ ምግባሮችን በማድረግና ሐጢያትን ባለመስራት ያንን ማድረግ እንደሚችሉ ያስባሉ...ጠንክረው ይሞክራሉ እነርሱን ማየት ያሳዝነኛል፡፡

ብዙ ሰዎች ይህን ጥቅስ ባለመረዳታቸው ስህተቶችን ይሰራሉ ስለዚህ ሁላችንም የእግዚአብሄርን ፈቃድ አውቀን በዚያ እንኖር ዘንድ ይህንን ጥቅስ በግልፅ ላብራራው እወዳለሁ፡፡


በመጀመሪያ ልጁ የሕዝቡን ሐጢያቶች እንደወሰደና ከሐጢያት ነፃ እንዲያደርገን የእግዚአብሄር ፈቃድ መሆኑን ማወቅ አለብን፡፡

በኤፌሶን 1:5 ላይ እንዲህ ይላል *«በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን፡፡»*

በሌላ አነጋገር የእርሱ አላማ ኢየሱስ ክርስቶስ ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ያስወገደበትን እውነተኛ ወንጌል

አውቀን ዳግም እንድንወለድ መፍቀድ ነው ሐጢያቶቻችንን በሙሉ ወደ ልጁ ወደ ኢየሱስ በማሻገር ከውሃና ከመንፈስ ዳግም እንድንወለድ ይፈልጋል ይህ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው፡፡

## «ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ!» ማለት ብቻ





*«በሰማያት ያለውን የአባቴን ፈቃድ የሚያደርግ እንጂ ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ የሚለኝ ሁሉ መንግስተ ሰማያት የሚገባ አይደለም» (ማቴዎስ 7:21)*

የአብን ፈቃድ በሁለት መንገድ መረዳት አለብን በቅድሚያ ለኃጥያታችን ምህረት እንደተደረገልን እና ከውሃ እና ከመንፈስ ዳግም መወለዳችን የእርሱ ፈቃድ እንደሆነ ማወቅ አለብን ሁለተኛ በዚህ እምነት መሰረት መስራት አለብን፡፡

በምድር ላይ ያሉትን ሰዎች ሁሉ ኃጥአት መደምሰስ የእርሱ ፈቃድ ነው ሰይጣን ቅድመ አያታችን አዳም በኃጥያት እንዲወድቅ አድርጓል ነገር ግን የአባታችን ፈቃድ የሰውን ኃጥአት በሙሉ ማጥፋት ነው አሥራትን በታማኝነት መክፈል፣ የንጋት ፀሎት መፀለይ ለእኛ የአብ ፈቃድ አይደለም ለእኛ የአብ ፈቃድ ሁላችንም ከሐጢያት መዳን መሆኑን መረዳት ይገባናል የሰውን ልጅ በኃጢአት ባህር ውስጥ ከመስመጥ ማዳን የእርሱ ፈቃድ ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ማንም «ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ» የሚል ሁሉ መንግስተ ሰማያት እንደማይገባ ይናገራል ይህም ማለት በኢየሱስ ማመን ብቻ ሳይሆን አባታችን ከእኛ የሚሻውንም ማወቅ ይኖርብናል አዳምና ሔዋን ያስቀመጡልን ቅርስ ቢኖር በሐጢያት ውስጥ መኖር መሆኑን ስለሚያውቅ ከሐጢያትና ከሲዖል ፍርድ ያድነን ዘንድ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው::

## የእግዚአብሔር ፈቃድ




ማቴዎስ 3:15 *«እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና»* ይላል ኢየሱስ ሁላችንንም ለማዳን ወደዚህ አለም የመጣው የእግዚአብሄርን ፈቃድ ለመፈፀም ነበር ኢየሱስ በአጥማቂው ዮሐንስ በተጠመቀ ጊዜ የእግዚአብሄር ፈቃድ ተፈፀመ::

እርሱ እኛን ለማዳንና የእርሱ ልጆች ለማድረግ ፈለገ ያንን ለማድረግ የእርሱ ልጅ የእኛን ኃጢአት ሁሉ መውሰድ ነበረበት ሕዝቡን ሁሉ የእርሱ ልጆች ማድረግ የእርሱ ፈቃድ ነበር ለዚህም በሠይጣን ወጥመድ ውስጥ የወደቁትን ሰዎች ኃጢአት በሙሉ ለመውሰድ የእርሱን ልጅ ላከ ሕዝቡ ሁሉ የእርሱ ልጆች ይሆኑ ዘንድ የገዛ ልጁን ሕይወት ለእነርሱ ሲል ማቅረብ ነበረበት::

ኢየሱስ በተጠመቀና በመስቀል ላይ በሞተ ጊዜ የእግዚአብሔር ፈቃድ ተፈጸመ ኢየሱስ በተጠመቀ ጊዜ ኃጢያቶቻችን ወደ እረሱ እንደተሻገሩና በመስቀል ላይ ሞቱም የመተላለፎቻችንን ፍርዶች በሙሉ እንደወሰደ ማመን እግዚአብሄር ለእኛ ያለው ፈቃድ ነው::

*«እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» (ዮሐንስ 3:16)* እግዚአብሔር ህዝቡን ከኃጢአት አድኗል ኢየሱስ በይፋ በጀመረው አገልግሎቱ መጀመሪያ ያደረገው ነገር ቢኖር በአጥማቂው ዮሐኝስ መጠመቅ ነው::

*«ኢየሱስም መልሶ አሁንስ ፍቀድልኝ እንዲህ ጽድቅን ሁሉ መፈጸም ይገባናልና አለው ያን ጊዜ ፈቀደለት» (ማቴዎስ 3:15)* ኢየሱስ ወደ እዚህ ዓለም መምጣቱ በጥምቀቱ አማካይነትም የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ መውሰዱ በመስቀል ላይ መሞቱና መነሳቱም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር::

ይህንን በግልጽ ማወቅ አለብን ብዙዎች ማቴዎስ 7:21 በማንበብ ቤተክርስቲያናትን ለመገንባት አለማዊ ሐብቶቻችንን በሙሉ በመስጠት እስከ ሞት ድረስ ጌታን ማገልገል እግዚአብሄር ለእኛ ያለው ፈቃድ ይህ እንደሆነ ያስባሉ::

ውድ ወዳጆች እኛ በኢየሱስ የምናምን መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ከዚያም መፈጸም አለብን የእርሱን ፈቃድ ሳታውቁ ራሳችሁን ለቤተክርስቲያን ቀድሶ መስጠት ስህተት ነው::

ሰዎች በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያኖቻቸው አምኖ ከመኖር ውጭ ሌላ ምን አማራጭ አለ ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ ነገር ግን እኔ ራሴ በፕሪስቤተሪያን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የካልቪን ትምህርት ተምሬያለሁ እንደ ማንኛውም መጋቢ ሐይማኖተኛ በነበረች አሳዳጊ እናት እጅም አድጌያለሁ

የተማርሁት ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተብሎ በሚጠራ ቤተክርስቲያን ውስጥ ነበር፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ከብንያም ነገድ በመሆኑና በወቅቱ በነበረው በገማልያል ስር ሕግን በመማሩ ትምክህት ነበረው ጳውሎስ ዳግመኛ ከመወለዱ በፊት በኢየሱስ የሚያምኑትን ለማሰር እየተጓዘ ነበር ነገር ግን በደማስቆ መንገድ ላይ በኢየሱስ አምኖ ከውሃና ከመንፈስ ዳግም በመወለድ በረከት አማካይነት ፃድቅ ሆነ፡፡

## የእግዚአብሔርን ፍቃድ ከማድረጋችን በፊት ልናውቀው ይገባናል

*በኢየሱስ ከማመናችን በፊት*
*በመጀመሪያ ምን ያስፈልገናል?*

*ፈቃዱን ማወቅ አለብን፡፡*

ቅድስናችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው *«ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና» (1ኛ ተሰሎንቄ 4:3)* በውኃውና በመንፈሱ አማካይነት ሙሉ በሙሉ ተቀድሰን በሕይወት ዘመናችን ሁሉ በእምነት እንኖር ዘንድ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው፡፡

ማንም ሰው በኢየሱስ የሚያምንና በልቡ ግን አሁንም ድረስ ኃጢአት እንዳለበት የሚያስብ ከሆነ ይህ ሰው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እየኖረ አይደለም ማለት ነው የእርሱን ፈቃድ መከተል በኢየሱስ በተገኘው ደህንነት አማካይነት

መቀደስን ይጠይቃል ይህንን ማወቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ ነው::

«በኢየሱስ ብታምኑም አሁንም ድረስ በልባችሁ ውስጥ ሐጢያት አለን?» ብዬ ስጠይቃችሁ መልሳችሁ አዎን ከሆነ በግልጽ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደማታውቁ መናገር ይቻላል በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ባለን እምነት መቀደሳችንና ከኃጢአት መንጻታችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው::

በአንድ ወቅት ታዛዥ ልጆች ያሉት አንድ ሰው ነበር አንድ ቀንም ከሁሉም ታላቅየውን ጠርቶ «ልጄ ከሜዳው ባሻገር ወዳለው መንደር ሂድ...» አለው::

አባቱ ንግግሩን ሳይጨርስ ልጁ «እሺ አባቴ» ብሎ ወደዚያ መንደር ጉዞ ጀመረ እዚያ ሄዶ ምን መስራት እንዳለበት ለመስማት ሳይጠብቅ በቀጥታ ተጓዘ::

አባትየውም ከኋላው ተከትሎት «ልጄ የምልህን መስማትህና ታዛዥ መሆንህ መልካም ነው ነገር ግን እኔ እንድታደርገው የምፈልገውን ነገር ማወቅ አለብህ» አለው::

ልጁ ግን አሁንም «አባቴ ችግር የለውም ከእኔ በላይ የሚታዘዝህ ማን አለ?» አለው::

ነገር ግን ባዶ እጁን ተመለሰ አባቱ ምን እንደፈለገ ሳያውቅ ሊያደርገው የሚችለው ምንም ነገር አልነበረም በእውር ድንብር ታዘዘ::

ኢየሱስን የማናውቀው ከሆነ ልክ እንደ ልጁ እንሆናለን ብዙዎች የነገረ መለኮት ትምህርቶችን በመከተል፣ አስራትን በታማኝነት በመክፈል፣ ሌሊቱን ሁሉ በመፀለይ፣ በመፆም ራሳቸውን ቀድሰው ይሰጣሉ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፈቃድ አያውቁም::

በልቦቻቸው ውስጥ ኃጢአት እያለ ከሞቱ ከሰማይ በር ይመለሳሉ የእግዚአብሔርን ስራ ለመስራት በጣም ጉጉቱ

ያላቸው ቢሆኑም እግዚአብሔር ምን እንደሚፈልግ ግን በትክክል አላውቁም፡፡

*አመፅን ማድረግ ማለት ምን ማለት ነው?*

*የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል ሳያውቁ ሐጢያተኛ ሆኖ በኢየሱስ ማመን ነው፡፡*

*«በዚያን ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ ጌታ ሆይ በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህ ብዙ ተዓምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ፡፡» (ማቴዎስ 7:22-23)*

እግዚአብሔር እኛ እንድንሰራቸው የሚፈልጋቸው ነገሮች አሉ እንዲሁም ደግሞ እኛ እንድንከተለው የሚፈልገው እምነት አለው ኢየሱስ ኃጢአቶቻችንን በሙሉ በጥምቀቱ እንደወሰደልን እንድናምን ይፈልጋል ይህንን ይጠይቀናል ብዙዎች ትንቢት ይናገራሉ አጋንንትን ያወጣሉ የውሃውንና የመንፈሱን እውነት ሳያውቁም በስሙ ድንቆችን ያደርጋሉ፡፡

ድንቆችን ማድረግ ማለት በርካታ ቤተ ክርስቲያናትን መገንባት ንብረትን ሁሉ ለቤተክርስቲያን መለገስና የገዛ ራስን ሕይወት ለእግዚአብሄር መስጠት ማለት ነው፡፡

በስሙ ትንቢትን መናገር ማለትም መሪ መሆን ማለት ነው እንደ እነዚህ ያሉ ሰዎች ኢየሱስን እየተቃወሙት በሕጉ እንደሚኖሩ የሚታበዩ ፈሪሳውያንን ይመስላሉ ይህ ኦርቶዶክስ

ክርስቲያኖች ነን የሚሉትንም ይመለከታል።

አጋንንትን ማውጣት ማለት ስልጣንን መጠቀም ማለት ነው ሁሉም በእምነታቸው የጋሉ ናቸው ነገር ግን ጌታ በመጨረሻው ቀን እንደማያውቃቸው ይነግራቸዋል እርሱ ሳያውቃቸው እነርሱ እንዴት ሊያውቁት እንደቻሉም ይጠይቃቸዋል።

ጌታም *«የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ»* ይላል በዚህ ቀንም ብዙ ሰዎች «ጌታ ሆይ! እኔ አምንብሃለሁ አዳኜ እንደሆንክ አምናለሁ» እያሉ ይጮኃሉ እንደሚወዱት ይናገራሉ በልባቸው ውስጥ ግን ሐጢያት አለ ኢየሱስ አመፃን የሚያደርጉ (ያልዳኑ ኃጢአተኞች) ብሎ ይጠራቸዋል ከእርሱ እንዲርቁም ይጠይቃቸዋል።

በዚያ ቀን ዳግም ውልደትን ሳያገኙ የሞቱትም በኢየሱስ ፊት ያለቅሳሉ «እኔ ትንቢትን ተናግሬኣለሁ ቤተ ክርስትያናትንም ገንብቻለሁ እንዲሁም በስምህ 50 ሚሽነሪዎችን ልኬያለሁ።»

ኢየሱስ ግን ለእነዚያ ሐጢያተኞች *«ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ»* ይላቸዋል።

«ምን ማለትህ ነው? በስምህ ትንቢት መናገሬን አታውቅምን? በቤተክርስቲያን ለብዙ አመት አገልግያሁ...ሌሎችም በአንተ ያምኑ ዘንድ አስተምሬኣቸዋለሁ እንዴት እኔን አታውቀኝም?»

እርሱም ሲመልስ «ከቶም አላወኩህም አንተ እኔን እንደምታውቅ ብትናገርም አሁንም በልብህ ውስጥ ሐጢአት ስላለ ከእኔ ራቅ» ይለዋል።

በልብ ውስጥ ኃጢአት እያለ ማመን ወይም በደህንነት ሕግ

መሠረት አለማመን በእግዚአብሄር ፊት አመፀኝነት ነው ከውኃና ከመንፈስ ዳግም የመወለድን እውነት ሳያውቁ የእርሱን ፈቃድ ለመፈፀም መሞከርም አመፀኛነት ነው ፈቃዱን ሳይቀበሉ እርሱን መከተልም አመፀኝነት ነው አመፀኝነት ደግሞ ኃጢአት ነው::

## የእግዚአብሔር ፈቃድ በመጽሐፍ ቅዱስ

*ፃድቃን እነማን ናቸው?*

*ምንም ኃጢያት የሌለባቸው ቅዱሳኖቹ ናቸው::*

ከውኃና ከመንፈስ ዳግም በምንወለድበት ወንጌል እንድናምን የእርሱ ፈቃድ ነው እውነተኛው ወንጌል ዳግም ውልደታችንን ያጠናክራል የእርሱ ልጆች ሆነን ለወንጌሉ መኖራችንም የእርሱ ፈቃድ ነው እኛም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ አለብን ነገር ግን እጅግ ብዙዎች ከውኃና ከመንፈስ ዳግም የምንወለድበትን ወንጌል አያውቁም::

ሰዎችን ለምን በኢየሱስ እንደሚያምኑ ስጠይቃቸው ብዙዎቹ የሚሰጡኝ መልስ ከኃጢአታቸው ለመዳን እንደሆነ ነው::

«በልባችሁ ውስጥ ኃጢአት አለ?» ብዬ ስጠይቅ፣
መልሳቸው «አዎን አለብኝ» ነው::
«ድናችኋል ወይስ አልዳናችሁም?» ለዚህም ሲመልሱ:-
«በእርግጥ ድኛለሁ» ይላሉ::

«በልቡ ውስጥ ኃጢአት ያለበት ኃጢአተኛ ወደ መንግስተ ሰማያት ሊገባ ይችላልን?» ብዬ ስጠይቅም መልሳቸው:-

«አይችልም» ነው::

«ታዲያ እናንተስ የምትሄዱት ወደ መንግስተ ሰማያት ነው ወይስ ወደገሃነም እሳት ነው?» ብዬ ስጠይቅ፣

ወደ መንግስተ ሰማያት ነው ይሉኛል ነገር ግን መግባት ይችላሉን? ወደ ሲዖል ይወርዳሉ::

አንዳንዶች በልባቸው ውስጥ ኃጢት ያለ ቢሆንም እንኳን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ብቻ ወደ መንግስተ ሰማያት ለመግባት የሚችሉ ይመስላቸዋል ሆኖም ግን እግዚአብሔር ኃጥአንን ወደ መንግስቱ አይቀበልም::

የእግዚብሔር ፈቃድ ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚናገረው የእግዚአብሔር ፈቃድ በልጁ ማመን በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ደሙ ቤዛነትን የማግኘት በረከት ማመን ነው::

ከውኃና ከመንፈስ ዳግም በመወለድ በረከት የሚያምኑ የእርሱ ልጆች ይሆናሉ የእርሱ ልጆች መሆን ክብራችን ነው የእርሱ ልጆች ደግሞ ፃድቃን ናቸው::

እግዚአብሔር እኛን ፃድቃን ብሎ ሲጠራን ኃጢአተኛ የሆነውን ክርስቲያን ፃድቅ አድርጎ ይቆጥረዋልን? እግዚአብሔር መቼም አይዋሽም ስለዚህ በእርሱ ፊት እናንተ ወይ ሐጢያተኛ አለበለዚያም ፃድቃን ናችሁ «ያለ ሐጢያት ሆኖ መቆጠር» የሚባል ነገር ሊኖር አይችልም ለቅድስና የሚጠራቸው በውሃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑትን ብቻ ነው::

*የእግዚአብሔር ልጆች መሆን የምንችለው እንዴት ነው?*

*የውኃውንና የደሙን ወንጌል በመቀበል ነው።*

እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ኃጢኣት በሙሉ ወደ ልጁ እንዲተላለፍ ስላደረገ ልጁ ራሱ በመስቀል ላይ ፍርድን ተቀበለ እግዚአብሔር መቼም ቢሆን ውሸት ሊናገር አይችልም እንደተናገረውም *«የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነው» (ሮሜ 6:23)* ልጁ በሞተ ጊዜም በምድር ላይ ለ3 ሰዓታት ያህል ጭለማ ነግሶ ነበር።

*«ኤሎሄ፣ ኤሎሄ፣ ላማ ሰበቅታኒ? ብሎ በታላቅ ድምፅ ጮኸ ይህም አምላኬ! አምላኬ! ስለምን ተውከኝ? ማለት ነው» (ማቴዎስ 27:46)*

ኢየሱስ የሰው ልጆችን በሙሉ ከኃጢአት ለማዳን በጥምቀቱ ኃጢአታቸውን በሙሉ ወደ ራሱ አሻግሮዋል እንደሚሰቀልና አባቱ እግዚአብሄር እንደሚረሳው እያወቀ የሰውን ዘር ሐጢያቶች ወሰደ ስለዚህ እግዚአብሄር በዮርዳኖስ በወሰዳቸው ሐጢያቶች የተነሳ በልጁ ላይ ፈረደ ለሦስት ሰአታትም ፊቱን ከልጁ መለሰ።

*«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ስልጣን ሰጣቸው።» (ዮሐንስ 1:12)*

እናንተ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁን? እኛ ከውኃውና ከመንፈሱ ዳግም የምንወለድበትን ወንጌል የተቀበልን ስለሆንን

ፃድቃን ነን ከውኃና ከመንፈሱ የተወለዱት ፃድቃን ናቸው አሁን እኛ ሁላችንም ፃድቃን ሆነናል፡፡

*«እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ይቃወመናል?» (ሮሜ 8:31)* ፃድቅ ሰው ራሱን በእግዚብሔርና በሰዎች ፊት ፃድቅ ብሎ ሲጠራ ቤዛነትን ያላገኙት ሊፈርዱበት ያዘነብላሉ ሐዋርያው ጳውሎስ *«እግዚአብሔር የመረጣቸውን ማን ይከስሳቸዋል? የሚያጸድቅ እግዚአብሔር ነው የሚኮንንስ ማነው?»* ያለው ለዚህ ነው *(ሮሜ 8:33)* እግዚአብሔር ኃጢአቶቻችንን በሙሉ በልጁ በኢየሱስ አማካኝነት ካፀዳልን በኋላ እኛን ቅዱሳን፣ ፃድቃንና፣ የከበርን የእግዚአብሔር ልጆች ዘንድም መብትን ሰጥቶናል፡፡

እነዚያ ከውኃና ከመንፈስ ዳግም የተወለዱት የእርሱ ልጆች ናቸው ከእርሱ ጋርም ለዘላለም ይኖራሉ ከዚህ በኋላ እነርሱ በምድር ላይ የሚኖሩ ፍጡራን ብቻ ሳይሆኑ የሰማይ ዜጋ የሆኑ ወደ የእግዚአብሔር ልጆች ናቸው፡፡

እነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ከመሆናቸው የተነሳየሚከሳቸው የሚፈርድባቸው የለም ወይም ደግሞ ከእግዚአብሔር የሚለያቸው ማንም የለም፡፡

በኢየሱስ በትክክል ለማመን የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል ማወቅ አለብን መጽሐፍ ቅዱስንም በደንብ ማወቅ አለብን እንደ እርሱ ፈቃድ ልንተገብረው እንችል ዘንድ የእግዚአብሄርን ፈቃድ ማወቅና ማመን አስፈላጊ ነው፡፡

# ኃጢአተኞች ከውኃና ከመንፈስ ዳግም ይወለዱ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው

*እግዚአብሔር ልጁን*
*በኃጢአተኛ ሰው ስጋ የላከው*
*ለምንድን ነው?*

*ኃጢአት ሁሉ ወደ እርሱ*
*እንዲተላለፍ ነው።*

ቤዛነትን አግኝተን ከውኃና ከመንፈስ ዳግም እንወለድ ዘንድ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው *«ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና።» (1ኛ ተሰሎንቄ 4:3)*

ኃጢአቶቻችን በሙሉ ወደ እርሱ ተሸግረው እኛ መዳን እንችል ዘንድ ልጁን መላኩ የእግዚአብሄር ፈቃድ ነው ይህ ከውኃና ከመንፈስ ለመወለድ የሚያስችለን የመንፈስ ቅዱስ ሕግ ነው ይህም ከኃጢአቶቻችን በሙሉ ነፃ አውጥቶናል።

እኛ ቤዛነትን አግኝተናል አሁንስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ተገንዝባችኋልን? ሁላችንንም ማዳን የእርሱ ፈቃድ ነው እርሱ የሚፈልገው እኛ ከአለም ጋር እንድንደራደር ሳይሆን በእርሱ ቃሎች እንድናምን ነው።

እንዲሁም ደግሞ ሌሎች ነፍሳቶችን ወደ እግዚአብሄር መልሰው በማምጣት ስራ ውስጥ ተጠምደው ወንጌሉን እንዲሰብኩና በቤተክርስቲያን ውስጥ እንዲኖሩ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

ኃጢአትን የምንሰራው መስራት ፈልገን ሳይሆን ደካሞች

ስለሆንን ነው ሆኖም ግን ኢየሱስ እነዚህን ኃጢአቶች በሙሉ አስወግዶልናል እግዚአብሔር የዓለምን ኃጢአቶች በሙሉ በአጥማቂው ዮሐንስ አማካኝነት ወደ ኢየሱስ አስተላልፏል የራሱን አንድያ ልጁን የላከው ለዚሁ ጉዳይ ሲሆን በአጥማቂው ዮሐንስ እጅም እንዲጠመቅ አድርጎታል እኛም በዚህ በማመናችን ድነናል ይህም የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው::

## እርሱ በላከው በኢየሱስ ማመናችንም የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው

*ኢየሱስ በሐጢያተኛ ሰው ምሳሌ የመጣው ለምንድን ነው?*

*የሰው ልጆችን ኃጢአት በሙሉ ለማስወገድ ነው::*

መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈፀም ማለት እርሱ በላከው ማመን ማለት ነው ይለናል *«እንግዲህ የእግዚአብሔርን ስራ እንድንሰራ ምን እናድርግ? አሉት ኢየሱስም መልሶ ይህ የእግዚአብሔር ስራ እርሱ በላከው እንድታምኑ ነው አላቸው እንግዲህ እንኪያ አይተን እንድናምንህ አንተ ምን ምልክት ታደርጋለህ? ምንስ ትሰራለህ? ይበሉ ዘንድ ከሰማይ እንጀራ ሰጣቸው ተብሎ እንደ ተጻፈ አባቶቻችን በምድረ በዳ መና በሉ አሉት::» (ዮሐንስ 6:28-31)*

ሰዎች ሙሴ ወደ ከነዓን እየተጓዘ ሳለ መናን ከሰማይ ለእስራኤሎች በመስጠት ምልክት እንዲሰጠውና በዚያ የተነሳም

በእግዚአብሄር እንዳመኑ ለኢየሱስ ነገሩት (ዮሐንስ 6:32-39) ሰዎችም ኢየሱስን *«እንግዲህ የእግዚአብሔርን ስራ እንድንሰራ ምን እናድርግ?»* ብለው ጠየቁት::

ኢየሱስም የእግዚአብሔርን ስራ ይሰሩ ዘንድ በእርሱ ማመን እንዳለባቸው መለሰላቸው እኛም የእግዚአብሔርን ስራ መስራት ካለብን በኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ማመን አለብን ወንጌሉን መስበክ ብቻ ሳይሆን ወንጌሉን መኖርም እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፈቃዱ ነው::

እግዚአብሔር እንዲህ አዞናል *«እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኳችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው እነሆ እኔ እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስ ሁል ጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ::» (ማቴዎስ 28:19-20)*

ኢየሱስ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ መጠመቅ እንዳለብን በግልፅ ነግሮናል ለአባቱና ለመንፈስ ቅዱስ ያደረጋቸው ነገሮችም በሙሉ በጥምቀቱ ውስጥ ተካትተዋል ይህንን ስንረዳ በእግዚአብሔር ልናምንና ኢየሱስ በዚህ አለም ያደረገውንና መንፈሱም ስለዚያ የመሰከረውን ማመን እንችላለን::

ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተላከው የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል እንዲመሰክር ነው ልንድን የምንችለውም በእግዚአብሔር እውነተኛ ቃልና በአገልጋዩ ስናምን ብቻ ነው::

# የእግዚአብሔርን ስራ ለመሥራት

*የኑሮአችን ጥቅም ምንድን ነው?*

*ወንጌሉን በመላው ዓለም በማሰራጨት የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈፀም፡፡*

የእግዚአብሔርን ስራ የምንሰራ ከሆንን በመጀመሪያ በኢየሱስ ጥምቀትና በመስቀል ላይ ባፈሰሰው ደሙ ማመን አለብን እግዚአብሔር በላከው እንድናምንም የእርሱ ፈቃድ ነው በኢየሱስ ለማመንም በመጀመርያ በውኃውና በመንፈሱ እንዳዳነን ማመን አለብን፡፡

የእግዚአብሔር ፈቃድ የሚፈፀመው እኛ በኢየሱስ ስናምንና ወንጌልንም ስንሰብክ ነው በዚህም መንገድ የእግዚአብሔርን ስራ እንሰራለን እርሱ እንደነገረንም ከውኃውና ከመንፈሱ ዳግም በምንወለድበት ወንጌል የሚያምኑት ብቻ መንግስተ ሰማያት እንደሚገቡም ተናግሮናል፡፡


ቀጣዮቹን መሠረታዊ እውነቶች በመገንዘብ በመንግስተ ሰማያት ውስ የተቀመጠልንን ስፍራችንን እንውሰድ ሐጢያቶቻችን በሙሉ በጥምቀቱ ወደ ኢየሱስ መሻገራቸውን በማወቅና በማመን እውነተኛውን የእግዚአብሄር ፈቃድ እንገነዘባለን በመጨረሻም እስከ ዕለተ ሞታችሁ ድረስ ወንጌልን ስበኩ፡፡

ውድ ክርስትያኖች! እነዚያ የእግዚአብሔርን ስራ የሚሰሩት ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም የተወለዱት ናቸው እግዚአብሔር በላከው ማመን ማለት የእግዚአብሔርን ስራ

መስራት ማለት ነው እግዚአብሔር ወደላከው ወደ ኢየሱስ ኃጢአቶቻችን በሙሉ መተላለፋቸውን ማመንና ይህንንም መስበክ የእግዚብሔርን ስራ መስራት ነው::

የሰው ልጅ ኃጢአቶች በሙሉ እግዚአብሄር ወደላከው ወደ እርሱ መሻገሩንና ኢየሱስ ክርስቶስም አዳኛችን መሆኑን ማመን ፈቃዱን መፈፀም ነው::

እኛ ዳግም የተወለድን ወንጌልን እስከ አለም ፍፃሜ ድረስ በመስበክ መኖር ይገባናል::




*«በዚያን ቀን ብዙዎች ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ! በስምህ ትንቢት አልተናገርንምን? በስምህ አጋንንት አላወጣንምን? በስምህ ብዙ ተዓምራትን አላደረግንምን? ይሉኛል የዚያን ጊዜም ከቶ አላወቅኋችሁም እናንተ አመፀኞች ከእኔ ራቁ ብዬ እመሰክርባቸዋለሁ::» (ማቴዎስ 7:22-23)*

ይህ ምንባብ ኃጢአተኞቹ እነማን እንደሆኑና አመፃን የሚያደርጉትም እነማን እንደሆኑ በግልጽ ያሳየናል::

«ጌታ ጌታ» በሚሉት መካከል ዳግም ያልተወለዱት በርካቶች ናቸው በልባቸው ውስጥ ሐጢያት ስላለ እየተሰቃዩ ነው ስለዚህ ከፊል ማጉረምረም በሚመስል መንገድ እውነተኛ የአምልኮ ፀሎት በማይመስል ሁኔታ «ጌታ ጌታ» እያሉ

በመጣራት ወደ እግዚአብሄር ይጮኻሉ::

በፀሎት ቢጮሁ ሕሊናቸው እንደሚፀዳላቸው ያምናሉ ነገር ግን ኃጢአታቸው በልባቸው ውስጥ ስለሚቀር ይህ የሚቻል አይደለም እግዚአብሔር ሩቅ ያለ ይመስልም በስቃይ እየጮሁ በተራሮች ይፀልያሉ ምሉዕ የሆነ እምነት ከሌለን በተደጋጋሚ «ጌታ ጌታ» ብለን ወደ መጣራቱ እናዘነብላለን::

ጉባኤው ዳግም ባልተወለደባቸው አንዳንድ ቤተ ክርስቲያናት ውስጥ በከፍተኛ የስሜት ግለት ስለሚፀልዩ ምስባኩ ይሰበራል::

ነገር ግን በመፅሐፍ ቅዱስ ላይ ለማየት እንደምንችለው «ጌታ ሆይ! ጌታ ሆይ!» ያለ ሁሉ ወደ መንግሰተ ሰማያት አይገባም የእግዚብሔርን ስራ የሚሰሩት በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል የሚያምኑ ብቻ ናቸው::

እግዚአብሔር አንድ ሰው በልቡ ኃጢኣት እያለበት የእግዚአብሔርን ስም ቢጠራ ይህ አመፀኝነት መሆኑን ይናገራል በተራራ ላይ በሚደረጉ የፀሎት ስብሰባዎች ላይ ተገኝታችሁ ታውቃላችሁን? አንዳንድ ዕድሜ ጠገብ ሴት ዲያቆናት የእርሱን ስም በመጥራት ደጋግመው ያለቅሳሉ ምክንያቱም ኢየሱስን በእውነት አልተገናኙትም መንፈሱንም በልባቸው ውስጥ አልተቀበሉትም ከውሃና ከመንፈስም አልተወለዱም ስሙን በጥድፊያ ይጠሩታል ምክንያቱም ወደ ሲዖል እንወርዳለን በሚል ስጋት ይኖራሉና::

መጋቢ ወይም ሚሽነሪ ሆኖ ቤተክርስቲያንን ለማገልገል ሕይወቱን የሰጠ ሰው በእግዚአብሄር ዘንድ ተቀባይነት አጣ ብላችሁ ገምቱ ወላጅ ወይም ሚስት ቢተዉዋችሁ ልባችሁ ይሰበራል የነገስታት ንጉሥና የነፍሳቶች ሁሉ ፈራጅ የሆነው እግዚአብሄር ቢተዋችሁ የት ትደርሳላችሁ?

ይህ በእናንተ ላይ እንደማይደርስ ተስፋ አደርጋለሁ

የውኃውንና የመንፈሱን ወንጌል አድምጣችሁ እመኑበት ከውኃውና ከመንፈሱ ወንጌል ዳግም መወለዳችን የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው::

እኛ ክርስትያኖች በውኃውና በመንፈሱ ወንጌል ማመን አለብን ጥንካሬንም ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ማግኘት አለብን ከእግዚአብሄር ፍርድ ልንድን የምንችለው ያን ጊዜ ብቻ ነው:: ⌧

This **eBook** was created to preach the gospel of the Water and the Spirit all over the world through **Paul C. Jong's Christian Book Series .**

For more information on
Paul C. Jong's Christian Book Series,
visit us on the Web at "**www.bjnewlife.org**" **&**
"**www.nlmission.com**"

**ወደ አማዞን ኪንደል ኢ-ቡክስቶር** (www.amazon.com) **በመሄድ የሪቨረንድ ፖውል ሲ.ጆንግን የክርስቲያን መጽሐፎች በአይፎን በአይፓድ ወይም በብላክቤሪ ላይ መገልበጥ ትችላላችሁ::**